

# ነቢዩ ሙሐመድ
# ተምሳሌታዊ ስብእና

በዑስማን ኑሪ ቶኘባሽ

# ነቢዩ

# ሙሐመድ ﷺ

# ተምሳሌታዊ ስብእና


## በዑስማን ኑሪ ቶኘባሽ

**ትርጉም፡- ሐሰን ታጁ**



***አሳታሚ፡- አልበያን ሊሚትድ***

***ስልክ ቁጥር ፡- 0913 87 87 88 ወይም 0911 19 98 22***

***አዲስ አበባ ኢትዮጵያ***

የአሳታሚው መብት በሕግ
የተጠበቀ ነው።
All rights are reserved

አንደኛ እትም ጥር 2003

AFKAD 2

*Addis Ababa Ethiopia*

First Edition Jan.2011

# ማውጫ


ርእስ ገጽ

ክፍል አንድ....12
ልዩና ተምሳሌታዊ ስብእና....13
መልካም አርአያ....26
ክፍል ሁለት....38
የአላህ መልእክተኛ የመጠቁ ባህሪያት....39
የገጽታ ውበትና የባህሪ ማማር....39
ትህትናቸው....44
ቸርነታቸው....47
ተቅዋቸው....48
ዙህዳቸው....50
አደብና አይናፋርነት....55
ጀግንነታቸው....57
ሆደ ሰፊነታቸው....58
ርህራሄያቸው....60
ይቅር ባይነታቸው....62
የጎረቤትን ሐቅ መጠበቅ....66
ድሆችን መንከባከብ....68
የምርኮኞችና የአገልጋዮች አያያዝ....70
የሴቶች አያያዝ....74
ከየቲሞች ጋር....79
የእንስሳት አያያዝ....80
ወደር የማይገኝላቸው መስፈርቶች....86
ክፍል ሦስት....89
ረሱሉን በፍቅር መከተል....92
የደስታ ዘመን- የነቢዩ ስነ ምግባርና ፍቅር መስታወት....97
የረሱሉ ፍቅር ዜማዎች....103
ሶሐቦች ለመልእክተኛው የነበራቸው ፍቅር....107
ከሶሐቦች በኋላ....115
በነቢዩ ላይ ሶለዋት ማውረድ....122
ክፍል አራት....126

ርእስ ገጽ


የተምሳሌታዊ ስብእና አስፈላጊነት ........ 127
አርአያ የመያዝና የመከተል ዝንባሌ ........ 135
የአላህ መልእክተኛ ተምሳሌታዊ ስብእና ........ 137
የአላህን መልእክተኛ ምን ያህል እንወዳለን? ........ 139
ቀልብንም አእምሮንም መጠቀም ........ 139
አእምሯችንን እንዴት እንጠቀም? ........ 139
ቀልባችንን እንዴት እንጠቀምበት? ........ 139
ተምሳሌታዊው ስብእና ........ 140
ቁርአን -ታላቁ ተአምር ........ 140
ዓይነ ስውር ጸሐይን ያማርራል ........ 141
አፍቃሪ ታዛዥ ነው ........ 144
ነቢዩን መከተል መንፈሳዊ ስልጠናን ይሻል ........ 145
የነብዩን ደረጃ ምን ያህል ተረድተናል? ........ 147
የፍቅር እና የአደብ ፈተና ........ 149
ረሱሉን የመውደድ መመዘኛ ........ 150
ነቢዩን የመውደድ ምልክት ........ 152
ነቢዩን መግለጽ አስቸጋሪ ነው ........ 152
ማጠቃለያ ........ 154

## በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው።

አላህ መልእክተኛውን ﷺ እንዲህ በማለት አስቀዋውቆናል፡-

﴿ وَمَآ أَرۡسَلۡنَٰكَ إِلَّا رَحۡمَةٗ لِّلۡعَٰلَمِينَ ١٠٧ ﴾ الأنبياء: ١٠٧

*‹‹(ሙሐመድ ሆይ!) ለዓለማት እዝነት አድርገን እንጅ አላክንህም።››
(አል አንቢያእ 107)*

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّبِيُّ إِنَّآ أَرۡسَلۡنَٰكَ شَٰهِدٗا وَمُبَشِّرٗا وَنَذِيرٗا ٤٥ وَدَاعِيًا إِلَى ٱللَّهِ بِإِذۡنِهِۦ وَسِرَاجٗا مُّنِيرٗا ﴾ الأحزاب: ٤٥ - ٤٦

*“አንተ ነቢዩ ሆይ! እኛ መስካሪ፣ አብሳሪና አስጠንቃቂ አድርገን ላክንህ። ወደ አላህም -በፈቃዱ- ጠሪና ብርሃን ሰጋሽ መብራት (አደረግንህ)።” (አል አህዛብ 45-46)*

﴿ لَّقَدۡ كَانَ لَكُمۡ فِي رَسُولِ ٱللَّهِ أُسۡوَةٌ حَسَنَةٞ لِّمَن كَانَ يَرۡجُواْ ٱللَّهَ وَٱلۡيَوۡمَ ٱلۡأٓخِرَ وَذَكَرَ ٱللَّهَ كَثِيرٗا ٢١ ﴾ الأحزاب: ٢١

*“የአላህ መልዕክተኛ፣ (ከመካከላችሁ) አላህንና መጭውን ዓለም ተስፋ ለሚያደርግ፣ አላህንም በብዛት ለሚያወሳ፣ መልካም አርአያ ነው።”
(አል አህዛብ 21)*

﴿ وَإِنَّ لَكَ لَأَجۡرًا غَيۡرَ مَمۡنُونٖ ٣ وَإِنَّكَ لَعَلَىٰ خُلُقٍ عَظِيمٖ ٤ ﴾ القلم: ٣ - ٤

*‹‹ላንተ (ከጌታህ) የማይቋረጥ ምንዳ አለህ። አንተ የላቀ ሥነ-ምግባር ባለቤት ነህ።›› (አል ቀለም 3-4)*

﴿ وَٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَعَمِلُواْ ٱلصَّٰلِحَٰتِ وَءَامَنُواْ بِمَا نُزِّلَ عَلَىٰ مُحَمَّدٖ وَهُوَ ٱلۡحَقُّ مِن رَّبِّهِمۡ كَفَّرَ عَنۡهُمۡ سَيِّـَٔاتِهِمۡ وَأَصۡلَحَ بَالَهُمۡ ٢ ﴾

*‹‹እነዚያ ያመኑትና መልካም ሥራዎችን የሠሩት፥ ከጌታቸው ለሙሐመድ በተወረደው እውነትም ያመኑት (አላህ) ኃጢአቶቻቸውን ይምርላቸ ዋል። ውሏቸውንም ፈር ያስይዛል።›› (ሙሐመድ 2)*

﴿ وَمَن يُطِعِ ٱللَّهَ وَٱلرَّسُولَ فَأُوْلَٰٓئِكَ مَعَ ٱلَّذِينَ أَنْعَمَ ٱللَّهُ عَلَيْهِم مِّنَ ٱلنَّبِيِّـۧنَ وَٱلصِّدِّيقِينَ وَٱلشُّهَدَآءِ وَٱلصَّٰلِحِينَۚ وَحَسُنَ أُوْلَٰٓئِكَ رَفِيقًا ٦٩ ﴾ النساء: ٦٩

*‹‹አላህንና መልዕክተኛውንም የሚታዘዝ (በመጭው ዓለም) አላህ ፀጋውን ከለገሳቸው ከነቢያት፥ ከጻድቃንም፥ ከሰማዕታትና ከደጋጎች ጋር ይሆናል። ከነኝህ ጋር መጐዳኘት እጅግ ድንቅና ውብ፥ እጅግ ማራኪ ነው።›› (አል ኒሳእ 69)*

﴿ إِنَّ ٱللَّهَ وَمَلَٰٓئِكَتَهُۥ يُصَلُّونَ عَلَى ٱلنَّبِيِّۚ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ صَلُّواْ عَلَيْهِ وَسَلِّمُواْ تَسْلِيمًا ٥٦ ﴾ الأحزاب: ٥٦

*‹‹አላህና በመላእክቱ በነቢዩ ላይ "ሶለዋት" ያወርዳሉ። እናንተ ያመናችሁ ሆይ! በርሱ ላይ "ሶለዋት" አውርዱ።›› (አል አህዛብ 56)*

# መቅድም

አላህን እናመሰግነዋለን፡፡ ዘወትር እናወድሰዋለን፡፡ ጸጋውን ስለለገሰን፣ ውለታም ስለዋለልን፣ የተላቁት መልእክተኛው ﷺ ተከታይ ስላደረገን፣ የነብያት ዘውድ የሆኑትን ሙሐመድን ﷺ ነብይና መልክተኛ አድርጎ ስለላከልን ምስጋናችን ከፍ ያለ፣ ውዳሴያችን ዘልዓለማዊ ነው፡፡

የአለም ብርሃንና የሰውን ልጅ ወደ ዘልዓለማዊ ደስታ የሚመሩ በሆኑት በነቢዩ ሙሐመድ ﷺ ላይ የአላህ እዝነትና ሰላም ይውረድ፡፡ የሰው ልጅ በጣም በተቸገረበት ዘመን ላካቸው፡፡ ዓለም ከጨለማና ከግፍ ባህር ውስጥ በተነከረችበት ዘመን የዓለማት እዝነት አደረጋቸው፡፡ አላህ እርሳቸውን በመለገስ አላቀን፡፡ ነቢዩ ﷺ የጨለማ ብርድ ልብስ ለብሳ የነበረችውን ዓለም በብርሃን ያደመቁ አንጸባራቂ ስብእና ናቸው፡፡ በወንጀል እስከ አንገቱ ተነክሮ የነበረውን የሰው ልጅ ሕይወት አድሰው እንዲጸዳ አድርገዋል፡፡

ነቢዩ ሙሐመድ ﷺ ለፍጡራን ሁሉ ባጠቃላይ፣ ለሕያውያንንም፣ ለግኡዛንም፣ ለድንጋዩ፣ ለዛፉ፣ ለወንዙ፣ ለባህሩ፣ ለምድሩ፣ ለሰማዩ፣ ለዘመንና ቦታ፣ እንዲሁም ለሰው ልጅ በተለይ የማይቋረጥ ችሮታ ናቸው፡፡ በረከት፣ የመቀናት፣ የእዝነትና የመዳን መንገድም ናቸው፡፡

ረህመት ናቸው፡፡ ምክንያቱም መላ ዩኒቨርሱ ለተፈጠረለት የሰው ልጅ ተምሳሌት ናቸውና፡፡ ዩኒቨርሱ በሐቅ እይታ ለርሳቸው ባለው ፍቅር መጠን ልቅናው ይጨምራል፡፡

ረህመት ናቸው -ምክንያቱም እዝነታቸው የሰውን ልጅ ሁሉና ሌሎች ፍጡራንንም አጠቃልሏል፡፡

ረህመት ናቸው- ምክንያቱም አላህ የመንፈስና የአእምሮ ሕይወት፣ የሕሊና እርካታና በረከት ዘልዓለማዊ ምንጭ አድርጓቸዋልና፡፡

ረህመት ናቸው- ምክንያቱም አላህ ለዝንተ ዓለም መመሪያ የሆነውን ቁርአንን በመስጠት አልቋቸዋልና፡፡

ረህመት ናቸው- ምክንያቱም ከአላህ ዘንድ ከሁሉም ነብያት የበለጠ ተወዳጅ፣ አላህ በሚእራጅ ጉዞ ያላቃቸው የፍጡራን ሁሉ ፈርጥ ናቸውና፡፡

ረህመት ናቸው -ምክንያቱም እርሳቸው ባይኖሩ ኖሮ ዓለም ወደ አውሬ ጫካነት በተቀየረች ነበርና፡፡

ረህመት ናቸው- ምክንያቱም ዓለም ከበረካቸው ተቋድሷልና፡፡

ረህመት ናቸው- ምክንያቱም አላህ በርሳቸው ላይ ሁሌም ሶለዋት በማውረድ ክብራቸውን አልቆታል፡፡ ማንነታቸውን አግዝፎታል፡፡ ዓለም በርሳቸው ነብይነት እውነተኛ ውስጠ ሰላምንና የሕሊና ረፍትን አግኝቷል፡፡ በወንጀል ጭጋግ ታፍኖ ጣእረ ሞት ላይ የነበረው የሰው ልጅ የአላህ መልእክተኛ በከፈቱት የእውነተኛ እውቀት በር በረከት የሕይወት እስትንፋስ ዳግም መተንፈስ ችሏል፡፡

እንደ አለት ጠጣር የነበሩ ሕሊናዎች በርሳቸው በረከት እንደ ጭቃ ለዝበዋል፡፡ በቆሻሻ ተውጠው የነበሩና የዛጉ ቀልቦች በርሳቸው የእውቀት ውሃ ታጥበው ጸድተዋል፡፡ ጨለማቸው ተገፎም የብርሃን ማረፊያዎች ሆነዋል፡፡

ሐበሻዊው ወህሽይ ከመስለሙ በፊት የሰው ነፍስ እንደዘበት የሚያጠፋ ጨካኝ ነበር፡፡ የሕሊና ልጓሙን ለአላህ መልእክተኛ ﷺ ካስረከበ በኋላ ግን ቀልቡ የለዘበ፣ ስሜቱ ስስና አልቃሽ ሶሐብይ ለመሆን በቃ፡፡ ሌሎች በርካታ ሶሐቦችም የርሱ ዓይነት ለውጥ አሳይተዋል፡፡

መንፈሳቸው በእኩይ ባህሪያት ተውጦ ሊጠፋ ተቃርቦ ነበር፡፡ ከነቢዩ ﷺ የቅን መመሪያ ምንጭ ከተጎነጩ በኋላ ግን ዘልዓለማዊውን ሕይወት አወቁ፡፡ ክብርንና ልእልናን ተጎናጸፉ፡፡ ስማቸው ከነብያት ፈርጥ ስም ጋር ተቆራኘ፡፡

ይህ ሁሉ የሚያሳየው የተላቁት ነብያችን አላህ ከፈጠራቸው ተአምራት ሁሉ የላቁ፣ ከለገሰን ጸጋዎች ሁሉ ወደር የማይገኝላቸው መሆኑን ነው፡፡ በሁሉም ገጽታዎች ተአምር ናቸው፡፡ እጅግ ድንቅና ምሉእ፣

እጅግ ልዑልና ተወዳጅ ነብይ ናቸው፡፡ የልእልናና የልግስና ባለቤት ከሆነው ከቸሩ ፈጣሪያችን ዘንድ ለዓለማት የተበረከቱ እዝነት፣ ታላቅ ኩራትና በረከት በመሆናቸው በረኸሙ የእስልምና ታሪክ ወቅት የነበሩ ሁሉም አዋቂዎች፣ ጥበበኞች፣ ደጋግ ሰዎች፣ ታላላቅ ስብእናዎች የርሳቸው እንጽብራቂ እንጅ ሌላ አይደሉም፡፡ ከዚህም አልፎ የርሳቸው አካል ናቸው፡፡ የጸሐይ ብርሃን ከጨረቃ እንደተቀዳው የነርሱም ታላቅነት ከነቢዩ ልእልና የተቆነጠረ ነው፡፡

ይህም በመሆኑ ወደ አላህ ለመቃረብ እና የርሱን ውዴታ ለማግኘት መንገዱ እርሳቸውን መውደድና ሱንናቸውን መከተል ነው፡፡ አላህ ይህን እውነታ በበርካታ የቁርአን አናቅጽ ገልጿል፡፡ እንዲህ ይላል፡-

﴿ قُلۡ إِن كُنتُمۡ تُحِبُّونَ ٱللَّهَ فَٱتَّبِعُونِي يُحۡبِبۡكُمُ ٱللَّهُ وَيَغۡفِرۡ لَكُمۡ ذُنُوبَكُمۡۚ وَٱللَّهُ غَفُورٞ رَّحِيمٞ ٣١ ﴾

آل عمران: ٣١

*‹‹እነዚያ የካዱትና ክህደት ውስጥ እንዳሉ የሞቱት ከነርሱ አንዳቸው (ራሱን ከቅጣት ለማዳን) ምድርን የሚሞላ ወርቅ ቤዛ ቢያቀርብ ተቀባይነት የለውም። እነዚያ ለነርሱ አሳማሚ ቅጣት ተዘጋጅቶላቸዋል። (ከአላህ ቅጣት የሚያድናቸው አንድም) ረዳት አያገኙም።››* (አሊ ዒምራን 31)

በሌላ ቦታም እንዲህ ብሏል፡-

﴿ مَّن يُطِعِ ٱلرَّسُولَ فَقَدۡ أَطَاعَ ٱللَّهَۖ وَمَن تَوَلَّىٰ فَمَآ أَرۡسَلۡنَٰكَ عَلَيۡهِمۡ حَفِيظٗا ٨٠ ﴾

النساء: ٨٠

*‹‹መልዕክተኛውን የታዘዘ አላህንም ታዟል። (ከዚህ መንገድ) ያፈገፈገ ግን (አያሳስብህ) እነርሱን (ከኃጢአት) ጠባቂ አድርገን አልላክንህም።››* (አል ኒሳእ 80)

በአንቀጹ በግልጽ እንደተመለከተው አላህን የመውደድ ትክክለኛ መመዘኛ የመልእክተኛውﷺ እውነተኛ ተከታይ መሆን ነው፡፡ ይህ ካልሆነ እምነት ትክክለኛ ፍሬውን ይዟል አይባልም፡፡ ይህን እውነታ በአላህ የሚያምን

ሁሉ አይዘነጋውም፡፡ ይህም በመሆኑ ነቢዩ ﷺ በየትኛውም ወቅት ከኛ ጋር ሊሆኑ ይገባል፡፡ በእያንዳንዱ የሕይወት ክንውናችን ሚና ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ተምሳሌታዊ ስብእናቸው ስብእናችንን ለማነጽ፣ መመዘኛና ብቸኛ ናሙና ሊሆን ይገባል፡፡ ከዚህ አኳያ የአላህን መልእክተኛ ﷺ በቅርበት ማወቅ እጅግ አስፈላጊና አንገብጋቢ ጉዳይ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ጥቃቅን የሕይወት ክንውኖቻቸውን ሳይቀር ማወቅ አስፈላጊ ነው፡፡ የቀልባችን ምት ከርሳቸው የቀልብ ምት፣ እስትንፋሳችንን ከእስትንፋሳቸው ማጣጣም ግድ ይለናል፡፡ ልቦናቸው በርሳቸው ፍቅር እንደተሞላው፣ በናፍቆታቸው እንደተቃጠለው ሶሐቦች ልንሆን ግድ ነው፡፡

በእርግጥ በዚህ ረገድ የሚገባንን ያህል ወደ ላይ ላንመጥቅ እንችላለን፡፡ ግና አርአያነታቸውን መከተል፣ ቅን መመሪያቸውን ያቅማችንን ያህል መተግበር ከቻልን በቂ ነው፡፡ አምሳያ ከሌለው እና የዘልዓለማዊ ስኬት መዳረሻ ከሆነው ስብእናቸው ኢምንት ታህል መቋደስ ከቻልን ታላቅ ስኬት ነው፡፡

ይህን ዓላማ ለማሳካት ሲባል ይህን መጽሐፍ አዘጋጅተናል፡፡ የታላቁን ነብይ ስብእና በቅርበት እንድታውቁ እገዛ ያደርግላችኋል ብለን ተስፋ እናደርጋለን፡፡፡ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ መረጃዎች ከዚህ ቀደም ካዘጋጀናቸው መጽሐፍት ተጨምቀው የተወሰዱ ናቸው፡፡

ስለ ነቢዩﷺ ስብእና የቱን ያህል ብንጽፍም በተሟላ መልኩ ለመግለጽ አቅም እንደሚያንሰን እሙን ነው፡፡ ስለዚህም ስለርሳቸው ታሪክና ሱንና ለማውጋትና ፈለጋቸውን ለመከተል እድሉን በማመቻቸት ታላቅ ጸጋ የሆኑትን መልእክተኛውን ለለገሰን አላህ የላቀ ምስጋና እናቀርባለን፡፡

የኛ ትልቁ ሚና በአዳዲስ ቀውሶች በመናጥ ላይ ለሚገኘው ለዘመናችን ሰው ሁሉንም ፍጡራን ያካተተውን የነቢዩንﷺ እዝነት ለማድረስ ያቅማችንን ያህል ድልድይ መሆን ነው፡፡ እንደዚሁም የምሉእነትን ጫፍ የደረሰውን ይህን ታላቅ ተአምራዊ ስብእና የሰው ልጅ ባጠቃላይ

በሚገባው ቋንቋ እንዲያውቃቸው መርዳት ነው፡፡ የነብዩን ﷺ ስብእና ማስተዋወቅ ለኛ ታላቅ ክብር ነውና፡፡

አምላካችን ሆይ፣ ወደር ከሌለው ተምሳሌታዊ ስብእናቸው ተቋዳሽ አድርገን፡፡ ቀልባችንንም በርሳቸው ፍቅር አድምቀው፡፡ የተቅዋ መመዘኛ የሆነውን ለርሳቸው ትእዛዝ የማደርን ፈተና የምንወጣ፣ እንዲሁም ያንተን ውዴታ ለማግኘት ተገቢ ሰዎች አድርገን፡፡ አሚን፡፡[1]

[1] ይህን መጽሐፍ ለማዘጋጀት ለደከሙ ተማሪዎቻችን ስራቸውን ምንዳው የማይቋረጥ ሶደቃ ያደርግለቸው ዘንድ አላህን እለምናለሁ፡፡

# ክፍል አንድ

⇒ልዩና ተምሳሌታዊ ስብእና

⇒መልካም አርአያ

## ልዩና ተምሳሌታዊ ስብእና

አላህ ነቢዩ ሙሐመድን ﷺ ለሰው ልጆች በታላቅ ስጦታነት አበረከተ፡፡ ይህም የሆነው ከአላህ ዘንድ እጅግ የላቀ ክብር ስላላቸው ነው፡፡ ወዳጁን ነቢዩን ﷺ መታዘዝን እርሱን የመታዘዝ አካል፣ ከርሳቸው ጋር ቃል መጋባትን ከርሱ ጋር ቃል መጋባት እንደሆነ ገለጸ፡፡ የርሱን ውዴታ ለማግኘትም ዋነኛው መስፈርት ነቢዩን ﷺ መከተል መሆኑን አሳወቀ፡፡ ተከታዮች የቁርአን አናቅጽ ይህን መልእክት ያዘሉ ናቸው፡-

﴿ وَمَآ أَرۡسَلۡنَٰكَ إِلَّا رَحۡمَةٗ لِّلۡعَٰلَمِينَ ١٠٧ ﴾ الأنبياء: ١٠٧

*‹‹(ሙሐመድ ሆይ!) ለዓለማት እዝነት አድርገን እንጅ አላክንህም፡፡›› (አል አንቢያእ 107)*

ነቢዩ ﷺ እንዲህ ይሉ ነበር፡-

‹‹እናንተ ሰዎች ሆይ፣ እኔ እዝነትና ቅን መመሪያ ነኝ፡፡›› (ዳሪሚ)

﴿ مَّن يُطِعِ ٱلرَّسُولَ فَقَدۡ أَطَاعَ ٱللَّهَۖ وَمَن تَوَلَّىٰ فَمَآ أَرۡسَلۡنَٰكَ عَلَيۡهِمۡ حَفِيظٗا ٨٠ ﴾
النساء: ٨٠

*‹‹መልዕክተኛውን የታዘዘ አላህንም ታዟል፡፡ (ከዚህ መንገድ) ያፈገፈገ ግን (አያሳስብህ) እነርሱን (ከኃጢአት) ጠባቂ አድርገን አልላክንህም፡፡›› (አል ኒሳእ 80)*

﴿ إِنَّ ٱلَّذِينَ يُبَايِعُونَكَ إِنَّمَا يُبَايِعُونَ ٱللَّهَ يَدُ ٱللَّهِ فَوۡقَ أَيۡدِيهِمۡۚ فَمَن نَّكَثَ فَإِنَّمَا يَنكُثُ عَلَىٰ نَفۡسِهِۦۖ وَمَنۡ أَوۡفَىٰ بِمَا عَٰهَدَ عَلَيۡهُ ٱللَّهَ فَسَيُؤۡتِيهِ أَجۡرًا عَظِيمٗا ١٠ ﴾ الفتح: ١٠

*‹‹እነዚያ አንተን ቃልኪዳን የሚጋቡህ፥ ቃልኪዳን የሚጋቡት አላህን ነው፡፡ የአላህ እጅ ከእጆቻቸው በላይ ነው፡፡ ቃልኪዳኑን ያፈረሰ የሚጐዳው ራሱን ነው፡፡ ግና ለአላህ የገባውን ቃልኪዳን የሞላ፥ (አላህ) ታላቅ ምንዳን ይለግሰዋል፡፡›› (አል ፈትህ 10)*

﴿ قُلۡ إِن كُنتُمۡ تُحِبُّونَ ٱللَّهَ فَٱتَّبِعُونِي يُحۡبِبۡكُمُ ٱللَّهُ وَيَغۡفِرۡ لَكُمۡ ذُنُوبَكُمۡۚ وَٱللَّهُ غَفُورٞ رَّحِيمٞ ٣١ ﴾ آل عمران: ٣١

*በላቸው፡- "አላህን የምታፈቅሩ ከሆናችሁ ተከተሉኝ፤ አላህ ያፈቅራችኋል፤ ኃጢአቶቻችሁንም ይምራል፤ አላህ መሓሪ፥ አዛኝ ነው።" (አሊ ዒምራን 31)*

አንድም ሰው እርሳቸውን መቅደም እንደሌለበት አላህ በግልጽ አዟል፡-

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ لَا تُقَدِّمُواْ بَيۡنَ يَدَيِ ٱللَّهِ وَرَسُولِهِۦۖ وَٱتَّقُواْ ٱللَّهَۚ إِنَّ ٱللَّهَ سَمِيعٌ عَلِيمٞ ١ ﴾ الحجرات: ١

*‹‹እናንተ ያመናችሁ ሆይ! በአላህና በመልዕክተኛው ፊት (ነፍሶቻችሁን) አታስቀድሙ። አላህንም ፍሩ። አላህ ሰሚም ተመልካችም ነውና።›› (አል ሁጁራት 1)*

ይህ አንቀጽ በቁርአንና በሐዲስ ማእቀፍ ውስጥ መሆንን ያዛል፡፡ ስለሆነም ከአላህና ከመልእክተኛውﷺ ትእዛዛት፣ ከቁርአንና ከሐዲስ መመሪያዎች መውጣት ፈጽሞ የሚፈቀድ አይደለም፡፡

የአላህ መልእክተኛﷺ ባልደረቦቻቸውን ከቁርአን መመሪያ አኳያ ቀርጸዋቸዋል፡፡ ይህም በመሆኑ ሶሐቦች አንዳች ነገር በተጠየቁ ጊዜ፡- ‹‹አላህና መልእክተኛው ያውቃሉ፡፡›› የማለት ልምድ ነበራቸው፡፡ አጀንዳውን የሚያውቁት ቢሆን እንኳ ምላሻቸው ይህ ነበር፡፡ ከዚህ የተነሳ ስብእናቸው መጠቀ፡፡ የመልካም ስርዓት ባለቤት ሆኑ፡፡ የቀልብን መርጠብ አገኙ፡፡ የአደብን ጣሪያ ደረሱ፡፡

አላህ ሙእሚኖችን ከነቢዩﷺ ዘንድ እጅግ ስርዓታማና አንደበታቸው የታረመ እንዲሆን፣ ድምጻቸውን ከርሳቸው ፊት ከፍ አድርገው እንዳይናገሩ አዟል፡፡ ከዚህ ስርዓት ከወጡ ስራቸው እንደሚበላሽ አስጠንቅቋል፡፡ ይህን የሚመለከቱ የቁርአን አናቅጽ በርካታ ናቸው፡፡

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ لَا تَرۡفَعُوٓاْ أَصۡوَٰتَكُمۡ فَوۡقَ صَوۡتِ ٱلنَّبِيِّ وَلَا تَجۡهَرُواْ لَهُۥ بِٱلۡقَوۡلِ كَجَهۡرِ بَعۡضِكُمۡ لِبَعۡضٍ أَن تَحۡبَطَ أَعۡمَٰلُكُمۡ وَأَنتُمۡ لَا تَشۡعُرُونَ ٢ ﴾ الحجرات: ٢

*‹‹እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ድምጾቻችሁን ከነቢዩ ድምጽ በላይ ከፍ አታድርጉ፤ እርሱን ስታናግሩም፥ አንዳችሁ ሌላኛውን ሲያናግር እንደሚጮኸው፥ አትጩሁ፤ ሥራዎቻችሁ ሳታውቁት እንዳይበላሹባችሁ፡፡›› (አል ሁጁራት 2)*

ነቢዩን ማላቅን የቀልብ ተቅዋ መመዘኛ አደረገው፡፡ የሰው ልጅ የአላህ ተገዥነትን (ዐቡድያን) ክብር ለማግኘት ነቢዩን ማላቅ አብይ መስፈርት መሆኑን ገለጸ፡፡ ከነቢዩ ጋር ባለ ግንኙነት አደብ አለመያዝ የመሐይምነት ትልቅ ምልክት መሆኑን አብራራ፡፡

﴿ إِنَّ ٱلَّذِينَ يَغُضُّونَ أَصۡوَٰتَهُمۡ عِندَ رَسُولِ ٱللَّهِ أُوْلَٰٓئِكَ ٱلَّذِينَ ٱمۡتَحَنَ ٱللَّهُ قُلُوبَهُمۡ لِلتَّقۡوَىٰۚ لَهُم مَّغۡفِرَةٞ وَأَجۡرٌ عَظِيمٌ ٣ إِنَّ ٱلَّذِينَ يُنَادُونَكَ مِن وَرَآءِ ٱلۡحُجُرَٰتِ أَكۡثَرُهُمۡ لَا يَعۡقِلُونَ ٤ ﴾ الحجرات: ٣ - ٤

*‹‹እነዚያ ከአላህ መልዕክተኛ ዘንድ ድምጾቻቸውን ዝቅ የሚያደርጉት - አላህ ልቦቻቸውን ለ“ተቅዋ” ያሰናዳቸው ናቸው፡፡ ለነርሱ ምሕረትም፥ ታላቅ ምንዳም አላቸው፡፡ እነዚያ ከጉጆዎች ውጭ ሆነው የሚጠሩህ ብዙዎቹ አስተዋዮች አይደሉም፡፡›› (አል ሁጁራት 3-4)*

ከዚህ ርእሰ ጉዳይ ጋር በተያያዘ ተከታዩን የቁርአን አንቀጽ መረጃ አድርገን ማምጣትም ጠቃሚ ሳይሆን አይቀርም፡-

﴿ لَّا تَجۡعَلُواْ دُعَآءَ ٱلرَّسُولِ بَيۡنَكُمۡ كَدُعَآءِ بَعۡضِكُم بَعۡضٗاۚ قَدۡ يَعۡلَمُ ٱللَّهُ ٱلَّذِينَ يَتَسَلَّلُونَ مِنكُمۡ لِوَاذٗاۚ فَلۡيَحۡذَرِ ٱلَّذِينَ يُخَالِفُونَ عَنۡ أَمۡرِهِۦٓ أَن تُصِيبَهُمۡ فِتۡنَةٌ أَوۡ يُصِيبَهُمۡ عَذَابٌ أَلِيمٌ ٦٣ ﴾ النور: ٦٣

*‹‹በመካከላችሁም የመልዕክተኛውን ጥሪ እርስ በርስ እንደምትጠራሩት አታድርጉ፡፡ ከናንተ ውስጥ እነዚያ አንዱ በሌላው እየተከለለና እየሾለኩ (ያለ ፍቃድ) የሚወጡትን አላህ ያውቃቸዋል፡፡ እነዚያ*

*ትእዛዙን የሚጥሱት አንዳች መከራ እንዳይደርስባቸው ወይም አሳማሚ ቅጣት እንዳያገኛቸው ይጠንቀቁ።›› (አል ኑር 63)*

ኢብን አባስ ይህን አንቀጽ እንዲህ በማለት ተርጉመውታል፡-

ሙሐመድ ወይም አቡል ቃሲም በማለት ብቻ ነቢዩን ﷺ አንጠልጥሎ መጥራትን በዚህ አንቀጽ አላህ ከልክሏል፡፡ ይህን ያደረገው ነቢዩን ለማላቅ ነው፡፡ ‹‹የአላህ ነብይ ሆይ፣ የአላህ መልእክተኛ ሆይ›› በማለት እንድንጠራቸውም አዟል፡፡[1]

አላህ ነቢዩ ሙሐመድን ﷺ እንደሌሎች ነብያት በስማቸው ከአንድም ቦታ ላይ ጠርቶ አላናገራቸውም፡፡‹፣የአላህ ነብይ ሆይ፣ የአላህ መልእክተኛ ሆይ፡›› የሚለውን የክብር ስም ምንጊዜም በመጠቀም ለርሳቸው ያለውን ክብር ገልጿል፡፡ ለኛ ለባሮቹም ወዳጃችንን ሙሐመድን በተመለከተ ልንከተለው የሚገባንን ስርዓት አስተምሮናል፡፡

የነቢዩን ﷺ የላቀ ደረጃ ና ክብር የሚዘነጉ ሰዎችንም የቁርአን ሕያው ማብራሪያ በሆነ ሕይወታቸው በመማል አስጠንቅቋል፡፡

﴿ لَعَمْرُكَ إِنَّهُمْ لَفِي سَكْرَتِهِمْ يَعْمَهُونَ ﴿٧٢﴾ ﴾ الحجر: ٧٢

*‹‹(ሙሐመድ ሆይ!) በሕይወትህ እምላለሁ። እነርሱ በእርግጥም በስካራቸው ውስጥ ይዋልላሉ።›› (አል ሂጅር 72)*

ከነቢዩ ﷺ ውጭ በሌላ ሰው ሕይወት አላህ የማለበትን ሁኔታ በቁርአን ውስጥ ፈጽሞ አናገኝም፡፡ ይህ በእርግጥ ልቅናቸውን ያሳያል፡፡ ከአላህ ዘንድ የተለየ ደረጃቸውን ያመለክታል፡፡ አላህ ራሱና መላኢኮች በርሳቸው ላይ ሶለዋት ማውረዳቸው፣ አማኞችም ሶለዋት እንዲያደርጉ መታዘዛቸው ለልእናቸው ሌላ ምስክር ነው፡፡

---

[1] ኢብን ከሲር ለአንቀጹ ከሰጡት ማብራሪያ የተወሰደ፡፡

﴿ إِنَّ ٱللَّهَ وَمَلَٰٓئِكَتَهُۥ يُصَلُّونَ عَلَى ٱلنَّبِيِّۚ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ صَلُّواْ عَلَيۡهِ وَسَلِّمُواْ تَسۡلِيمًا ٥٦ ﴾ الأحزاب: ٥٦

*‹‹አላህና መላእክቱ በነቢዩ ላይ "ሶለዋት" ያወርዳሉ፡፡ እናንተ ያመናችሁ ሆይ! በርሱ ላይ "ሶለዋት" አውርዱ፡፡ የክብር ሰላምታ አቅርቡለትም፡፡›› (አል አህዛብ 56)*

አላህ ለነቢዩﷺ የዋለው በጎ ውለታና የቸረው ልቅና መቼም ቢሆን የሚቋረጥ አይደለም፡፡ እስከ እለተ ቂያማ ድረስ ይቀጥላል፡፡

﴿ وَلَسَوۡفَ يُعۡطِيكَ رَبُّكَ فَتَرۡضَىٰٓ ٥ ﴾ الضحى: ٥

*‹‹ወደፊት ጌታህ (በርካታ ፀጋዎችን) ይለግስሃል፡፡ (በስጦታውም) ትደሰ ታለህ፡፡›› (አል ዱሐ 5)*

ከዚህ ሁሉ በተጨማሪ አላህ የመልእክተኞች ፈርጥ አድርጓቸዋል፡፡ ከሁሉም ነብያት እና መልእክተኞች በከፍተኛ ሁኔታ አልቋቸዋል፡፡ ከነርሱ መሐል የተለየ ክብርና ደረጃ እንዲኖራቸው ወዷል፡፡ እንዲህ ብሏል፡-

﴿ تِلۡكَ ٱلرُّسُلُ فَضَّلۡنَا بَعۡضَهُمۡ عَلَىٰ بَعۡضٖۘ ﴾ البقرة: ٢٥٣

*‹‹እነኚህን መልዕክተኞች ከፊላቸውን ከከፊሉ አስበለጥን፡፡››(አል በቀራህ 253)*

‹‹በእድ›› (ከፊል) የሚለው ቃል አንዳቸውን ተብሎ ተተርጉሟል፡፡ የቃሉ የዓረብኛ ይዘት ይህን መልእክት በውስጡ ሊያካትት ይችላል፡፡ ይህም ማለት ከነብያት መሐከል ለአንዱ ከሌሎች የተለየና የላቀ ደረጃ አላህ ሰጥቶታል ማለት ነው፡፡ የዚህ እድል ባለቤት ደግሞ ያለ ጥርጥር ወዳጃችንና ነብያችን ሙሐመድ ናቸው፡፡

ኢብን አባስ እንዳስተላለፉት አንድ ቀን ሶሐቦች ነቢዩ ሙሐመድንﷺ ተቀምጠው ይጠባበቋቸው ጀመር፡፡ ጥቂት ቆይተውም ነቢዩ መጡ፡፡ ወደ ሰዎቹም ቀረቡ፡፡ ሲነጋገሩም ሰሟቸው፡፡ አንደኛው፡- ‹‹አላህ ከፍጡራን

በኩል ፍጹም ወዳጅ (ኸሊል) ማበጀቱ የሚገርም ነው፡፡ ኢብራሂምን ኸሊል አድርጓቸዋል፡፡›› አለ፡፡ ሌላኛው ደግሞ ‹‹ከዚህ ይበልጥ የሚያስገርመውስ አላህ ሙሳን ማነጋገሩ ነው፡፡›› አለ፡፡ ሌላኛውም፡- ‹‹ኢሳ የአላህ መንፈስ እና ቃሉ ነው፡፡›› አለ፡፡ አራተኛው ሰው፡- ‹‹አላህ አደምን መርጧቸዋል፡፡›› ሲል ተናገረ፡፡ ነቢዩﷺ ሰላምታ አቀረቡላቸውና እንዲህ አሉ፡-

‹‹ወጋችሁን ሰማሁ፡፡ ኢብራሂም የአላህ ኸሊል በመሆኑ መገረማችሁን አደመጥኩ፡፡ በእርግጥ ኢብራሂም እንዳላችሁት ነው፡፡ ሙሳንም ማናገሩ፣ ኢሳም የርሱ መንፈስና ቃሉ መሆኑ እርግጥ ነው፡፡ አደምንም መርጧቸዋል፡፡ አዋጅ፣ እኔ ደግሞ የአላህ ፍጹም ወዳጅ (ሐቢብ) ነኝ፡፡ ለጉራ አይደለም፡፡ በእለተ ቂያማ አደምንና ሌሎችንም ነብያት በስሩ የሚያሰልፈውን የምስጋና አርማ የምሸከመው እኔ ነኝ፡፡ ለጉራ አይደለም፡፡ በእለተ ቂያማ የመጀመሪያው አማላጅና ምልጃውም ቀድሞ ተቀባይነት የሚያገኝለት የመጀመሪያው ሰው እኔ ነኝ፡፡ ይህም ጉራ አይደለም፡፡ የጀነትን በር ዘለበት መጀመሪያ የማንቀሳቅሰው እኔ ነኝ፡፡ ለጉራ አይደለም፡፡ አላህም ይከፍትና እኔንና ከአማኞች መሐል ድሆችን ቀድሞ ያስገባል፡፡ ጉራ አይደለም፡፡ እኔ ከአላህ ዘንድ ከጥንቶቹም ከአሁኖቹም ሁሉ የተላቅኩ ነኝ፡፡ ጉራ አይደለም፡፡›› (ቲርሚዚ እና ዳሪሚ)

የአላህ መልእክተኛﷺ እንዲህም ብለዋል፡-

‹‹እኔ በእለተ ቂያማ የአደም ልጆች ሁሉ አለቃ ነኝ፡፡ ጉራ አይደለም፡፡ የምስጋና አርማም በእጄ ይሆናል፡፡ ጉራ አይደለም፡፡ አደምና ከርሱ በኋላ የተነሱ ነብያት ሁሉ አንዳቸውም ሳይቀሩ ከኔ አርማ ስር ይሰለፋሉ፡፡ ምድር ቀድማ የምትሰነጠቀውም ለኔ ነው፡፡ ጉራ አይደለም፡፡›› (ቲርሚዚ)

የአላህ መልእክተኛﷺ የዚህ ክብርና ልቅና ባለቤት በመሆናቸው ሙእሚኖች የርሳቸው ፍጹም ታዛዥ እንዲሆኑና እያንዳንዱን ተግባራቸውን ለርሳቸው እያቀረቡና ይሁንታቸውን እያገኙ ብቻ የሚሰሩ ያህል እንዲሰማቸው ያሻል፡፡ ለተሸሁድ ሲቀመጡ እንኳ ነቢዩ

ሙሐመድﷺ ከአጠገባቸው የቆሙ ያህል ተሰምቷቸው ለርሳቸው ሰላምታ እንዲያቀርቡ አላህ አዟል፡፡ እንዲህ እንዲሉ ያስተምራል፡-

السلام عليك أيها النبى ورحمة الله وبركاته

‹‹አንተ ነብይ ሆይ፣ የአላህ ሰላም፣ እዝነትና በረከት ይስፈንብህ፡፡››

በሶላት ውስጥ ሆኖ ሰላምታ ማቅረብ ሶላት ያበላሻል፡፡ ለነቢዩﷺ የሚቀርበው ሰላምታ ግን የሶላት አካል ሆኗል፡፡ ኢማም አቡ ሐሚድ አልገዛሊ የዚህን እውነታ ጥበብ ሲያብራሩ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹በተሸሁድ ጊዜ በአደብ ተቀመጥ፡፡ የምትፈጽመው ሶላት እና በጎ ምግባር፣ እንዲሁም መልካም ስነ ምግባር ሁሉ ለአላህ መሆኑን ዓለጽ፡፡ ንግስናም የአላህ መሆኑን ግለጽ፡፡ ‹‹አተህያቱ›› የሚለው ቃል ትርጉም ይህ ነው፡፡ በልቦናህ ታላቁን ነብይﷺ አስባቸውና እንዲህ በል፡-

‹‹አንተ ነብይ ሆይ፣ የአላህ ሰላም፣ እዝነትና በረከት ባንተ ላይ ይስፈን፡፡››

አንተ ካቀረብክላቸው ሰላምታ የተሻለ ምላሽ እንደሚሰጡህ ተስፋ አድርግ፡፡››[1]

ሸኽ ኻሊድ አልበግዳዲ ‹አልመክቱባት› ከተባለው መጽሐፋቸው ውስጥ እንዳሰፈሩት ሸህ ሸሃብ ቢን ሐጀር አል መክይ የተሸሁድን መልእክት ሲያራሩ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹አላህ ለነቢዩﷺ ከኡመታቸው መካከል ሰጋጆችን እንደሚገልጽላቸው ይህ የተሸሁድ ስርዓት ይጠቁማል፡፡ ከሶላታቸው ውስጥ ነቢዩ ተገኝተው፣ በጎ ስራዎችን የሚመለከቱ ያህል ሰጋጆቹ እንዲሰማቸው ይፈለጋል፡፡ ይህ ስሜት ለተጨማሪ ተመስጦና መተናነስ ይረዳል፡፡››[2]

---

[1] ኢህያእ ዑሉሙዲን 1/224

[2]

ነቢዩ ሙሐመድﷺ ከአላህ ዘንድ ከማንም በላይ የተላቁ፣ ይበልጥ ተወዳጅ ፍጡር በመሆናቸው የዚህችም ሆነ የመጭው ዓለም ጌጥ፣ ለሰው ልጆች በዱንያ ቅኑን ጎዳና መሪያቸው፣ በአኼራ ደግሞ አማላጃቸው ናቸው፡፡ ሁሉም ነብያት የነቢዩ ሙሐመድን ታላቅነት አውቀዋል፡፡ ልእልናቸውን ተረድተዋል፡፡ ሙሳ የነቢዩ ሙሐመድን በረከትና ችሮታ ያገኙ ዘንድ የርሳቸው ተከታይ መሆንን ተመኝተዋል፡፡ ቀታዳ ቢን ነውማን እንዳስተላለፉት ነቢዩ ሙሣ እንዲህ ማለታቸው ተዘግቧል፡-

‹‹ሙሳ፡- ጌታዬ ሆይ፣ በመልካም የሚያዙና ከመጥፎ የሚከለክሉ ኡምማ እንደሚወጡ አውቋያለሁ፡፡ የኔ ሕዝብ አድርጋቸው አሉ፡፡ አላህም፡- እነርሱ የሙሐመድ ተከታዮች ናቸው፣ አለ፡፡››

ጌታዬ ሆይ፣ በመጨረሻ ተፈጥረው በመጀመሪያ ጀነት የሚገቡ ሕዝቦችን (አንተ ከሰጠህኝ) ሰሌዳዎች አይቻለሁ፡፡ የኔ ኡመት አድርጋቸው አሉ፡፡ ‹‹የሙሐመድ ኡመት ናቸው፡፡› አላቸው፡፡

ጌታዬ ሆይ፣ ኪታባቸውን በልቦናቸው አጥንተው የሚያነብቡ ኡመት አይቻለሁ፡፡ ቀደምት ሕዝቦች ግን መጽሐፋቸውን እያዩ ነበር የሚያነብቡት፡፡ እናም እነርሱ ሲወገዱ የመጽሐፍቱ መልእክትም አብሮ ይወገዳል፡፡ ለነዚህ ግን ከሌሎች በተለየ ሁኔታ የማስታወስ ችሎታ እንደሰጠሃቸው አውቄያለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ፣ የኔ ኡመት አድርጋቸው፣ አሉ፡፡ ‹‹እነዚህ የሙሐመድ ኡመት ናቸው›› አላቸው፡፡

ጌታዬ ሆይ፣ በመጀመሪያውና በመጨረሻውም መጽሐፍ የሚያምኑ፣ የጥመትን ሐይል የሚጋፈጡ፣ ሐሳዊ እና አንድ አይና የሆነውን ደጃልን ሳይቀር የሚዋጉ ሕዝቦችን ከሰሌዳዎች ውስጥ አግኝቻለሁ፡፡ የኔ ተከታዮች አድርጋቸው፣ አሉ፡፡ ‹‹እነርሱ የሙሐመድ ተከታዮች ናቸው፡፡›› አላቸው፡፡

ምጽዋታቸውን ለድሃ መግበው ምንዳውን የሚያገኙ ሕዝቦችን ከሰሌዳዎች ውስጥ አግኝቻለሁ፡፡ ቀደምት ሕዝቦች ምጽዋታቸው

ተቀባይነት ስታገኝ አላህ እሳት በመላክ እንድትበላው ያደርግ ነበር፡፡ ተቀባይነት ካላገኘችም እንዲሁ ትተዋለች፡፡ አውሬዎችና አዕዋፋትም ይመገቧት ነበር፡፡ ከነዚህ ግን አላህ ከሐብታሞቻቸው ምጽዋት ይዞ ለድሆቻቸው ይሰጣል፡፡ አምላኬ ሆይ፣ የኔ ኡመት አድርጋቸው፣ አሉ፡፡ ‹‹እነዚህ የሙሐመድ ኡመት ናቸው›› አላቸው፡፡ አምላኬ ሆይ፣ ከመካከላቸው ደግ ነገር ለመስራት አስቦ ሳይሰራው የቀረ አንድ ምንዳ የሚጻፍለትን፣ ከሰራው ደግሞ ከአስር እስከ ሰባት መቶ እጥፍ የሚከተብለትን ሕዝቦች ከሰሌዳዎች ውስጥ አግኝቻለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ፣ የኔ ኡመት አድርግልኝ፣ አሉ፡፡ ‹‹እነዚህ የሙሐመድ ኡመት ናቸው›› ተባሉ፡፡

በዚህ ጊዜ ነቢዩላህ ሙሣ ሰሌዳዎችን ወረወሩና እንዲህ አሉ፡-

‹‹አላህ ሆይ፣ የሙሐመድ ተከታይ አድርገኝ››[1]

እያንዳንዱ ነብይ የነቢዩ ሙሐመድንﷺ መምጣት ለተከታዮቹ አብስሯል፡፡ በመጨረሻም ይጠበቅ የነበረው ታላቅ ብርሃን በ671 ዓ.ል በወርሃ ረቢአል አወል 12ኛ ቀን በእለተ ሰኞ ለዓለም ተገለጸ፡፡ በዚህ ክስተት ሁሉም ዘመናትና ቦታዎች ልቅናን ተቸሩ፡፡

የርሳቸውን ይፋ መሆን ተከትሎ የአላህ ረህመት ተንቧቧ፡፡ መጠኑም በዓለም ውስጥ ጨመረ፡፡ የምሽትና የንጋት ቀለሞች ተለወጡ፡፡ በምድራችን ላይ ጥልቅ እና ልዩ ስሜት ነገሰ፡፡ አንደበቶች ተናነሱ፡፡ ሁሉም ነገር የተለየ ትርጉምና ውጤትን ተጎናጸፉ፡፡ ጣኦታት ረገፉ፡፡ የፋርስ ቤተ መንግስት ምሰሶዎች ተሰባበሩ፡፡ የሳዋ ሐይቅ ገነፈለ፡፡ቀልቦች በበረከት ተሞሉ፡፡ ጻእዳነትንም ተቸሩ፡፡ ይህ በረከት መላ ዩኒቨርሱን አጠቃለለ፡፡ በየትኛውም ቦታና ዘመን የሚገኙ ፍጡራንን ሁሉ አካተተ፡፡

ይህች ዓለም ነቢዩን ባትታደል ኖሮ የሰው ልጅ በጽልመት ውስጥ እስከ እለተ ቂያማ ድረስ ይቆይ ነበር፡፡ ደካሞች የባለ ጸጎች ምርኮኛ ሆነው ይቀጥሉ ነበር፡፡ ክፋት በበጎነት ላይ ድል በተቀዳጀ ነበር፡፡ ዱንያን

[1] ኢብን ከሲር ለአዕራፍ 154 ከሰጡት ማብራሪያ የተወሰደ፡፡

ባለጌዎችና አምባገነኖች በተቆጣጠሯት ነበር፡፡ ጣኦታትን የሰባበሩት ፍትህን በምድር ላይ ያነገሱትና በደልን ከልቦናዎች ላይ ያስወገዱት ነብይ መምጣታቸው ታላቅ ጸጋ እና ውለታ መሆኑ ይሰማን ዘንድ ጀላሉዲን ሩሚ እንዲህ ሲሉ ጽፈዋል፡-

‹‹የዚህ ዘመን ሙስሊሞች ሆይ፣ በነቢዩ ሙሐመድ ትግል፣ ወኔና የላቀ ዓላማ ጣኦታት ባይሰባበሩ ኖሮ አንተም እንደ አጎቶችህ ጣኦት አምላኪ በሆንክ ነበር፡፡››

ከስልጣኔ ከራቀ መሐይም ሕዝብ መካከል የወጡት እኒህ ያልተማሩ ነብይ በዘመናቸው የነበሩ ሰዎችን ሁሉ በእውቀትና በጥበብ መብለጥ ብቻ ሳይሆን እስከ እለተ ቂያማ ድረስ ማንም ሊፈጽመው የማይችለውን ታላቅ ተአምር ፈጽመዋል፡፡ እርሱም የቁርአን ተአምር ነው፡፡

ቁርአን ጥንት የተከሰቱ ታሪኮችን አውግቷል፡፡ ወደፊት የሚከሰቱ ትንቢቶችን ተናግሯል፡፡ ከ14000 ዓመታት ጀምሮ እርሱን የሚያስተባብል መረጃ ማቅረብ የቻለ አንድም ሰው የለም፡፡ ግና በአሁኑ ሰአት የሚገኙ እውቅ ኢንሳይክሎፒዲያዎች በየዓመቱ እንደገና ሲታረሙና አዳዲስ ነገሮችን እያካተቱ ሲታተሙ እናያለን፡፡

ይህ ነብይ ከአንድም ሰው ትምህርት አልቀሰሙም፡፡ የሰውን ልጅ ከውድቀት ሊታደጉ፣ የሩቅ ሚስጥሩ ዓለም ቃል አቀባይ፣ የሐቅ ትምህርት ቤት ታላቅ አስተማሪ ሆነው መጡ፡፡

ሙሣ የተወሰኑ ሕግጋትን አስተምረዋል፡፡ ዳውድ መሳጭ ዱዓዎችን አስተላልፈዋል፡፡ ኢሳ ለሰው ልጅ በጎ ስነ ምግባር ሊያስተምሩ ተልከዋል፡፡ የነቢዩ ሙሐመድﷺ ተልእኮ ግን ይህን ሁለቱ ያካትታል፡፡ ሕግጋትን አስተማሩ፡፡ በጎ ስነ ምግባርን ገለጹ፡፡ ነፍስን የማጽዳትን ስልት አሳወቁ፡፡ አላህን በንጹህ ልቦና የመለመንን ጥበብ ዘከሩ፡፡ የመልካም ስብእና አርአያ ሆነው አሳዩ፡፡ ጠፊ በሆነችው በዚህች ዓለም መሸንገልን አስጠነቀቁ፡፡ በጥቅሉ የሁሉንም ነብያት ዓላማና ተግባር

አካተዋል፡፡ የስብእናዎቻቸውን ሁሉ ገጽታ ይበልጥ ምሉእና ውብ በሆነ አኳኋን ይዘዋል፡፡ የደስታና የስኬት መሠረቶችን ሁሉ አስተምረዋል፡፡

የአላህ መልእክተኛﷺ በጃሂልያ ማሕበረሰብ ውስጥ ለአርባ አመታት ኖሩ፡፡ እርሳቸው ያስተምሯቸውና ይሰብኳቸው የነበሩ የመልካም ስብእና እሴቶች ለዚያ መሐይም ማሕበረሰብ እንግዳ ነገሮች ነበሩ፡፡ ነቢዩ ከነብይነታቸው በፊት በመንግስት መሪነት ወይም በተናጋሪነት አይታወቁም፡፡ የጦር መሪ መሆን ቀርቶ በተራ ወታደርነት እንኳ አልተሳተፉም፡፡

አርባ ዓመት ሲሞላቸው ግን ሁለንተናቸው በድንገት ተቀየረ፡፡ በሁሉም የሕይወት መስክ የክሕሎትን ዙፋን ተቆናጠጡ፡፡ የሰብአዊነትን ዳርቻ ደረሱ፡፡

ከዚህ እድሜ በፊት ስለ ጥንት ሕዝቦች ታሪክ፣ ስለ ጀነት እና እሳት ከአንድም ሰው አልሰሙም፡፡ ለራሳቸው ግን ከስብእና መቋሸሽ የጸዳ ንጹህ ሕይወት ይመሩ ነበር፡፡

ከሂራእ ዋሻ ይህን ትልቅ መለኮታዊ ተልእኮ ይዘው ከተመለሱ በኋላ ግን ይህ ሁሉ ተለወጠ፡፡ ጥሪያቸውን ሲጀምሩ መላ አረቢያ በግርምትና በፍርሃት ተናጠ፡፡ እጅግ የሚያስደምመው የነቢዩ ንግግር መሰጣቸው፡፡ የግጥምና የቋንቋ ክሕሎት ውድድሮች ሁሉ ትርጉም አጡ፡፡ በጊዜው በሚደረጉ ውድድሮች ያሸነፉ ገጣሚያን ስራዎች ከካእባ ግድግዳ ላይ መንጠልጠላቸው ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ በዓረቦች ባህል ቢሆንም ከቁርአን በኋላ ግን ግጥሙን ከካእባ ላይ ለማንጠልጠል የሚደፍር ገጣሚ ታጣ፡፡ ምክንያቱም የቁርአን እጅግ መሳጭ አወቃቀር ገጣሚያንን ሁሉ የሚያስንቅ፣ ስራዎቻቸውን የሚያስከነዳ ሆነና ነው፡፡ በዚህ ረገድ ተከታዩ ታሪክ ይጠቀሳል፡፡ የእውቁ ገጣሚ የእምሩአል ቀይስ እህት ተከታዩን የቁርአን አንቀጽ በሰማች ጊዜ የወንድሟ ግጥም ከካእባ ላይ እንዳይንጠለጠል እንዲህ በማለት መልሳለች፡-

‹‹የወንድሜ ግጥም ከካእባ ግድግዳ ላይ መንጠልጠሉ ፋይዳ የለውም፡፡ ምክንያቱም (የሙሐመድን) ቃል ሊፎካከር የሚችል ግጥም አይኖርምና፡፡››

ይህን እንድትል ያስገደዳትን አንቀጽ እነሆ፡-

﴿ وَقِيلَ يَٰٓأَرۡضُ ٱبۡلَعِي مَآءَكِ وَيَٰسَمَآءُ أَقۡلِعِي وَغِيضَ ٱلۡمَآءُ وَقُضِيَ ٱلۡأَمۡرُ وَٱسۡتَوَتۡ عَلَى ٱلۡجُودِيِّۖ وَقِيلَ بُعۡدٗا لِّلۡقَوۡمِ ٱلظَّٰلِمِينَ ٤٤ ﴾ هود: ٤٤

*‹‹ከዚያም፡- "ምድር ሆይ! ውሃሽን ምጠጪ። ሰማይ ሆይ! (ዝናብሽን) ያዢ" የሚል ትእዛዝ ተላለፈ። ውሃውም ሰረገ። (የአላህ) ትእዛዝም ተፈጻሚ ሆነ። (መርከቢም) ጁዲይ (ከተባለ ጋራ) ላይ ተደላደለች። "በዳዮች ሕዝቦች (ከአላህ እዝነት) ይራቁ።" ተባለም። (ሁድ 44)*

ይህች ሴት ከካእባ ላይ በግንባር ቀደምትነት ተሰቅሎ የነበረውን የወንድሟን ግጥም አወረደች፡፡ ሌሎች ሰባት ገጣሚያንም የርሷን አርአያነት በመከተል ግጥሞቻቸውን አወረዱ፡፡[1]

የአላህ መልእክተኛﷺ ለሰው ልጅ በምድር ላይ የአላህ ወኪል (ኸሊፋ) የመሆንን ትክክለኛ ትርጉም አስተምረዋል፡፡ በማሕበራዊ፣ በባህላዊ፣ በኢኮኖሚያዊ፣ በአስተዳደር በዓለም አቀፍ ግንኙነትና በሌሎችም የሕይወት መስኮች ሁሉ እጅግ ድንቅና ምሉእ የሆኑ መርሆዎችን አኑረዋል፡፡ እነዚህ መርሆዎች ታላላቅ ሊቃውንት እድሚያቸውን በምርምር ካሳለፉ እና ከብዙ ዓመት በኋላ የደረሱባቸው ናቸው፡፡ የሰው ልጅ በእውቀትና በተሞክሮ እያደገ በሄደ ቁጥር የነቢዩ ሙሐመድንﷺ ታላቅነት የበለጠ እየተረዳ እንደሚሄድ ጥርጥር የለውም፡፡

ነቢዩ ሙሐመድﷺ ከነብይነታቸው በፊት በጦርነት ከአንድ ጊዜ በላይ አልተሳተፉም፡፡ እዚህም ላይ ቢሆን ተመልካች እንጅ ተዋጊ አልነበሩም፡፡ በኋላ ላይ ግን ምንም ዓይነት ወታደራዊ ትምህርት ሳይወስዱ የተዋጣላቸው የጦር መሪ፣ ጀግና ተዋጊ ለመሆን በቁ፡፡ በወሳኝ ጦርነቶች

---

[1] አህመድ ጀውደት ባሻ፣ ቀሶሱል አንቢያእ፣ ፈታዋ ወተዋሪኹል ኹለፋእ፣ እስታንቡል 1976 ቅጽ 1 ገጽ 83

ላይ በግንባር ቀደምትነት ተሳተፉ፡፡ ተውሂድንና ማሕበራዊ ተሐድሶን ለማስፈን አስቸጋሪ ውጊያዎችን አደረጉ፡፡ እዝነታቸው የሰውን ልጅ ባጠቃላይ የሚያደርስ ከመሆኑ ጋርም በዚህ መስክም የተዋጣላቸው ሆኑ፡፡

ነቢዩﷺ የአላህን ዲን ለሰዎች ለማድረስ በሮችን አንኳኩተዋል፡፡ ጥሪያቸውን ያልተቀበሉትና በራቸውን የዘጉት፣ ብርሃኑ እንዳይደርሳቸው በመፍራት ራሳቸውን ከዘልዓለማዊ ጨለማ ውስጥ ዘግተው የቆለፉት እድለ ቢሶች ብቻ ናቸው፡፡

አንዳንዶቹ ቀልባቸው ከመድረቁ የተነሳ በነቢዩ ላይ ጨከኑ፡፡ ግና በርሳቸው ላይ ባሳዩት ጭካኔ ሳይሆን በመሐይምነታቸው የነቢዩ ልብ ይነካ ነበር፡፡ እንዲህ ይሏቸውም ነበር፡-

﴿ قُلْ مَآ أَسْـَٔلُكُمْ عَلَيْهِ مِنْ أَجْرٍ وَمَآ أَنَا۠ مِنَ ٱلْمُتَكَلِّفِينَ ﴿٨٦﴾ ﴾ ص: ٨٦

*በላቸው፡- "ለዚህ (መልዕክቴ) ምንም ዓይነት ክፍያ አልጠይቃችሁም፡፡ ከአስመሳዮችም አይደለሁም፡፡" (ሷድ 86)*

ይህም ማለት ነቢዩﷺ በዳእዋቸው የፈለጉት የአላህን ውዴታ እንጅ ሌላ ነገር አይደለም፡፡ በወታደራዊ መስክም ብዙ ጊዜ የጠላትን ሲሶ የሚመጥን ሰራዊት ይዘው እጅግ አስደናቂ ድሎችን ተቀዳጅተዋል፡፡ ስርዓት አልባ ዜጎችን ወታደራዊ ስርዓት አስተምረው፣ መንፈሳዊ ጉልበት አስታጥቀው እጅግ ኢምንት በሆነ የሕይወትና የንብረት ኪሣራ አገሮችን አቅንተዋል፡፡ የያኔዎቹን ሐያላን፣ የፋርስና የሮም ኢምፓየሮችን በአስገራሚ ሁኔታ በማሸነፍ የማይረሱት ትምህርት ሰጥተዋል፡፡

ነቢዩ በዚህ መልክ እጅግ ፈታኝ እና አሉታዊ በሆነ ሁኔታ ውስጥ ሆነው በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ አቻ የማይገኝለትን አብዮት አካሂደዋል፡፡ ተበዳዮችን ታድገዋል፡፡ የደካሞችን እንባ አብሰዋል፡፡ የተባረኩ እጆቻቸው

የየቲሞችን ራሶች ይዳብሱ ነበር፡፡ የእዝነታቸው ብርሃን ከልቦና ውስጥ የሐዘንን ጽልመት ይገፍ ነበር፡፡

የነቢዩﷺ ሐይማኖት በግዙፍ ውቅያኖስ ይመሰላል፡፡ የሌሎች ነቢያት ትምህርት ደግሞ ከዚህ ውቅያኖስ በሚፈሱ ወንዞች ይመስላሉ፡፡ ከርሳቸው በፊት እንደተላኩ የተነገረላቸውን የ124 ሺህ ነብያትን ልዩ ባህሪያት ነቢዩﷺ እጅግ በተዋጣለትና በደመቀ መልኩ ይዘዋል፡፡ ስለዚህም እስከ እለተ ቂያማ ድረስ የሚመጡ የሰው ልጆች የሚፈልጉትን የስብእና ምጥቀት በማካተት ***‹‹ተምሳሌታዊና ልዩ ስብእና››*** ለመሆን በቅተዋል፡፡ ይህም በመሆኑ ነው ***‹‹የመጨረሻው ዘመን ነብይ››*** ተደርገው ለሰው ልጆች ባጠቃላይ የተላኩት፡፡

የአላህ መልእክተኛﷺ ባህሪያቸውንና ተልእኳቸውን ባጭሩ ሲገልጹ፡- ‹‹እኔ የተላክኩት መልካም ስነ ምግባራትን ለማሟላት ነው፡፡›› (ሙወጠእ)

በመጨረሻም ነቢዩ ሲሞቱ ቁሳዊ ውርስ አልተውም፡፡ ለሰው ልጆች ትተውት ያለፉት ትልቁ ውርሳቸው ታላቅ ስብእናቸውንና ስነ ምግባራቸውን ብቻ ነው፡፡

## መልካም አርአያ

እያንዳንዷ የሕይወት እንቅስቃሴያቸው በዝርዝር የተጻፈ ብቸኛው ስብእና ነቢዩ ሙሐመድﷺ ብቻ ናቸው፡፡ ሌሎች ነብያት በባህሪያቸው የሰውን ልጅ ወደ ሐቅ ጎዳና የሚመራ ተምሳሌታዊ ስብእና ይላበሳሉ፡፡ መልካም ድርጊታቸው እስካለንበት ዘመን ድረስ ከትውልድ ትውልድ በተወሰነ ደረጃ ሲሸጋገር ኖሯል፡፡ የመጨረሻው ዘመን ነብይ ግን የሕይወታቸውን እያንዳንዷን ቅጽበት፣ ከትንሽ እስከ ትልቅ፣ እያንዳንዷን ንግግራቸውንና ተግባራቸውን ቁልጭ አድርጎ በሚያሳይ መልኩ ልቅም ተደርጎ ተመዝግቦ ለትውልድ ተላልፏል፡፡ ሕይወታቸው ኢምንት ክፍሉ ሳይዘነጋ ተጽፏል፡፡ እርሳቸው ከኖሩበት ዘመን አንስቶ እስካለንበት ዘመን ድረስም

ትውልዶች ተቀባብለውታል፡፡፡ ቅብብሎሹ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሳይቋረጥ ይቀጥላል፡፡

የሕይወትን ፈተናዎች ለመከላከልና ለመቋቋም የነቢዩን ﷺ የተላቁ ባህሪያት ልንላበስ ግድ ይላል፡፡ ለምሳሌ አመስጋኝነት (ሹክር)፣ በአላህ መመካት (ተወኩል)፣ የአላህን ውሳኔ በጸጋ መቀበል፣ መከራ ሲመጣ መታገስ፣ ቆራጥነት፣ ጀግንነት፣ መስዋእትነት፣ ከእጅ ባለ ነገር መብቃቃት፣ የቀልብ ሐብታምነት፣ ለሌሎች ደህንነትና ደስታ መስራት፣ ቸርነት፣ ተዋዱእ፣ በሕይወታችን ውስጥ የሚያጋጥሙ ክስተቶችን በጽናት መዋጋትና መሰል ባህሪያትን መላበስ አስፈላጊ ነው፡፡

በነዚህ ባህሪያት ሕያው ተምሳሌት እናገኝ ዘንድ አላህ ለሰው ልጆች አንድ ትልቅ ስጦታ አበርክቷል፡፡ አዋጅ፣ ይህ ስጦታ ድንቅና ንጹህ በሆነ ተምሳሌታዊ ሕይወታቸው ወደ ቅን ጎዳና የሚመሩት የአላህ መልእክተኛ ﷺ ናቸው፡፡

የነቢዩ ሕይወት ﷺ ለመጭዎቹ ትውልዶች ሁሉ እስከ እለተ ቂያማ ድረስ ተምሳሌት ሆኖ ይቀጥላል፡፡ አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿ وَإِنَّكَ لَعَلَىٰ خُلُقٍ عَظِيمٍ ﴾ القلم: ٤

*‹‹አንተ የላቀ ሥነ-ምግባር ባለቤት ነህ፡፡›› (አል ቀለም 4)*

የመልእክተኛው ﷺ ስብእናና የተባረከ መመሪያቸው ለሁሉም የሰው ልጅ ሕይወት መስኮች ተምሳሌት ነው፡፡ የሰው ልጅ ሊደርስባቸው የሚችሉ የስብእና የመጨረሻ ምጥቀቶችን ያመለክታሉ፡፡ የአላህ መልእክተኛ ﷺ ራሳቸው ከሰዎች መሐል በሕይወት በመኖር በእያንዳንዱ የሕይወት ዘርፍ የመጠቀ ባህሪ ምሳሌ ሆነው አሳይተዋል፡፡

አላህ የነቢዩን ስብእና -በቁርአን አገላለጽ- ***መልካም አርአያ (ቁድዋ ሐሰናህ)*** ይሆኑ ዘንድ አደራጅቶ ለሰው ልጆች አበርክቶታል፡፡ አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿ لَّقَدْ كَانَ لَكُمْ فِي رَسُولِ اللَّهِ أُسْوَةٌ حَسَنَةٌ لِّمَن كَانَ يَرْجُو اللَّهَ وَالْيَوْمَ الْآخِرَ وَذَكَرَ اللَّهَ كَثِيرًا ﴿٢١﴾ ﴾ الأحزاب: ٢١

*‹‹የአላህ መልዕክተኛ፥ (ከመካከላችሁ) አላህንና መጭውን ዓለም ተስፋ ለሚያደርግ፥ አላህንም በብዛት ለሚያወሳ፥ መልካም አርአያ ነው፡፡›› (አል አህዛብ 21)*

የነቢዩ ሙሐመድﷺ እያንዳንዱ የሕይወት ገጽታ የምሉእነትን፣ የምጥቀትን እና የውበትን ዳርቻ የደረሰ ነው፡፡ ይህም በመሆኑ ሰዎች ከነቢዩ ሙሐመድ ሕይወት ውስጥና ከአንጸባራቂ ሱንናቸው የተሟላና ምሉእ ትምህርት ያገኛሉ፡፡ ከስብእናቸው ገጽታዎች አንዱን በመምረጥ ለመከተል በጥቅል ወይም በዝርዝር ቀርቦላቸዋል፡፡

የአላህ መልእክተኛﷺ በሐይማኖት መሪነት አርአያ ናቸው፡፡ በርእሰ ብሔርነት አርአያ ናቸው፡፡ በመለኮታዊ ፍቅር አርአያ ናቸው፡፡ አንዳች ጸጋ ሲያገኙ አላህን በማመስገን እና በመተናነስ አርአያ ናቸው፡፡ በመከራ ጊዜና አጋጣሚዎች በመታገስ አርአያ ናቸው፡፡ በቸርነት እና ከአለማዊ ጸጋዎች በላይ በመሆን አርአያ ናቸው፡፡ ለቤተሰቦቻቸው፣ ለደካሞች፣ ለአገልጋዮችና ለሌሎችም የሕብረተሰብ ክፍሎች በማዘን አርአያ ናቸው፡፡ ጥፋተኞችን ይቅር በማለት አርአያ ናቸው፡፡

ሐብታም ሰው ከሆንክ የርሳቸውን የትህትናና የቸርነት ባህሪ አስታውስ፡፡ መላ አረቢያን በፍቅር አስተሳስረዋል፡፡ ታላላቅ እና እውቅ ሰዎችን በፍቅር ወደርሳቸው መርተዋል፡፡

የተራው የሕብረተሰብ ክፍል አባል ከሆንክም ከርሳቸው ሕይወት አርአያነትን ታገኛለህ፡፡ መካ ውስጥ በጣኦት አምላኪያን በግፍ የተሞላ አገዛዝ ስር ኖረዋል፡፡

ድል አድራጊ የጦር መሪ ከሆንክም ጠላቶቻቸውን በጀግንነት ከተፋለሙትና በበድር፣ በሁነይንና በሌሎችም የጦር ግንባሮች አንጸባራቂ ድል ካስመዘገቡት ከነቢዩ ሙሐመድﷺ ሕይወት አርአያነትን ታገኛለህ፡፡

ሽንፈት ከገጠመህም በኡሁድ ዘመቻ የሞቱና የቆሰሉ ባልደረቦቻቸውን እየተዘዋወሩ ካጽናኑት፣ በፍጹም ጀግንነትም የጦርነቱን ሚዛን ከለወጡት ከነቢዩ ሙሐመድ ﷺ ሕይወት ውስጥ የትእግስትና የጀግንነት አርአያነትን ታገኛለህ፡፡

መምህር ከሆንክም መለኮታዊ ትእዛዛትን ስላስተማሩት፣ በመስጊዳቸው ውስጥ የነበሩ የአስሐበ ሶፋ ድሆችን በበረከት ስለሞላው ስሜተ ስስና አዛኝ ቀልባቸው አስብ፡፡

ተማሪ ከሆንክም ወህይ ይዞላቸው ከሚመጣው ከጅብሪል ፊት በአደብና በጥንቃቄ ተቀምጠው ይማሩ የነበሩትን ነቢዩ ሙሐመድን ﷺ አስብ፡፡

ሰዎችን የሚመክርና የሚገስጥ ሰባኪ ከሆንክም በነቢያዊው መስጊድ ውስጥ ንግግሮችን ያደርጉ የነበሩትን ነቢዩ ሙሐመድን ﷺ በእዝነ ሕሊናህ አድምጥ፡፡

ሐቅን የያዝክና ለርሱ ተሟጋች ሆነህ ረዳት ካላገኘህም መካ ውስጥ ከግፈኞች ፊት ቆመው ወደ ሐቅ የጠሯቸውን እና ያለ አንዳች ረዳት ይህን ያደረጉትን የነቢዩ ሙሐመድን ﷺ ሕይወት አስብ፡፡

ጠላትን ማሸነፍና ሐይሉን ማንኮታኮት፣ ሐሰትን መጣልና ሐቅን ማንገስ ከከጀልክም የነቢዩን ተምሳሌትነት አስተውል፡፡ መካን በድል በከፈቱ ጊዜ ድል አድራጊ መሪ ነበሩ፡፡ ይህም ሆኖ ግን በዚህ ቅጽበት አምላካቸውን አልረሱም፡፡ አመስጋኝ ባሪያው ነበሩ፡፡ እናም ከግመላቸው ጀርባ ላይ በትህትና ተቀምጠው፣ አንገታቸውን ደፍተው ወደ ተቀደሰው የሐረም መስጊድ ገቡ፡፡

ገበሬ ከሆንክና ስራህን በአግባቡ ለማከናወን ከከጀልክ የነቢዩን የግብርና ሕይወት ገጽታ አስተውል፡፡ በኒ ነድር፣ ፈድክና ኸይበር በተሰኙ ቦታዎች መሬት ነበራቸው፡፡ ለቦታው ብቁ የሆኑ ሰዎችን በመቅጠር መሬታቸውን በወጉ አልምተዋል፡፡

ረዳት አልባ ብቸኛና ባይተዋር ከሆንክም የአሚናና የአብደላህ የዓይን ማረፊያ የነበረውን የቲም ሕጻን (ሙሐመድን) አስብ።

ወጣት ከሆንክም ለአጎታቸው አቡ ጧሊብ በመካ ፍየል ይጠብቁ የነበሩትን ንጹህና መልካም ወጣት ሙሐመድን አስተውል። ነጋዴም ከሆንክ ወደ ሻምና ወደ የመን ከሚያቀኑ ቅፍለቶች ጋር ለንግድ የወጣውን የብርቅዬ ስብእና ባለቤት በልቦናህ አስብ።

ዳኛም ከሆንክ የነቢዩን ፍትሃዊና ብልህ ስብእና አስብ። በተለይም የመካ መሪዎች ሐጀረል አስወድን ከካእባ ላይ ማን ነው የሚያስቀምጠው በሚለው ሐሳብ ዙሪያ በተወዛገቡ ጊዜ የሰጡትን፣ ታላቅነታቸውንና በጥበብ የከበረ ስብእናቸውን የሚያጎላውን ፍርድ አስብ። ከነቢያዊው መስጊድ ውስጥ ተቀምጠው ሃብታም ከድሃ ሳያበላልጡ ይሰጧቸው የነበሩ ፍትሃዊ ብይኖችን አስታውስ።

ባልም ከሆንክ በዚህ ረገድ ያስተላለፏቸውን የተባረኩ መመሪያዎች አጢን። ለባለቤቶቻቸው የነበራቸውን የጥንቃቄ ስሜትና እዝነት መርምር።

አባት ከሆንክም የፋጡማ አባት፣ የሐሰንና የሑሰይን አያት እንደመሆናቸው በዚህ መስክ ከነበራቸው ድንቅ የአባትነት ስብእና ትምህርት ቅሰም።

ምንም ሁን ምን ከነቢዩ ስብእና መልካም አርአያነትን፣ የተሟላ መመሪያን፣ አንጸባራቂ ተምሳሌትነትን ለራስህ ታገኛለህ።

እርሳቸው መሪህ ስለሆኑ ድርጊትህን በድርጊታቸው መዝንና ስህተትህን አርም። ሱንናቸውን በመከተል ተግባሮችህን ሁሉ አስተካክል። በርሳቸው ብርሃንና አመራር ጥላ ስር የሕይወትን እንቅፋቶች ሁሉ ታልፋለህ። እውነተኛ ደስታም ታገኛለህ።

የሕሊናና የቀልብ አጸዳቸው የተለያዩ ቀለማት ባላቸውና ሽታቸው በሚያውዱ ልዩ ልዩ አበቦች እንደተሞላ አጸድ ማለት ነው። የነቢዩﷺ ሕይወት በተለያየ የማሕበረሰብ እርከን ላይ ለሚገኙ ሰዎች ሁሉ

ተምሳሌት እንደሆነ አይተናል፡፡ በአንጻሩ በሌሎች ሰዎች ስብእና ውስጥ ይህ አይስተዋልም፡፡ ለምሳሌ የገዥዎች ሕይወት ለተገዥዎች፣ በድሎት የተከበበ ሐብታም ሕይወት በድህነት ለሚሰቃይና የእለተ ጉርስ ለማግኘት አሳሩን ለሚያይ ባተሌ አርአያ ሊሆን አይችልም፡፡

የነቢዩ ሙሐመድﷺ ሕይወት ግን ከተቃራኒ ጫፍ ላሉ ወገኖች ሁሉ አርአያ ይሆናል፡፡ ምክንያቱም አላህ ሕይወታቸውን በየቲምነት አስጀምሮታል፡፡ የቲምነት በሰው ልጅ ማሕበራዊ ሕይወት ውስጥ የደካማነት ጥግ ነው፡፡ በመጠቀልም የሕይወትን የተለያዩ እርከኖች ደረጃ በደረጃ እየረገጡ ከላይኛው ጫፍ ላይ እንዲደርሱ አደረጋቸው፡፡ እርሱም የመንግስት ርእሰ ብሄርነት እና ነብይነት ነው፡፡ ነቢዩ ሙሐመድﷺ ያሳለፏቸው የሕይወት እርከኖች ለእያንዳንዱ የሕይወት ውጣ ውረድ አርአያ በሚሆኑ ተምሳሌታዊ የባህሪያት የከበሩ ናቸው፡፡ ስለዚህም አንድ ግለሰብ ማሕበራዊ ደረጃውና ቦታው ምንም ይሁን ምን ከነቢዩ ሙሐመድﷺ ሕይወት ይማራል፡፡ ሰዎች እንደየ አቅማቸው ሊከተሉት እና ሊተገብሩት የሚችሉት የተሟላ መልካም አርአያ በነቢዩ ሕይወት ውስጥ ያገኛል፡፡

ነቢዩ አላህ ለሰው ልጆች ያበረከታቸው ታላቅ ጸጋ፣ ወደር የለሽ ስጦታ፣ አስደናቂ ተአምር ናቸው፡፡ ከዝቅተኛው የሕብረተሰብ ክፍል ጀምሮ እስከ ከፍተኛው ድረስ ለእያንዳንዱ የሕይወት እርከንና ዘመን ተምሳሌት ሊሆኑ የሚችሉ አንጻባራቂ ስብእና ናቸው፡፡ ልዩ የሆነ ስብእናቸውን በአርአያነት ለሚከተሉ ሙእሚኖችም የስራዎቻቸው መለኪያ ሚዛን ናቸው፡፡

ለሰው ልጅ የሐሴትን አቅጣጫ እናመለክታለን የሚሉ፣ ራሳቸውንም ለሰው ልጅ በተምሳሌትነት ያቀረቡ ወገኖች ሁሉ፣ በተለይም ሁሉንም ነገር በደካማ አእምሯቸው ለማብራራት የሞከሩ ፈላስፎች በዚህ ረገድ በጣም ደካማ ናቸው፡፡ ነብያትና የነርሱን ፈለግ የተከተሉ ደጋግ ሰዎች ሲቀሩ፡፡ ምክንያቱም ነብያት መነሻቸው መለኮታዊ መልእክት ነውና፡፡ አምላካዊ መመሪያ ይዘው መጥተዋል፡፡ ይህም መመሪያ

እውነተኝነታቸውን ያረጋግጣል፡፡ አምላካዊውን ትእዛዝና ድንጋጌ አድርሰዋል፡፡ ሁሌም የሚሉት፡- ‹‹አምላክ ይህን አዟል›› ነው፡፡ በአንጻሩ ፈላስፎች ዓላማቸው የሰውን ልጅ ወደተሻለ አቅጣጫ መምራት ቢሆንም አምላካዊ እገዛ በሚጎድለውና የስሜታቸው ተከታይ በሆነ ደካማ አእምሯቸው ብቻ ስለሚወሰኑ እይታቸው የግለሰብ አስተያየት ከመሆን አያልፍም፡፡ ‹‹እኔ እንዲህ አስባለሁ፣ ለኔ እንዲህ ይታየኛል፡፡›› ከማለት ሌላ አማራጭ የላቸውም፡፡ ከዚህም የተነሳ በመካከላቸው እጅግ የተራራቀ የሐሳብ ልዩነት ይስተዋላል፡፡ አንዱ የገነባውን ቲየሪና ምልከታ ሌላው ሲያፈርሰው፣ አንዱ ያጸደቀውን ሌላው ሲያስተባብለው ማየት የተለመደ ነው፡፡ ከዚህ የተነሳ ራሳቸውንም ሆነ ሕብረተሰቡን ወደ ቅን ጎዳና መምራት አልቻሉም፡፡

ለምሳሌ አርስቶትል በሞራልና በሌሎች መስኮች በርካታ የፍልስፍና መሠረቶችን የጣለ ቢሆንም አምላካዊ መገለጥን የተነፈገ በመሆኑ በፍልስፍናው የሚያምንለት፣ ፍልስፍናውን ወደ ተግባር ለውጦ ደስታን የተጎናጸፈ አንድም ግለሰብ አላገኘም፡፡ የዚህ ምክንያት ፈላስፎች ቀልባቸውን አላጸዱም፡፡ ነፍሳቸውን አልገሩም፡፡ አስተሳሰባቸውና ተግባራቸው በወህይ እገዛ ሊበስልና ሊጎለብት አልቻለም፡፡

ስለዚህም የሰው ልጅ በወህይ ያልተገሩ አእምሮዎችና ልቦናዎች ከሚያመጧቸው ሙከራዎች ሊወጣ የሚችልበት ብቸኛው መንገድ የተከበረው ቁርአን ነው፡፡ ቁርአን አላህ ለሰው ልጆች ከመጨረሻው ነብይ ጋር የሰጠው ጠንካራ ገመድ ነው፡፡፡

በቁርአን ውስጥ የተካተቱ የእውቀትና የተግባር እውነታዎች በነቢዩ ሙሐመድﷺ ሕይወት ውስጥ በጉልህ ሰፍረዋል፡፡ እናም የሰው ልጅ የተፈጠረለትን ዓላማ ለማሳካት የሚያስፈልገው ቁርአንንና ሱንናን ተከትሎ መንቀሳቀስ ብቻ ነው፡፡ የአላህ መልእክተኛ ሁለት መመሪያዎችንና ምንጮችን ትተውልናል፡፡ ቁርአንና ሱንናን፡፡ እነዚህ ሁለት ምንጮች ለሁለቱም ዓለማት ስኬት ቁልፎች ናቸው፡፡

ነቢዩﷺ መልእክት ከሰማይ ሳይወርድላቸው በፊት እንኳ ከወገኖቻቸው ዘንድ ተወዳጅ ነበሩ፡፡ ሰዎች አልሲዲቅ (እውነተኛ)፣ አልአሚን (ታማኝ) በማለት እንዲጠሯቸው ማድረግ የጀመሩት የፍጹም እውነተኛነት እና ታማኝነት ባህሪ በስብእናቸው ውስጥ ከነገሰ በኋላ ነው፡፡

ሰዎች መልካም ባህሪያቸውን፣ ጥሩ ስነ ምግባራቸውን፣ ቀጥተኛነታቸውንና ታማኝነታቸውን ከነብይነታቸው በፊት አውቀው ወደዋቸዋል፡፡ ‹‹አል አሚን›› የሚል ማእረግም ሰጥተዋቸዋል፡፡ በካእባ ግንባታ ወቅት ለተከሰተው ውዝግብ ፍርዳቸውን ያለተቃውሞ ተቀብለዋል፡፡

የነቢዩን እውነተኛነት ከሚያረጋግጡ ምስክሮች መሐል የሮማው ንጉስ ሂረቅል የነቢዩ ዋነኛ ጠላት የነበረውን አቡ ሱፍያንን ከመስለሙ በፊት እንዲህ በማለት ጠየቀው፡- ‹‹ነብይ ነኝ ከማለቱ በፊት ዋሽቶ ያውቃልን?›› አቡ ሱፍያን፡- ‹‹በፍጹም›› ከማለት ውጭ መልስ አልነበረውም፡፡ ‹‹ሸፍጥ ፈጽሞ ያውቃልን?›› ሲልም ጠየቀው፡፡ ‹‹አያውቅም፡፡ በእርግጥ ከኛ ለተወሰነ ጊዜ ርቋል፡፡ በዚህ ጊዜ ውስጥ የፈጸመው ነገር መኖሩን አላውቅም፡፡›› አለ፡፡ ‹‹ከዚህ ውጭ ሌላ ነገር ለመጨመር አልተቻለኝም፡፡›› ሲል አቡ ሱፍያን አስተያየቱን አክሏል፡፡[1]

የመካ ሰዎች የነቢዩን ቃል ሙሉ በሙሉ ያምኑ ነበር፡፡ ምክንያቱም ከርሳቸው ታማኝነትን እንጅ ሌላን አያውቁምና፡፡ አንድ ቀን አቡ ጀህልና ባልንጀሮቹ የነቢዩ ቀንደኛ ጠላቶች ቢሆኑም እንዲህ ብለዋቸዋል፡፡ ‹‹ሙሐመድ ሆይ፣ እኛ ሐሰተኛ ነህ አንልም፡፡ ከኛ ዘንደ አንተ እውነተኛ ነህ፡፡ ግና ያመጣህውን መልእክት እናስተባብላለን፡፡›› ይህን ክስተት አስመልክቶ ተከታዩ የቁርአን አንቀጽ ወረደ፡-

﴿ فَإِنَّهُمۡ لَا يُكَذِّبُونَكَ وَلَٰكِنَّ ٱلظَّٰلِمِينَ بِـَٔايَٰتِ ٱللَّهِ يَجۡحَدُونَ ٣٣ ﴾ الأنعام: ٣٣

[1] ቡኻሪ

*‹‹ፈጽሞ አያስተባብሉህም። ግና በዳዮች የሚክዱት የአላህን አናቅጽ ነው።›› (አል አንዓም 33)*

ነቢዩ ሙሐመድን ﷺ ሰዎች -ጣኦታውያንን ሳይቀሩ- ‹‹ታማኙ ሙሐመድ›› በሚል ቅጽል እንዲጠሯቸው ካደረጉት ምክንያቶች አንዱ ከታሪክ መጽሐፍት እንዲህ ተጠቅሷል፡-

በኸይበር ዘመቻ ጊዜ አንድ የአይሁድ እረኛ ወደ አላህ መልእክተኛ መጣ፡፡ ከርሳቸው ጋር ተነጋገረ፡፡ መስለምና ከሙስሊሞች ጋር መቀላቀል እንደሚፈልግም ነገራቸው፡፡ የአላህ መልእክተኛም ﷺ ይጠብቃቸው የነበሩ የፍየል መንጋዎችን ለባለቤቶቻቸው እንደዲመልስና ከዚያ በኋላ መጥቶ ከሙስሊሞች ጋር መቀላቀል እንደሚችል ነገሩት፡፡ ይህ የሆነው ከአይሁድ ጠላቶቻቸው ጋር እየተፋለሙ ባሉበት ጊዜ ነው፡፡ የፍየል መንጋው የጠላቶቻቸው ሐብት ነው፡፡ በዚያ ላይ ሙስሊሞች አስከፊ የስንቅ እጥረት ነበረባቸው፡፡ ይህ የነቢዩ ድርጊት እጅግ አስቸጋሪና ፈታኝ በሆኑ ሁኔታዎች ውስጥ እንኳ ነቢዩ ሙሐመድ ﷺ ይሰማቸው የነበረውን የሐላፊነትና የአደራ ጠባቂነት ስሜት ያጎላል፡፡

ባልንጀራቸው አቡበክር በዚህ የነቢዩ ባህሪ ተመስጠዋል፡፡ በየትኛውም ሁኔታ ውስጥ ታማኝ እንደሆኑ ከልብ አምነዋል፡፡ ከዚህም የተነሳ የሚእራጅ እለት ዝንተ ዓለም ሲዘከር የሚኖር ምስክርነታቸውን ሰጡ፡፡ ይህውም ነቢዩ ከሰማይ ደርሰው እንደተመለሱ መናገራቸው ሲወሳላቸው እንዲህ አሉ፡-

‹‹በእርግጥ ይህን ተናግሮ ከሆነ እውነቱን ነው፡፡››

‹‹ቃሉ ከነቢዩ አንደበት መውጣቱን አረጋግጡልኝ›› ነው ነገሩ፡፡ ‹‹እርሱን ካረጋገጣችሁልኝ እኔ ደግሞ እውነት መሆኑን አረጋግጥላችኋለሁ፡፡››

በነቢዩ ﷺ ሕይወት ውስጥ የተስተዋሉ ለቁጥር የሚታክቱ የፍትህና የእዝነት ክስተቶች ለዚህች ዓለም እስከ እለተ ቂያማ ድረስ አንጸባራቂ ምሳሌ ሆነው ይቀጥላሉ፡፡

ቅን ሕሊና ያለው ሰው ከብቸኛው ምንጭ ፈንጥቆ ዓለምን ያበራውን አንጸባራቂ ብርሃን ቢያንስ በውስጡ ሊያስተባብል አይችልም፡፡ ሙስሊም ያልሆኑ ባለ ቅን ልቦና ምሁራን የነቢዩ ሙሐመድን ﷺ ታላቅነት እና ስኬት መስክረዋል፡፡ ቶማስ ካርላይል ስለርሳቸው ሲናገር እንዲህ ብሏል፡-

‹‹የርሳቸው አነሳስ ከጽልመት ተፈልቅቆ የወጣ ብርሃን ዓይነት ነበር፡፡››

ኢንሳይክሎፒዲያ ብሪታኒካ ላይ ስለነቢዩ ሙሐመድ ﷺ እንዲህ የሚል ተጽፏል፡-

‹‹ነቢዩ ሙሐመድ ያስመዘገበውን ዓይነት ስኬት ያስመዘገበ የተሐድሶ አራማጅ በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ አይገኝም፡፡››

ስሚዝ እንዲህ ብሏል፡-

‹‹ሙሐመድ የተሐድሶ አራማጆች ሁሉ አውራ መሆኑን የሚጠራጠር ማንም የለም፡››

እውቁ ጸሐፊ ስታንሊ ሊበል እንዲህ ሲል ጽፏል፡-

‹‹‹ሙሐመድ በጠላቶቹ ላይ ከፍተኛ ወታደራዊ ድል ባስመዘገበበት በዚያው ቅጽበት እጅግ አንጸባራቂ የሞራል ድል ተቀዳጅቷል፡፡ ይህውም ለዘመናት ያሰቃዩትን ቁረይሾች ማለትም የዚያን ዘመን የመካ ነዋሪዎች ሁሉ ይቅር ብሏል፡፡››

አርሰር ጀልማን እንዲህ ብሏል፡-

‹‹የሙሐመድን ታላቅነት መካን በድል በከፈተ ጊዜ ተመልክተናል፡፡ ጠላቶቹ ባለፉት ዘመናት የፈጸሙትን ግፍ ሁሉ ይቅር አለ፡፡ ድርጊታቸው እነርሱን በሚገባ ለመበቀል በቂ ምክንያት ነበር፡፡ ግና ሙሐመድ ለሰራዊቱ አንዲት ጠብታ ደም እንዳያፈሱ ጥብቅ ትእዛዝ አስተላለፈ፡፡ እጅግ የላቀ እዝነትም አሳየ፡፡ ለዚህ ድርጊቱም አላህን አመሰገነ፡፡››

ለ1789 የፈረንሳዮች አብዮት፣ የአስተሳሰብ መሠረት ከጣሉ ፈላስፎች መካከል አንዱ የሆነው ላውሬት የተሰኘ ፈላስፋም፣ ሰብአዊ መብቶች

ከመደንገጋቸው በፊት የዓለምን የህግ ስርዓቶች ከመረመረ በኋላ የእስልምና ሕግ ﷺከሁሉም የላቀ መሆኑን በተረዳ ጊዜ እንዲህ ሲል ተናዟል፡-

‹‹ሙሐመድ ሆይ፣ ታላቅ ሰው ነበርክ፡፡ እስከ ዛሬ ድረስ ማንም ያልደረሰበትንና ወደፊትም ማንም ሊደርስበት የማይችልን የፍትህ የመጨረሻ ጫፍ አንተ ደርሰህበታል፡፡››[1]

ጠላት እንኳ ሊያስተባብለው ያልቻለና የመሰከረለት የነቢዩ ሙሐመድﷺ ታላቅነት ይህ ነው፡፡ በነቢዩ የሚያምኑ ሁሉ ታላቅነታቸውን አምነዋል፡፡ ብልህነታቸውን መስክረዋል፡፡ የነቢዩ ልዩ የሕይወት ታሪክ በውስጡ ያካተተው የተሟላ ሞራላዊ ሕይወት፣ ብርሃን ለሚሹ አጥኚዎች ሁሉ ብርሃን የለገሰ ነው፡፡ በምድር ላይ የሚገኙ የሰው ልጆችን ሁሉ ለማስተማርም መሠረት ሆኗል፡፡

የነቢዩ ትግል ከማንም የተሰወረ አይደለም፡፡ ለአጥኚዎች ትክክለኛውን መንገድ አመላክቷል፡፡ በእርግጥ አቻ የማይገኝላቸው የሰው ልጅ መምህር ናቸው፡፡

የአላህ መልእክተኛ ﷺ ትምህርት ከሚሰጡባቸው ቦታዎች ላይ የተለያየ ቋንቋ፣ ዘርና ማሕበራዊ ደረጃ ያላቸው ሰዎች ይገኙ ነበር፡፡ የነቢዩ ትምህርቶች እነዚህን ሁሉ በአንድ አስተናግደዋል፡፡፡ ከርሳቸው የትምህርት ማእድ ለመቋደስ ምንም ዓይነት የተለየ መስፈርት አልነበረም፡፡ ሁሉም የሰው ዓይነት መሳተፍ ይችላል፡፡ በሰው ልጅ ላይ የሚያተኩሩ የትምህርት ማእከላት ነበሩ፡፡ እናም ደካማው ከጠንካራው ሳይነጠል ሁሉም ከበረከታቸው ይቋደሱ ነበር፡፡

የነቢዩን ሶሐቦች ስናጠና የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎችን የሚወክሉ ግለሰቦችን እናገኛለን፡፡ ለምሳሌ የሐበሻው ንጉስ ነጃሺ፣ የዑመይር ጎሳ አለቃ ዙል ኩልየህ፣ ፌሩዝ ደይለሚ፣ ፋርወት አዚም መዑን፣ የአማን

[1] ካሚል ሚራስ፣ ተርጀመት ተጅሪድ ሶሪህ ፣ አንካራ፣ 1972 ፣ ቅጽ 9፣ ገጽ 289

ገዥ አቢድ ቢን ጃእፈር፣ የየመን ገዥ መርከቡድ ይገኙባቸዋል፡፡ ከነዚህ የሕዝቦች መሪዎች በተጓዳኝ ደግሞ ቢላል፣ ያሲር፣ ሱሐይብ፣ ኸባብ፣ አማርና ሌሎችም የዝቅተኛው የሕብረተሰብ ክፍል አባላት፣ እንዲሁም እንደ ሱመያህ፣ ለቢነህ፣ ዘኒረህ፣ ነህድያህና ኡም ኡበይስ ያሉ ባሮችን እና ባል አልባ እንስቶችን ታገኛለህ፡፡

ከነቢዩ የእውቀት ማእድ ላይ እውቀተ ሰፊ እና ጥበበኛ ሰዎች፣ ሃገር ለማስተዳደር የሚበቁ ታላላቅ ስብእናዎች ይገኙ ነበር፡፡

ከነቢዩ ተከታዮች መካከል ሃገር የሚያስተዳደሩ መሪዎች ፈልቀዋል፡፡ እነዚህ ሰዎች በሕዝቡ መሐል ሰላምን አስፍነዋል፡፡ መረጋጋትን አንግሰዋል፡፡ ከሚገዙት ሕዝብ ጋር ልክ እንደ ወንድማማች ተጣጥመው ኖረዋል፡፡ በነርሱ ጥላ ስር የሰው ልጅ ደስታን አግኝቷል፡፡ በአስተዳደራቸው የፍትህን ለዛ አጣጥሟል፡፡

# ክፍል ሁለት

- የአላህ መልእክተኛ የመጠቁ ባህሪያት
- አንጻባራቂ የታላቅነት መለኪያዎች

## የአላህ መልእክተኛﷺ የመጠቁ ባህሪያት

የሰውን ልጅ ታሪክ ስንፈትሽ፣ የሕይወቱ እያንዳንዱ እርከን እና ገጽታ በጥልቀትና በስፋት የተዳሰሰችለት ግለሰብ ከአላህ መልእክተኛ ﷺ ውጭ አይገኝም፡፡ ከልደት እስከ ሞታቸው ድረስ ሕይወታቸው በዝርዝር ተጠንቷል፡፡ በጥንቃቄ ተፈትሾ ተመዝግቧል፡፡ የአላህን መልእክተኛ ተምሳሌታዊ ስብእና ሁሉንም ገጽታዎች ለመዳሰስ ብንሞክር ብዙ መጽሐፍት ማዘጋጀት ግድ ይሆንብናል፡፡

ሁሉም የኢስላማዊ እውቀት መስኮች መነሻ ምንጭ የነቢዩ ሙሐመድ ﷺ ስብእና ነው፡፡ የዑለሞች ምርምር (ኢጅቲሐድ) የርሳቸውን ስብእና መሠረት ያደረገ ነው፡፡ ይህም በመሆኑ በየትኛውም የኢስላማዊ እውቀት መስክ ውስጥ የሚሰሩ ምሁራን የነቢዩን ሕይወት የተለያዩ ገጽታዎች ትኩረት ችረው በጥንቃቄና በጥልቀት ፈትሸዋል፡፡

ከ1000 ዓመታት በላይ የመጽሐፍት ድርሰት ታሪካችን ውስጥ የተከተቡ እጅግ በርካታ መጽሐፍት ዓላማቸው የቁርአንን መልእክት ማብራራት እና የነቢዩ ሙሐመድን ﷺ የተለያዩ የሕይወት ገጽታዎች መተንተን ነው፡፡

ስብእናቸው ትልቅ ተአምር የነበረውን የነቢዩ ሙሐመድን ﷺ ሕይወት በደካማው የሰው ልጅ ጭንቅላታችን በተሟላ መልክ መረዳት ይከብደናል፡፡ ስለሆነም ከዚህ ታላቅ ሰው የስብእና ውቅያኖስ ውስጥ ያቅማችንን ያህል እየጨለፍን ለማስተዋወቅ ሙከራ እናደርጋለን፡፡

## የገጽታ ውበትና የባህሪ ማማር

የአላህ መልእክተኛ ﷺ ወደር አይገኝላቸውም፡፡ ገጽታቸው ውብ፣ ባህሪያቸውም ያማረ ነበር፡፡ እርግጥ መልክና ጸባያቸውን በተሟላ መልኩ ማስቀመጥ ይከብደናል፡፡ ኢማም ቁርጡቢ ይህን በማስመልከት ሲናገሩ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹የአላህ መልእክተኛ ውበት በተሟላ መልኩ አልተገለጸም፡፡ ምክንያቱም ውበትን ሁሉ ያካተተ ማንነታቸው በተሟላ መልኩ ቢገለጽ ኖሮ ሶሐቦች ገጽታቸውን ለማየት አቅም አይኖራቸውም ነበር፡፡››[1]

ሶሐቦች የአላህ መልእክተኛﷺ ዘወትር አብረዋቸው ቢሆኑም ከአደባቸው የተነሳ የመልእክተኛውን ውበት ብርሃን እስኪጠግቡ ድረስ ማየት የቻሉት ጥቂቶቹ ብቻ ናቸው፡፡ አቡበክርና ዑመር ባሉበት የአንሷሮችና የሙሐጅሮች ስብስብ ነቢዩ ሙሐመድﷺ ሲመጡ ከአቡበክርና ከዑመር በስተቀር ሌሎች ሶሐቦች አንገታቸውን አቅንተው ሊያዩአቸው አይደፍሩም ነበር፡፡ ሁለቱ ግን ያዩአቸዋል፡፡ ፈገግታም ይለዋወጣሉ፡፡ (ቲርሚዚ)

ግብጽን ያቀናው አምር ቢን አልአስ በእድሜው መጨረሻ ላይ ስለዚህ ሁኔታ ሲያወጋ እንዲህ ብሏል፡-

‹‹ከአላህ መልእክተኛ ይበልጥ ተወዳጅና የተከበረ ሰው ከኔ ዘንድ አልነበረም፡፡ ለርሳቸው ካለኝ ክብር የተነሳ አይኔን ሞልቼ ላያቸው አልደፍርም፡፡ ገጽታቸውን እንዳብራራ ብጠየቅ እንኳ ይህን ማድረግ አልችልም፡፡›› (ሙስሊም)

የተባረከው የነቢዩ ፊት በዙሪያቸው ላሉ ሰዎች የስክነትንና የመረጋጋትን መንፈስ የሚያሰፍን እጅግ ውብና ንጹህ ገጽታ ነበረው፡፡

ከመስለሙ በፊት ከአይሁድ የሐይማኖት ሊቃውንት መካከል አንዱ የነበረው አብደላህ ቢን ሰላም እስልምናን ከመቀበሉ በፊት የስደት ሐገር ከሆነችው መዲና እንደደረሰ የነቢዩን የተባረከ ፊት ባየ ጊዜ እንዲህ ለማለት ተገዷል፡-

‹‹ይህ ፊት የሐሰተኛ ሰው ፊት አይደለም፡፡›› (ቲርሚዚ፣ ቢን ማጃህና አህመድ)

[1] አሊ ያርደም፣ የነብያችን ባህሪያት፣ እስታንቡል፣ 1992 ዓ.ል፣ ቅ 4 ገጽ 199

የነቢዩ ውበት፣ ግርማ ሞገስና የገጽታቸው ብርሃን ነብይነታቸውን የሚመሰክር ከመሆኑ የተነሳ የአላህ መልእክተኛ ለመሆናቸው ሌላ ዋቢ ወይም ተአምር አያስፈልጋቸውም ነበር። የአላህ መልእክተኛ አንድ የማይፈልጉት ነገር ሲከሰት ፊታቸው ይለዋወጣል። የሚያስደስት ነገር ሲያጋጥማቸው በደስታ ይበራል።

ገጽታቸው ትህትናን፣ ቆራጥነትንና ጽናትን፣ እንዲሁም የላቀ አላማን የተሸከመ ሕያው ነበር። የአዛኝነታቸውን ጥልቀትማ መግለጽ ይቸግራል።

ነቢዩﷺ ፊታቸው የውበት ቋት ነበር። ንግግራቸው ይመስጣል። ገለጻቸው ያፈዝዛል። አንደበታቸው ርቱእ ነው። አረማመዳቸው ይማርካል። ንግግራቸው ምክርና ጥበብ ብቻ ነበር። አሉባልታ እና ፍሬ አልባ ወግ አያውቁም። እያንዳንዱ ሰው ሊረዳው በሚችል ግልጽ ቋንቋ ይናገራሉ።

ትሁትና ልዝብ ነበሩ። ተንከትክተው አይስቁም። ሳቃቸው ፈገግታ ነበር። በድንገት ያያቸው ከግርማ ሞገሳቸው የተነሳ ልቡ በፍርሃትና በክብር ይሞላል። የተላመዳቸው ደግሞ ከልቡ ይወዳቸዋል።

ለእያንዳንዱ ሰው ተገቢውን ክብር ይሰጣሉ። ዘመዶቻቸውን ያቀርባሉ። ሌሎች ሰዎችንም ልክ እንደቤተሰቦቻቸው ይንከባከባሉ። አገልጋዮቻቸውን ያልቃሉ። ከሚለብሱት ያለብሷቸዋል። ከሚጎርሱት ያጎርሷቸዋል። ቸር እና አዛኝ ከመሆናቸው በተጎዳኝ አስፈላጊ ሲሆን የተዋጣላቸው ጀግና፣ እንዲሁም ሆደ ሰፊ ነበሩ።

ቸርነታቸው ሊገለጽ ከሚችለው በላይ የበዛ ነበር። ድህነትን የማይፈራ ሰው ዓይነት አሰጣጥ ይሰጡ ነበር። ጃቢር እንዲህ ሲሉ ይህን እውነታ ገልጸዋል፡-

‹‹የአላህ መልእክተኛ አንዳች ነገር ተጠይቀው አይከለክሉም ነበር።›› (ሙስሊም)

የመልእክተኛው አደብ ወደር አልባ ነው፡፡ ዘመዶቻቸውን በብዛት ይጠይቃሉ፡፡ ለፍጡራን በጣም ያዝናሉ፡፡ ከሰዎች ጋር ይግባባሉ፡፡ ይንከባከባሉ፡፡ ከመጥፎ ባህሪያት ፈጽሞ የራቁ ነበሩ፡፡ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹በእለተ ቂያማ ከሙእሚን ሚዛን ላይ ከመልካም ስነ ምግባር የከበደ ነገር የለም፡፡ አላህ አንደበቱ ያልተገራ ባለጌን ይጠላል፡፡›› (ቲርሚዚ)

ንግግራቸው እውነተኛ ነው፡፡ ሲበዛ ብልህ ናቸው፡፡ ባህሪያቸው ባጠቃላይ ሊወደስና ሊሞገስ የሚገባው ዓይነት ነው፡፡ በጥልቀትና በተከታታይ ያስባሉ፡፡ ዝምታቸው ረዥም ነው፡፡ ሲናገሩ ንግግርን ይሞላሉ፡፡ በጥቂት ቃላት ብዙ መልእክት የማስተላለፍ ክህሎት ነበራቸው፡፡ ንግግራቸው የሚቆጠር ነበር፡፡ ትርፍ ንግግር አይወዱም፡፡ በባህሪያቸው ስሜተ ስስ ነበሩ፡፡ ሞገሳማ ከመሆናቸው ጋር ሐቅ ካልተደፈረና ሰዎች ከሐቅ ለማደር አሻፈረን ካላሉ በቀር የአላህ መልእክተኛ አይቆጡም፡፡ ሐቅ ሲደፈር ግን ውሃው ወደ ቦዩ እስኪፈስ፣ ሐቅ ወደ ቦታው እስኪመለስ ድረስ ቁጣቸው አይበርድም ነበር፡፡ ነገሮች ሲስተካከሉ ወደ ዘወትር የሰከነ ባህሪያቸው ይመለሳሉ፡፡ ለራሳቸው ጉዳይ ፈጽሞ አይቆጡም፡፡ ስለራሳቸውም አይሟገቱም፡፡ ከየትኛውም ሰው ጋር ክርክር ውስጥ አይገቡም፡፡

ወደ ሌሎች ሰዎች ቤት ፈቃድ ሳይጠይቁ አይገቡም፡፡ ወደቤታቸው ሲገቡ ቆይታቸውን ለሦስት ይከፍላሉ፡፡ አንደኛ፡- አላህን ለማምለክ፣ ሁለተኛ፡- ለቤተሰቦቻቸው፣ ሦስተኛ፡- ለራሳቸው፡፡ ለራሳቸው የመደቡትን ጊዜ ለሕዝባዊ አገልግሎት ያውሉታል፡፡ የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች ያለ ገደብ ያገኟቸዋል፡፡ ቀልባቸው ለሁሉም በእኩል ክፍት ነው፡፡

ከመስጊዳቸው ውስጥ ከአንድ የተለየ ቦታ ላይ አይቀመጡም፡፡ በሁሉም የመስጊዱ መስኮች ይቀመጣሉ፡፡ ይህን የሚያደርጉት ከአንድ የተለየ ቦታ ላይ መቀመጥን በማዘውተር ያን ቦታ ሰዎች የተቀደሰ አድርገው እንዳይወስዱት ለመጠንቀቅ ነው፡፡ እንደዚሁም ከሌሎች የተለየ ስፍራ በመያዝ ራሳቸውን ከሌሎች ሰዎች የተለዩ ማድረግ ስላልፈለጉ ነው፡፡ ወደ አንድ ስብስብ ሲመጡ ክፍት ካገኙት ቦታ ይቀመጣሉ እንጅ ሰዎች

ተነስተው እንዲያስቀምጧቸው አይፈቅዱም፡፡ ሌሎች ሰዎችም ልክ እንደርሳቸው እንዲያደርጉ ይመክሩ ነበር፡፡

አንድ ሰው አንዳች ጉዳይ በጠየቃቸው ጊዜ ጉዳዩን ይነስም ይብዛ ሳይፈጽሙለት ረፍት አያደርጉም፡፡ ጉዳዩን ሊፈጽሙለት ካልቻሉ እንኳ ባዶ እጁን አይመልሱትም፡፡ በመልካም ንግግር ቀልቡን ያፈኩታል፡፡

ነቢዩ የሰዎችን ስቃይ ይጋሩ ነበር፡፡ ከርሳቸው ዘንድ ሰዎች ሁሉ ማሕበራዊ ቦታቸው ምንም ይሁን ምን እኩል ናቸው፡፡ ድሃ ከሐብታም፣ አዋቂ ከመሐይም አይለዩም፡፡ የርሳቸው የትምህርት ማእድ ታጋሽነት፣ እውቀት፣ ትህትና፣ ሆደ-ሰፊነት፣ በአላህ መመካት፣ ታማኝነትና ሌሎች ድንቅ ባህሪያት በተግባር የሚገለጹበት ነበር፡፡

ማንንም ጉድለት ወይም ነውር ስላለበት ብቻ አይረግሙትም፡፡ በትህትና ያስተምሩታል፡፡ ስሜቱን ሳይጎዱ ይመክሩታል፡፡ በሰዎች ነውር አይጠመዱም፡፡ የሌሎችን ነውር ማነፍነፍንም አጥብቀው ከልክለዋል፡፡

የሚናገሩት ምንዳ የሚያስገኝ ንግግር ብቻ ነበር፡፡ ከባልንጀሮቻቸው ጋር የሚያደርጉት ቆይታ በፍቅር የተከበበ ነበር፡፡ እርሳቸው ሲናገሩ በዙሪያቸው ያሉ ሰዎች በተመስጦ ያደምጧቸዋል፡፡ በስርዓትና በርጋታ ይሰሟቸዋል፡፡ በዚህ ጊዜ ይታይባቸው የነበረውን አደብ አንደኛው ሲገልጽ እንዲህ ብሏል፦

‹‹ከራሳችን ላይ በራሪ ያረፈ ይመስል አንገታችንን እንደፋ ነበር፡፡›› (አቡ ዳውድ)

የነቢዩ አደብና ሐያእ ወደ ባልንጀሮቻቸው ሰርጿል፡፡ ከዚህ የተነሳ ለአላህ መልእክተኛ ጥያቄ ለማቅረብ እንኳ አይደፍሩም ነበር፡፡ እናም ከገጠር በደዊን መጥቶ ጥያቄ የማቅረቡን እድል በናፍቆት ይጠባበቃሉ፡፡ እርሱ ሲጠይቅ ከነቢዩ መልስ ይጠቀማሉ፡፡ በማእዳቸው ላይ ከሚነግሰው የመንፈሳዊነት ድባብ ያጣጥማሉ፡፡

የአላህ መልእክተኛ ሕይወታቸውን በሙሉ የቅንነት ተምሳሌት ሆነው ኖረዋል፡፡ ከልባቸው የሌለ ነገር አይናገሩም፡፡ ባህሪያቸው ፍጹም

ቁርአናዊ ነበር። ራሳቸው የማይተገብሩትን ለሌሎች አያዙም ወይም አይመክሩም። የሚናገሩትን ይሰራሉ። የማይሰሩትን አይናገሩም።[1]

# ትህትናቸው

የአላህ መልእክተኛﷺ በዚህች አለም የትኛውም ንጉስ ሊያልመው የማይችለውን ሰፊ ግዛት ባጭር ጊዜ ውስጥ መቆጣጠርና ንጉስ መሆን፣ እንዲሁም እንደታላቅ እና ተምሳሌታዊ መምህር የብዙ ሰዎችን ቀልብ መግዛት ቢችሉም ለዓለማዊ ጸጋ ትኩረት አይሰጡም ነበር። ከግራቸው ስር የነበረችውን ዱንያን ንቀው በመተው እስከ መጨረሻው በትሁት ባህሪያቸው ቀጠሉ። ልክ እንደ ወትሯቸው ሁሉ ከጭቃ በተሰራች ደሳሳ ጎጆ ውስጥ መኖራቸውን፣ እሳር በተጎዘጎዘ ምንጣፍ ላይ መተኛታቸውን፣ ቀላል አልባሳት መልበሳቸውን ቀጠሉ። አንዳንድ ጊዜ የሚበሉት አያገኙም ነበር። ይህ ሲሆን አምላካቸውን ያመሰግናሉ። ከረሃባቸው የተነሳ ከሆዳቸው ላይ ድንጋይ ያስራሉ። አላህ ያለፈውንም የሚመጣውንም ግድፈታቸውን የማረላቸው ቢሆንም ሁሌም እርሱን አመስጋኝ ነበሩ። ሌሊቱን እግራቸው እስኪሰነጠቅ ድረስ ሲሰግዱ ያነጋሉ።

ድሀን ይደግፋሉ። የቲምንም ይንከባከቡ ነበር። ታላቅ ከመሆናቸው ጋር ደካሞችን በመደገፍ እና በመንከባከብ ብዙ ጊዜያቸውን ያሳልፋሉ። የምንዱባንን እንባ በማበስ በብዛት ይጠመዳሉ።

መካን በድል በተቆጣጠሩ ጊዜ ሰዎች ከዚያ ቀደም አይተውት የማያውቁት ግዙፍ ሐይል በማየታቸው ልባቸው በፍርሃት በሚርድበት ቅጽበት አንደኛቸው መጣና፡- ‹‹የአላህ መልእክተኛ ሆይ፣ እስልምናን ያስተምሩኝ›› አላቸው - በፍርሃት እየተንቀጠቀጠ። እርሳቸውም እንዲህ በማለት አረጋጉትና እስልምናን ያስተምሩት ጀመር፡-

---

[1] ኢብን ሰዕድ፣ በበጠቃተል ኩብራ፣ ቤይሩት፣ ዳረሷዲር ቅጽ 1 ገጽ 121፣ 365‹ 422-425

‹‹አይዞህ፣ አትፍራ፡፡ እኔ ንጉስ ሳልሆን ደረቅ ቂጣ ትመገብ የነበረች እንስት ልጅ ነኝ፡፡›› (ቢን ማጃህ፣ ጦበራኒ፣ አህመድ፣ ሐይሰሚና ቢን ሰእድ)

መካ ውስጥ የነበሩበትን ደካማነት እና ተራ ሕይወት አስታውሱትና አረጋጉት፡፡ የእስልምናን ትምህርትም መገቡት፡፡

ይህ የነቢዩﷺ አባባል የትህትናን የመጨረሻ ጫፍ መድረሳቸውን ያመለክታሉ፡፡ የትኛውም ታላቅ ሰው የዚህን ልቅና ሽርፍራፊ እንኳ መድረስ አይችልም፡፡፡ በዚሁ ቀን የዋሻ ውስጥ ጓደኛቸውና የመከራ ጊዜ አጋራቸው የሆኑት አቡበክር አባታቸውን ይዘው ወደ መስጊዱ በገቡ ጊዜ የአላህ መልእክተኛ ﷺ ሲያዩአቸው እንዲህ በማለት ልብ የሚነካ የትህትና ንግግር ተናገሩ፡-

‹‹ሽማግሌውን ከቤታቸው ብትተዋቸውና እኔ ሄጄ ብጠይቃቸው መልካም ነበር፡፡›› (አህመድና ሐይሰሚ)

የአላህ መልእክተኛ ራሳቸውን የሚያስተዋውቁት ፍጹም ትህትና በተሞላበት ገለጻ ነበር፡፡ እንዲህ ይላሉ፡-

﴿ قُلۡ إِنَّمَآ أَنَا۠ بَشَرٞ مِّثۡلُكُمۡ يُوحَىٰٓ إِلَيَّ أَنَّمَآ إِلَٰهُكُمۡ إِلَٰهٞ وَٰحِدٞۖ ﴾ الكهف: ١١٠

*“እኔ -ወሕይ የሚገለጽልኝ (ቢሆንም) -እንደናንተው ሰው ነኝ፡፡ አምላካችሁ አንድ አምላክ ብቻ ነው፡፡›› (አል ከህፍ 110)*

ተከታዮቻቸው የጥንት ሕዝቦች የፈጸሙትን ስህተት እንዳይደግሙ ለማስጠንቀቅ ሲሉ መልእክተኛነታቸውን በሚገልጹባቸው አጋጣሚዎች ሁሉ ‹ዓብዱላህ›› (የአላህ ባሪያ) የሚለውን ቅጽል ማከልን አይዘነጉም ነበር፡፡

ከወሰን ያለፈ ክብር ለሰጣቸው ሰው እንዲህ ብለውታል፡-

‹‹ክርስትያኖች የመርየምን ልጅ ኢሣን ከልክ በላይ እንዳላቁት እኔን አታልቁኝ፡፡ እኔ የአላህ ባሪያ ነኝ፡፡ ስለዚህም የአላህ ባሪያና መልእክተኛ ብቻ በሉኝ፡፡›› (አልሐይሰሚ)

አንድ ቀን ነቢዩ ﷺ የኢደል አድሐ ሶላት ከሰገዱና ኡዱህያ ካረዱ በኋላ ከባልንጀሮቻቸው ጋር በአንድ ማእድ ዙሪያውን ከበው ይመገቡ ጀመር፡፡ ነቢዩ ቦታው ስላላመቻቸው በጉልበታቸው በርከክ አሉ፡፡ አንድ በደዊንም፡- ‹‹እንዴት ዓይነት አቀመመጥ ነው?›› ሲል ጠየቃቸው፡፡ (ለተራ ሰው እንጅ ለንጉስ አይገባም ማለቱ ነው፡፡) ነቢዩም ﷺ እንዲህ አሉት፡- ‹‹አላህ የተከበረ ባሪያው እንጅ አምባገነን አላደረገኝም፡፡›› እንዲህም ሲሉ አከሉ፡- ‹‹ማእዱ የተባረከ ይሆንላችሁ ዘንድ ዙሪያውን ተመገቡት፡፡ የመሐሉንም ተውት፡፡›› (አቡ ዳውድ)

ነቢዩ ﷺ በሕይወታቸው ውስጥ በኩራት የተኮፈሱበት አንድም አጋጣሚ የለም፡፡ ይህን የትህትና ባህሪ እንዲህ ሲሉ ያብራራሉ፡-

‹‹ቀጥተኛ ሁኑ፡፡ ካልቻላችሁትም ሞክሩ፡፡ ብስራት ይድረሳችሁ፡፡ ከናንተ አንዳችሁን ስራው ብቻ ጀነት አያስገባውም፡፡›› ሶሐቦች፡-- ‹‹እርስዎም ቢሆኑ?›› በማለት ጠየቋቸው፡፡፡ ‹‹አዎ፣ እኔም ብሆን፣ አላህ በምህረቱና በእዝነቱ ካልሸፈነኝ በስተቀር›› አሉ፡፡ (ቡኻሪና ሙስሊም)

ልብሱን በኩራት ስሜት የለበሰና በአልባሳቱ የተኮፈሰ በእለተ ቂያማ አላህ ውርደት እንደሚያከናንበው ተናግረዋል፡፡ በዚህ ረገድ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹ልብሱን በኩራት የጎተተን አላህ በእለተ ቂያማ አያየውም፡፡›› (ቡኻሪ)

‹‹በዱንያ ውስጥ የኩራት ልብስ የለበሰ በእለተ ቂያማ አላህ የውርደት ልብስ ያለብሰዋል፡፡ እሳትም ያቀጣጥልበታል፡፡›› (ቢን ማጃህ)

የአላህ መልእክበኛ ﷺ የራሳቸው ድርሻ የሆነውን ምርኮ ሳይቀር ለሰዎች አከፋፍለው እርሳቸው ከሚያስተዳድሩት ሕዝብ መሐል የመጨረሻው

ድሃ ግለሰብ የሚኖረውን ዓይነት የድህነት ሕይወት መግፋትን መርጠዋል፡፡

## ቸርነታቸው

የአላህ መልእክተኛ ﷺ ቸርነት ባህሪያቸው እንዲሆን መታዘዛቸውን ገልጸዋል፡፡ ‹‹አላህ ሰጭ ነው፡፡ በነገሮች ሁሉ ባለቤቱም እርሱ ነው፡፡›› ብለዋል፡፡

ሱፍዋን ቢን ኡመያህ ከመስለሙ በፊት በሁነይንና በጧኢፍ ዘመቻዎች ተሳትፏል፡፡ ያኔ ከቁረይሽ ባላባቶች መካከል አንዱ ነበር፡፡ ከርሳቸው ጋር ሆኖ ከጦርነቱ የተገኘውን ምርኮ እየተዘዋወረ ተመለከተ፡፡ በእንስሳት የተሞላ ሸለቆም ተመለከተ፡፡ ትኩር ብሎም በግርምት አየው፡፡ የአላህ መልእክተኛምﷺ አስተዋሉትና፡- ‹‹ሱፍያን ሆይ፣ የዚህ ሸለቆ (እንስሳት) ያስደስቱሐልን?›› አሉት፡፡ ‹‹አዎ›› አላቸው፡፡ ‹‹እንግዲያውስ ትወስዳቸው ዘንድ ፈቅጀልሐለሁ፡፡›› አሉት፡፡ እርሱም፡- ‹‹እንዲህ ዓይነት ቸርነት ከነብይ ልቦና እንጅ ከሌላ ሊመነጭ አይችልም፡፡ ከአላህ ሌላ አምላክ እንደሌለና ሙሐመድም ባሪያውና መልእክተኛው መሆናቸውን እመሰክራለሁ፡፡›› በማለት እዚያው በቆመበት ሰለመ፡፡[1]

ወደ ወገኖቹ ሲመለስም እንዲህ በማለት ለለበ፡-

‹‹ወገኖቼ ሆይ፣ ስለሙ፡፡ ሙሐመድ ድህነትን የማይፈራ ሰው አሰጣጥ ይሰጣልና፡፡›› (ሙስሊም)

አንድ ሰው ወደ አላህ መልእክተኛﷺ መጣ፡፡ አንዳች ነገርም ጠየቃቸው፡፡ የሚሰጡት አልነበራቸውም፡፡ ከሰው ተበድረው ሰጡት፡፡ ብድራቸውንም ለመክፈል ቃል ገቡ፡፡ (ሐይሰሚ)

ልክ እንደ አያታቸው እንደ ኢብራሂም እንግዳን በጣም ያልቃሉ፡፡ እጅግ ይንከባከባሉ፡፡ ብቻውን እንዲመገብ አይተውትም፡፡ እዳ እያለበት ለሞተ ወይም እንዲከፍሉለት ለጠየቃቸው ሰው እዳውን ይከፍሉለታል፡፡

[1] አልዋቂዲ፣ አልመጋዚ፣ በይሩት፣ 1989 ቅጽ 2 ገጽ 854-855

እዳውን ከፍሎ ካላጠናቀቀ ሰው ጀናዛ ላይ አይሰግዱም ነበር፡፡ እንዲህ ሲሉ ተናግረዋል፡-

‹‹ቸር ለአላህ ቅርብ ነው፡፡ ለጀነት ቅርብ ነው፡፡ ለሰዎችም ቅርብ ነው፡፡ ከእሳትም የራቀ ነው፡፡ በአንጻሩ ንፉግ ከአላህ የራቀ ነው፡፡ ከጀነትም የራቀ ነው፡፡ ከሰዎችም የራቀ ነው፡፡ ለእሳት ግን የቀረበ ነው፡፡›› (ቲርሚዚ)

በሌላ ሐዲስ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹በሙእሚን ስብእና ውስጥ ሁለት ነገሮች ፈጽሞ አይገኙም፡፡ እነርሱም ንፉግነትና መጥፎ ስነ ምግባር ናቸው፡፡›› (ቲርሚዚ)

## ተቅዋቸው

የአላህ መልእክተኛ ﷺ ከየትኛውም ሰው በላይ አላህን ይፈሩ ነበር፡፡ ተቅዋ ይለግሳቸው ዘንድ አላህን አጥብቀው ለምነዋል፡፡ ይህን በተመለከተ ሲናገሩ፡-

‹‹አላህ ሆይ፣ ለነፍሴ ተቅዋ ለግሳት፡፡ አጽዳትም፡፡ የምትጸዳው ባንተ ብቻ ነው፡፡፡ አንተ አለኝታዋ እና አምላኳ ነህና፡፡›› (ሙስሊም)

እንዲህም ብለዋል፡- ‹‹አላህ ሆይ፣መቀናትን፣ አንተን መፍራትን፣ ቁጥብንትንና ሐብትን እጠይቅሐለሁ፡፡›› (ሙስሊም)

በዚህ ተቅዋቸው ምክንያት እንደ ድሆች ሆነው ኖረዋል፡፡ አኢሻ እንዲህ ብላለች፡-

‹‹የሙሐመድ ቤተሰቦች ከስንዴ ዳቦ ለሦስት ተከታታይ ቀናት ጠግበው ተመግበው አያውቁም፡፡ አላህን እስከተገናኙበት እለት ድረስ ኑሯቸው እንደዚህ ነበር፡፡›› (ቡኻሪና ሙስሊም)

መልእክተኛው ኡመታቸውን  እንዲህ በማለት ለተቅዋ ያበረታቱ ነበር፡-

‹‹ለኔ ይበልጥ ተገቢ የሆኑ ሰዎች አላህን የሚፈሩት ናቸው፡፡ ማንምና የትም ቢሆኑ፡፡›› (አህመድና ሐይተሚ)

‹‹የኔ ወዳጆች አላህን የሚፈሩት ናቸው፡፡›› (አቡ ዳውድ)

‹‹የትም ቦታ ብትሆን አላህን ፍራ፡፡ ወንጀልን በበጎ ስራ አስከትል - ታብስልሐለችና፡፡ ከሰዎች ጋርም በመልካም ስነ ምግባር ተኗኗር፡፡›› (ቲርሚዚ)

እውነተኛ ተቅዋ የሚገኝበትን መንገድም እንዲህ ሲሉ አመላክተዋል፡-

‹‹ሰውየው ከተከለከለው ለመታቀብ ሲል ያልተከለከሉ ነገሮችን እስካልተወ ድረስ የተቅዋ ደረጃን አይደርስም፡፡›› (ቲርሚዚና ቢን ማጃህ)

የአላህ መልእክተኛﷺ በሰዎች መካከል ልዩነት አያደርጉም ነበር፡፡ ሁሉንም በእኩል አይን ይመለከታሉ፡፡ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹ዓረብ ከሌላው፣ ሌላውም ከዓረብ፣ ቀይ ከጥቁር፣ ጥቁርም ከቀይ በተቅዋ ቢሆን እንጅ አይበልጥም፡፡›› (አህመድ)

ነቢ ኢሣ የተቅዋን ትርጉም ድንቅ በሆነ ሁኔታ ነግረውናል፡፡ አንድ ሰው መጣና፡- ‹‹አንተ የደግነት አስተማሪ ሆይ፣ እኔ የማላውቀውንና አንተ የምታውቀውን፣ እኔን የሚጠቅመኝንና አንተን ግን የማይጎዳህን ነገር አስተምረኝ፡፡›› አላቸው፡፡ እርሳቸውም ‹‹እርሱ ምንድን ነው?›› አሉት፡፡ ‹‹አንድ ሰው አላህን በትክክል እንዴት እንደሚፈራ ንገረኝ፡፡›› አላቸው፡፡ እንዲህ በማለት መለሱለት፡- ‹‹በቀላል ነገር ተቅዋን ማግኘት ትችላለህ፡፡ ይህውም አላህን ከልብህ ውደደው፡፡ ለርሱም የቻልከውን ያህል በርትተህ ስራ፡፡ ለራስህ የምታዝነውን ያህል ለወገኖችህ እዘን፡፡››

‹‹አንተ የደግነት መምህር ሆይ፣ ወገኖቼ እነማን ናቸው?›› ሲል ጠየቃቸው፡፡‹‹የአደም ልጆች ሁሉ ወገኖችህ ናቸው፡፡ በአንተ ላይ እንዲፈጸም የማትፈልገውን ነገር በሌሎች ላይ አትፈጽም፡፡ ይህን ካደረግክ አንተ በእርግጥ አላህን የምትፈራሰው ነህ፡፡››አሉት፡፡

ዑመር ቢን አልኸጧብ አንድ ቀን ኡበይ ቢን ከእብን ‹‹ተቅዋ ምንድን ነው›› በማለት ጠየቁ፡፡ ኡበይም፡- ‹‹ዑመር ሆይ፣ በእሾሐማ መንገድ ተጉዘህ ታውቃለህን?››

‹‹አዎ››

‹ምን አደረግክ?››

‹‹አረማመዴ ጥንቃቄ የተሞላበት ሆነ፡፡››አሉ፡፡

ኡበይም፡- ‹‹ተቅዋ ማለት ይህው ነው፡፡›› ሲሉ መለሱ፡፡[1]

ወደ አላህ መልእክተኛﷺ ቀልብ ከማንም ይበልጥ የቀረቡት አላህን የሚፈሩት ሰዎች ናቸው፡፡ ሙአዝ ቢን ጀበል የአላህ መልእክተኛﷺ በላኩት ጊዜ ሊሸኙት አብረውት ወጡ፡፡ እርሱ እየጋለበ እርሳቸው ግን በእግራቸው ይጓዙ ጀመር፡፡ ተገቢውን መመሪያና ምክርም ለገሱት፡፡ ከዚያም እንዲህ አሉት፡-

‹‹ሙዓዝ ሆይ፣ ከዚህ ዓመት በኋላ ዳግም ላታገኘኝ ትችላለህ፡፡ ወይም ደግሞ በዚህ በመስጊዴ ወይም በቀብሬ አጠገብ ልታልፍ ትችላለህ፡፡››

ሙዓዝ ይህን ሲሰማ ከርሳቸው የመለየቱ ነገር ታሰበውና ተንሰቅስቆ አለቀሰ፡፡ ነቢዩም ወደ መዲና ፊታቸውን አዞሩና እንዲህ አሉት፡-

‹‹ለኔ ይበልጥ ተገቢ የሆኑ ሰዎች ማንም ይሁኑ የት አላህን የሚፈሩት ሰዎች ናቸው፡፡›› (አህመድና ሐይሰሚ)

## ዙህዳቸው

አብዛኞቹ መንግስታትና ሕዝቦች ወደውና ፈቅደው በአላህ መልእክተኛﷺ ስር ሁነዋል፡፡ መላ አረቢያን ያስተዳድሩ ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ የሚፈልጉትን ነገር ማድረግ ይችሉ ነበር፡፡ ይህም ሆኖ ግን እንደድሮው ቀላል ሕይወት መግፋትን መረጡ፡፡ እንዲህ ይሉ ነበር፡- ‹‹ለራሴ አንዳች ነገር የማድረግ አቅም የለኝም፡፡››

ሁሉም ነገር በአላህ ውሳኔ ብቻ እንደሚፈጸም አስተማሩ፡፡ ጊዜን ጊዜ ወልዶ ሐብት በገፍ ወደ መዲና የሚጎርፍበት ዘመን ደረሰ፡፡ የአላህ

[1] ኢብን ከሲር፣ ተፍሲረል ቁርአነል አዚም፣ በይሩት፣ 1988፣ ቅጽ 1 ገጽ 42

መልእክተኛﷺ ሁሉንም ንብረት ለተገቢ ሰዎች አከፋፍለው እርሳቸው ግን የዙህድ ሕይወትን መግፋት ቀጠሉ፡፡ እንዲህ ይሉ ነበር፡-

‹‹የኡሁድን ጋራ የሚያህል ወርቅ ቢኖረኝ የምደሰት አይደለሁም፡፡ ለእዳ ከምከፍለው ውጭ አንድም ዲናር ከእጄ የሌለኝ ሆኖ ወር ያልፋል፡፡›› (ቡኻሪና ሙስሊም)

‹‹ከአላህ መልእክተኛ ቤት ውስጥ የምግብ ማብሰያ እሳት ሳይነደድ ቀናት ያልፉ ነበር፡፡ ብዙ ጊዜ እየራባቸው የሚቀመስ አጥተው ባዶ ሆዳቸውን ይተኛሉ፡፡›› (አህመድ)

አነስ እንዲህ ሲሉ አውግተዋል፡-

አንድ ቀን ከአላህ መልእክተኛ ﷺ ዘንድ ገባሁ፡፡ ከአልጋቸው ላይ ተጋድመው ነበር፡፡ ኩታ ለብሰዋል፡፡ ከራሳቸው ስር በሳር የተጎዘጎዘ የቆዳ ትራስ ይገኛል፡፡ ሶሐቦቻቸው ወደርሳቸው ገቡ፡፡ ዑመርም አብረው ገቡ፡፡ መልእክተኛው ትንሽ ቀና አሉ፡፡ ከባዶ ሰሌን ላይ ጨርቅ ሳይነጠፍበት መተኛታቸውን ዑመር ተመለከቱ፡፡ የሰሌኑ ቅርጽ ከአካላቸው ላይ ወጥቷል፡፡ ዑመር ይህን ሲያዩ አለቀሱ፡፡ ነቢዩም፡- ‹‹ምን አስለቀሰህ?›› አሏቸው፡፡ ‹‹በአላህ እምላለሁ፣ እርስዎ ከኪስራና ከቀይሰር ይበልጥ ከአላህ ዘንድ የተከበሩ መሆንዎትን አውቃለሁ፡፡ እነርሱ በዓማዊ ጸጋዎች እየተጫወቱ እርስዎ ከሌጣ ሰሌን ላይ መተኛትዎ አሳዘነኝ፡፡›› አለ፡፡ ነቢዩም፡- ‹‹ዱንያ ለነርሱ፣ አኼራ ደግሞ ለኛ ቢሆን አትወድምን?›› አሏቸው፡፡ ዑመርም፡- ‹‹እወዳለሁ›› አሉ፡፡ ‹‹እንደዚሁ ሆኗል›› አሏቸው፡፡ (አህመድ)

የአላህ መልእክተኛﷺ የዚህች ዓለም ሕይወታቸውን በተመለከተ ሲናገሩ፡- ‹‹እኔና ዱንያ ምን አገናኘን፡፡ በዚህች ዓለም ውስጥ የኔ ምሳሌ ከአንዲት ዛፍ ጥላ ስር እንደተጠለለና ከዚያም ትቷት እንደሄደ ሰው ማለት ነን፡፡›› (ቲርሚዚ)

ሕይወታቸው ልክ እንደዚሁ ነበር፡፡ በዱንያ ጸጋዎች መጠየቅን ይፈሩ ነበር፡፡ እንዲህ በማለት ዱዓ ያደርጉ ነበር፡- ‹‹አላህ ሆይ፣ ሚስኪን

አድርገህ አኑረኝ። ሚስኪን አድርገህም ግደለኝ። በእለተ ቂያማም ከሚስኪኖች ጋር ቀስቅሰኝ።›› (ቲርሚዚና ቢን ማጃህ)

ነብያት ጀነት እንደሚገቡ ከአላህ ዋስትና የተሰጣቸው ቢሆንም እንደማንኛውም ሰው ጥያቄ እንደሚቀርብባቸው ያውቃሉ። መልእክታቸውን በትክክል ስለማድረሳቸው፣ አላህ ለሰጣቸው ጸጋ ተገቢውን ምስጋና ስለማድረሳቸው እንደሚጠየቁ እሙን ነው። አላህ እንዲህ ብሏል፦

﴿ فَلَنَسْـَٔلَنَّ ٱلَّذِينَ أُرْسِلَ إِلَيْهِمْ وَلَنَسْـَٔلَنَّ ٱلْمُرْسَلِينَ ۝٦ ﴾ الأعراف: ٦

*‹‹(መልዕክተኛ) የተላከላቸውን (ሕዝቦች) እንጠይቃለን። (መልዕክቱን አድራሽ) መልዕክተኞቹንም እንጠይቃለን።›› (አል አዕራፍ 6)*

ዙህድ፣ ተቅዋና ኢህሳን የሚሉት ቃላት ተቀራራቢ መልእክትና ይዘት ያላቸው ጽንሰ ሐሳቦች ናቸው። አስኳል መልእክታቸው የነፍስያን አደብ አልባ ጉጉት መገደብ፣ ለሽህዋ ልጓም ማበጀት ነው። ይህ ሲሆን፣ መንፈሳዊ ዝግጁነት ይፈጠራል። ሰውየው የቀልብ ንቃትንና የነፍስ ጥራትን ይጎናጸፋል። በቁርአን፦ ***‹‹ቀልበን ሰሊም›› (ሰላማዊ ቀልብ)*** የተባለው ይህ እንጅ ሌላ አይደለም። አላህን የመገዛት ዓላማ ይህን ቀልብ ማግኘት ነው። አላህ እንዲህ ብሏል፦

﴿ إِلَّا مَنْ أَتَى ٱللَّهَ بِقَلْبٍ سَلِيمٍ ۝٨٩ ﴾ الشعراء: ٨٩

*“አላህን በንጹሕ ልብ የተገናኘ ሲቀር።” (አል ሹዓራእ 89)*

የአላህ መልእክተኛ ﷺ ስሜተ ስስ ናቸው። ጥሩ ነገር ያስደስታቸዋል። መጥፎ ነገር ያስከፋቸዋል። አንድ ቀን አንድ ሰው ከመሬት ላይ ሲተፋ ተመለከቱትና ፊታቸው ቀላ። ባሉበት ሳይንቀሳቀሱ ቆሙ። ሶሐቦችም ፈጥነው አክታውን በአፈር ሸፈኑት። ከዚያ በኋላ ነቢዩ ﷺ ጉዟቸውን ቀጠሉ።

አለባበስን እና አካላዊ ገጽታን ማሳመርን አጥብቀው ያዝዙ ነበር፡፡ ሰውየው አለባበሱ ቆሻሻና የተዝረከረከ እንዲሆን አይፈልጉም፡፡ የተንጨባረረ ጸጉር፣ የቋሸሸ አካልና ልብስ ማየት አይሹም፡፡ አንድ ቀን መስጊድ ውስጥ እያሉ የራሱና የጺሙ ጸጉር የተንጨባረረ አንድ ሰው ገባ፡፡ ‹‹ውጣ›› ሲሉ በእጅ ምልክት አሳዩት፡፡ ጸጉሩን አስተካክሎ እንዲመለስ ማዘዛቸው ነበር፡፡ ሰውየው እንደታዘዘው አድርጎ ተመለሰ፡፡ እርሳቸውም እንዲህ አሉ፡-

‹‹ልክ እንደ ሰይጣን ጸጉሩ ተንጨባርሮ ከመምጣት ይህ የተሻለ አይደለምን?›› (በይሐቂ)

ሌላ ቀን ጸጉሩ በስርዓት ያልተያዘ እና የተንጨባረረ ሰው ተመለከቱና ፡- ‹‹ይህ ሰው ጸጉሩን የሚያበጅበት ነገር የለውምን?›› ሲሉ ተናገሩ፡፡ የቋሸሸ ልብስ የለበሰ ሰው አይተውም፡-

‹‹ይህ ሰው ልብሱን የሚያጥብበት ውሃ አጣን?›› አሉ፡፡ (አህመድና ነሣኢ)

በሌላ ጊዜ የነተበ ልብስ የለበሰ ሰው ተመለከቱና ፡- ‹‹ገንዘብ አለህን?›› አሉት፡፡ ‹‹አዎ››አለ፡፡ ‹‹ከምን አይነት ሐብት›› አሉት፡፡ ‹‹አላህ ግመሎች፣ ፍየሎች፣ ፈረሶችና ባሮች ሰጥቶኛል፡፡›› አላቸው፡፡ እንዲህ አሉት፡-

‹‹አላህ ገንዘብ ከሰጠህ የጸጋውንና የልቅናውን ፋና ካንተ ላይ ይመልከተው፡፡›› (አቡ ዳውድ፣ ነሣኢና አህመድ)

በሌላ ሐዲስ እንዲህ ማለታቸው ተዘግቧል፡-

‹‹አላህ የጸጋውን ፋና ከባሪያው ላይ ማየት ይፈልጋል፡፡›› (ቲርሚዚና አህመድ)

የአላህ መልእክተኛ ስብእና የስሜተ ስስነትን፣ የመልካም ባህሪን፣ የእዝነትንና የልዝብነትን ጫፍ የደረሰ ነው፡፡ ከርዳዳ ባህሪ ያላቸው ሰዎች ‹‹ሙሐመድ ሆይ››  በማለት አንጠልጥለው በመጥራት በቆረፈደ ቋንቋ

ቢያናግሯቸውም፡- ‹‹ምን ጉዳይ ልፈጽምላችሁ›› በማለት በለዘብታ ከማስተናገድ ባሻገር ክፉ አይመልሱም፡፡ (ሙስሊምና ቲርሚዚ)

‹‹የአላህ መልእክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እጅግ አዛኝ እና ትሁት ከመሆናቸው የተነሳ አገልጋዮቻቸውን ያግዙ ነበር፡፡›› (በይሐቂ)

በሕጻንነት ዘመናቸው እንኳ በጉንጭ አልፋ ክርክር ውስጥ ከአንድም ሰው ጋር አልተሳተፉም፡፡ እርሳቸው እጅግ የላቀ ስብእና ባለቤት ከመሆናቸው ጋር ቤተሰቦቻቸውንም በዚሁ ዓይነት ባህሪ ቀርጸዋል፡፡ ለዚህ አባባል ዓይነተኛው ናሙና የልጅ ልጃቸው ሐሰን ቢን አሊ ናቸው፡፡

በአንድ ወቅት ሐሰን የአላህን ቤት ጠዋፍ አደረጉ፡፡ ከዚያም ወደ መቃመ ኢብራሂም ሄዱና ሁለት ረከዓዎችን ሰገዱ፡፡ ቀጥሎም ጉንጫቸውን ከመቃሙ ላይ አደረጉና እያለቀሱ እንዲህ አሉ፡-

‹‹ባርያህ ከደጅህ ቆሟል፡፡ አገልጋይህ ከደጅህ ቆሟል፡፡ ለማኝህ ከደጅህ ቆሟል፡፡ ያንተ ድሃ ከደጅህ ቆሟል፡፡››

ይህንኑ ደጋግመው ካሉ በኋላ ሄደ፡፡ ዳቦ በሚመገቡ ድሃዎች አጠገብ ሲያልፉም ሰላምታ አቀረቡላቸው፡፡ ድሆችም ወደ ምግቡ ጋበዟቸው፡፡ ሐሰን አብረዋቸው ተቀመጡና ‹‹የሶደቃ ምግብ ባይሆን ኖሮ አብሪያችሁ እመገብ ነበር፡፡››አሉ፡፡ ከዚያም እንዲህ አሉ፡- ‹‹ተነሱና ወደቤት እንሂድ፡፡›› ሰዎች አብረዋቸው ሄዱ፡፡ ሐሰን መገቧቸው፣ አለበሷቸው፡፡ ገንዘብ እንዲሰጣቸውም አዘዙ፡፡ ይህ ልስልስ ባህሪ፣ ይህ አዛኝነት፣ ይህ ድንቅ ስነ ምግባር፣ ለፍጡራኑ እጅግ አዛኝ በሆነው አምላክ ባህሪ የመቀረጽ ጥሩ ተምሳሌት ነው፡፡

የሐሰን ሌላ አጋጣሚ የላቀ ስብእናቸውን ያመለክታል፡፡ ይህውም በአንድ የአትክልት ቦታ አጠገብ ሲያልፉ አንድ ልጅ እግር አገልጋይ አዩ፡፡ በእጁ ምግብ ይዟል፡፡ለራሱ  አንድ ሲጎርስ ለውሻውም አንድ ያጎርሳል፡፡ እንዲህ እያለ ምግቡን ከውሻው ጋር ተጋርቶ ተመገበ፡፡ ይህን ያስተዋሉት ሐሰን በዚህ ልጅ የአዛኝነት ድርጊት ተመሰጡ፡፡ የአላህን የእዝነት ባህሪ ከልጁ

ላይ ተመለከቱ፡፡ ‹‹ካንተ ጋር ምግብ እንዲጋራ ለምን አደረግክ፡፡ ለምን ለብቻው አልሰጠህውም?›› ሲሉ ጠየቁት፡፡ ‹‹ይሉኝታ ያዘኝ፡፡›› አላቸው፡፡ ‹‹የማን አገልጋይ ነህ›› አሉት፡፡ ‹‹የኢብን ዑስማን›› አለ፡፡ ‹‹የአትክልት ቦታህስ የማን ነው?›› ‹‹የኢብን ዑስማን ነው››  ይህ ባሪያ ከርሳቸው ጋር እንዲሆን ፈለጉ፡፡ ላዩን ሲያዩት ባሪያ ይመስላል፡፡ ውስጡ ግን ለአላህ በጣም የቀረበ ነው፡፡ ‹‹ተመልሸ እንደምመጣ በአላህ ምዬ አረጋግጥልሐለሁ›› አሉት፡፡ ከርሱ ተለይተው ሄዱና ባለቤቱን አግኝተው ባሪያውንም የአትክልት ቦታውንም ገዝተው ተመለሱ፡፡ ‹‹አንተ ልጅ ሆይ፣ ገዛሁህ›› አሉት፡፡ ‹‹አላህን፣ መልእክተኛውንና አንተን ለመታዘዝ ዝግጁ ነኝ›› አላቸው፡፡ ይህን ቃል ሲሰሙ ለልጁ ያላቸው ግምት ጨመረ፡፡ መገረማቸው ይበልጥ አከለ፡፡ ይህ ልጅ እውነተኛና ቀልበ ንጹህ ነው፡፡ እናም እንዲህ አሉት፡-

‹‹ለአላህ ስል ነጻ ለቅቄሃለሁ፡፡ የአትክልት ቦታውንም ሰጥቸሃለሁ፡፡››

ልጁም፡- ‹‹ጌታዬ ሆይ፣ የአትክልት ስፍራውን ለርሱ ስትል ለሰጠህኝ አምላክ  ሰጥቸዋለሁ፡፡››[1]

# አደብና አይናፋርነት

የአላህ መልእክተኛﷺ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው አይናገሩም፡፡ ሰዎችን በፈገግታ እና በለዘብታ ይቀበላሉ፡፡ ከርዳዳ ንግግር ሲሰሙም ከሰው ፊት ምንም ነገር አይናገሩም፡፡ ግና ንግግሩን አለመውደዳቸውን ገጽታቸው ይናገር ነበር፡፡ ይህም በመሆኑ በዙሪያቸው ያሉ ሰዎች ለንግግራቸውና ለእንቅስቃሴያቸው ይጠነቀቁ ነበር፡፡

ከአይናፋርነታቸው የተነሳ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው አይስቁም ነበር፡፡ ሳቃቸው ከፈገግታ ያለፈ አይደለም፡፡ ሶሐቦች የአላህን መልእክተኛ ﷺ አይናፋርነት ከጫጉላ ቤት ውስጥ ካለች ሙሽራ ጋር ያመሳስሉት ነበር፡፡

የአላህ መልእክተኛﷺ አይናፋርነትን (ሐያእ) ሲገልጹ እንዲህ ብለዋል፡-

---

[1] ቢን ሙንዚር፣ ሙኽተሰር ታሪኹ ደመሽቅ ቅ 7 ገጽ 25

‹‹ሐያእ የኢማን አካል ነው፡፡›› (ቡኻሪ)

‹‹ሐያእና ኢማን የማይነጣጠሉ ጓደኞሞች ናቸው፡፡ አንደኛው ከሌለ ሌላኛው አይኖርም፡፡›› (ቡኻሪ)

እዝነት ከአንድ ነገር ላይ ሲታከል ያስውበዋል፡፡ ከአንድ ነገር ላይ ሲጎድል ደግሞ አስቀያሚ ያደርገዋል፡፡›› (ሙስሊምና አቡ ዳውድ)

እውነተኛ ሐያእ ሞትን ማስታወስ ነው፡፡ ሞትን ማስታወስ የዱንያን ፍቅር ከልቦና ለማውጣት ጥሩ መንገድ ነው፡፡ የአላህ መልእክተኛﷺ ባልንጀሮቻቸውን አላህን ሐያእ እንዲያደርጉት ያዙ ነበር፡፡ አንድ ቀን ተከታዩን ምክር ለግሰዋል፡-

‹‹ለአላህ እውነተኛ ይሉኝታ ይኑራችሁ፡፡›› -ሶሐቦችም፡- ‹‹እኛ- አላህ የተመሰገነ ይሁን- ሐያእ አለን፡፡›› አሉ፡፡ እንዲህ አሏቸው፡- ‹‹ይህን ማለቴ አይደለም፡፡ ለአላህ ትክክለኛ ይሉኝታ ማለት ራስንና የያዘችውን፣ ሆድንና የሰበሰበችውን መጠበቅ፣ እንዲሁም ሞቶ መበስበስን ማስታወስ ነው፡፡ አኼራን የፈለገ የዱንያን ሽልማት ይተው፡፡ ይህን ያደረገ ለአላህ እውነተኛ ይሉኝታ (ሐያእ) አለው፡፡›› (ቲርሚዚ)

የአላህ መልእክተኛﷺ አንድን ሰው አተኩረው አያዩም፡፡ ዓይናቸውን ይመልሳሉ፡፡ ከሰማይ ይልቅ ወደ ምድር የሚያዩበት ጊዜ ይረዝማል፡፡ ከይሉኝታቸው የተነሳ እርሳቸው ባሉበት የሌላ ሰው ነውር እንዲነሳ አይፈቅዱም፡፡ አኢሻ እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛﷺ ስለ አንድ ሰው መጥፎ ድርጊት ከደረሳቸው፡- ‹‹እገሌ ለምን ይህን አደረገ›› በማለት ስሙን ጠርተው አይተቹትም፡፡ ይልቁንም፡- ‹‹አንዳንድ ሰዎች ይህን ማድረጋቸው አግባብ አይደለም›› ሲሉ በደፈናው ይተቻሉ እንጅ፡፡ (አቡ ዳውድ)

የአላህ መልእክተኛ ﷺ የሰዎችን ስህተት ማረም ሲፈልጉ፡- ‹‹እንዲህ እንዲህ ሲደረግ ማየቴ ለምንድን ነው›› ይሉ ነበር፡፡ (ሙስሊም)

አንድን ሰው ሲመክሩ ስሜቱ ተነክቶ እንዳይቆጣ ወይም እንዳያዝን ከፍተኛ ጥንቃቄ ያደርጉ ነበር፡፡ በእርግጥም የእዝነት የላቁ ተምሳሌት ነበሩና፡፡ መውላና ጀላሉ ዲን ሐቢበል ሐቅ ይህ ባህሪ ከሚንጸባረቅባቸው ሰዎች መካከል አንዱ እንደሆኑ ተስተውሏል፡፡ እንዲህ ይሉ ነበር፡-

‹‹አእምሮዬ ቀልቤን፡- ኢማን ምንድን ነው? በማለት ጠየቀው፡፡ ቀልቤም ወደ አእምሮዬ ጆሮ ጠጋ አለና፡- ኢማን ማለት አደብ ነው፣ አለው፡፡››

## ጀግንነታቸው

ከአላህ መልእክተኛﷺ የበለጠ ጀግና ይኖር እንደሁ ማሰብ ፍጹም ስህተት ነው፡፡ በሕይወታቸው ውስጥ አንድም ጊዜ በፍርሃት ሲረበሹ አልታዩም፡፡ አደጋዎችን በጽናት መጋፈጥ ባህሪያቸው ነበር፡፡ ፍርሃት እና መታወክ አንድም ጊዜ አሸንፏቸው አያውቅም፡፡ ሊገድሏቸው ባሰቡ ሰዎች አጠገብ ተከታዩን የቁርአን መልእክት እየቀሩ በድፍረት አልፈዋል፡-

﴿ إِنَّا جَعَلْنَا فِيٓ أَعْنَٰقِهِمْ أَغْلَٰلًا فَهِيَ إِلَى ٱلْأَذْقَانِ فَهُم مُّقْمَحُونَ ۝٨ وَجَعَلْنَا مِنۢ بَيْنِ أَيْدِيهِمْ سَدًّا وَمِنْ خَلْفِهِمْ سَدًّا فَأَغْشَيْنَٰهُمْ فَهُمْ لَا يُبْصِرُونَ ۝٩ ﴾ يس: ٨ - ٩

*‹‹በአንገቶቻቸው ዙሪያ እስከ አገጮቻቸው ድረስ ሰንሰለት (ቀንበር) አደረግን፡፡ በመሆኑም ራሳቸውን ዝቅ ማድረግ አይቻላቸውም፡፡ ከፊት ለፊታቸው ግርዶን አደረግን፡፡ ከኋላቸውም ግርዶን አደረግን፡፡ ሸፈንናቸውም፡፡ ስለዚህ እነርሱ አያዩም፡፡›› (ያሲን 8-9)*

አሊ ቢን አቢ ጧሊብ እንዲህ ሲሉ የነቢዩን ጀግንነት መስክረዋል፡-

‹‹በበድር እለት የአላህ መልእክተኛ ወደ ጠላት ከሁላችንም ይበልጥ የቀረቡ ነበሩ፡፡ ከሁላችንም በላቀ ጀግንነት ተፋልመዋል፡፡ እኛም ከጠላት ጥቃት በርሳቸው እንከለል ነበር፡፡›› (አህመድ)

በራእ የአላህን መልእክተኛ ጀግንነት ሲገልጽ እንዲህ ብሏል፡-

‹‹በአላህ እምላለሁ፣ አደጋ ሲበረታ በርሳቸው እንከለል (እንጠበቅ) ነበር፡፡ ከመካከላችን በጣም ጀግናው ከርሳቸው ጎን ተሰልፎ የሚፋለመው ነበር፡፡›› (ሙስሊም)

የአላህ መልእክተኛ ﷺ የአላህን ቃል የበላይ ለማድረግ የሚፋለሙት ምንጊዜም የመጀመሪያውን ረድፍ ይዘው ነበር፡፡ የሁነይን ዘመቻ እለት በጅማሬው ላይ የሙስሊሞች ጦር ሲፍረከረክ እርሳቸው ባሉበት ጸንተው በጀግንነት ተፋልመዋል፡፡ የጠላትን ረድፍ ሰንጥቀዋል፡፡ በቅሏቸውን እየጋለቡ ወደ ጠላት ወረዳ ሲገሰግሱ የሶሐቦቻቸውም ወኔ ተነሳሳ፡፡ ጀግንነታቸው ጨመረ፡፡ የጦርነቱ ሚዛንም ተቀየረ፡፡ በመጨረሻም ሙስሊሞች በአላህ ችሮታ እና እገዛ ድል ሊጨብጡ ቻሉ፡፡ (ሙስሊም)

የአላህ መልእክተኛﷺ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹የሙሐመድ ነፍስ በእጁ በሆነችው ጌታ እምላለሁ፣ በአላህ መንገድ ስፋለም ብገደል፣ እንደገና ዘምቼ ብገደል፣ ደግሞም ዘምቼ ብገደል እወዳለሁ፡፡›› (ሙስሊም)

## ሆደ ሰፊነታቸው

የአላህ መልእክተኛﷺ ገራገር ሰው ነበሩ፡፡ እናታችን አኢሻ እንዲህ ብለዋል፡-

ከአላህ መልእክተኛ የተሻለ ባህሪ ያለው አንድም ሰው የለም፡፡ ከባልደረቦቻቸው ወይም ከቤተሰቦቻቸው መሐከል አንዱ ሲጠራቸው ምላሻቸው ‹‹ለበይክ›› ብቻ ነው፡፡

በዚህ የላቀ ባህሪያቸው ሰበብ ተከታዩ የቁርአን መልእክት ወርዷል፡-

﴿ وَإِنَّكَ لَعَلَىٰ خُلُقٍ عَظِيمٍ ﴾ القلم: ٤

*‹‹አንተ የላቀ ሥነ-ምግባር ባለቤት ነህ፡፡›› (አል ቀለም 4)*

የአላህ መልእክተኛﷺ በግል ጉዳያቸው ተበቅለው አያውቁም፡፡ ሁሌም ይቅር ይላሉ፡፡ አኢሻ የነቢዩን ገራገርና ልስልስ ባህሪ የሚያጎሉ በርካታ ነገሮችን ታወጋናለች፡-

‹‹የአላህ መልእክተኛ እንስትን፣ አገልጋይን ሆነ ሌላን ሰው መትተው አያውቁም፡፡ በአላህ መንገድ በሚደረግ ትግል ውስጥ ቢሆን እንጅ፡፡ ለግል ጉዳያቸው ሰውን ተበቅለው አያውቁም፡፡ የአላህ እቀባ ካልተደፈረ በስተቀር፡፡ እንዲያ ሲሆን ግን ለአላህ ሲሉ ክብሩን ደፋሪውን ይቀጣሉ፡፡›› (ሙስሊም)

አነስ ስለ አላህ መልእክተኛﷺ ባህሪ ሲናገር እንዲህ ይላል፡-

‹‹ከአላህ መልእክተኛ ይበልጥ የሚያውድ ሽቶ አሽትቼ አላውቅም፡፡ ከአላህ መልእክተኛ የበለጠ ለስላሳ ሐር ወይም ሌላ ነገር ነክቼ አላውቅም፡፡››

ሳቢትም፡- ‹‹አቡ ሐምዛ ሆይ፣ የአላህ መልእክተኛ ﷺ አሁንም ድረስ አይታዩህምን? ቅላጼያቸውስ አይሰማህምን?›› በማለት ጠየቃቸው፡፡ አነስ እንዲህ አሉ፡-

‹‹አዎ፣ በአላህ እምላለሁ፣ በእለተ ቂያማ እንደማገኛቸውና፡- የአላህ መልእክተኛ ሆይ አገልጋይህ ነኝ፣ እንደምላቸው ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ መዲና ውስጥ ለአስር ዓመታት ያህል አገልግያቸዋለሁ፡፡ ልጅ ስለነበርኩ እንደሚፈልጉት አልሆንኩላቸውም፡፡ ግና አንድም ቀን ገላምጠውኝ ወይም ይህን ለምን አደረግክ፣ ይህን ለምን ሳታደርግ ቀረህ? ብለውኝ አያውቁም፡፡›› (ቡኻሪና ሙስሊም)

አቡ ሁረይራ እንዳወጉት አንድ በደዊን ከነቢዩﷺ መስጊድ ውስጥ ሸና፡፡ ሰዎች ተቆጡ፡፡ ሊያስቆሙትም አሰቡ፡፡ የአላህ መልእክተኛም እንዲህ አሉ፡-

‹‹ተውት፡ ከሽንቱም ላይ ባልዲ ውሃ አፍስሱበት፡፡ የተላካችሁት አግራሪዎች እንጅ አጥባቂዎች ሆናችሁ አይደለም፡፡›› (ቡኻሪ)

ከዚህ በኋላ የአላህ መልእክተኛ ለዚህ ሰው  የመስጊዱን ስነ ስርዓት በለዘብታ አስረዱት፡፡ አነስ የነቢዩን ሆደ ሰፊነት ሲገልጹ እንዲህ ብለዋል፡-

አንድ ቀን ከአላህ መልእክተኛﷺ ጋር በመሄድ ላይ ነበርን፡፡ ወፍራምና ከርዳዳ የነጅራን ኩታ ለብሰው ነበር፡፡ አንድ በደዊን አገኛቸውና ከአንገታቸው ላይ የመፈግፈግ ምልክት እስኪወጣ ድረስ ኩታቸውን በሐይል እየሳበ፡- ‹‹ሙሐመድ ሆይ፣ ካንተ ዘንድ ካለው የአላህ ገንዘብ እዘዝልኝ››አላቸው፡፡ መልእክተኛው ወደርሱ ዘወር አሉና ሳቁ፡፡ ገንዘብ እንዲሰጥጠውም አዘዙ፡፡ (ቡኻሪና ሙስሊም)

የአላህ መልእክተኛﷺ መልእክታቸውን በማድረሱ ሂደት ስኬታማ የሆኑት በዚህ የላቀ ስነ ምግባራቸውና ሆደሰፊነታቸው በረከት ነው፡፡ ይህን በተመለከተ አላህ ሲናገር እንዲህ ብሏል፡-

﴿ فَبِمَا رَحْمَةٍ مِّنَ ٱللَّهِ لِنتَ لَهُمْ ۖ وَلَوْ كُنتَ فَظًّا غَلِيظَ ٱلْقَلْبِ لَٱنفَضُّوا۟ مِنْ حَوْلِكَ ۖ ﴾ آل عمران: ١٥٩

*‹‹ለነርሱ ፀባየ መልካም መሆንህ ከአላህ እዝነት የመነጨ ነው፡፡ ፀባየ ክፉና ልበ ደረቅ በሆንክ ኖሮ ከዙሪያህ በተበተኑ ነበር፡፡›› (አል ዒምራን 159)*

የዚያ ዘመን የጃሂልያ ሰዎች ከአላህ መልእክተኛﷺ ለስላሳ ስብእና ፊት እንደ ሻማ ይቀልጡ ነበር፡፡ በይቅርባይነታቸው፣ በመልካም ባህሪያቸው፣ በሆደሰፊነታቸው በቀላሉ ይማረኩ ነበር፡፡ በመጨረሻም ከስርዓት አልባና አውሬያዊ ባህሪያቸው ተላቀው እጅግ ለስላሳና ምቹ ሆኑ፡፡ የአላህ መልእክተኛﷺ አንድንም ሰው ማጣት አይፈልጉም ነበር፡፡ ለሁሉም መቀናትን ይመኛሉ፡፡ የቅጣት ሳይሆን የእዝነት ተምሳሌት ሆነው ኖረዋል፡፡

## ርህራሄያቸው

የአላህ መልክተኛﷺ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹ለአዛኞች አዛኝ አምላክ ያዝንላቸዋል፡፡ ስለዚህም ከሰማይ ውስጥ ያለው ያዝንላችሁ ዘንድ ከምድር ላይ ላሉት እዘኑላቸው፡፡›› (ቲርሚዚ)

ሶላት ውስጥ ሆነው የሕጻን ለቅሶ ሲሰሙ እናቱ እንዳትታወክ በመስጋት ሶላታቸውን ያሳጥራሉ። ሌሊት ሶላት ውስጥ ቁመው ለኡመታቸው እያለቀሱ ዱዓ ሲያደርጉ ያድራሉ። ሙሉ ጊዜያቸውን ሰዎችን ከእሳት ለማዳን ተግባር ያውላሉ። እነዚህ ሁሉ የአላህን መልእክተኛ ጥልቅ የርህራሄ ስሜት የሚያመለክቱ ናቸው።

ምክንያቱም የተላኩት የአለማት እዝነት ተደርገው ነውና። እዝነታቸውና ፍቅራቸው ፍጡራንን ሁሉ አጠቃልሏል። አንድ ቀን በጣኦታውያን ላይ ዱዓ ያደርጉ ዘንድ ሶሐቦች ሲጠይቋቸው ምላሻቸው እንዲህ የሚል ነበር፡-

‹‹የተላክኩት አዛኝ እንጅ ተራጋሚ ተደርጌ አይደለም።›› (ሙስሊም)

የእስልምናን መልእክት ለማድረስ ወደ ጧኢፍ በተጓዙ ጊዜ ጣኦታውያን በድንጋይ እየደበደቡ አደሟቸው። ወዲያውም የተራራው መላኢካ ከጅብሪል ጋር በመምጣት፡- ‹‹እነዚህን ሕዝቦች እንዳጠፋልህ ከፈለግክ ተራራዎችን አጋጥሜ አጠፋቸዋለሁ›› አላቸው። ምላሻቸው ተከታዩ ነበር፡-

‹‹አላህን ያለ ተጋሪ በብቸኝነት የሚያመልኩ ልጆችን አላህ ከአብራካቸው እንደሚፈጥር ተስፋ አደርጋለሁ።›› (ቡኻሪና ሙስሊም)

የአላህን መልእክተኛﷺ በጣም ያሰቃዩ እና ደብድበው ከአገራቸው ያባረሯቸው፣ እስከ ዘጠነኛው ዓመተ ሂጅራ ድረስም ሙስሊሞችን ያሰቃዩና ብዙ ኪሣራ ያደረሰባቸው የጧኢፍ ሰዎችን በተመለከተ መልእክተኛውﷺ እንዲህ ሲሉ ዱዓ አድርገውላቸዋል፡-

‹‹አላህ ሆይ፣ የሰቂፍን ጎሳ አቅና። አምጣቸውም።››

ይህን ዱዓ ማድረጋቸውን ቀጠሉ። በመጨረሻ የጧኢፍ ሰዎች ወደ መዲና መጡ። እስልምናንም ተቀበሉ። (ኢብን ሂሻምና ቲርሚዚ)

አቡ ኡበይድ ከባህረይን ምርኮ ይዞ መጣ። ከመሐከል አንዲት እንስት ነበረች። ስታለቅስ የአላህ መልእክተኛ አዩአት፡- ‹‹ምን ሆነሽ ነው?››

ሲሉ ጠየቋት፡፡ ‹‹ልጄን ሸጠብኝ›› አለች፡፡ ‹‹እውነት ነውን?›› ሲሉ አቡ ኡበይድን ጠየቁት፡፡ ‹‹አዎ›› አላቸው፡፡ ‹‹ለማን››አሉት፡፡ ለበኒ አብስ ጎሳ ሰው አላቸው፡፡ ‹‹ራስህ ጋልበህ ሄደህ ይዘህላት ና››አሉት፡፡ (ከንዘል ኡማል)

የአላህ መልእክተኛﷺ እዝነት ዱንያን ሁሉ አጠቃልሏል፡፡ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹እስካልተዋደዳችሁ ድረስ አታምኑም፡፡ የምትዋደዱበትን ነገር ላመላክታችሁን?›› ‹‹አዎ››አሏቸው፡፡ ‹‹በመካከላችሁ ሰላምታን አብዙ፡፡ ትዋደዳላችሁ፡፡ ነፍሴ በእጄ በሆነችው ጌታ እምላለሁ፡፡ እስካልተዛዘናችሁ ድረስ ጀነት አትገቡም፡፡›› አሉ፡፡ ‹‹የአላህ መልእክተኛ ሆይ፣ ሁላችንም እናዝናለን›› አሏቸው፡፡ ‹‹የእርስ በርስ መተዛዘናችሁን ማለቴ አይደለም፡፡ አጠቃላይ የሆነን መተዛዘን እንጅ፡፡›› አሉ፡፡ (አል ሐኪም)

## ይቅር ባይነታቸው

አላህ ይቅርባይነትን ይወዳል፡፡ አንድ ሰው ለጥፋቱ ከልቡ ከተጸጸተ አላህ ተውበቱን ሊቀበለው ቃል ገብቷል፡፡ ይህም በመሆኑ ባሮቹም ልክ እንደርሱው ይቅርባይ እንዲሆኑ ይከጅላል፡፡ የይቅርባይነት መስፈርት ጸጸትና የአላህን ትእዛዝ ማክበር፣ እርሱ ከከለከለው መታቀብ ነው፡፡ በአላህ መልእክተኛﷺ ሕይወት ውስጥ በርካታ የይቅርባይነት አድራጎቶችን እናገኛለን፡፡ ለምሳሌ ሂንድን ይቅር ብለዋታል፡፡ መካን በድል በተቆጣጠሩ ቀን ነበር የሰለመችው፡፡ ሃምዛን የኡሁድ እለት ያስገደለችና ጉበታቸውን ያኘከች እንስት ናት፡፡

ሁባር ቢን ኡሰይድ የእስልምና ቀንደኛ ጠላት ነበር፡፡ የመልእክተኛው ልጅ ዘይነብ ወደ መዲና በተሰደደች ጊዜ ግመሏን በቀስት ወግቶ አስበርግጎታል፡፡ ዘይነብም ወደቀች፡፡ ክፉኛ ተጎዳች፡፡ ጽንሷንም አስወረዳት፡፡ ብዙ ደም ፈሰሳት፡፡ ለከፋ አደጋም አጋለጣት፡፡ በዚህ ጦስ ሰበብ ለሕልፈት በቃች፡፡ ሁባር ከዚህም በላይ ሌሎች በርካታ ወንጀሎችን ፈጽሟል፡፡ ነቢዩ ﷺ መካን በድል በተቆጣጠሩ ጊዜ አመለጠ፡፡

መልእክተኛው ﷺ አንድ ቀን ከባልደረቦቻቸው ጋር መዲና ውስጥ ተቀምጠው እያለ ሁባር በድንገት ከፊታቸው ቆመና እንዲህ አለ፡-

‹‹የአላህ መልእክተኛ ሆይ፣ ሰላም ባንተ ላይ ይስፈን፡፡ ከአላህ ሌላ አምላክ እንደሌለና ሙሐመድም መልእክተኛው እንደሆኑ እመሰክራለሁ፡፡ ካንተ ሸሽቸ ሄድኩ፡፡ ከባዕድ ሕዝቦች ጋርም ለመቀላቀል ወሰንኩ፡፡ ግና ወደ መዲና መመለስህን፣ ቸርነትህን፣ በጎ አድራጊነትህን እና ለበደሉህ ሁሉ ይቅር ባይነትህን ሰምቼ ተመለስኩ፡፡ የአላህ መልእክተኛ ሆይ፣ ጣኦት አምላኪዎች ነበርን፡፡ አላህ ባንተ አማካይነት መቀናትን ለገሰን፡፡ ከጥፋትም አዳነን፡፡ ስለዚህም ጥፋቴን ይቅር በለኝ፡፡ ባንተ ላይ የፈጸምኩትን ክፉ ድርጊት ሁሉ ማረኝ፡፡ ጥፋቴን አምኛለሁ፡፡ ሐጢአቴን ተናዝዣለሁ፡፡››

የአላህ መልእክተኛ ﷺ እንዲህ አሉ፡-

‹‹ይቅር ብዬሐለሁ፡፡ አላህ ወደ እስልምና ስለመለሰህ ትልቅ ውለታ ውሎልሐል፡፡ ኢስላም ከርሱ በፊት የተፈጸሙ ጥፋቶችን ሁሉ ያብሳል፡፡››

ማንም ሰው እንዳይሰድበውና እንዳይወቅሰው መልእክተኛው ﷺ ከለከሉ፡፡[1]

ዒክሪመት ቢን አቡ ጀህል የታወቀ የኢስላም ጠላት ነበር፡፡ የፈትህ እለት ከመካ ሸሽቶ አመለጠ፡፡ ባለቤቱ ኡም ሐኪም ቢንት ሐሪስ ቢን ሂሻም ትባላለች፡፡ አስተዋይ እንስት ናት፡፡ እስልምናን ተቀበለች፡፡ ወዲያውም ለባሏ ከመልእክተኛው ዘንድ የደህንነት ዋስትና ጠየቀች፡፡ ወደ መካ እንድትመልሰው አዘዟት፡፡ ፍለጋ ጀመረች፡፡ እንዳገኘችውም እንዲህ አለችው፡-

‹‹ከማንም በላይ ዝምድናን ቀጣይ፣ በጎ ሰሪ እና መልካም ከሆነ ሰው ዘንድ ነው የመጣሁት፡፡ የደህንነት ዋስትና ጠይቄው ሰጥቶኛል፡፡››

---

[1] አል ዋቂዲ ቅ 2 ገጽ 857-858

ኢክሪማ ከርሷ ጋር ተመለሰ፡፡ ወደመካ ሲቃረብ የአላህ መልእክተኛﷺ ለሶሐቦቻቸው እንዲህ አሉ፡-

‹‹ኢክሪማ ቢን አቡ ጀህል አማኝ ሆኖ ወደናንተ ይመጣል፡፡ ስለዚህ አባቱን አትስደቡበት፡፡ ሟችን መስደብ ሕያውያንን ይጎዳል፡፡ ለሟችም አይደርሰውም፡፡››

ከመልእክተኛውﷺ በር ላይ ሲደርስ አበሰሩት፡፡ በደስታ ፈካ፡፡ ቆመውም ተቀበሉት፡፡ (ሐኪም)

‹‹ስደተኛው ጋላቢ እንኳን ደህና መጣህ››አሉት፡፡ (ቲርሚዚ)

ይቅር አሉትም፡፡ የፈጸመባቸውን ክፉ ነገር ፈጽሞ አላወሱም፡፡

የአላህ መልእክተኛﷺ ተከታዩን ዱዓ አብዝተው ያደርጉ ነበር፡-

‹‹አላህ ሆይ፣ ወገኖቼን አያውቁምና ማርልኝ፡፡›› (ቡኻሪ)

የተሚማህ ጎሣ አለቃ ሱማመት ቢን አሳል የሰለመ ጊዜ እንዲህ አለ፡-

‹‹ከአላህ ሌላ አምላክ እንደሌለና ሙሐመድም የአላህ መልእክተኛ መሆናቸውን እመሰክራለሁ፡፡ ሙሐመድ ሆይ፣ በአላህ እምላለሁ እንዳንተ የምጠላው ሰው በምድር ላይ አልነበረም፡፡ አሁን ግን ከማንም በላይ ከኔ ዘንድ ተወዳጅ ሆንክ፡፡ በአላህ እምላለሁ፣ እንደ ሐይማኖትህ የምጠላው ሌላ ሐይማኖት አልነበረም፡፡ አሁን ግን ከየትኛውም ሐይማኖት በላይ ያንተ ሐይማኖት ከኔ ዘንድ ተወዳጅ ሆነ፡፡ በአላህ እምላለሁ፣ ከአንተ አገር ይበልጥ የምጠላው አገር አልነበረም፡፡ አሁን ግን ሃገርህን ከየትኛውም ሃገር በላይ እወደዋለሁ፡፡ ዑምራ እንዳደርግ ፍቀድልኝ፡፡››

የአላህ መልእክተኛ ﷺ አበሰሩት፡፡ ዑምራ እንዲያደርግም ፈቀዱለት፡፡ መካ በደረሰ ጊዜ አንድ ሰው፡- ‹‹ከአያት ቅድመ አያቶችህ እምነት አፈነገጥክ›› አለው፡፡ እርሱም እንዲህ ሲል መለሰ፡-

‹‹ትክክል አይደለህም። የአላህ መልእከተኛ ከሆነው ከሙሐመድ ጋር ሰለምኩ እንጅ። በአላህ እምላለሁ፣ ነቢዩ እስኪፈቅዱ ድረስ ከየማማ አንዲት ፍሬ ስንዴ አይመጣላችሁም።›› (ቡኻሪ)

ሱማማ ከጣኦታውያን ጋር የነበረውን የንግድ ግንኙነት አቋረጠ። ቁረይሾች የምግብ እህል የሚሸምቱት ከየመን ነበር። የመካ ሰዎች ለረሃብ ተጋለጡ። ከዚህ መከራ ይታደጓቸው ዘንድም የአላህን መልእክተኛ ተማጸኑ። የአላህ መልእክተኛም ﷺ የንግድ ግንኙነቱን እንዲቀጥል የሚያዝ ደብዳቤ ለሱማማህ ጻፉለት።[1]

ጣኦታውያን ሙስሊሞችን ለስድስት አመታት ያህል አጠቃላይ ማእቀብ በመጣል በረሃብ እንደቀጧቸው ዘንግተዋል። የአላህ መልእክተኛም ﷺ ይህን ድርጊታቸውን ይቅር አሏቸው።

በሰባተኛው ዓመተ ሂጅራ፣ ከኸይበር ድል በኋላም የመካ ሰዎች በድርቅ መጠቃታቸውን ነቢዩ ﷺ ሰሙ። እህልህና ወርቅም ላኩላቸው። አቡ ሱፍያን እርዳታቸውን ተቀብሎ ለድሆች አከፋፈለ። እንዲህ ሲልም አመሰገናቸው፦

‹‹የወንድሜን ልጅ አላህ ምንዳ ይክፈለው። ሲበዛ ዝምድናን ቀጣይ ነው።››[2]

የመካ ሰዎች እስልምናን እንዲቀበሉ፣ ቀልባቸው እንዲለዝብ ያደረገው ይህ የአላህ መልእክተኛ ﷺ ድንቅ ስብእና ነበር። የሁደይቢያህ ዘመቻ ጊዜ የጣኦታውያን ጦር የአላህን መልእክተኛ ﷺ አጠቃ። ዓላማው እርሳቸውን መግደል ነበር። አልተሳካለትም። ሁሉም አባላቱ ተማረኩ። መልእክተኛው ግን ይቅር አሏቸው። (ሙስሊም)

ከኸይበር ዘመቻ በኋላ አንዲት አይሁድ እንስት በአላህ መልእክተኛ ﷺ ምግብ ላይ መርዝ አረደገች። መልእክተኛው ﷺ ምግቡን ወደ አፋቸው

---

[1] ቢን አብዱልባር

[2] አል የእቁብ፣ አልታሪኽ ቅ 2 ገጽ 56

አስጠግተው መለሱት። ሴትዮዋ ተይዛ ቀረበች። መርዝ ማድረጓንም አመነች። መልእክተኛው ግን ይቅር አሏት። (ቡኻሪ)

ለቢድ የተባለው አይሁዳዊ ሙናፊቅ ድግምት እንዳደረገባቸው እና ለከፋ በሽታ እንደዳረጋቸው ቢያውቁም እንደዚሁም ይህን ወንጀል እንዲፈጸም የገፋፋው ማን እንደሆነ ቢያውቁም ወንጀሉን በይቅርታ አልፈውታል። ለቢድንም ሆነ ከጎሳው አባላት አንዱንም ሰው አልተቀበሉም። (ቡኻሪና ሙስሊም)

አላህ ይቅርባይነትን በማስመልከት እንዲህ ብሏል፡-

﴿ خُذِ ٱلۡعَفۡوَ وَأۡمُرۡ بِٱلۡعُرۡفِ وَأَعۡرِضۡ عَنِ ٱلۡجَٰهِلِينَ ١٩٩ ﴾ الأعراف: ١٩٩

*‹‹ይቅር ባይ ሁን። በመልካምም እዘዝ። ከማሃይማንም ራስህን አግልል።›› (አል አዕራፍ 199)*

የአላህን መልእክተኛﷺ የሚወዱና አርአያነታቸውን የሚከተሉ ደጋግ የአላህ ባሮችም ይቅርባይነት መገለጫቸው ነበር። የአላህን ይቅርታ ለማግኘት ተስፋ በማድረግ ሰዎችን ይቅር ይላሉ።

# የጎረቤትን ሐቅ መጠበቅ

የአላህ መልእክተኛﷺ የጎረቤትን ሐቅ ለመጠበቅ በጣም ጉጉ ነበሩ። እንዲህ ሲሉ ተናግረዋል፡-

‹‹ጅብሪል ስለ ጎረቤት፣ የውርስ ባለመብት ያደርገዋል ብዬ እስካስብ ድረስ፣ ኑዛዜ አስተላለፈልኝ።›› (ቡኻሪና ሙስሊም)

በሌላ ሐዲስ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹ጎረቤቶች ሦስት ዓይነት ናቸው። ሦስት መብቶች ያሉት ጎረቤት አለ። ሁለት መብቶች ያሉት ጎረቤት አለ። አንድ መብት ብቻ ያለው ጎረቤት አለ። ሦስት መብቶች ያሉት ጎረቤት ሙስሊም የቅርብ ዘመድ የሆነ ሲሆን፣ የጉርብትና፣ የሙስሊምነትና የዝምድና መብት አለው። ሁለት

መብቶች ያሉት ደግሞ ዘመድ ያልሆነ ሙስሊም ጎረቤት ሲሆን፣ የጉርብትናና የሙስሊምነት መብቶች አሉት፡፡ አንድ መብት ያለው ደግሞ ሙስሊምም የቅርብ ዘመድም ያልሆነ ጎረቤት ሲሆን፣ የጉርብትና መብት አለው፡፡›› (በይሐቂና ሱዩጢ)

የጎረቤትን መብት መጋፋት በብዙ መልኩ ይገለጻል፡፡ ለምሳሌ አጮልቆ ሚስጥሩን ማየት፣ በምግብ ሽታ ማወክ፣ የማይወደውን ድርጊት መፈጸም፡፡ ይህም በመሆኑ የአላህ መልእክተኛﷺ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹ከአላህ ዘንድ መልካሙ ባልንጀራ ለባልንጀራው መልካም የሆነው ነው፡፡ ከአላህ ዘንድ መልካሙ ጎረቤት ለጎረቤቱ መልካም የሆነው ነው፡፡›› (ቲርሚዚ)

በሌላ ሐዲስ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹እርሱ ጠግቦ፣ ከጎኑ ያለው ጎረቤቱ ግን ተርቦ የሚያድር ሰው አማኝ አይደለም፡፡›› (አልሐኪም)

አቡ ዘር እንዳወጉት ምግብ በሚሰሩ ጊዜ መረቁን አብዝተው እንዲቀቅሉትና ለጎረቤቶቻቸው እንዲያቀምሱ የአላህ መልእክተኛﷺ አዘዋቸዋል፡፡ እንዲህ ብለዋቸዋል፡-

‹‹አቡ ዘር ሆይ፣ ምግብ ስታበስል መረቁን አብዛው፡፡ ጎረቤቶችህንም አቋጥር፡፡›› (ሙስሊም)

‹‹ምግብ ስታበስል መረቁን አብዛው፡፡ ለጎረቤቶችህም እየጨለፍክ አቃምስ፡፡›› (ቢን ማጃህ)

አቡ ዘር ከሶሐቦች ሁሉ መሐል ድሃው ሶሐባ ነበሩ፡፡ ይህም ማለት ድሆች እንኳ ጎረቤቶቻቸውን ላለማቋጠር ድህነት ምክንያት ሊሆናቸው አይችልም ማለት ነው፡፡

አቡ ሁረይራ እንዳወጉት የአላህ መልእክተኛ ﷺ፡- ‹‹በአላህ እምላለሁ፣ አላመነም፡፡ በአላህ እምላለሁ አላመነም፡፡ በአላህ እምላለሁ አላመነም፡፡›› በማለት ተናገሩ፡፡ ‹‹የአላህ መልእክተኛ ሆይ፣ ያላመነው ማንነው?››

ተብለው ተጠየቁ፡፡ ‹‹ጎረቤቱ ተንኮሉን የማያምነው ሰው አላመነም›› ሲሉ መለሱ፡፡ (ቡኻሪና ቲርሚዚ)

በሌላ ዘገባም እንዲህ ማለታቸው ተወስቷል፡-

‹‹ጎረቤቱ ተንኮሉን የማያምነው ሰው ጀነት አይገባም፡፡›› (ሙስሊም)

## ድሆችን መንከባከብ

የአላህ መልእክተኛﷺ ለድሆች፣ ለየቲም፣ ለባል አልባ እንስቶች እና ለባይተዋሮች የተለየ እንክብካቤ ያደርጉ ነበር፡፡ (ቡኻሪና ሙስሊም)

እጅግ ያዝኑላቸዋል፡፡ ችግራቸውን እንዲረሱ ፣ መከራቸውን እንዳያስታውሱ ለማድረግ በተለየ ሁኔታ ይንከባከቧቸዋል፡፡ አቡ ሰኢድ አልኹድሪ እንዲህ ሲሉ አውግተዋል፡-

አንድ ቀን ከተወሰኑ የሙሐጅር ድሆች ጋር ተቀመጥኩ፡፡ ከመታረዛቸው የተነሳ አንዱ በሌላው እየተከለለ ሃፍረተ ገላውን ይሸፍናል፡፡ ከመካከላችን አንዱ ቁርአን ያነብልን ነበር፡፡ የአላህ መልእክተኛﷺ መጡና ካጠገባችን ቆሙ፡፡ በዚህ ጊዜ ቁርአኑን የሚያነበው ሰው ጸጥ አለ፡፡ ሰላምታ አቀረቡልን፡፡ ‹‹ምን እያደረጋችሁ ነው?›› ሲሉም ጠየቁን፡፡ ‹‹የአላህ መልእክተኛ ሆይ፣ ከመካከላችን አንዱ ቁርአን እያነበበልንና እኛም እያደመጥን ነው፡፡›› አልናቸው፡፡ ‹‹ዘወትር ከነርሱ ጋር እሆን ዘንድ የታዘዝኩባቸውን ሰዎች ከተከታዮቼ መካከል ያደረገ አምላክ የተመሰገነ ይሁን፡፡›› አሉና ከኛው ጋር ከመሐከላችን ተቀመጡ፡፡ ክብ እንድንሰራም በእጃቸው አመላከቱን፡፡ እንዲህም አሉ፡-

‹‹የሙሐጅር ድሆች ሆይ፣ በእለተ ቂያማ በሙሉ ብርሃን አበስራችኋለሁ፡፡ ከሃብታሞች ግማሽ ቀን ቀድማችሁ ጀነት ትገባላችሁ፡፡ ይህም ማለት አምስት መቶ ዓመታት ማለት ነው፡፡›› (አቡ ዳውድ)

አንድ ቀን የአላህ መልእክተኛﷺ መዲና ውስጥ ተቀምጠው እያለ ባዶ እግራቸውን የሆኑና የተራቆቱ፣ ከረሃባቸውና ከሐሩሩ ጥናት የተነሳ አጥንታቸው የቀረ ሰዎች መጡ፡፡ የአላህ መልእክተኛﷺ የችግራቸውን

ጥናት ሲመለከቱ ፊታቸው ተቀያየረ። ወደ ውስጥም ገቡ። ወዲያውም ቢላል መጣ። አዛንና ኢቃማም አደረገ። ነቢዩﷺ አሰገዱ። ሶሐቦቻቸውንም እነዚህን ድሆች እንዲረዱና እንዲመጸውቱ አነሳሱ። ሶሐቦች እርዳታቸውን አጎረፉ። ነቢዩ ይህን ሲመለከቱ ፊታቸው ፈካ። እፎይታም ተሰማቸው። (ሙስሊም)

የመልእክተኛው ﷺ ሕይወት በቸርነት፣ በቀጥተኛነት፣ በእውነትና ታማኝነት፣ እንዲሁም በእዝነትና በርህራሄ የተሞላ ነው። ለአኢሻ ተከታዩን ምክር ለግሰዋታል፡

‹‹አኢሻ ሆይ፣ ድሃን አትመልሽ። የተምር ክፋይ እንኳ ቢሆን መጽውች። አኢሻ ሆይ፣ ድሆችን ውደጅ። አቅርቢያቸውም። አላህ በእለተ ቂያማ ያቀርብሽ ዘንድ።›› (ቲርሚዚ)

ኡባዳ ቢን ሽራሐይቢል እንዲህ ሲል አውግቷል፡-

ረሃብ ተሰማኝና ከመዲና የአትክልት ቦታዎች ወደ አንዱ ገባሁ። የእህል እሸት ዘንጣፊም ተመገብኩ። በልብሴም ያዝኩ። ባለቤቱ መጣና መታኝ። ልብሴንም ወሰደብኝ። ከነቢዩﷺ ዘንድ መጣሁ። እንዲህ አሉት፡-

‹‹አላዋቂ ከሆነም አላስተማርከውም። እርቦት ከሆነም አላበላህውም።››

ልብሴን እንዲመልስልኝም አዘዙት። መለሰልኝ። አንድ ወይም ግማሽ ‹‹ወሰቅ››[1] እህልም ሰጡኝ። (አቡ ዳውድና ነሣኢ)

ይህ ሐዲስ እንደሚያመለክተው ኢስላም በመጀመሪያ የወንጀሉን ምክንያት ይፈትሻል። ሰበቡን ለማጥፋትና ወንጀለኞችን ለማስተካከልም ይጥራል። ከዚህ የተነሳ በእስልምና ሸሪዓ ውስጥ የወንጀሎች መቅጫ ሕግጋት በወላጅ ቁንጥጫ ይመሰሏሉ። ወላጆች ልጆቻቸውን የሚቀጡት እንዲስተካከል እንጅ ለመጉዳት ወይም ለመበቀል አይደለም። ኢስላማዊ የሸሪዓ ቅጣቶችም እንደዚሁ አላማቸው ወንጀለኛውን ከማሕበራዊ

[1] የእህል መለኪያ

ሕይወት ማባረር ሳይሆን አስተካክሎና ገርቶ ለአዲስ ሕይወት ማዘጋጀትና ወደ ማሕበረሰቡ መቀላቀል ነው፡፡

# የምርኮኞችና የአገልጋዮች አያያዝ

የአላህ መልእክተኛﷺ እዝነት ለጦር ምርኮኞች ሳይቀር ተትረፍርፏል፡፡ ምርኮኞች በእንክብካቤ እንዲያዙ መልእክተኛው ያስተምሩ ነበር፡፡ የሙስአብ ቢን ዑመይር ወንድም አቡ ዓዚዝ እንዲህ ሲል አውግቷል፡-

ከበድር ምርኮኞች መሐል አንዱ ነበርኩ፡፡ የአላህ መልእክተኛﷺ እንዲህ የሚል ትእዛዝ አስተላለፉ፡-

‹‹ምርኮኞችን በበጎ ሁኔታ ትይዙ ዘንድ አደራ እላችኋለሁ፡፡››

ከአንሷሮች ዘንድ ሆንኩ፡፡ በሚመገቡ ጊዜ የነቢዩን አደራ ለመጠበቅ ሲሉ እነርሱ ተምር በልተው እኔን ግን ስንዴ ይመግቡኛል፡፡ ከመካከላቸው አንዱ ቁራሽ ዳቦ ሲያገኝ ምንጊዜም ለኔ ይሰጠኛል፡፡ እኔ ይሉኝታ ይዞኝ ስመልስት ቅንጣት ሳይነካለት መልሶ ይሰጠኛል፡፡›› (አልሐይሰሚና ቢን ሂሻም)

የአላህ መልእክተኛﷺ ከርሳቸው መምጣት በፊት በዓለም ላይ ሰፍኖ የነበረውን የባሪያ አሳዳሪ ስርዓት በሂደትና ደረጃ በደረጃ ለማስወገድ የሚረዱ እርምጃዎችን መውሰዳቸው ይታወቃል፡፡ ሰዎች ባሮቻቸውን ነጻ ይለቁ ዘንድ በየአጋጣሚው ያበረታቱ ነበር፡፡ ባሪያን ነጻ መልቀቅ ትልቅ ኢባዳ መሆኑን አስተምረዋል፡፡ የወንጀል ዋነኛው ማካካሻ ባሪያን ነጻ መልቀቅ ነበር፡፡ መልእክተኛውﷺ ይህን ጉዳይ ትኩረት ሰጥተው አስተምረዋል፡፡ በመሆኑም የነቢዩﷺ የቅርብ ወዳጅ አቡበክር አብዛኛውን ገንዘባቸውን ያዋሉት ባሮችን እየገዙ ነጻ ለመልቀቅ ተግባር ነው፡፡

መዕሩር ቢን ሱወይድ እንዲህ ሲሉ አውግተዋል፡-

‹‹አቡዘርን በረበዛህ ውስጥ አገኘሁኋቸው፡፡ የሚያምር ልብስ ለብሰዋል፡፡ አገልጋያቸውም ተመሳሳይ ልብስ ለብሷል፡፡ ስለዚህ ጉዳይ ጠየቅኋቸው፡፡ ተከታዩን ነገሩኝ፡-

አንድን ሰው ተሳደብኩ። እናቱን አነወርኩበት። ነቢዩም ﷺ እንዲህ አሉኝ፡-

‹‹አቡ ዘር ሆይ፣ እናቱን ማነወርህ ተገቢ አይደለም። የጃሂልያ ቅሪት ያለብህ ሰው ነህ። አገልጋዮቻችሁ ወንድሞቻችሁ ናቸው። አላህ ወንድሙን ከስሩ ያደረገለት ሰው ከሚመገበው ይመግበው። ከሚለብሰው ያልብሰው። የማይችሉትን ስራም አትዘዟቸው። ካዘዛችኋቸውም እርዷቸው።›› (ቡኻሪና ሙስሊም)

አንድ ሰው ባሪያውን ከእንስት አገልጋዩ ጋር አጋባ። ቆይቶ ግን ሊያፋታቸው ፈለገ። አገልጋዩ ከነቢዩ ﷺ ዘንድ በመቅረብ ይህን ጉዳይ ነገራቸው። እንዲህ አሉ፡-

‹‹እንስት እና ተባእት አገልጋዮቻችሁን ካጋባችሁ በኋላ ለማፋታት ማሰባችሁ አግባብ አይደለም።። የፍች መብት ያለው ባል ብቻ ነው።›› (ቢን ማጃህና ጦበራኒ)

ሶሐቦች ከአገልጋዮቻቸው ጋር ባላቸው ግንኙነት የሚፈጽሙትን ስህተት ለመጠንቀቅ ሲሉ ባሮቻቸውን ነጻ መልቀቅን ይመርጡ ነበር። በሂደት የባሪያ አሳዳሪ ስርዓት እየተደመሰሰ ሄደ። በመጨረሻም ሊከስም ቻለ።

ኢስላም የባርነትን ቀንበር ከሰው ልጅ ትከሻ ላይ አስወግዷል። ባርነት በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ልክ እንደ አንድ የጦርነት ውጤት ይታይ ነበር። ኢስላም ግን ባሮችን በመልካም ሁኔታ መያዝን ማስተማር ጀመረ። ባለቤቱ የሚመገበውን እንዲመግበው፣ የሚለብሰውን እንዲያለብሰው፣ ከአቅሙ በላይ የሆነ ትእዛዝ እንዳያዘው፣ ፍላጎቱን እንዲያሟላለት አዘዘ። ባሪያን ነጻ መልቀቅ ብዙ ምንዳ የሚያስገኝ በጎ ስራ መሆኑን አስተማረ። ሙእሚኖች የሚድኑበት የተረጋገጠ መንገድ መሆኑን ሰበከ። ባሪያ የሌለውን ሰው ከባሪያ ባለቤት የተሻለ የሚያደርጉ የባሪያ መብቶችን ደነገገ። እናም የባሪያ ባለቤት እነዚህን የባሪያ መብቶች ለማሟላት ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግ ያለበት ከመሆኑ አኳያ እርስ ራሱ

ባሪያ የሆነ ያህል ጫናው ይሰማዋል፡፡ የአላህ መልእክተኛﷺ ጣእረ ሞት ላይ እያሉ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹ሶላትን አደራ በአግባቡ ስገዱ፡፡ በስሮቻችሁ ያሉ ባሮቻችሁን መብትም አታጓድሉ፣ ጠብቁ፡፡›› (አቡ ዳውድና ቢን ማጃህ)

ይህ ኑዛዜ ለተከታዮቻቸው ካስተላለፏቸው ድንቅ ኑዛዜዎች መካከል አንዱ ነው፡፡ የአላህ መልእክተኛﷺ ለባርነት የሚያበቁ በሮችን ሁሉ ዘግተው ባሪያ ነጻ የሚሆንበትን በር በሰፊው ከፈቱ፡፡ በየአጋጣሚው ባሪያን ነጻ መልቀቅን አበረታቱ፡፡ የባሪያ አሳዳሪን ስርዓት ለማንኮታኮት ከዚህ የተሻለ ስልት አለን?

ኢስላም ለአገልጋዮች የሰጠውን ክብርና ደረጃ ለማወቅ ከላይ የተጠቀሱ ናሙናዎች በቂ ናቸው፡፡ ቢላል ከመስለሙ በፊት ባሪያ ነበር፡፡ ከሰለመ በኋላ ግን የአላህ መልእክተኛﷺ የአዛን አድራጊዎች አውራ አደረጉት፡፡ በአሁኑ  ሰአት በሙእሚኖች ማእከላት ላይ ‹‹ቢላል አልሐበሺ›› የሚል ስም ተጽፎ መገኘቱ ኢስላም ለባሮች ለሰጠው ክብር ቋሚ ምስክር ነው፡፡

ዘይድ ቢን አልሐሪስ ባሪያ ነበር፡፡ እመት ኸዲጃ ለነቢዩ ሙሐመድ ﷺአገልጋያቸው ይሆን ዘንድ ሰጧቸው፡፡ ነቢዩ ግን ነጻ ለቀቁት፡፡ እናም ለነቢዩ በነበረው ፍቅር ተምሳሌት የሆነ ታላቅ ሶሐባ ለመሆን በቃ፡፡ ልጁን ኡሳማንም አላህ በወጣትነቱ የሙስሊሞች ጦር መሪ አደረገው፡፡

አንደሉስን ያቀናው ጧሪቅ ቢን ዚያድ በአንገቱ ዙሪያ ዘለበት የሚታሰርበት፣ የሚሸጥና የሚለወጥ ባሪያ ነበር፡፡ ግና ይህ ባሪያ በእስልምና ጥላ ስር ለሰብአዊ ክብሩ ተገቢ የሆነን ታላቅ ደረጃ አገኘ፡፡ የሙስሊሞች ሰራዊት መሪ ለመሆን በቃ፡፡

በጥቅሉ ኢስላም የባሮችን ሕይወት ለውጧል፡፡ ከባለቤቶቻቸው ጋር እኩል ሰብአዊ ክብር አጎናጽፏቸዋል፡፡ ጣኦታውያን ኢስላምን በጽኑ ከተቃወሙባቸው ምክንያቶች አንዱ ይህ ነው፡፡ በዛሬው ዘመን የእስልምና ጠላቶች ተመሳሳይ ግድፈት አልፈጸሙምን? ሐገር እየወረሩ በርካታ የሰው ልጆችን በባርነት አላጠቁምን? በነጻነት ስም የተፈጥሮ

ሃብታቸውን ለመዝረፍና ቁሳዊ ጥቅም ለማግኘት ሲሉ ብቻ የነጻና ደካማ ሕዝቦችን መብት አልጨፈለቁምን? የሰው ልጅ በዛሬው ዘመን ለጆሮ በሚጥሙ የተለያዩ ስያሜዎች ስር በሚኖርባቸው ጨካኝ ስርዓቶች አማካይነት የተሸከመው የባርነት ቀንበር ከጥንቱ የባሰ አይደለምን?

ትላንት የባርነትን ስርዓት በድንቅ መርሆዎቹና እሴቶቹ የገረሰሰው ኢስላም ዛሬም ለሰው ልጆች ዳግም ፈውስ መለገስ አይሳነውም፡፡

የሰው ልጅ ወደ ኢስላም ካልተመለሰ በቁሳዊ ሽኩቻ ራሱን ወደባሰ ጥፋትና መከራ ውስጥ መክተቱ ጥርጥር የለውም፡፡

የደካሞችን ደም በመምጠጥ፣ እነርሱን ወደባርነት በመለወጥና በማማቀቅ ላይ ያለውን አስከፊ የቅኝ ግዛት ስርዓት፣ ነቢዩﷺ ባሮችን፣ አገልጋዮችንና ምርኮኞችን አስመልክተው ከተናገሩት ከተከታዩ ቃላቸው ጋር ስናነጻጽር ኢስላም በእርግጥ ምጡቅና አንጸባራቂ ስርዓት ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ነቢዩﷺ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹ወንድሙ በስሩ ያለ ሰው ከሚበላው ያብላው፣ ከሚለብሰውም ያልብሰው፡፡›› (ቡኻሪና ሙስሊም)

እነዚህ ቃላት በእርግጥም ኢስላም በየትኛውም ቦታና ጊዜ የሚኖርን የትኛውንም ሰው ክብር ያላቀባቸውን መልእክቶች ያዘሉ ናቸው፡፡

የሰው ልጅ አሁን ካሉበት ችግሮች መውጣት የሚችለው ጥንት በወጣበት መንገድ ብቻ ነው፡፡ እርሱም የነቢዩ ሙሐመድንﷺ መመሪያ መከተል ነው፡፡ እርሳቸው ለሰው ልጆችመልካም ግንኙነት መሠረት አኑረዋል፡፡ ለሰው ልጅ የላቀ ክብር ለግሰዋል፡፡ ትክክለኛውን እሴት አስቀምጠዋል፡፡ ድሃ ከሐብታም፣ ገዥ ከተገዥ፣ አለቃ ከአገልጋይ ሳይለዩ ለሁሉም የሚበጅ እና እኩል የሚያደርግ እሴት አበጅተዋል፡፡ አንድ ሶሐባ፡- ‹‹አገልጋዮቻችንን በቀን ለምን የህል ጊዜ ይቅር እንበል?›› በማለት ሲጠይቃቸው፡- ‹‹በየቀኑ ሰባ ጊዜ ይቅር በሏቸው›› አሉ፡፡ (አቡ ዳውድና ቲርሚዚ)

**የነቢዩﷺ እዝነት ዳርቻ የሌለው ውቅያኖስ ነው፡፡ የሰዎችን ቀልብ ለመጠበቅ የሚያደርጉት ጥረት አምሳያ የለውም፡፡ ይህን የሚያመላክት አንድ ንግግራቸውን ላስፍርላችሁ፡-**

**‹‹ከናንተ አንዳችሁ አገልጋዩ ምግብ ይዞለት ሲመጣ፣ አብሮት ይመገብ ዘንድ ባያስቀምጠው እንኳ አንድ ወይም ሁለት ጉርሻ ያጉርሰው፡፡ ምክንያቱም የማዘጋጀቱን ኃላፊነት የተሸከመው እርሱ ነውና፡፡›› (ቡኻሪ)**

**አላህ ቢሻ ኖሮ አገልጋዩን አለቃ፣ አለቃውን አገልጋይ ማድረግ ይችል ነበር፡፡ ስለዚህም ለአላህ ተገቢውን ምስጋና ማድረስና ከስሮቻችን ያሉ ሰዎችን በአግባቡ መያዝ ይገባናል፡፡**

## የሴቶች አያያዝ

**በጃሂልያ ዘመን ሴቶች ክብር አልባ አያያዝ ይያዙ ነበር፡፡ የጃሂልያ ሰዎች ሴቶቻቸውን ያለ ርህራሄ ከነሕይወታቸው ይቀብሩ ነበር፡፡ ይህን የሚያደርጉት በሕብረተሰቡ የሚደርስባቸውን መነወርና ውግዘት በመፍራት ነው፡፡ ከአለት የጠጠረ ቀልባቸው ይህን ወንጀል ምንም ሳይመስለው ይፈጽማል፡፡ እንስት ሲወለድ ይሰማቸው የነበረውን የሐፍረት ስሜት አላህ እንዲህ በማለት ገልጾታል፡-**

﴿ وَإِذَا بُشِّرَ أَحَدُهُم بِٱلْأُنثَىٰ ظَلَّ وَجْهُهُۥ مُسْوَدًّا وَهُوَ كَظِيمٌ ﴿٥٨﴾ ﴾ النحل: ٥٨

***‹‹ከነርሱ መካከል አንዱ በሴት ልጅ በተበሰረ ጊዜ ፊቱ በሐዘን ይጠቁ ራል፡፡ ቅስሙ ይሰበራል፡፡›› (አል ነህል 58)***

**በጃሂልያ ዘመን ሰዎች እንስቶችን ደረጃቸውን እጅግ ዝቅ በሚያደርግ አያያዝ ይይዟቸው ነበር፡፡ ክብርን በእጅጉ በሚነካ አኳኋን ለሴሰኝነት ብቻ ይጠቀሙባቸዋል፡፡ የአላህ መልእክተኛﷺ ሲመጡ የእንስት መብት እውቅና አገኘ፡፡ ሴቶች በሕብረተሰቡ ውስጥ የንጽህናና የመልካም ስነ ምግባር ተምሳሌት ሆኑ፡፡ የእናትነት ተቋም የልቅና ተምሳሌት ተደርጎ**

ተቆጠረ፡፡ እንስት በተከታዮ ነብያዊ መልእክት አማካይነት ተገቢውን የክብር ደረጃ አኘች፡፡ ነቢዩﷺ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹ጀነት ከእናቶች እግር ስር ትገኛለች፡፡›› (አልነሣኢ)

ተከታዩ አጋጣሚ የአላህ መልእክተኛﷺ የእንስቶችን ክብር ይበልጥ ያጎሉበተ፣ ለነርሱ የሚገባውን አያያዝ በውብ አኳኋን የገለጹበት፣ እርሳቸው ለሴቶች ያላቸው ክብርና ወሰን የለሽ እዝነት የተንጸባረቀበት ነበር፡፡ ይህውም የአላህ መልእክተኛﷺ በጉዞ ላይ ነበሩ፡፡ አንጀሽህ የተባለ አገልጋያቸው አብሯቸው ነበር፡፡ ግመሎችን የሚነዳው እርሱ ነበር፡፡ ግመሎች በፍጥነት ይጓዙ ጀመር፡፡ የአላህ መልእክተኛምﷺ ከግመሎቹ ላይ የተሳፈሩ ሴቶች እንዳይከላተሙ ስጋት ገባቸው፡፡ ለዚህ አገልጋያቸው እንዲህ አሉት፡-

‹‹አንጀሽህ ሆይ፣ ረጋ በል፡፡፡ ለእነዚህ ስስ ብርጭቆዎች እዘንላቸው፡፡›› (ቡኻሪና አህመድ)

በሌላ ሐዲስ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹አላህ ሆይ፣ የሁለት ደካሞች፣ የየቲምና የሴቶች መብት ክብደት ይሰማኛል፡፡›› (ቢን ማጃህ)

‹‹አማኝ ወንድ አማኝ ሴትን አይጥላ፡፡ አንድ ባህሪዋን ቢጠላ ሌላውን ይወደዋልና፡፡›› (ሙስሊም)

እንስት ጥላቻ የሚገባት፣ በአሜኬላ እሾህ የተሞላች መሬት አይደለችም፡፡ ሊያፈቅሯት እና ሊናፍቋት፣ ሊንከባከቧትና ሊሳሱላት የምትገባ በውብ አትክልቶች እና አበቦች የተሞላች አጸድ እንጅ፡፡ የሴት ፍቅር ከአላህ ዘንድ የተሰጠ ጸጋ ነው፡፡ የአላህ መልእክተኛﷺ ይህን በማስመልከት ሲናገሩ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹ከዱንያ ውስጥ ሁለት ነገሮች ከኔ ዘንድ የበለጠ ተወዳጅ ሆነዋል፡፡ እነርሱም ሴትና ሽቶ ናቸው፡፡ ሶላት የዓይኔ ማረፊያ ተደርጋለች፡፡›› (ነሣኢና አህመድ)

ይህ ፍቅር በቸልታ መያዝ የለበትም፡፡ የሴት ማሕጸን በምድር ላይ የአላህ ወኪል የሆነው የሰው ልጅ ማረፊያ መሆኑን መዘንጋት ተገቢ አይደለም፡፡ አላህ ከወንድ ልጅ ተፈጥሯዊ ስሪት ውስጥ የሴት ልጅን ፍቅር አኑሯል፡፡ ተፈጠሮውንም ይህን የተቀደሰ ፍቅር ሊያስተናግድ በሚችል አኳኋን አበጅቶታል፡፡ ስለዚህም የአላህ መልእክተኛﷺ ለሴቶች ያላቸው ፍቅር ጾታዊ ዝንባሌ ብቻ ተደርጎ መታየት የለበትም፡፡ ይልቁንም በርሳቸው የተባረከ ልቦና ውስጥ ክብራቸውን የሚመጥን ቦታ ማግኘታቸውን ያመለክታል፡፡

ሴት ልጅ በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ይህን መለኮታዊ ደረጃና ዋጋ ያገኘችው በእስልምና ጥላ ስር ብቻ ነው፡፡

ለሴት ልጅ ክብርና ደረጃ ሰጥተናታል በማለት የሚመጻደቁት ከእስልምና ውጭ ያሉ አስተሳሰቦችና ስርዓቶች በሙሉ ክብር የቸሩት ለአካላዊ እሷነቷ ብቻ ነው፡፡ ስብእናዋን ግን እንደ ቁስ ከመጠቀም፣ የኢኮኖሚና የወሲብ መጠቀሚያ ከማድረግ ተቆጥበው አያውቁም፡፡

ስለዚህም የሰው ልጅ ባለንበት ዘመን ስለሴት ያለውን እይታ መፈተሽና ማስተካከል ይጠበቅበታል፡፡ ይህም እውን ሊሆን የሚችለው በተባረከውና በላቀው ኢስላማዊ እሳቤ ስር ብቻ ነው፡፡

ሴትና ወንድ ከተፈጠሩበት ቅጽበት አንስቶ አንዱ ሌላውን የሚሞላ ሁለት ዓለማት ናቸው፡፡ አላህ ለሁለቱም የየራሳቸው የሕይወት ሚና ቢሰጣቸውም የእንስት ተጽእኖ ይበልጥ ጉልህና ጠንካራ እንዲሆን ፈቅዷል፡፡ የሕብረተሰቡ መበላሸትና መስተካከል በሴት ልጅ እጅ ነው፡፡ ይህ ከመሆኑ አኳያ ሴት ልጅን በተገቢው መንገድ ቀርጾ ማሳደግ በእስልምና እይታ ትልቅ ደረጃ ተሰጥቶት እናያለን፡፡ ነቢዩﷺ ይህን አስመልክተው ሲናገሩ፡-

‹‹ሦስት ሴት ልጆች ወይም ሦስት እህቶች፣ እንደዚሁም ሁለት ሴት ልጆች ወይም ሁለት እህቶች ኖረውት ተንከባክቦ ያሳደጋቸው፣ በነርሱ

ጉዳይም አላህን የፈራ ጀነትን ያገኛል፡፡›› (ቲርሚዚ፣ አቡ ዳውድና አህመድ)

በሌላ ሐዲስ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹ሁለት ሴት ልጆችን ለአካለ መጠን እስኪደርሱ ድረስ ተንከባክቦ ያሳደገ እኔና እርሱ ጀነት ውስጥ እንደዚህ እንሆናለን፡፡›› ጣቶቻቸውን አጠጋግተው አሳዩ፡፡ (ሙስሊምና ቲርሚዚ)

የአላህ መልእክተኛ ﷺ የመልካም ሴትን ዋጋ ሲያጸኑ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹ዱንያ መደሰቻ ናት፡፡ ከዚህች ዓለም አስደሳች ነገሮች ሁሉ በላጯ መልካም ሚስት ናት፡፡›› (ሙስሊም፣ነሣኢና ቢን ማጃህ)

ከታላላቅ ሰዎች ጀርባ እንስት ትገኛለች፡፡ ለምሳሌ ከነቢዩ ሙሐመድﷺ ጀርባ ባለቤታቸው ኸዲጃ ነበረች፡፡ ዳእዋቸውን ሲጀምሩ ከማንም ቀድማ ደገፈቻቸው፡፡ አበረታታቻቸው፡፡ ስለዚህም የአላህ መልእከተኛﷺ እድሜ ልካቸውን አልረሷትም፡፡ ፋጡመቱ ዘህራእም እንደዚሁ ለአላህ መልእክተኛﷺ ስኬት ጉልህ ሚና ነበራት፡፡

እናም መልካም ሚስት ከዚህች ዓለም ጸጋዎች ሁሉ በላጯ ናት፡፡ የአላህ መልእክተኛﷺ የእንስትን አያያዝ ለአንድ ሰው ደግነት መመዘኛ መስፈርት አድርገው አስቀምጠውታል፡፡ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹ከአማኝ ወንዶች መሐል ኢማኑ ይበልጥ የሞላው ስነ ምግባሩ ይበልጥ ያማረው ሲሆን፣ ከመካከላችሁ በላጬ ለሚስቱ ባህሪው ይበልጥ መልካም የሆነው ነው፡፡›› (ቲርሚዚ)

ስለዚህም እንስት እንደ ወሲብ እቃ ብቻ መታየቷ፣ ለአካላዊ እርካታ፣ ለስጋዊ ደስታ ብቻ መዋሏ፣ አካላዊ እሷነቷ ብቻ ትኩረት ማግኘቱ ስብእናዋን ማዋረድ ነው፡፡ አላህ ለሴት ልጅ የሰጣትን የላቁ ባህሪያት መዘንጋትና ለርሷ ተገቢውን ክብር አለመስጠት ነው፡፡

እንስት በአሁኑ ዓለም ውስጥ ያላት ቦታ ከዚህ የተለየ አይደለም፡፡ ለማስታወቂያ ስራ፣ ለሸቀጥ ማሻሻጫነት ብቻ ትውላለች፡፡ ይህ በእርግጥም የእንስትን ቦታ በጣም የሚያዋርድና የሚያዘቅጥ ነው፡፡

ሴት ልጅ መታነየት ያለባት የሕብረተሰቡ እውነተኛ መሐንዲስና መስራች መሆኗ ግንዛቤ ባገኙበት መልክ ነው፡፡ ታላላቆችን በእቅፏ ውስጥ የምታሳድግ የትውልድ ቀራጭ መሆኗ ግንዛቤ ማግኘት አለበት፡፡ ከእናትነት የበለጠ ለርሷ እውነተኛ ፍቅርና ክብር የሚያሰጣት ሌላ ሚና ከቶውንም ሊኖር አይችልም፡፡ እውነተኛ እናት በሆዷ ውስጥ ለወራት ተሸክማ፣ ለዓመታት በእጇ ታቅፋ፣ በልቦናዋ ውስጥም እስከትሞት ድረስ ይዛ የምትኖር፣ ሕይወቷን ለቤተሰቦቿ የሰጠች እንስት ናት፡፡ ይህም በመሆኑ የእድሜ ሙሉ ምስጋና፣ ጥልቅ ፍቅርና አክብሮት ልታገኝ ተገቢ ሆኗል፡፡

የአላህ መልእክተኛﷺ በሐዲሱ ላይ ከእንስት ቀጥሎ በጣም እንደሚወዱ የገለጹት ነገር ሽቶ ነው፡፡ የአላህ መልእክተኛ ምንጊዜም ሽታቸው መልካም ነበር፡፡ መጥፎ ጠረን ከርሳቸው ወጥቶ አያውቅም፡፡ መላ አካላቸው መልካም ጠረን ያውዳል፡፡

መልካም ጠረን የንጽህና ምልክት ነው፡፡ መልካም ጠረን ያለው ሰው ንጽህናውን መጠበቁን ያመለክታል፡፡ የአላህ መልእክተኛ አካል ምንጊዜም ሽታው ያውዳል፡፡ ላበታቸው ልዩ ማአዛ እንደነበረው ይነገራል፡፡ የአንድን የቲም ራስ ሲያብሱ የዚያ ልጅ ራስ መልካም መዓዛቸውን እንደያዘ ለረዥም ጊዜ ይቆያል፡፡

ይህን በተመለከተ ኢብራሂምን ጠቅሰው አእመሽ እንደዘገቡት፡- ‹‹የአላህ መልእክተኛ በሌሊት በንፋሱ መልካም ሽታ ያሉበት አካባቢ ይታወቃል፡፡›› (ዳሪሚ)

በሐዲሱ ላይ፡- ‹‹ሶላትን የዓይኔ ማረፊያ›› ብለዋታል፡፡ በእርግጥም ሶላት እንደዚህ ናትና፡፡ አፈጻጸሟ ይህን ሚናዋን ባጣመረ መልኩ በትክክል ሊሆን ይገባል፡፡ ሰጋጁ አላህን እንደሚያየው አድርጎ ቢፈጽማት መልካም

ነው፡፡ እርሱ ባያየውም አላህ ያየዋልና፡፡ ሶላት የአላህ መልእክተኛ የዓይን ማረፊያ የሆነችውም ከዚህ አኳያ ነው፡፡

## ከየቲሞች ጋር

አላህ መልእክተኛውን ﷺ ወደዚህች ዓለም የቲም አድርጎ የላካቸው የቲምነት የተለየ ትኩረት እንዲቸረው በመሻት ነው፡፡ የአላህ መልእክተኛﷺ ለየቲሞች በጣም ያዝኑ ነበር፡፡ የተለየ ትኩረትም ይሰጧቸው ነበር፡፡ ቁርአን ውስጥ የየቲምን መብት መጠበቅን የሚመለከቱ በርካታ አናቅጽን እናገኛለን፡፡ የቲሞችን ሰዎች እንዴት መንከባከብ እንዳለባቸው አላህ በበርካታ ስፍራዎች መመሪያ ሰጥቷል፡፡ ለአብነት፡-

﴿ فَأَمَّا ٱلۡيَتِيمَ فَلَا تَقۡهَرۡ ٩ ﴾ الضحى: ٩

(ስለዚህ) የቲምን ፈጽሞ አትበድል። (ዱሓ፡9)

የአላህ መልእክተኛﷺ በተከበረው ሐዲሳቸው እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹ከሙስሊሞች ቤቶች መካከል መልካሙ የቲም በእንክብካቤ የተያዘበት ቤት ነው፡፡ ከሙስሊሞች ቤቶች ውስጥ መጥፎው የቲም በመጥፎ አያያዝ የተያዘበት ቤት ነው፡፡›› (ቢን ማጃህ)

በሌላ ሐዲስ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹የቲምን ያበላና ያጠጣ፣ ምህረት የማያስገኝ ወንጀል ካልፈጸመ በቀር ጀነት ይገባል፡፡›› (ቲርሚዚ)

በሌላ ሐዲስ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹ለአላህ ሲል የየቲምን ራስ የዳበሰ እጁ ባረፈባቸው ጸጉሮች ልክ ምንዳ ያገኛል፡፡ ከርሱ ዘንድ ለሚገኝ የቲም በጎ የዋለ እኔና እርሱ ጀነት ውስጥ እንደዚህ እንጎራበታለን፡፡›› በማለት የአውራና የመሐከለኛ ጣታቸውን አጠጋግተው አሳዩ፡፡ (አህመድ)

የአላህ መልእክተኛﷺ የሩህሩህ ልቦና ባለቤቶች የሆኑ አስሐቦቻቸውን የቲምን ይንከባከቡ ዘንድ ዘወትር ያሳስቡ ነበር፡፡ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹እኔና የቲምን የሚንከባከብ ልክ እንደዚህ ነን፡፡›› በማለት የአውራና የመሐከለኛ ጣታቸውን አሳዩ፡፡

ቀልቡ እንደደረቀበት ስሞታ ለነገራቸው አንድ ሶሐባ ተከታዩን ምክር ለግሰውታል፡፡

‹‹ቀልብህን ማለዘብ ከፈለግክ ድሃን አብላ፡፡ የየቲምን ራስም ዳብስ፡፡›› (አህመድ)

የአላህ መልእክተኛﷺ እንዲህ በማለት የእዝነትንና የሩሩህነትን ጫፍ ይደርሳሉ፡-

‹‹እኔ ለእያንዳንዱ ሙስሊም ከራሱ ይበልጥ ተገቢው ነኝ፡፡ ገንዘብ የተወ ለቤተሰቡ ነው፡፡ እዳ የተወ ግን እዳውን የመክፈሉ ሐላፊነት በኔ ላይ ነው፡፡›› (ሙስሊም)

# የእንስሳት አያያዝ

የነቢዩ ሙሐመድﷺ እያንዳንዱ እንቅስቃሴ ከፍቅርና ከርህራሄ መሠረት ላይ የታነጸ ነው፡፡ ወደፍጡራን በእዝነት ይቀርባሉ፡፡ ጉዳያቸውንም ይፈጽማሉ፡፡ እንስሳትም ከርሳቸው የፍቅር ውቅያኖስ ውስጥ የድርሻቸውን ተቋድሰዋል፡፡

የጃሂልያ ሰዎች ለእንስሳት አያዝኑም ነበር፡፡ በመጥፎ አያያዝ ይይዟቸዋል፡፡ እነርሱን የሚጎዳ ድርጊት ይፈጽሙባቸዋል፡፡ እንስሳትን እርስ በርስ እያዋጉ እና እያጋደሉ ይዝናናሉ፡፡ የአላህ መልእክተኛﷺ እነዚህን ከመልካም ስነ ምግባር ጋር የማይጣጣሙ ድርጊቶች ሁሉ ከለከሉ፡፡ አቡ ዋቂደ ለይሲ እንዲህ ሲል አውግቷል፡-

የመዲና ሰዎች የግመል ሻኛ እና የፍየል ላት ይወዱ ስለነበር ከነሕይወታቸው እየቆረጡ ይመገቧቸው ነበር፡፡ የአላህ መልእክተኛ ግን ይህን ድርጊት እንዲህ በማለት ከለከሉ፡-

‹‹እንስሳት በሕይወት እያሉ ከአካላቸው የሚቆረጥ ስጋ ሁሉ በክት ነው፡፡›› (ቲርሚዚና አህመድ)

ጃቢር እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛﷺ ፊቱ የተጠበሰ አንድ አህያ ተመለከቱና እንዲህ አሉ፡-

‹‹ይህን ድርጊት አልከለከልኳችሁም ነበርን? ይህን የፈጸመውን ሰው አላህ ረገመው፡፡››

የእንስሳትን ፊት መምታትንም ከለከሉ፡፡ (አቡ የእላእ)

አብዱረህማን ቢን አብደላህ አባቱን በመጥቀስ የሚከተለውን አውግቷል፡-

ከአላህ መልእክተኛﷺ ጋር በጉዞ ላይ ነበርን፡፡ ለጉዳይ ከኛ ተነጠሉ፡፡ እኛ ደግሞ አንድ የወፍ ጎጆ አየን፡፡ ሁለት ጫጩቶች ነበሩበት፡፡ ወሰድናቸው፡፡ እናታቸው ልጆቿን ተከትላ መጣች፡፡ በላያችንም ላይ ታንዣብብ ጀመር፡፡ ነቢዩﷺ ይህን ሲያዩ እንዲህ አሉ፡-

‹‹የዚህችን አሞራ ልጆች የወሰደ ማን ነው፡፡ መልሱላት፡፡››

የጉንዳን ቀዬ ተቀጣሎም ተመለከቱ፡፡ ‹‹ማን ነው ያቃጠለው?›› በማለት ጠየቁ፡፡ ‹‹እኛ›› አልናቸው፡፡ ‹‹በእሳት የመቅጣት መብት ያለው የእሳት አምላክ ብቻ ነው፡፡›› አሉ፡፡ (አቡ ዳውድ)

አንድ ጊዜ የአላህ መልእክተኛ ﷺ ለሐጅ ኢህራም አድርገው ወደ መካ አቀኑ፡፡ ኡሳየህ ከተባለበ ቦታ ሲደርሱ ከአንዲት ዛፍ ጥላ ስር ተዘርግቶ የተኛ ሚዳቋ ተመለከቱ፡፡ እንቅልፉን እስኪጨርስ ድረስ ሰዎች እንዳያውኩት ይጠብቅ ዘንድ አንድ ሶሐባቸውን አዘዙት፡፡

የአላህ መልእክተኛﷺ መካን ለመቆጣጠር አስር ሺህ ሰራዊት ይዘው በዘመቱ ጊዜ መንገድ ላይ አንዲት እናት ውሻ ተንጋላ ልጆች ስታጠባ

ተመለከቱ፡፡ እርሷንም ሆነ ልጆቿን ወታደሮች እንዳያውኳቸው ይከላከል ዘንድ አንድ ሶሐባቸውን አዘዙት፡፡ (አልዋቂዲ)

አንድ ቀን በአንድ ግመል አጠገብ አለፉ፡፡ ከመክሳቱ የተነሳ ጀርባው ከሆዱ ጋር ተጣብቋል፡፡ እንዲህ አሉ፡-

‹‹አንደበት በሌላቸው እንስሳዎቻችሁ ጉዳይ አላህን ፍሩ፡፡ በመልካም አያያዝ ጋልቧቸው፡፡ በመልካም አኳኋንም ተመገቧቸው፡፡›› (አቡ ዳውድ)

አብደላህ ኢብን ጃእፈር እንዲህ ሲሉ አውግተዋል፡-

የአላህ መልእክተኛ ﷺ አንድ ቀን ከመጓጓዣቸው ላይ አፈናጠጡኝ፡፡ ለማንም የማላወጋው አንድ ሚስጥርም አጫወቱኝ፡፡ ወደ አንድ የአንሷር ሰው የአትክልት ቤት ሲገቡ ግመል አገኙ፡፡ ነቢዩን ሲያይ አላዘነ፡፡ እንባም ከዓይኖቹ መነጨ፡፡ ነቢዩ ተጠጉትና እንባውን አበሱለት፡፡ ዝም አለ፡፡ ‹‹የዚህ ግመል ባለቤት ማን ነው?›› ሲሉ ጠየቁ፡፡ አንድ የአንሷር ወጣት መጣና፡- ‹‹እኔ ነኝ›› አላቸው፡፡ እንዲህ አሉት፡-

‹‹አላህ በባለቤትነት በሰጠህ በዚህ እንስሳ ጉዳይ አላህን አትፈራምን? እንደምታስርበውና ረፍት እንደማትሰጠው ስሞታ ነገረኝ፡፡›› (አቡ ዳውድ)

አንድ ጊዜ ከእንስሳዎቻቸው አጠገብ በቆሙ ሰዎች ጥግ ሲያልፉ እንዲህ አሉ፡-‹‹በመልካም አኳኋን ጋልቧቸው፡፡ በመልካም አኳኋንም ተዋቸው፡፡ በገበያ ቦታም በመንገድም ለምታወጉት ወግ በመቀጣጫነት አትጠቀሙባቸው፡፡ ከጋላቢዋ የተሻለች ተጋላቢ እንስሳ ስንት አለች፡፡ አላህንም በብዛት አውሱ፡፡›› (አህመድ)

አንድ ሰው ፍየል ለማረድ እርሷን አጋድሞ ቢላዋ ሲስል ተመለከቱትና እንዲህ ሲሉ የጭካኔ ተግባሩን ኮነኑ፡- ‹‹ብዙ ጊዜ ልትገድላት ትሻለህን? ሳታጋድማት በፊት ቢላዋህን አትስልም ነበርን?›› (ሐኪም)

ኢብን መስዑድ እንዳስተላለፉት ነቢዩ ﷺ፡- ‹‹እሣት ለማን እርም እንደምትሆን ልንገራችሁን?›› በማለት ጠየቁ፡፡ ‹‹አዎ›› አሏቸው፡፡

‹ገራገር፣ ልዝብና ልስልስ ለሆነ ሁሉ ነው፡፡›› አሉ፡፡ (ቢን ሒባንና አህመድ)

የአዛኝና የጨካኝ ሰዎችን ቦታ ሲገልጹ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹አንድ ሰው በጉዞ ላይ እያለ ውሃ ጥም ጠናበት፡፡ ወደ አንድ ጉድጓድ ወርዶ ጠጣ፡፡ ሲወጣ አንድ ውሻ በጥም ተቃጥሎ እርጥብ አፈር ሲግጥ ተመለከተው፡፡ ‹‹እኔን ያገኘኝ አይነት ብርቱ ጥማት ይህንንም ውሻ አግኝቶታል፡፡›› አለና ወደ ጉድጓዱ በመውረድ በጫማው ውሃ ይዞለት በአፉ ተሸክሞት ወጣ፡፡ ከዚያም ለውሻው አፈሰሰለት፡፡ ውሻው ጠጣ፡፡ አላህም ድርጊቱን ወደደለት፡፡ ምህረትም አደረገለት፡፡››

‹‹የአላህ መልእክተኛ ሆይ፣ በእንስሳት አጅር እናገኛለን?››ሲሉ ጠየቋቸው፡፡ ‹‹አዎ፣ እርጥብ ጉበት ሁሉ አጅር ያስገኛል፡፡›› አሉ፡፡(ቡኻሪ)

በሌላ ሐዲስ ደግሞ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹አንዲት ሴት በአንዲት ድመት ምክንያት ተቀጥታለች፡፡ ይህውም ድመቷን ወይ አታበላትና አታጠጣት ወይም ደግሞ ራሷ የምድር ነፍሳትን እንድትበላ አልለቀቀቻት፡፡ እንዲሁ አስራ ስላስቃያቻት በዚህ ሰበብ እሳት ገባች፡፡›› (ቡኻሪና ሙስሊም)

የአላህ መልእክተኛ ﷺ በነዚህ ትምህርቶች ያን የጃሂልያ ማሕበረሰብ ወደ መልካም ማሕበረሰብ፣ የነበሩበትን ትውልድ ወደ መልካም ትውልድ ለወጡት፡፡ ሴት ልጆቻቸውን ከነሕይወታቸው ይቀብሩ የነበሩ ጨካኞች ለእንስሳት ሳይቀር የሚራሩ የማይነጥፍ የእዝነት ምንጮች ለመሆን በቁ፡፡

ምክንያቱም በሁሉም ጉዳዮች አርአያቸው የአላህ መልእክተኛ ﷺ ነበሩና፡፡ እርሳቸው የሁሉንም ነገር መብት ይጠብቁ ነበር፡፡ የበራሪ እንስሳ ሕጻን መብት ሳይቀር ጠብቀዋል፡፡ ሶሐቦችም ሊገለጽ የማይችል የእዝነት ስሜት አዳበሩ፡፡ አደገኛ የሆኑ እንስሳትን፣ ለምሳሌ ጊንጥንና እባብን እንኳ አደጋቸውን ለመከላከል መግደል ግድ ሲሆንባቸው

እንዳያሰቃዩአቸው መልእክተኛው ﷺ አዘዙ፡፡ ቶሎ ይገላገሉ ዘንድ በአንድ ምት እንዲገድሏቸው አደራ አሉ፡፡ እንዲህ ሲሉ አስተማሯቸው፡-

‹‹እባብን በአንድ ምት የገደለ ይህን ያህል አጅር አለው፡፡ በሁለት ምት የገደለ ከመጀመሪያው ያነሰ አጅር አለው፡፡ በሦስት ምት የገደለ ይህን ያህል (ከሁለቱ ያነሰ) አጅር አለው፡፡›› (ሙስሊም)

የአላህ መልእክተኛ ﷺ በዚህ መልኩ መገደል ያለባቸውን እንስሳት እንኳ በርህራሄ መግደልን ያስተምሩ ነበር፡፡ ይህ ሁሉ የአላህ መልእክተኛ ﷺ በተከበረው ቀልባቸው ውስጥ የተሸከሙትን ወሰን የለሽ እዝነት አያመለክትምን?

የአላህ መልእክተኛ ﷺ በዚህ ድንቅ ስነ ምግባራቸው የተነሳ ሙገሳን አይወድም፡፡ አላህ የለገሳቸውን ጸጋዎች ሲያወሱ እንኳ ‹‹ጉራ አይደለም፡፡›› የሚል ሐረግ ማከልን ምንጊዜም አይዘነጉም፡፡ (ቲርሚዚ)

ከወሰን ያለፈ ሙገሳ በኩራት የመበከልን ስሜት፣ እንዲሁም አምባገነንነትን በመፍጠር ለአደጋ ያጋልጣል፡፡፡

የአላህ መልእክተኛ ﷺ የሰው ልጆች ፈርጥ ከመሆናቸውና አላህም ያሞገሳቸው ከመሆኑ ጋር ራሳቸውን አስመልክተው እንዲህ ይሉ ነበር፡-

‹‹ክርስትያኖች ኢሳን ከወሰን እንዳሳለፉት እናንተም አታሳልፉኝ፡፡ እኔ የአላህ ባሪያ በመሆኔ የአላህ ባሪያና መልእክተኛ ብቻ በሉኝ፡፡›› (ቡኻሪ)

በእርግጥ የተገዥነት ባህሪ በእያንዳንዱ ሰው ውስጥ ይገኛል፡፡ ሰውየው አንድም ለጥቅምና ለስጋዊ ፍላጎቱ፣ ለከንቱ ስሜቱ ተገዥ ይሆናል፡፡ ወይም ደግሞ ለአምላኩ ተገዥ ይሆናል፡፡ አምላክን የሚገዛ ለስጋዊ ፍላጎትና ለስጋዊ ስሜቱ፣ ለጥቅምና ለንዋይ ባሪያ ከመሆን ይታደገዋል፡፡

የአላህ መልእክተኛ ﷺ ለተለያዩ የሕይወት ዘርፎች ያስቀመጡትን ሚዛናዊነት ሳያዛንፉ ኖረዋል፡፡ በዚህ ረገድ የርሳቸውን ስብእና የሚመጥን ሌላ ተምሳሌት በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ማግኘት አይቻልም፡፡ በእርግጥ ከሕይወት መስኮች በአንዱ ወይም በሁለቱ

በሙያቸው የተሳካላቸው ጀግኖችን ልናገኝ እንችል ይሆናል፡፡ የአላህ መልእክተኛﷺ ግን በሁሉም የሕይወት መስኮች ተሳክቶላቸዋል፡፡ መሳካት ብቻ ሳይሆን አቻ የለሽና ተምሳሌትም መሆን ችለዋል፡፡

የሰው ልጅ እስካለንበት ዘመን ድረስ በተለያየ መስክ ያወቃቸውን ታላላቅ ስብእናዎች በልቅና ያስከነዱ አምሳያ የለሽ ተምሳሌታዊ ስብእና ናቸው፡፡

የአላህ መልእክተኛﷺ በኢባዳ፣ በንግድና በስራ፣ በስነ ምግባር መስክ ወደር ሊገኝላቸው የማይችሉ መልካም ባህሪያትንና እሴቶችን ለሰው ልጆች አበርክተዋል፡፡ አቻ የሌላቸውን ቁሳዊና መንፈሳዊ እሴቶች ለግሰዋል፡፡

እናም የሰው ልጅ የዝንተ ዓለም ቅን መሪ እንደሆኑ ይቀጥላሉ፡፡ በንጹህ ተፈጥሯቸው ለዓለም ተምሳሌት የመሆንን ከባድ ሐላፊነት ተገንዝበዋል፡፡

የአላህ መልእክተኛﷺ ለሶላት የተለየ ክብደት ይሰጡ እንደነበር ማስታወሱ ጠቃሚ ይመስለናል፡፡ ከሌሊቱ በእንቅልፍ የሚያሳልፉት ጥቂቱን ነው፡፡ የተከበረው አካላቸው በአብዛኛው ፍራሽ አያውቅም፡፡ ሰዎች በጥልቅ እንቅልፍ ውስጥ ሲሆኑ፣ የርሳቸው አይኖች ከሱጁድ ላይ ሲያለቅሱ ያድራሉ፡፡ በጣም ታመው ለሞት በተቃረቡበት ጊዜ እንኳ አቅማቸውን አሰባስበው ከቤታቸው በመውጣት መስጊድ ውስጥ በጀመዓ ይሰግዱ ነበር፡፡

የአላህ መልእክተኛ ﷺ በሶላት ውስጥ የነበራቸውን ተመስጦ አብደላህ ቢን ሹኸይር እንዲህ ሲል አውግቷል፡-

ከአላህ መልእክተኛﷺ ዘንድ መጣሁ፡፡ እየሰገዱም አገኘኋቸው፡፡ እንደተጣደ ምንቸት የመንፈቅፈቅ ድምጽ ከሆዳቸው ውስጥ እሰማ ነበር፡፡›› (እየተንሰቀሰቁ ያለቅሱ ነበር ማለቱ ነው፡፡) (አቡ ዳውድና ነሣኢ)

ከረመዷን ውጭ የአላህ መልእክተኛﷺ ሱንና ጾም ያልጾሙበት አንድም ወር አላለፈም፡፡ እናታችን አኢሻ እንዲህ ይላሉ፡-

‹‹የአላህ መልእክተኛ የሚያፈጥሩ እስከማይመስለን ድረስ አከታትለው ይጾማሉ:::  እንዲሁም ደግሞ የሚጾሙ እስከማይመስለን ድረስ አከታትለው ያፈጥራሉ::›› (ቡኻሪ)

ከየወሩ አስራ ሦስት፣ አስራ አራትና አስራ አምስተኛውን ቀናት ምንጊዜም በጾም ያሳልፋሉ:: የሸዋል ወርን ስድስት ቀናት፣ ከሙሐረም ወራት ዘጠኝንና አስርን ወይም አስር እና አስራ አንደኛውን ቀን በጾም ያሳልፋሉ:: በየሳምንቱ ሰኞና ሐሙስ መጾም ልምዳቸው ነው::

የዘካ ቁርአናዊ መልእክት በወረደ ጊዜ መልእክተኛውﷺ ሙእሚኖችን ዘካ እንዲሰጡ አዘዙ:: ትእዛዛቸውን ቀድመው የተገበሩት ግን ራሳቸው ናቸው:: የምጽዋትን ድንቅ ምሳሌ በገቢር አሳዩ:: ‹‹ከሰጠናቸው ሲሳይ የሚመጸውቱ›› የሚለውን የአላህ ቃል ወደ ሕይወት ቀየሩት:: (አል በቀራህ 3)

ለበጎ ነገር የሚውልን ገንዘብ አሞግሰዋል:: ገንዘባቸውን በሐቅ መንገድ ሰብስበው በአላህ መንገድ ለበጎ ተግባር የሚያውሉ ነጋዴዎችንም አወድሰዋል::

## ወደር የማይገኝላቸው መስፈርቶች

የአላህ መልእክተኛﷺ ቁሳዊ ሐብት አላከማቹም:: የሚያገኙትን ገንዘብ ሁሉ በአላህ መንገድ ይመጸውታሉ:: ይህ የርሳቸው ልዩ ባህሪ ሆነ:: አቡዘር አልጊፋሪ እንዲህ ብለዋል፦

መዲና ውስጥ ከአላህ መልእክተኛﷺ ጋር እየተጓዝን እያለን የኡሁድን ተራራ ከፊት ለፊታችን አየን:: ‹‹አቡዘር ሆይ፣›› አሉኝ:: ‹‹ለበይክ ያረሱለላህ›› አልኳቸው:: እንዲህ አሉ፦

‹‹የኡሁድን ተራራ በሚያህል የወርቅ ሐብት ቢኖረኝ ያለብኝን እዳ ለመክፈል ከማስቀረው ነገር ውጭ ከኔ ጋር ለሦስት ቀናት ያህል እንኳ እንዲቆይ አልፈቅድም:: እዚህም እዚያም በመመጽወት እበትነዋለሁ::››

አሉ፡፡ ወደኋላቸው፣ ወደ ፊታቸው፣ ወደ ቀኝና ወደ ግራቸው እያመላከቱ፡፡ ከዚያም ጉዟችንን ጠቀልን፡፡ እንዲህ ሲሉ አከሉ፡-

‹‹በዚህም በዚያም የመጸወቱት ሲቀሩ ብዙዎቹ ሐብታሞች በእለተ ቂያማ ድሆች ናቸው፡፡›› አሉ፡፡ በስተቀኝና በስተግራ፣ በፊትና በኋላ እያመላከቱ፡፡ ‹‹ይህን የሚያደርጉት ደግሞ በቁጥር አናሳ ናቸው፡፡››አሉ፡፡ (ቡኻሪና ሙስሊም)

አንዳንድ ጊዜ የአላህ መልእክተኛﷺ ለሁለት ወይም ለሦስት ቀናት እህል ባፋቸው ሳይዞር አከታትለው ይጾሙ ነበር፡፡ ሶሐቦች እንደርሳቸው ለማድረግ ፈቃድ ሲጠይቁ፡- ‹‹እንደዚህ አታድርጉ፡፡›› በማለት ይከለክሏቸዋል፡፡ ‹‹እርስዎ አከታትለው ይጾሙ የለ?›› ሲሏቸው ‹‹እኔ እንደናንተ አይደለሁም፡፡ ጌታዬ ይመግበኛል፡፡ ያጠጣኛል፡፡›› በማለት ይመልሳሉ፡፡ አከታትለው እንዳይጾሙ የከለከሏቸው ለነርሱ በማዘን ነው፡፡ (ቡኻሪ)

የአላህ መልክተኛﷺ በሁሉም የሕይወት መስክ ስብእናቸው የመጠቀ ከመሆኑ የተነሳ እርሳቸው የደረሱበትን የታላቅነት ደረጃ መድረስ ለኛ ለተራ ሰዎች የሚሞከር ላይሆን ይችላል፡፡ ይሁንና ሁላችንም እንደየ አቅማችን እንሞክረው ዘንድ በአርአያነት ተቀምጦልናል፡፡

በእርግጥ ከርሳቸው የልቅና ደረጃ መድረስ የሚችል አይገኝም፡፡ ግና ፈለጋቸውን በመከተል በአቅሙ ልክ እና በራሱ ዓለም ውስጥ ትንሹ ሙሐመድ መሆን የሚቸግረው የለም፡፡ ከኛ የሚፈለገው ይህ ነው፡፡

አላህ ከሰጠን ገንዘብ ማውጣት ያለብን የዘካ መጠን ምን ያህል እንደሆነ አውቀን መመጽወት እንችላለን፡፡ አላህ በሰጠን አቅም መስራት ያለብን በጎ ስራ መጠኑ ምን ያህል እንደሆነ ግን በትክክል ማወቅም አንችልም፡፡ ስለሆነም እስከ መጨረሻው እስትንፋሳችን ድረስ ባለን አቅም ሁሉ ለአላህ ተገዥ ሆነን ለመገኘት መጣር ይኖርብናል፡፡

ያለንበትን ሁኔታ በትክክል ለመመዘን ጥሩ ሚዛን አንሷርና ሙሐጅር የሆኑ ሶሐቦች ናቸው፡፡ የአላህ መልእክተኛﷺ ኮትኩተው ለፍሬ

ያበቋቸው ተማሪዎቻቸው  የአላህን ምስጋና ለማድረስ እስከ ቻይናና ሰመርቀንድ ድረስ ተጉዘዋል፡፡ ይህን ዲንና ኢማን በዓለም ላይ ለማሰራጨት ደከመን ሰለቸን ሳይሉ ብርቱ ጥረት አድርገዋል፡፡ ደክመዋል፡፡ ሰርተዋል፡፡ መስዋእትነት ከፍለዋል፡፡

# ክፍል ሦስት

- ቀልብ የሚስተካከለው ነቢዩን ﷺ በመከተል ነው፡፡
- ረሱሉን ﷺ በፍቅር መከተል
- የደስታ ዘመን -የነቢዩ ﷺ ስነ ምግባርና ፍቅር መስተዋት
- የረሱሉ ﷺ ፍቅር ዜማዎች
- በርሳቸው ላይ ሶለዋት ማውረድ

## ቀልብ የሚስተካከለው ነቢዩን በመከተል ነው

ሶሐቦች ከአላህ መልእክተኛﷺ መልካም አርአያነት በሚገባ ተጠቅመዋል፡፡ የሶሐቦችን ባህሪ መላበስ ከፈለግን በመጀመሪያ ቀልባችንን ማስተካከል ይጠበቅብናል፡፡ ስለ መልካም አርአያ የሚያወሳው የቁርአን አንቀጽ እንዲህ ይላል፡-

﴿ لَّقَدۡ كَانَ لَكُمۡ فِي رَسُولِ ٱللَّهِ أُسۡوَةٌ حَسَنَةٞ لِّمَن كَانَ يَرۡجُواْ ٱللَّهَ وَٱلۡيَوۡمَ ٱلۡأٓخِرَ وَذَكَرَ ٱللَّهَ كَثِيرٗا ٢١ ﴾ الأحزاب: ٢١

*‹‹የአላህ መልዕክተኛ፥ (ከመካከላችሁ) አላህንና መጭውን ዓለም ተስፋ ለሚያደርግ፥ አላህንም በብዛት ለሚያወሳ፥ መልካም አርአያ ነው፡፡›› (አል አህዛብ 21)*

በአንቀጹ እንደተገለጸው የአላህን መልእክተኛﷺ መልካም ስብእና በአርአያነት ለመከተል ውስጣዊና መንፈሳዊ ዝግጅት ያስፈልገናል፡፡ ይህም ዝግጅት አላህንና መጭውን ዓለም ተስፋ ማድረግና አላህን በብዛት ማስታወስ ናቸው፡፡

ኢባዳዎች የሚከናወኑበት የየራሳቸው ወቅት አላቸው፡፡ ኢማንን ግን ሁሌም መጠበቅና መንከባከብ ያስፈልገናል፡፡ እያንዳንዷ ቅጽበት በአላህ ያለንን እምነት ግዴታዎች የምንወጣባትና የአላህን ውዴታ የምንከጅልባት ናት፡፡

ስለዚህም ሙእሚን ቀልቡ እንዳይዳከምና የሰይጣንን ወስዋስ በተገቢው መልኩ መቋቋም እንዲችል አላህን ሁሌም ማስታወስ፣ ለቅጽበት እንኳ አለመዘንጋት ይጠበቅበታል፡፡ አላህ ይህን በማስመልከት ሲናገር፡-

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ ٱذۡكُرُواْ ٱللَّهَ ذِكۡرٗا كَثِيرٗا ٤١ ﴾ الأحزاب: ٤١

*‹‹እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን በብዛት አስታውሱ፡፡›› (አል አህዛብ 41)*

ይህ አንቀጽ አላህን ለምን ያህል ጊዜ ማስታወስ እንዳለብን ቁጥሩን መጥኖ አልነገረንም፡፡ በብዛት እንድናስታውስ ብቻ ነው የታዘዝነው፡፡ ብዛት ደግሞ ወሰን የለውም፡፡ ዳርቻው ምሉእነት ብቻ ነው፡፡ ስለዚህም የተሟላ የአላህ ባሪያ ለመሆን የፈለገ ሁሉ በእያንዳንዱ ቅጽበት በቻለው ልክ አላህን ማስታወስ ግድ ይሆንበታል፡፡ በሌላ አንቀጽ አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَتَطۡمَئِنُّ قُلُوبُهُم بِذِكۡرِ ٱللَّهِۗ أَلَا بِذِكۡرِ ٱللَّهِ تَطۡمَئِنُّ ٱلۡقُلُوبُ ٢٨ ﴾
الرعد: ٢٨

*“እነዚያ ያመኑትን፣ ልቦቻቸውም አላህን በማስታወስ የሚረኩትን (ይመራል)፡፡ አዋጅ ልቦች አላህን በማስታወስ ይረካሉ፡፡››(አል ረዕድ 28)*

የዚክር ዓላማ መልእክቱን ሳያስተነትኑ ቃላቱን መድገም ብቻ አይደለም፡፡ የቀልብን ሚና ይፈልጋል፡፡ ቀልብ አላህን የማስታወስን ለዛ ማጣጣም አለበት፡፡ አላህን ማስታወስ ከሙእሚን ቀልብ ውስጥ ሲኖር በሽታን ያስወግድለታል፡፡ ከቆሻሻና ከዝንጋታ ያጸዳዋል፡፡ በብርሃን ይሞላዋል፡፡ ለስላሳና እርጥብ ያደርገዋል፡፡ የአላህን ሚስጥሮች ለማወቅ ያለውን ጉጉት ይጨምርለታል፡፡ የቀልብ ምት ‹‹አላህ›› በሚለው የዚክር ቃል ሲቃኝ የሰውየው ኒያና ስራ ሁሉ የተስተካከለ ይሆናል፡፡ ነቢዩﷺ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹አላህን ማስታወስ እርሱን የመውደድ ምልክት ነው፡፡›› (በይሐቂ)

አፍቃሪ ፍቅረኛውን ያለ ለአፍታ እንኳ አይረሳውም፡፡ ቀልቡና ምላሱ ከማስታወስ አይቦዝኑም፡፡ የኢማንን ለዛ ማጣጣም የፈለገ በቀልቡም በምላሱም ዘወትር አላህን ማስታወስ አለበት፡፡ ቆሞም ተቀምጦም ተኝቶም ዚክር ማብዛት አለበት፡፡ አላህ ሰማያትንና ምድርን የፈጠረበትን ረቂቅ ሚስጥር እና ጥበብም ማስተንተን ይጠበቅበታል፡፡ አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿ ٱلَّذِينَ يَذۡكُرُونَ ٱللَّهَ قِيَٰمٗا وَقُعُودٗا وَعَلَىٰ جُنُوبِهِمۡ وَيَتَفَكَّرُونَ فِي خَلۡقِ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِ رَبَّنَا مَا خَلَقۡتَ هَٰذَا بَٰطِلٗا سُبۡحَٰنَكَ فَقِنَا عَذَابَ ٱلنَّارِ ١٩١ ﴾ آل عمران: ١٩١

*‹‹እነርሱ አላህን ቋመውም ተቀምጠውም፥ በጐኖቻቸው ተጋድመውም የሚያወሱትት፥ የሰማያትንና የምድርን (ድንቅ) አፈጣጠር የሚያስተነትኑት፥ "ጌታችን ሆይ! ይህን (ድንቅ ዓለም) እንዲሁ (ያለ ዓላማ) አልፈጠርከውም፤ ክብር ላንተ ይሁን። ከእሳት ቅጣት ጠብቀን።" (የሚሉት ናቸው)።›› (አሊ ዒምራን 191)*

በዚህ መልኩ ያልጠሩና ያልለዘቡ እንዲሁም ጥልቀትን የተነፈጉ ቀልቦች አላህን አይሹም። ይህም በመሆኑ አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿ أَفَمَن شَرَحَ ٱللَّهُ صَدۡرَهُۥ لِلۡإِسۡلَٰمِ فَهُوَ عَلَىٰ نُورٖ مِّن رَّبِّهِۦۚ فَوَيۡلٞ لِّلۡقَٰسِيَةِ قُلُوبُهُم مِّن ذِكۡرِ ٱللَّهِۚ أُوْلَٰٓئِكَ فِي ضَلَٰلٖ مُّبِينٍ ٢٢ ﴾ الزمر: ٢٢

*‹‹አላህ ልቦናውን ለኢስላም ክፍት ያደረገለትና ከጌታው ብርሃንን የተሞላ (ልቦናው በክህደት ከጨለመ ሰው ጋር እኩል ነውን?)። ልቦናዎቻቸው አላህን ከማስታወስ የደረቁ ለሆኑ ሰዎች ወዮላቸው። እነርሱ ግልጽ ስህተት ውስጥ ናቸው።›› (ዙመር 22)*

አንቀጹ እንደሚነግረን አላህን ማስታወስ የራቀ ሰው ቀልቡ ይደርቃል። ስሜት አልባ ደነዝ ይሆናል። ሰብአዊ ባህሪውን ይነፈጋል። በጥቅሉ አንድ ሰው ከአላህ መልእከተኛﷺ አርአያነት ይጠቀም ዘንድ ቀልቡ በአላህ ፍቅር መሞላት ይኖርበታል። ከከንቱ ስሜትና ከዱንያ ፍቅር መጽዳት አላህንና መጭውን አለም ተስፋ ማድረግ፥ ዚክርን ማዘውተር ግድ ይለዋል።

## ረሱሉንﷺ በፍቅር መከተል

የአላህን መልእክተኛﷺ በትክክል ማፍቀር፣ እርሳቸውን ማላቅና ትእዛዛቸውን በሙሉ ልብ መቀበል ነው። ምክንያቱም ስብእናቸው በሁሉም ገጽታው አላህ ለሰው ልጆች የለገሰው እዝነትና ችሮታ ዋነኛ

መግለጫ ነውና፡፡ የአላህ መልዕክተኛ ቀልብ ለአማኞች ምን ያህል በእዝነት እና በርህራሄ የተሞላ እንደነበር ተከታዩ የቁርአን አንቀጽ ያመለክታል፡፡

﴿لَقَدْ جَآءَكُمْ رَسُولٌ مِّنْ أَنفُسِكُمْ عَزِيزٌ عَلَيْهِ مَا عَنِتُّمْ حَرِيصٌ عَلَيْكُم بِٱلْمُؤْمِنِينَ رَءُوفٌ رَّحِيمٌ ١٢٨﴾ التوبة: ١٢٨

*‹‹ከናንተ ውስጥ የሆነ፣ ችግራችሁ የሚያሳስበውና (ለስኬታችሁ) ጉጉ የሆነ፥ (ለአማኞችም) እጅግ ርኅሩኅና አዛኝ መልዕክተኛ መጣላችሁ፡፡››* *(አል ተውባ 128)*

ተከታዩ ሐዲስ ለኡመታቸው የነበራቸውን ርህራሄ ያጎላል፡፡ አብደላህ ቢን መስዑድ እንዲህ አውግተውታል፡-

የአላህ መልእከተኛﷺ ሊሞቱ አንድ ወር ሲቀራቸው እንደሚሞቱ አረዱን፡፡ መለያያችን ሲደርስ ከእናታችን አኢሻ ቤት ሰበሰቡን፡፡ ወደኛ እየተመለከቱም አይኖቻቸው በእንባ አረገዙ፡፡ እንዲህ አሉን፡-

‹‹እንኳን ደህና መጣችሁ፡፡ አላህ ሰላም ያድርጋችሁ፡፡ ይዘንላችሁም፡፡ ያስጠጋችሁም፡ ይርዳችሁም፡፡ ከፍም ያድርጋችሁ፡፡፡ ይጥቀማችሁ፡፡ ያቅናችሁ፡፡ ሲሳይ ይለግሳችሁ፡፡ ለመልካም ተግባር ይግጠማችሁ፡፡ ደህንነትን ይስጣችሁ፡፡ ስራችሁን ይቀበላችሁ፡፡ አላህን እንድትፈሩ አደራ እላችህኋለሁ፡፡ እናንተንም ለአላህ አደራ ሰጥቻችኋለሁ፡፡ እርሱን ተክቸላችኋለሁ፡፡›› (ጦበራኒ)

የአላህ መልእክተኛ ﷺ ስነ ምግባራዊ በሆነ ንግግራቸው፣ ተግባራቸውና ሕይወታቸው ቅን መሪ ናቸው፡፡ እዝነታቸውም የሰውን ልጅ ባጠቃላይ ያካተተ ነው፡፡

የእስልምናን መልእክት ለማድረስ ብዙ መከራዎችን ተሸክመዋል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ሰዎች መቀናትን ያገኙ ዘንድ በመሻት ራሳቸውን ለአደጋ እስከማጋለጥ ይደርሳሉ፡፡ አላህም በዳእዋ ሂደታቸው ለኡመታቸው

በሚያሳዩት ጭንቀት ራሳቸውን ለአደጋ እንዳያጋልጡ እንዲህ ሲል አስጠንቅቋቸዋል፡-

﴿ فَلَعَلَّكَ بَـٰخِعٌ نَّفْسَكَ عَلَىٰٓ ءَاثَـٰرِهِمْ إِن لَّمْ يُؤْمِنُوا۟ بِهَـٰذَا ٱلْحَدِيثِ أَسَفًا ﴿٦﴾ ﴾ الكهف: ٦

*‹‹በዚህ መልዕክት ባለማመናቸው የኋላ ኋላ ራስህን በቁጭት እንዳታጠፋ ያሰጋል፡፡›› (አል ከህፍ 6)*

በሌላ አንቀጽ እንዲህ ብሏቸዋል፡-

﴿ لَعَلَّكَ بَـٰخِعٌ نَّفْسَكَ أَلَّا يَكُونُوا۟ مُؤْمِنِينَ ﴿٣﴾ ﴾ الشعراء: ٣

*‹‹(አማኞች ባለመሆናቸው ራስህን (በቁጭት) እንዳታጠፋ ያሰጋል፡፡›› (አል ሹዓራእ 3)*

እነዚህ አናቅጽ እንደሚያመለክቱት ሁሉም ሰው ቢሰልምና ከእሳት ቢድን የአላህ መልእክተኛ ፍላጎት ነበር፡፡

የአላህ መልእክተኛﷺ ለኛ የነበራቸው ፍቅርና ርህራሄ ይህን ያህል ከሆነ እኛ ለዚህ ውለታቸው ምን ምላሽ መስጠት ይጠበቅብናል? የአላህን መልእክተኛﷺ የመውደዳችን መለኪያ ቁርአንንና ሱንናን መከተላችን፣ ባህሪያችን በርሳቸው ባህሪ መቀረጹ ነው፡፡ ለርሳቸው ደህንነት ሲሉ ሁሉንም ነገር ለመስዋእትነት ያቀረቡ ሶሐቦች እርሳቸውን በተመለከተ የነበራቸው ስሜት ምን ይመስላል? ባህሪያቸውን ወደ እርሳቸው ባህሪ እንዴት ቀየሩ? የነቢዩ ስነ ምግባር በነርሱ ሕይወት ላይ እንዴት ተንጸባረቀ? እኛ ከነርሱ አንጻር ያለንበት ተጨባጭ ሁኔታ ምን ይመስላል? ለረሱሉﷺ ያለንን ፍቅር በነዚህ መለኪያዎች መመዘን ግድ ይለናል፡፡ ቀልባችንን በርሳቸው ስነ ምግባር መመዘን ይኖርብናል፡፡ ነፍሳችንን ከወንጀል አጽድተን፣ ከርክሰት አንጽተን የርሳቸውን ንጹህና የተላቀ ባህሪ መውረስ ግድ ይለናል፡፡ የርሳቸውን ሕይወት በአርአያነት ተከትለን መንፈሳዊና ሞራላዊ ሕይወት ልንኖር ግድ ይለናል፡፡

ወደ አላህ የሚያቃርበው ሚስጥር የአላህን ኪታብና የነቢዩን ﷺ ሱንና በንጹህ ልቦና በመመርመር፣ የነቢዩን ስነ ምግባርና መመሪያ በመከተል፣ አላህንና መልእክተኛውን የሚወድን ሁሉ በመውደድ፣ እነርሱን የሚጠላን ሁሉ በመጥላት ይገኛል፡፡

አላህን መውደድ ቀልብን ሕያው ያደርጋል፡፡ ጤንነትና ሰላም ይለግሰዋል፡፡ ቀጥተኛነትን ያጎናጽፈዋል፡፡ ፍቅርና ጥላቻ በአንድ ቀልብ ውስጥ በአንድነት ሊኖሩ አይችሉምና፡፡ አንደኛው ከሌለ ቀልብ በሌላኛው መሞላቱ አይቀርም፡፡ በሁለቱ ባህሪያት መካከል ያለው ልዩነት ልክ እንደ ምስራቅና እንደ ምእራብ ሲሆን ወደ አንዱ ስትቀርብ በዚያው መጠን ከሌላው ትርቃለህ፡፡ አንድ ገጣሚ የአላህን መልእክተኛ ﷺ ከመውደድና ሱንናቸውን ከመከተል የራቁ አማኞችን እንዲህ ብሏቸዋል፡-

ዋ፣ ማሳዘናቸው

ከእርሳቸው እዝነት የራቁ

ፍቅራቸውን የተነፈጉ

በዝንጉነታቸው

ሁለቱን ሐገር ማጣታቸው፡፡

አዎ፣ በእርግጥም ነቢዩን ﷺ ያልወደደ ተዘናግቷል፡፡ ሁለቱንም ዓለማት አጥቷል፡፡ አላህ ሆይ፣ ለርሳቸው ፍቅር ተገቢ ሰዎች አድርገን፡፡ አቻ የለሽ የፍቅርና የእዝነት ውቅያኖስ ናቸውና፡፡

መልእክተኛው ﷺ ለተቀናቃኞቻቸው የነበራቸው ስሜት ይገርማል፡፡ እርሳቸው ወደ ቅኑ ጎዳና ሊመሯቸው ጥረት በሚያደርጉ ጊዜ እነርሱ ቢያዋርዷቸውም፣ በድንጋይ ቢደበድቧቸውም የዓለማት እዝነት የሆኑት መልእክተኛ ግን ለነርሱ በጎ ይውሉላቸው ነበር፡፡ ቅኑን ጎዳና ይመራቸው ዘንድም አላህን ይለምኑላቸው ነበር፡፡ ዘይድ ቢን አልሐሪስ በሁኔታቸው በመገረም እንዲህ ሲል ጠየቃቸው፡-

‹‹የአላህ መልእክተኛ ሆይ፣ እነርሱ ይህን ያህል እየደበደቡዎት በነርሱ ላይ ለምን ዱዓ አያደርጉም?››

ነቢዩﷺ ግን እንደተለመደው ለነርሱ በጎ ነገርን መመኘታቸውን፣ መልካም ዱዓ ማድረጋቸውን ቀጠሉ፡፡ የዓለማት እዝነት እንጅ ጥፋት ተደርገው አልተላኩምና፡፡ እንዲህ አይነት ድንቅ መስዋእትነት፣ መልካም ቀልብ ባለቤትነትና አዛኝነት ታይቶ ይታወቃልን? ከመልእክተኛውﷺ ውጭ ይህን ስብእና ማን የተጎናጸፈ አለ?

የሰው ልጅ በነቢዩﷺ አማካይነት ወደላቀ ዓለም ያሸጋግረው ዘንድ ይጠብቀው የነበረውን መሪ አግኝቷል፡፡ ስለዚህም የነቢዩንﷺ እጅግ ጽድቅና ተምሳሌታዊ ስብእና ካየ በኋላ በእንስሳዊ ሕይወቱ የቀጠለ እርሳቸው ሳይላኩ በፊት በመሐይምነት ዘመን ከነበሩት ሰዎች የበለጠ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

ባለንበት ዘመን በሐይል ስካርና እርስ በርስ በመበዳደል ላይ የሚገኘው የሰው ልጅ እንደ ነቢዩ አይነት መሪ ስብእና ይሻል፡፡

በታሪካችን አንጸባራቂ ዘመናት ትልቅ ስኬት ሊመዘገብ የቻለው የነብዩን ስብእና በመላበስ ራሳቸውን ለሕብረተሰባቸው በተምሳሌትነት ያቀረቡ ታላላቅ ስብእናዎች በመኖራቸው ነው፡፡ ዙሪያችንን ስንቃኝ፣ ያለንበትን ተጨባጭ ሁኔታ ስንፈትሽ የሚያጋጥመን አሳዛኝ ነገር ሕዝባችን ተምሳሌታዊ ስብእናዎችን በማጣት በመንፈሳዊ እና ሞራላዊና አመራር መክሰሩ ነው፡፡

የኢማን ጀግኖች ሆነን ነቢዩንﷺ በትክክል የተከተሉ እና ቀልቦቻቸው በወኔ የተሞሉ፣ በታሪክ አቻ የማይገኝላቸው ሶሐቦች ከደረሱበት ደረጃ እንደርስ ዘንድ የስነ ምግባር ተምሳሌት ስብእናዎች ሊኖሩን ይገባል፡፡ ይህ ይሆን ዘንድ የሶሐቦችን ሕይወት በጥሞና መመርመር፣ ቃላቸውን መስማት፣ መልእክታቸውን መረዳት፣ እነርሱ የኖሩበትን የኢማን አለም መኖር ይጠበቅብናል፡፡

ከዚህች ጠፊ ዓለም ጋር የነበራቸው ግንኙነት ምን ይመስላል? አላህ የለገሳቸውን የአእምሮ፣ የመንፈስና የሕሊና ጸጋ ለራሳቸውም ሆነ ለሰው ልጅ የደስታ መንገድ ለማበጀት እንዴት እንደተጠቀሙበት በወጉ መረዳት ያስፈልገናል፡፡

## የደሰታ ዘመን- የነቢዩﷺ ስነ ምግባርና ፍቅር መስታወት

የመልእክተኛው መንፈሳዊ ተጽእኖና ኩትኮታ ሰብአዊነትን የማያውቀውንና የአውሬ ሕይወት ይኖር የነበረውን ያን የጃሂልያ ማሕበረሰብ በአጭር ጊዜ ውስጥ በመለወጥ የሰው ልጅ በእስካሁኑ ታሪኩ ወዳልደረሰበትና በአድናቆት ወደሚመለከተው እጅግ አንጸባራቂና ስልጡን ማሕበረሰብ ለወጠው፡፡ ይህ ማሕበረሰብ የሶሐቦች ማሕበረሰብ ነው፡፡ በነቢዩﷺ ጥረት በአንድ ሐይማኖት፣ በአንድ ስልጣኔና ባህል፣ በአንድ ሕግና መንግስት ስር የተሟላ ሰብአዊ ሕብረተሰብ ማነጽ ተቻለ፡፡

የነቢዩﷺ ትምህርትና ኩትኮታ መሐይማን አረቦችን ወደ ምሁርነት፣ አውሬና ስርአት አልባ ወንጀለኞችን ወደፍጹም ሐይማኖተኝነትና ደግነት ለወጣቸው፡፡ በአላህ ፍቅርና ፍርሃት የተሞሉ፣ ሕይወታቸውንም በዚሁ አግባብ የሚመሩ አስደናቂ ሰዎች አደረጓቸው፡፡

በረዥሙ ታሪኩ አንድም እንኳ ሊወሳ የሚችል ግለሰብ ማፍራት ያልቻለው ያ ማሕበረሰብ በመልእክተኛውﷺ መንፈሳዊ እነጻ አማካይነት በአስደናቂ ስብእናዎች የተዋቡ እጅግ በርካታ ታላላቅ ሰዎች ፈለቁበት፡፡

እነዚህ ስብእናዎች ከነቢዩ ﷺ የቀሰሙትን የኢማን ብርሃን ይዘው ወደ አራቱም የዓለማችን ማእዘናት ተበተኑ፡፡ እያንዳንዳቸውም የእውቀትና የጥበብ ተቋማት ለመሆን ታደሉ፡፡

በአረቢያ በረሃ ላይ የፈነጠቀው ብርሃን ለሰው ልጅ ዘልዓለማዊ ብርሃንን ለገሰ፡፡ ፍትህንና እውነትን ከአጽናፍ አጽናፍ አዳረሰ፡፡ አላህ የሰውን ልጅ የፈጠረበት ዓላማም ተሳካ፡፡

ነቢዩ ሙሐመድﷺ ያነጿቸው እነዚያ ግለሰቦች የእውቀት ማሕበረሰብ አነጹ፡፡ ያ ዘመን ሰዎች በጥልቀት የሚያስቡበት፣ አላህንና መልእክተኛውን በወጉ እና በቅርበት ያወቁበት ዘመን ነበር፡፡ አላህ ለሶሐቦች ተውሂድን የአስተሳሰባቸው እና የእምነታቸው አስኳል አደረገው፡፡ ሶሐቦች ቀልቦቻቸውን ከዱንያዊ ጥቅም ሙሉ በሙሉ አጸዱ፡፡ የእምነትን ለዛ አጣጣሙ፡፡ ገንዘብ የዓላማ ማስፈጸሚያ እንጀ ዓላማ የመሆኑ ነገር አከተመ፡፡ የእዝነትን አድማስ አሰፉ፡፡ ዋነኛ መርሃቸው ሌሎችን ማገልገል ሆነ፡፡ እናም ዓለም አይታቸው የማታውቅ አስደናቂ የመስዋእትነት ድርጊቶች ተከናወኑ፡፡

አንዲት ሐዲስ ለመፈለግ ለአንድ ወር በእግሩ ተጉዞ መስዋእትነት የሚከፍል፣ በሐዲሱ ባለቤት ስብእና ባለመተማመኑም ያሰበውን ሳይፈጽም የሚመለስ፣ ይህን ሁሉ መስዋእትነት መክፈሉም ምንም መስሎ የማይታየው ስብእና ተፈጠረ፡፡

ሶሐቦች ከአላህ መልእክተኛﷺ ተከታዮቹን ቁም ነገሮች ቀሰሙ፡-

1) ባህሪያቸው ልክ እንደርሳቸው አንጸባራቂ ሆኗል፡፡

2) ከአላህ የተለየ ቅርበት አግኝተዋል፡፡

በነዚህ በሁለቱ እድሎቻቸው ሰበብ ሶሐቦች ከክፋትና ከሐሰት ጸዱ፡፡ የሐቅና የበጎነት ውበት ሕይወታቸውን አደመቀው፡፡ ስለ አላህ፣ ስለ ሕይወት፣ ስለ ዩኒቨርሱና ስለ ራሳቸው አዲስ ምልከታ አገኙ፡፡ የሕይወት ዓላማቸው የነቢዩንﷺ ባህሪ መላበስ ሆነ፡፡ ትንሽ መስታወት የጸሐይን ብርሃን እንደምታንጸባርቀው እነርሱም የነቢዩﷺ እንጸብራቂዎች ለመሆን ተጉ፡፡

መዲና ላይ በ400 ቤተሰቦች የታነጸው ኢስላማዊ መንግስት በ10 ዓመታት ጊዜ ውስጥ እስከ ኢራቅና ፍልስጥኤም ደረሰ፡፡ ነቢዩﷺ በሞቱ ጊዜ ይህ መንግስት ከሮማና ከፋርስ ሐያላን ጋር በመፋለም ላይ ነበር፡፡

ይህ ሁሉ ሆኖ ግን ሶሐቦች የአኗኗራቸውን አይነትና ደረጃ፣ እንዲሁም የቤታቸውን አቀላለስ ከ10 ዓመታት በፊት ከነበረው አልቀየሩም፡፡ በዙህድ ሕይወታቸው ቀጠሉ፡፡ የሶሐባ ትውልድ በቅንጦት ላይ የተመሠረተ ሕይወት አያውቅም፡፡ የአካላቸው የነገ ማረፊያ ቀብር መሆኑን ያውቁ ነበርና፡፡ ይህም በመሆኑ ዓለማዊ ድሎትን ከማጋበስና ከወሰን ባለፈ አኳኋን ከመጠቀም በከፍተኛ ሁኔታ ይጠነቀቁ ነበር፡፡ አላህ የሰጣቸውን ጸጋ ለሰው ልጅ መቀናት እና ደስታ በማዋል የኢማንን ለዛ ይበልጥ ያረጋገጡበት ነበር፡፡

በተበደለው እና በተጨቆነው የሰው ልጅ ማሕበረሰቦች ውስጥ ኢስላም እንደ ንጋት ብርሃን በፍጥነት ሊሰራጭ የቻለው ሶሐቦች በደረሱባቸው ቦታዎች ሁሉ ያሳዩት በነበረው ስብእና ሳቢያ ነው፡፡

ሶሐቦች የነቢዩን ﷺ ልዩ ኩትኮታ ያገኙ፣በኢማናቸው የተለየ፣ በኢባዳ፣ በእውነተኛነት፣ በፍትህ፣ በቀልብ ሐብታምነት፣ በመልእክቱ ብርሃን የተሞሉ ነበሩ፡፡ ስለዚህም ፍጡራንን በፈጣሪ ዓይን አዩ፡፡ የሰውን ልጅ በእዝነትና በርህራሄ ተመለከቱት፡፡

ከቀልባቸው ውስጥ አላህንና መልእክተኛውን ﷺ አኖሩ፡፡ ማንበብ እና መጻፍ የማይችለው ያ መሐይም ማሕበረሰብ በዚህ መልኩ የስልጣኔን ጣሪያ ደረሰ፡፡ ከቀልቦቻቸው ውስጥ ምንጊዜም ተከታዩ ጥሪ ያቃጭል ነበር፡-

‹‹አላህ ከኛ ምን ይፈልጋል? አላህን የሚያስደስት ስራ ምንድን ነው? ነቢዩ ﷺ እኛን በምን ሁኔታ ውስጥ ሆነን ማየት ይፈልጋሉ?››

ሶሐቦች በታላቅነታቸው ሁሉንም ዘመናት አስከነዱ፡፡ የኖሩበት ዘመንም በነርሱ በረከት በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ እጅግ አስደሳች ዘመን ለመሆን በቃ፡፡

እነዚህ አማኞች በክፉ ከምታዘው ነፍስ ክፋት ጸዱ፡፡ ነፍሳቸውን ገርተው ሁሌም የምትጠይቅ፣ የምትጠነቀቅና ራሷን የምትተች ጻእድ ነፍስ

አደረጓት፡፡ እናም እነዚያ ዘላንና የአውሬ ሕይወት ይኖሩ የነበሩ ግለሰቦች ወደ መላኢካነት ተቀየሩ፡፡

በኢስላም የሸሪዓ ጥናት ውስጥ ጉልህ ድርሻ ያላቸው ኢማም ቀራፊ (በ684 ሂጅሪያ የሞቱ) እንዲህ ሲሉ ጽፈዋል፡-

‹‹የአላህ መልእክተኛ የሶሐቦችን ስብእና ከማነጽ ውጭ ሌላ ተአምር ባይኖራቸው እንኳ ይህ ብቻ ለነብይነታቸው በቂ ማረጋገጫ ነው፡፡››

ሶሐቦች እያንዳንዳቸው የቁርአንን ተአምር የሚመሰክሩ ሕያው ተምሳሌቶች ነበሩ፡፡ ሰብአዊ እሴቶችን በመተግበር የመጨረሻውን የምጥቀት ጫፍ ደርሰዋል፡፡ በዚያ ዘመን አእምሮን ከቀልብ አዋደው፣ የሁለቱንም ፍላጎት በሚዛናዊነት አሟልተውና አጣጥመው ለመኖር ችለዋል፡፡ ወደምሉእነት ደረጃ ደርሰዋል፡፡ ጥልቅ አስተሳሰብ፣ በጥበብ የከበረ አእምሮና የንቁ ሕሊና ባለቤት ለመሆን ችለዋል፡፡ ይህች ዓለም ለነርሱ ፈተና መሆኗን ለአፍታም አልዘነጉም፡፡ ቀልቦቻቸውም የአላህን ችሎታና ታላቅነት፣ ልእልናውንና ሐያልነቱን በጥልቀት ተረድተዋል፡፡

ይህም ስለሆነ በመልካም ለማዘዝና ከመጥፎ ለመከልከል እስከ ቻይና፣ ስፔንና ሰመርቀንድ ተጉዘዋል፡፡ ያ መሐይም ማሕበረሰብ እውነትን በትክክል የተረዳና የሚኖር ስልጡን ሆነ፡፡ ከነርሱ ዘንድ ሌሊቱ ወደ ቀን ተቀየረ፡፡ አመቱ ሁሉ በልግ ሊሆን ቻለ፡፡ አስተሳሰባቸው ተለወጠ፡፡ በዙሪያቸው ስላሉ ነገሮች ሁሉ በጥልቀት ማሰብን ተካኑ፡፡ ሕይወታቸውን ከአላህ ፍላጎት አኳያ አደራጁ፡፡ እዝነትና ጥሩነት፣ እውነትን የመርዳት ፈቃድና ክህሎት የመጨረሻውን የምጥቀት ጫፍ ነካ፡፡

ሊሞት ጥቂት ደቂቃዎች የቀሩት ሶሐባ እነዚህን ደቂቃዎች ወደ አላህ ጥሪ ለማድረግ ሲጠቀምባቸው ማየት በእርግጥም በግርምት ያስደምማል፡፡ ቀልቡ በደስታ ተሞልቶ ሊገድለው ለተሰናዳው ሰው እንዲህ እንዳለው ተዘግቧል፡-

‹‹እነዚህን ቅጽበቶች ስላገኘሁ ተጽናንቻለሁ፡፡ ወደ አላህም እጠራሀለሁ፡፡››

ሶሐቦች በቁርአን ፣ ከቁራአን ጋር ለቁርአን ኖረዋል፡፡፡ ሕይወታቸውን ለርሱ ለግሰዋል፡፡ ታሪክ አይቶት የማያውቀውን ሚናና ጽናት፣ ትግልና መስዋእትነት አሳይተዋል፡፡ እጅግ አሰቃቂ ለሆነ በደልና ስቃይ ቢዳረጉም ከሚያምኑበት እሴት ፈቀቅ አላሉም፡፡ ቤት ንብረታቸውን ትተው፣ ሐገራቸውን ለቀው በአላህ ትእዛዝ ስር ለመኖር ተሰደዋል፡፡ ለዚህ የተቀደሰ ዓላማ ያላቸውን ሁሉ ነገር ሰውተዋል፡፡

ቁርአንን ለመማርና እያንዳንዱን አንቀጽ ወደ ሕይወት ለመቀየር የነበራቸው ጉጉት እጅግ አስገራሚ ነበር፡፡ እጅግ አደገኛ በሆነ ወቅት እንኳ ከቁርአን መነጠል አይፈልጉም፡፡ ዑባድ ቢን በሽር በአንድ ዘመቻ ያጋጠመውን እንዲህ አውግቷል፡-

ነቢዩﷺ በአንድ ቦታ ላይ አረፉ፡፡ ‹‹ዛሬ ሌሊት ለጥበቃ ተግባር ዝግጁ የሆነ ማን ነው?›› ሲሉም ጠየቁ፡፡ ከሙሐጀሮች መካከል አማር ቢን ያሲርን እና አንድ የአንሷር ሰው (ዑባድ ቢን በሽር)፡- ‹‹የአላህ መልእክተኛ ሆይ፣ እኛ ዝግጁ ነን››በማለት ተነሱ፡፡ ‹‹ከሸለቆው በር ላይ ሁኑ፡፡›› ሲሉ አዘዟቸው፡፡

ከታዘዙት ቦታ ሲደርሱ አንሷሩ ለሙሐጅሩ፡- ‹‹የትኛውን የሌሊቱን ክፍል እንድጠብቅ ትሻለህ›› ሲል ጠየቀው፡፡ ‹‹የመጀመሪያውን አጋማሽ›› አለና በሙሐህጅሩ ተኛ፡፡ አንሷሩ ይሰግድ ጀመር፡፡ ጠላት ከሩቅ አየው፡፡ ለጥበቃ መሠማራቱንም ተረዳ፡፡ በቀስት አስወንጭፎ ወጋው፡፡ አንሷሩ ግን ሶላቱን ማቋረጥ አልፈለገም፡፡ በቀስቱን ነቅሎ መስገዱን ቀጠለ፡፡ ለሁለተኛ ጊዜ ወጋው፡፡ ይህንንም ነቅሎ ሶላቱን ቀጠለ፡፡ ለሦስተኛ ጊዜ ወጋው፡፡ እርሱንም ነቀለና ቀጠለ፡፡ ሩኩዕና እና ሱጁድ አደረገ፡፡ ባልንጀራውንም ቀሰቀሰና፡- ‹‹ተነስ ጥቃት ደርሶብኛል፡፡›› አለው፡፡ ዘሎ ተነሳ፡፡ ያስወነጨፈው ሰው ይህን ሲያይ እግሬ አውጭኝ ፈረጠጠ፡፡ ሙሐጅሩ የአንሷሩን ደም ሲያይ፡- ‹‹ለምን ቀድመህ አልቀሰቀስከኝም?›› ሲል ጠየቀው፡፡ አንሷሩ ሰው እንዲህ ሲል የሚገርም ምላሽ ሰጠ፡-

‹‹አንዲት የቁርአን ምእራፍ (ሱረቱል ከህፍን) እያነበብኩ ነበር፡፡ ሳልጨርሳት ማቆም አልፈለግኩም፡፡ አከታትሎ ቀስት ሲያስወነጭፍ ጊዜ ሩኩእ ወረድኩና ቀሰቀስኩህ፡፡ በአላህ እምላለሁ፣ የአላህ መልእክተኛﷺ የጣሉብኝን የጥበቃ ሐላፊነት እንዳላጎድል ባልሰጋ ኖሮ ሳልጨርሳት በፊት ካልገደለኝ በቀር መቅራቴን አላቆምም ነበር፡፡›› (አቡ ዳውድ፣ አህመድና በይሐቂ)

ሶሐቦች በቁርአን ተማግሮ የተለሰነ ሕይወት ኖረዋል፡፡ በእያንዳንዱ የዲን መሠረት ወደር የማይገኝለት ደስታ ያገኙ ነበር፡፡ እያንዳንዱ የቁርአን አንቀጽ በነርሱ እይታ ከሰማይ የወረደ አምላካዊ ማእድ ነው፡፡ ቁርአንን ለመረዳትና ለመተግበር ብርቱ ጥረት አድርገዋል፡፡ ሊኖር የሚሹት ሕይወት አርአያ (Role Model) አድርገውታል፡፡

ለቁርአን የነበራቸውን ፍቅር የሚያመለክተው ሌላው አጋጣሚ እንስቶች ከባሎቻቸው የሚጠይቁት የጋብቻ ጥሎሽ (መህር) ቁርአን እንዲያስተምራቸው ብቻ ይሆን ዘንድ መስማማታቸው ነው፡፡

ሶሐቦች ሌሊት አዘውትረው ይሰግዳሉ፡፡ የእለት ዚክራቸውን (አውራድ) ሱህር ላይ ይፈጽማሉ፡፡ ከሞቀ ፍራሻቸው ላይ ቁርአን መቅራት ልዩ ሐሴት ይሰጣቸዋል፡፡ ሌሊት በቤታቸው አጠገብ ያለፈ እንደ ንብ ጩኸት የነርሱን የቁርአንና የዚክር ድምጽ ይሰማ ነበር፡፡

የአላህ መልእክተኛምﷺ እጅግ ፈታኝ በሆኑ ሁኔታዎች ውስጥ ሳይቀር ቁርአንን ያስተምሯቸው ነበር፡፡ አነስ እንዲህ ሲሉ አውግተዋል፡-

‹‹ጦልሐ አንድ ቀን ወደ ነቢዩﷺ መስጊድ ሲሄድ ነቢዩ አስሐበ ሱፋዎችን ቁርአን ሲያቀሩ ተመለከተ፡፡ በጣም የጠናባቸውን ረሃብ ለማስታገስ ከሆዳቸው ላይ ድንጋይ አስረዋል፡፡፡

ቁርአንን ለመማር ጊዜያቸውን ሁሉ አውለዋል፡፡ እርሱን በማንበብ ያዜማሉ፡፡ ከቁርአን ጋር በመሆን ይረካሉ፡፡[1]

---

[1] አቡ ኑዓይም፣ አልሁልያህ

ሶሐቦች የአላህን መልእክተኛﷺ ፈለግ አጥብቀው በመከተላቸው ምክንያት መዲና በታላላቅ የቁርአን፣ የሐዲስና የሸሪዓ ሊቃውንት ተሞላች፡፡ የእውቀት ማእከል ለመሆንም በቃች፡፡

እናም ያ ምእተ ዓመት የሰው ልጅ የደስታን የመጨረሻ ጫፍ የደረሱበት ምእተ ዓመት ሆነ፡፡ ያ ትውልድም በሰው ልጅ ታሪክ ወደር የማይገኝለት ድንቅ ትውልድ ለመሆን በቃ፡፡

በዓለማችን ውስጥ ያሉ ፈላስፎች፣ የስነ ልቦና ተመራማሪዎች፣ የማሕበራዊ ሳይንስና የትምህርት እንዲሁም የሌሎች መስኮች ሊቃውንት በአንድ ተሰባስበው፣ ያላቸውን እውቀትና ክህሎት ሁሉ ቢያፈሱ እንደዚያ የደስታ ትውልድ አይነት እጅግ የመጠቀ ትንሽ ማሕበረሰብ እንኳ ማነጽ ይችላሉን? በፍጹም፣ የዚያን ማሕበረሰብ ልእልና ሸራፊ እንኳ እውን ማድረግ አይቻላቸውም፡፡

ለምሳሌ ፋራቢ በምናቡ የሳለውን ‹‹የምርጥ ከተማ›› እሳቤ እንውሰድ፡፡ በተጨባጭ ዓለም እውን መሆን ተስኖት በቴዮሪ ብቻ ቀርቷል፡፡[1]

## የረሱሉﷺ ፍቅር ዜማዎች

የአላህ መልእክተኛﷺ አምሳያ የሌላቸው የእዝነትና የፍቅር ምንጭ ናቸው፡፡ የሰውን ልጅ ወደ አላህ ፍቅር ውቅያኖስ መርተዋል፡፡ መልእክተኛውንﷺ መውደድ አላህን የመውደድ አካል ነው፡፡ እርሳቸውን መታዘዝ አላህን የመታዘዝ አካል ነው፡፡ ትእዛዛቸውን መጣስ የአላህን ትእዛዝ ከመጣስ ይቆጠራል፡፡ ቁርአን ይህን በማስመልከት ሲናገር፡-

﴿ قُلْ إِن كُنتُمْ تُحِبُّونَ ٱللَّهَ فَٱتَّبِعُونِى يُحْبِبْكُمُ ٱللَّهُ وَيَغْفِرْ لَكُمْ ذُنُوبَكُمْ ۗ وَٱللَّهُ غَفُورٌ رَّحِيمٌ ﴿٣١﴾
آل عمران: ٣١ ﴾

---

[1] የነ አርስቶትል (utopia)፣ የነማርክስ የኮሚኒስት ማሕበረሰብ ወዘተ ከወረቀት ባለፈ በተጨባጩ ዓለም ውስጥ ሊታዩ ያልቻሉ ማሕበረሰቦች ናቸው፡፡ (ተርጓሚው)

*በላቸው፡- "አላህን የምታፈቅሩ ከሆናችሁ ተከተሉኝ፤ አላህ ያፈቅራችኋል፤ ኃጢአቶቻችሁንም ይምራል፤ አላህ መሓሪ፥ አዛኝ ነው።" (አሊ ዒምራን 31)*

በቃለ ተውሂድ ውስጥ ‹‹ላኢላሐ ኢለላህ›› ከሚለው ቃል ቀጥሎ ‹‹ሙሐመደን ረሱሉላህ›› የሚለው ቃል ምንጊዜም ይኖራል፡፡ ይህን ሐረግ መደጋገምና በርሳቸው ላይ ሶለዋት ማውረድ ወደ አላህ ፍቅር መቃረቢያ መንገድ ተደርጓል፡፡ የዚህችም ሆነ የመጭው ዓለም ደስታ የሚገኘው ነቢዩን ﷺ በመውደድ ብቻ ነው፡፡ ዱንያ የአላህ ፍቅር መገለጫ ናት፡፡ ነቢዩ ሙሐመድ ﷺ የዚህ መገለጥ አስኳል ናቸው፡፡ ወደ አላህ የሚደረገው ጉዞ የሚያልፈው ነቢዩ ሙሐመድን ﷺ በመውደድ መስመር ብቻ ነው፡፡

ውብ ነገሮች ሁሉ የተሳሰሩት ከርሳቸው ፍቅር ጋር ነው፡፡ አዎ፣ የአምልኮ መንፈሳዊነት፣ በዓለማዊ ግንኙነት፣ በንግድ፣ በስራ በጥሩ ባህሪ መቃኘትም፣ መልካም ስነ ምግባር፣ አዛኝነት፣ የነቃ ሕሊና፣ ጥልቅ አስተሳሰብ፣ እነዚህ ሁሉ የነቢዩ ﷺ ፍቅር እንጽብራቂዎች፣ የርሳቸው የእውቀትና የእነጻ ማእድ ትሩፋቶች ናቸው፡፡

የአላህን ውዴታ ለማግኘት የነቢዩን ﷺ ፈለግ መከተል ግድ ነው፡፡ ማለትም የትኛውም ሙእሚን የርሳቸውን ዱካ እስካልተከተለ ድረስ የተሟላ ሰው ሊሆን አይችልም፡፡

መመሪያቸውን እስካላከበረ ድረስ፣ ባህሪያቸውን በአርአያነት እስካልያዘ ድረስ እውነተኛ ሐይማኖታዊ እርካታና ደስታ አይኖረውም፡፡ አላህ የምሉእ ስብእና ተምሳሌት አድርጓቸዋል፡፡ ኢስላም ይህን ስብእና ማስገኘት ይሻል፡፡ ይህ ስብእና በነቢዩ ማንነት ውስጥ ተገልጿል፡፡ አላህ የዓለማት እዝነትና የአማኞች አርአያ አድርጓቸዋል፡፡

ስለዚህም እርሳቸውን መታዘዝ የግድ ነው፡፡ ነቢዩን ﷺ መከተልን አላህ የርሱ ፍቅር መለኪያ መስፈርት አድርጎታል፡፡ እንዴት እንታዘዛቸው?

እርሳቸውን መታዘዝ የሚጀምረው ከልብ በመውደድ ነው፡፡ ነቢዩን በጣም ልንወድ፣ ከመንፈሳዊ ዓለማቸው ልንቋደስ ይገባል፡፡ አላህ ‹‹መልካም አርአያ›› ብሏቸዋልና፡፡

﴿ ۞ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓاْ أَطِيعُواْ ٱللَّهَ وَأَطِيعُواْ ٱلرَّسُولَ وَلَا تُبۡطِلُوٓاْ أَعۡمَٰلَكُمۡ ٣٣ ﴾ محمد: ٣٣

*‹‹እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ታዘዙ፡፡ መልዕክተኛውንም ታዘዙ፡፡ ሥራዎቻችሁንም አታበላሹ፡፡›› (ሙሐመድ 33)*

﴿ وَمَن يُطِعِ ٱللَّهَ وَٱلرَّسُولَ فَأُوْلَٰٓئِكَ مَعَ ٱلَّذِينَ أَنۡعَمَ ٱللَّهُ عَلَيۡهِم مِّنَ ٱلنَّبِيِّـۧنَ وَٱلصِّدِّيقِينَ وَٱلشُّهَدَآءِ وَٱلصَّٰلِحِينَۚ وَحَسُنَ أُوْلَٰٓئِكَ رَفِيقٗا ٦٩ ﴾ النساء: ٦٩

*‹‹አላህንና መልዕክተኛውንም የሚታዘዝ (በመጭው ዓለም) አላህ ፀጋውን ከለገሳቸው ከነቢያት፥ ከጻድቃንም፥ ከሰማዕታትና ከደጋጐች ጋር ይሆናል፡፡ ከነኝህ ጋር መጐዳኘት እጅግ ድንቅና ውብ፥ እጅግ ማራኪ ነው፡፡›› (አል ኒሣእ 69)*

የሙስሊሞች መመሪያ የሆነው ቁርአን የነቢዩንﷺ የቀልብ ዓለም ያቀርባል፡፡ ስብእናቸውን ያስቃኛል፡፡ መንፈሳዊነታቸውን ያስጎበኛል፡፡ ቁርአንን ለመረዳት ይህን ነብያዊ ዓለም ማወቅ ግድ ነው፡፡ ሶሐቦች ያን በማወቃቸው ለቁርአን ያላቸው ግንዛቤ ከማንም በላይ ሆነ፡፡ ነቢዩንﷺ ማወቅ በሐሴት የሚያስዋኝ ድንቅ ጸጋ ነው፡፡

ይበልጥ ስናውቃቸው ይበልጥ እንወዳቸዋለን፡፡ በውዴታችን ልክ ትእዛዛቸውና እቀባቸው፣ ሌላው ቀርቶ ጥቆማቸው ሳይቀር መልእክቱ ይገባናል፡፡ ጥበቡ ይገለጽልናል፡፡

ነቢዩﷺ ለሰው ልጅ የፍቅር መምህር፣ የሰላም ት/ቤት፣ የሐሴት ንጉስ፣ የሕልውና አስኳል፡ የፍጡራን ፈርጥ ናቸው፡፡

ቀልባቸውን ለአላህና ለመልእክተኛውﷺ የሰጡ፣ እነርሱን ያፈቀሩ ሙእሚኖች እድለኛ ናቸው፡፡ የነርሱን ፍቅር ከሌሎች ሁሉ ፍቅር ያላቁ አማኞች መታደላቸው፡፡

ነቢዩንﷺ በፍቅር ይበልጥ እንቅረባቸው፡፡ ቀልባችን ይበልጥ ይወቃቸው፡፡ ሱወይባህ የአላህን መልእክተኛﷺ የማጥባት እድል ካገኙ እንስቶች መካከል አንዷ ናት፡፡ የአቡ ለሃብ ባሪያ ነበረች፡፡ በተወለዱ ጊዜ መካ ላይ የነቢዩ ቀንደኛ ጠላት ለሆነው ለአጎታቸው ለአቡ ለሐብ ብስራት ነገረች፡፡ አቡ ለሐብ ከደስታው የተነሳ ይህችን ባሪያ ነጻ ለቀቃት፡፡ ይህን ያደረገው በወገንተኝነት ስሜት ነበር፡፡[1]

ከወገንተኝነት ስሜቱ የመነጨው ይህ ደስታው እንኳ በየሳምንቱ ሰኞ የእሳት ቅጣት እንዲቀልለት ምክንያት ሆኗል፡፡ አባስ ይህን በተመለከተ ተከታዩን አስተላልፈዋል፡-

‹‹አቡ ለሐብ ከሞተ በኋላ ለአንድ አመት ያህል በሕልም አላየሁትም፡፡ በኋላ ላይ ግን በአስከፊ ሁኔታ ውስጥ ሆኖ አየሁት፡፡ እንዲህ አለኝ፡-

‹‹ከሞትኩ እለት አንስቶ ረፍት አላገኘሁም፡፡ ግና ዘወትር ሰኞ ቅጣት ይቀልልኛል፡፡››

ነቢዩﷺ የተወለዱበት ቀን ሰኞ ነበር፡፡ በዚያው እለት አቡ ለሐብ ብስራት ደረሰው፡፡ ከደስታው የተነሳ፡- ‹‹ነጻ ለቅቄሻለሁ›› በማለት ሱወይባህን አበሰራት፡፡ ይህ ድርጊቱ እሳት ውስጥ ሆኖ እንኳ ጠቀመው፡፡ አጎታቸው አቡ ጧሊብ ለነቢዩ ጠበቃ በመሆናቸው እንደተጠቀሙት፡፡[2]

ይህ የአላህ ጠላት በርሳቸው መወለድ በመደሰቱ የእሳት ቅጣት እንደሚቀልለት ከተናገረ እርሳቸውን የወደዱ፣ ፈለጋቸውን የተከተሉ አማኞስ?

[1] አል ሰላቢ ቅ 1 ገጽ 138
[2] ሱሐይሊ፣ ረውዱል ኡኑፍ ቅ 1 ገጽ 273

## ሶሐቦች ለመልእክተኛው ﷺ የነበራቸው ፍቅር

ሶሐቦች ለነቢዩ ﷺ የነበራቸው ፍቅር በቃላት ሊገለጽ ከሚችለው በላይ ነው፡፡ ይህን የታደሉት በአላህ ችሮታ ብቻ ነበር፡፡ እያንዳንዱ ሶሐባ ከመልእክተኛው ﷺ ጋር በወዳጅነት ተሳስሯል፡፡ በፍቅር ጥብቅ ገመድ ተቆላልፏል፡፡ እናም በዚህ ፍቅር እንደ ሰማይ ኮከብ ደምቀዋል፡፡ እንደ ጸሐይ አብርተዋል፡፡ ከእያንዳንዱ ሶሐባ ሕሊና ውስጥ፡- ‹‹ነቢዩ እንደዚህ ያደርጉ ነበር፡፡›› የሚል ደወል ሁሌም ያቃጭላል፡፡ እናም በእያንዳንዱ የሕይወት እርምጃቸው እርሳቸውን ይከተላሉ፡፡ በሄዱበት ይሄዳሉ፡፡ ያሸተቱትን አበባ ሳይቀር ያሸታሉ፡፡ የተቀቡትን ሽቶ ይቀባሉ፡፡ እርሳቸው ከቆሙበት ቦታ ይቆማሉ፡፡

ሶሐቦች ለነቢዩ ﷺ የነበራቸው ብርቱ ፍቅር መገለጫ ተቆጥሮ አይዘለቅም፡፡ ጥቂት ናሙናዎችን ብቻ እንዘክር፡፡ እመት አኢሻ ፍቅሯን በግጥም ገልጻለች፡-

ቢሰሙ የግብጽ ሰዎች ውበቱን
ቢያውቁ ጻእድ ማንነቱን
የዩሱፍን ውበት ባናናቁ
እነዚያ ዙለይኻን ያሙ
የሙሐመድን ውበት ቢሰሙ
ከእጃቸው ይልቅ ቀልቦቻቸውን መቁረጥን በመረጡ፡፡

የአላህ መልእክተኛ ﷺ በቃለ ተውሂድ እንደተገለጸው የአላህ ባሪያ ሲሆኑ፣ የመልእክተኞች ሁሉ ፈርጥ፣ የፍጡራን ዓይነታ ናቸው፡፡ የአላህ ፍቅር መገለጫ ናቸው፡፡ ሙእሚን ከስጋዊ ስሜት፣ ከከንቱ ፍላጎት ጸድቶ መንፈሳዊነት ሲሰማው ከርሳቸው የፍቅር በረከት ለመቋደስ የመጀመሪያውን እርምጃ ተራምዷል፡፡

የነቢዩ ﷺ ፍቅር በሁለቱም አለማት ልእልናን ያጎናጽፋል፡፡ በዚህ ፍቅር ሰበብ ሶሐቦች ከፍተኛ ደረጃን አግኝተዋል፡፡ ማንም ሊደርስበት

ያልቻለውን ፍቅር ተጎናጽፈዋል፡፡ ሶሐቦች ለርሳቸው ከነበራቸው ፍቅር መሐል ጥቂቱን ብቻ ላጫውትህ፡፡

ነቢዩﷺ ወደ መዲና ሲሰደዱ ዋሻ ውስጥ ለመደበቅ ግስጋሴያቸውን ቀጠሉ፡፡ ጠላት እንዳያገኛቸው አቡበክር ሰግተዋል፡፡ እናም አንድ ጊዜ ከፊት ለፊታቸው ሌላ ጊዜ ከኋላቸው በመኀዝ ጥቃት እንዳያገኛቸው ሊከላከሉላቸው ጣሩ፡፡ በስጋት መታወካቸውን ነቢዩﷺ ደረሱበትና እንዲህ አሉ፡-

‹‹አቡበክር ሆይ፣ ለምንድን ነው አንዳንድ ጊዜ ከፊት ለፊቴ ሌላ ጊዜ ከኋላዬ የምትሄደው?" የአቡበክር ምላሽ ይህ ነበር፡-

‹‹የአላህ መልእክተኛ ሆይ፣ ጠላት እየተከተለህ እንደሆነ ሲታሰበኝ ከኋላህ እሄዳለሁ፡፡ ከፊት ለፊት አድፍጦ እንደሚጠብቀን ሳስታውስ ደግሞ ከፊትህ እሆናለሁ፡፡››

ነቢዩምﷺ እንዲህ አሉ፡፡

‹‹አቡበክር ሆይ፣ ከእኔ ደህንነት ባሻገር ሌላ መከራ ቢደርስብህ ትመርጣለህ?› አሉት፡፡ አቡበክርም፡- ‹‹አዎ፣ በእውነት በላከህ ጌታ እምላለሁ፣ የትኛውም መከራ ቢደርስብኝ ባንተ ላይ ከሚደርስ ጥቃት ያነሰ ነው፡፡›› (አልሐኪም)

ከዋሻው ሲደርሱ አቡበክር እንዲህ አሉ፡-

‹‹የአላህ መልእክተኛ ሆይ፣ እባብ ካለ እኔን አስቀድሞ እንዲነክሰኝ ቀድሜ ልግባ፡፡ ››

ይህን ፍቅር ተመልከቱ፣

አቡበክር ወደ ዋሻው ገቡ፡፡ በእጃቸውም ይዳብሱት ጀመር፡፡ ቀዳዳ ባገኙ ቁጥር ልብሳቸውን እየቀደዱ ይደፍኑታል፡፡ ብዙ ቀደዳዎችን በዚህ አኳኋን ደፈኑ፡፡ አንዱ ቀዳዳ ብቻ ቀረ፡፡ ልብሳቸው ተቀዶ አልቋልና የሚደፍኑበት ጨርቅ አላገኙም፡፡ በተረከዛቸው ከደኑትና ነቢዩ ﷺእንዲገቡ ጋበዙ፡፡

ነቢዩﷺ ከጭናቸው ላይ አሸለቡ፡፡ እባብ መጣ፡፡፡ መውጫ ቀዳዳው በአቡበክር እግር ተደፍኗል፡፡ ተረከዛቸውን ነከሳቸው፡፡ ነቢዩንﷺ ላለመቀስቀስ ሲሉ ስቃዩን ዋጥ አደረጉት፡፡ እግራቸውን እንኳ አላንቀሳቀሱም፡፡ እንባቸውን ግን መቆጣጠር አልቻሉም፡፡ ግድቡን ጥሶ ከነቢዩ ﷺ ጉንጭ ላይ ፈሰሰ፡፡ ነቢዩﷺ ከእንቅልፋቸው ነቁ፡፡ የአቡበክር ፊት መለዋወጡንም አስተዋሉ፡፡ ማልቀሳቸውን ተመለከቱ፡፡ ምክንያቱን ጠየቋቸው፡፡ በእባብ መነደፋቸውን አሳወቁ፡፡ ነቢዩﷺ በቱፍታ አዳኗቸው፡፡ ደግሞ ልብሳቸው ከላያቸው ላይ የለም፡፡ ‹‹አቡበክር ሆይ፣ ልብስህን የት ጣልከው?›› ሲሉ ጠየቋቸው፡፡ አቡበክር ያደረጉትን ነገሯቸው፡፡ ነቢዩﷺ እጃቸውን ወደሰማይ አነሱና ዱዓ አደረጉላቸው፡፡[1]

የሱመይራ ቢንት ቀይስ ፍቅር ደግሞ ይበልጥ ይገርማል፡፡ በኡሁድ ዘመቻ አምስት የቤተሰቧን አባላት አጥታለች፡፡ ሁለት ልጆቿን፣ አባቷን፣ ባሏንና ወንድሟን›› ነቢዩﷺ ተገድለዋል የሚል ወሬ በመሰማቱ መዲና በድንጋጤ ተውጣለች፡፡ በሐዘን እና በጩኸት ተንጣለች፡፡ ሰዎች እርግጡን ወሬ ለማግኘት ቤቶቻቸውን ጥለው ወደ ጎዳና ወጥተዋል፡፡ አደባባይ ተሰጥተዋል፡፡ ይህች እንስት ከነርሱ መሐል አንዷ ናት፡፡ ቤተሰቦቿ በጦርነቱ ማለቃቸውን ብትሰማም ምንም መስሎ አልታያትም፡፡ የነቢዩንﷺ ደህንነት መጠየቋን ቀጠለች፡፡ ከዘመቻ ተመላሾችን፡- ‹‹የአላህ መልእክተኛስ እንዴት ናቸው?›› እያለች በሐዘን ተውጣ ጠየቀች፡፡ በሕይወት እንዳሉና ደህንነታቸው ሲነገራት፡- ‹‹አሳዩኝ›› ስትል ተማጸነች፡፡ ወደርሳቸው አመላከቷት፡፡ ስታያቸው እንዲህ አለች፡-

‹‹የአላህ መልእክተኛ ሆይ፣ ከርስዎ ባሻገር ያሉ መከራዎች ሁሉ ቀላል ናቸው፡፡››[2]

---

[1] አቡ ኑዓይም፣ አልሁልየህ ቅ 1 ገጽ 37፣ ኢብን ከሲር አልቢዳየቱ ወኒሐያ ቅ 3 ገጽ 222-223

[2] ቢን ሂሻም፣ አልዋቂዲና ሐይሰሚ

አነስ እንዲህ ሲሉ አውግተዋል፡-

አንድ ሰው ከአላህ መልእክተኛﷺ ዘንድ መጣና፡- ‹‹ቂያማ መቼ ነው? ›› አላቸው፡፡ ‹ለቂያማ ምን አዘጋጀህ?›› አሉት፡፡ ‹የአላህንና የመልእክተኛውን ፍቅር›› አላቸው፡፡ ‹‹አንተ ከወደድከው ጋር ትሆናለህ፡፡›› አሉት፡፡

ከእስልምና በኋላ እንደዚህ የነቢዩﷺ ቃል ያስደስተን ሌላ ነገር የለም፡፡ እኔ አላህን፣ መልእክተኛውን፣ አቡበክርንና ዑመርን እወዳለሁ፡፡ የነርሱን ስራ ባልሰራም እንኳ በውዴታዬ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ (ሙስሊም)

እያንዳንዱ ሙስሊም የዚህ ነብያዊ ብስራት ተቋዳሽ ይሆን ዘንድ ቀልቡን በነቢዩﷺ ፍቅር ማስዋብ አለበት፡፡ ነቢዩﷺ በሞቱ ጊዜ ሶሐቦች በደረሰባቸው ብርቱ ሐዘን ምክንያት በእሳት እንደሚቃጠል ሻማ አይነት ሆነው ነበር፡፡ ቀልቦቻቸው በሐዘን ተሰበሩ፡፡፡ በቁጭት እንደጧፍ ቀለጡ፡፡ ራሳቸውን እስከመሳትም ደረሱ፡፡ ዑመር ራሳቸውን ሳቱ፡፡ አቡበክር ሁኔታውን ለማረጋጋት ማሰኑ፡፡ አፍቃሪ ልባቸው ነቢዩንﷺ ሳያዩ አንድ ቀን እንኳ ማሳለፍ የሚችል አልነበረም፡፡ በዱንያ ውስጥ እንደማያዩአቸው ሲያውቁ ራሳቸውን መቆጣጠር፣ ሰቀቀኑን መሸከም አልሆነላቸውም፡፡

አብደላህ ቢን ዘይድ እንዲህ ሲል ዱዓ አደረገ፡-

‹‹አላህ ሆይ፣ ከነቢዩ በኋላ ሌላ ነገር ማየት አልፍልግምና እርሳቸውን እስከማገኝ ድረስ ዓይነ ስውር አድርገኝ፡፡››

እንባ እያዘነበ ይህን ዱዓ ከልቡ አደረገ፡፡ ወዲያውኑ ዓይኖቹ ታወሩ፡፡[1]

ነቢዩ ከሞቱ በኋላ አቡበክር ባወሷቸው ቁጥር በእንባ ይታጠባሉ፡፡ ሐዲሳቸውን መናገር ሲፈልጉ ሳግ ይተናነቃቸውና ያቋርጡታል፡፡ አቡ ሁረይራ ተከታዩን አውግተውናል፡-

[1] ቁርጡቢ፣ አልጃሚዕ፣ በይሩት 1985፣ ቅጽ 5 ገጽ 271

አንድ ቀን አቡበክር ሚንበር ላይ ወጡ፡፡ ‹‹የአላህ መልእክተኛ በመጀመሪያው ዓመት ሚንበር ላይ ሲወጡ›› በማለት መናገር ጀመሩና አቋርጠው አለቀሱ፡፡ እንደምንም ራሳቸውን ተቆጣጥረው፣ መናገር ጀመሩ፡፡ ይህንኑ ቃል ደግመው አሉት፡፡ መቀጠል ግን አልቻሉም፡፡ ለቅሶ አሸነፋቸው፡፡ ለሦስተኛ ጊዜ ሞከሩ፡፡ አሁንም አልቻሉም፡፡ ተንሰቀሰቁ፡፡ (ቲርሚዚና አህመድ)

አቡበክር ከመልእክተኛው ﷺ ተነጥለው አያውቁም፡፡ ይህም ሆኖ ግን ሁሌም ይናፍቋቸው ነበር፡፡ ነቢዩ ﷺ ሲሞቱ ናፍቆታቸው በረታ፡፡ አባቷ ከነቢዩ ጋር የነበራቸውን የጠበቀ ግንኙነት አኢሻ እንዲህ አውግታለች፡-

‹‹አቡበክር ሊሞቱ በተቃረቡ ጊዜ፡- ‹‹ዛሬ ቀኑ ማን ነው?›› አሉ፡፡ ‹‹ሰኞ››ነው ተባሉ፡፡ እንዲህ ሲሉ ተናዘዙ፡- ‹‹ዛሬ ሌሊት ከሞትኩ ጀናዛየን ሳታቆዩ ቅበሩኝ፡፡ ከኔ ዘንደ ይበልጥ ተወዳጅ ቀናቶችና ሌሊቶች ወደ አላህ መልእክተኛ ቀረብ የሚሉት ናቸው፡፡›› (አህመድ)

‹‹ማክሰኞ ማታ ሞቱ፡፡ ከመንጋቱ በፊትም ተቀበሩ፡፡›› (ቡኻሪ)

አንዳንድ ሶሐቦች ነቢዩን ﷺ እጅግ ከመውደዳቸው የተነሳ ሊሞቱ በደከሙ ጊዜ ወንድሞቻቸው በጣም ይቀኑባቸው ነበር፡፡ ምክንያቱም ቀድመው በመሞት መልእክተኛውን ቀድመው ሊያገኟቸው ስለሆነ፡፡ ለነቢዩ ﷺ ሰላምታ ያደርሱላቸው ዘንድም አደራ ይሏቸዋል፡፡ ጃቢር ለሞት ያበቃቸውን በሽታ በታመሙ ጊዜ ሙሐመድ ቢን ሙንከዲር ሊጠይቃቸው መጣ፡፡ እንዲህ ሲልም የከበደ አደራ አሸከማቸው፡- ‹‹ጃቢር ሆይ፣ ለአላህ መልእክተኛ ሰላምታ አቅርብልኝ፡፡›› (ቢን ማጃህ)

ነቢዩን ﷺ ከመጠን በላይ የሚያፈቅሩት ሶሐቦች ስለርሳቸው ሲነገር በደስታ ይዋጣሉ፡፡ በሐሴት ይፈካሉ፡፡ በራእ ቢን አዚብ እነሆ አባቱ ነቢዩን ﷺ ይዘክሩላቸው ዘንድ እያንዳንዱን አጋጣሚ ምን ያህል ይጠቀሙ እንደነበር ያወጋናል፡፡

አቡበክር ከአባቴ በ13 ዲርሃም መጓጓዣ ገዙ፡፡ ‹‹በራእን እዘዘውና ያምጣል,ኝ›› ሲሉም ነገሩት፡፡ አባቴም፡-‹‹አንተና የአላህ መልክተኛ ከመካ ስትወጡ ጣኦታውያን ባሳደዷችሁ ጊዜ ያጋጠማችሁን ሁኔታ ሳታወጋኝ በፊት አልሄድም›› አላቸው፡፡ እንዲህ ሲሉ በከፊል ተረኩ፡-

ከመካ ወጣን፡፡ ሙሉ ሌሊትና ቀን ስንጓዝ ቆየን፡፡ እኩለ ቀን ላይ ረፍት ማድረግ ፈለግን፡፡  ማረፊያ ጥላ በዓይኔ አማተርኩ፡፡ አንድ ቋጥኝ አገኘሁ፡፡ ከርሷ ስር ጥላ ነበር፡፡ ቦታውን አስተካከለኩት፡፡ ፈረሽኩላቸው፡፡ እንዲተኙም ጋበዝኳቸው፡፡ ጋደም አሉ፡፡ የሚያሳድደን ሰው ይኖር እንደሁ ለማረጋገጥ ዙሪያውን ቃኘሁ፡፡ አንድ ፍየል ጠባቂ ፍየሎች እየነዳ ወደ ቋጥኙ ሲመጣ ተመለከትኩ፡፡ ‹‹የማን አገልጋይ ነህ?›› ስለው የአንድ ቁረይሽ ስም ጠራልኝ፡፡ ‹‹ፍየሎችህ ወተት አላቸውን?›› አልኩት፡፡ ‹‹አዎ›› አለኝ፡፡ ‹‹አልበህ ታመጣልናለህን?›› አልኩት፡፡ ‹‹አዎ›› አለ፡፡ አለበልን፡፡ ወደ መልእክተኛው ይዥላቸው ስሄድ ነቅተው አገኘኋቸው፡፡ ‹‹ይጠጡ›› አልኳቸው፡፡ ጠጡ፡፡ ‹‹አሁን ጉዟችንን መቀጠል እንችላለን፡፡›› አልኳቸው፡፡ ‹‹ይሁን›› አሉ፡፡ ተጓዝን፡፡ ፈላጊዎቻችን አላገኙንም፡፡ ሱራቃ ግን በፈረስ ደረሰብን፡፡ እየተከታተለን መሆኑን ስነግራቸው፡- ‹‹አታስብ፡፡ አላህ ከኛ ጋር ነው፡፡›› አሉኝ፡፡ (ቡኻሪና አህመድ)

ሶሐቦች ነቢዩን ﷺ በጣም ይወዷቸዋል፡፡ ያልቋቸዋል፡፡ ከዚህም የተነሳ ነቢዩ ﷺ የዳበሱትን የራሱን ጸጉር ለመላጨት ወይም ለመጣል ፈቃደኛ የማይሆን ሶሐባ እናገኛለን፡፡ (አቡ ዳውድ)

የሶሐቦች ሚስቶች የአላህን መልእክተኛ በጣም ይወዷቸው እንደነበር የሚያመለክቱ በርካታ አጋጣሚዎች ተስተውለዋል፡፡ ልጆቻቸው መልእክተኛውን ሳያገኙ ለረዥም ጊዜ እንዲቆዩ አይፈቅዱላቸውም ነበር፡፡ ሁዘይፈት ቢን አልየማን እንዲህ ሲሉ አስተላልፈዋል፡-

እናቴ፡- ‹‹ነቢዩን ያገኘሀቸው መቼ ነው?” በማለት ጠየቀችኝ፡፡ ‹‹ከዚህ ጊዜ ወዲህ አላገኘኋቸውም›› አልኳት፡፡ በጣም ተቆጣችኝ፡፡ ቆነጠጠችኝ፡፡ ‹‹ተይኝ የመግሪብን ሶላት አብሪያቸው እሰግዳለሁ፡፡ ለኔም ላንችም

ምህረት ይለምኑልን ዘንድም እጠይቃቸዋለሁ›› አልኳት፡፡ መግሪብ ላይ ወደ መስጊዳቸው መጣሁ፡፡ አብሪያቸውም ሰገድኩ፡፡ እስከ ኢሻም ቆየን፡፡ ሰግደው ወደ ቤት ሲመለሱ ተከተልኳቸው፡፡ ድምጼን ሲሰሙ፡- ‹‹አንተ ማን ነህ? ሁዘይፋ ነህን?›› አሉኝ፡፡ ‹‹አዎ›› አልኳቸው፡፡ ‹‹ጉዳይህ ምንድን ነው? አላህ አንተንም እናትህንም ይማራችሁ›› አሉኝ፡፡ (ቲርሚዚና አህመድ)

የነቢዩ አዛን አድራጊ የቢላል ፍቅር ደግሞ ለየት ይላል፡ ነቢዩ ካለፉ በኋላ አዛን ማድረግ አልቻለም፡፡ ምላሱ ተሳሰረ፡፡ መዲናንም ጠላት፡፡

አቡበክር በኸሊፋነት ዘመናቸው የዚያን ወርቃማ ዘመን ትዝታ በቢላል አዛን መመለስ ፈለጉ፡፡ አዛን ያደርግ ዘንድ ቢላልን ደጋግመው ለመኑት፡፡ በመልእክተኛው ፍቅር ልቡ የቀለጠው ቢላል ግን እንዲህ በማለት አዛን ማድረግ እንደማይችል ገለጸ፡-

‹‹አቡበክር ሆይ፣ ከአላህ መልእክተኛ ሕልፈት በኋላ አዛን የማድረግ ፍላጎት የለኝምና ተወኝ፣ አታስገድደኝ፡፡›.

አቡበክር ግን ሕዝባቸው የወርቃማውን ዘመን ትዝታ እንዲያስታውስ ፈልገዋል፡፡ አጥብቀው ጠየቁት፡፡ እንዲህ ሲሉ ተመጸኑት፡-

‹‹ሕዝበ ሙስሊሙ የአላህን መልእክተኛﷺ እንደተነፈገው ሁሉ አዛን አድራጊያቸውንም እንዲነፈግ ትሻለህን?››

ቢላል የአቡበክርን ልመና መቋቋም አልቻለም፡፡ አዛን ለማድረግ ተስማማ፡፡ አይኖቹ እንባ እያዘነቡ፣ አንገቱን ደፍቶ ወደ አዛን ማድረጊያው አመራ፡፡ የፈጅር አዛን ለማድረግ ከቦታው ላይ ቆመ፡፡ ከአላህ መልእክተኛﷺ ጋር ያሳለፋቸው የደስታ ጊዜያት በዓይነ ሕሊናው መጡበት፡፡ ከውስጥ ፈንቅሎ ሊወጣ የሚታገለውን ለቅሶውን አፍኖ አዛን ጀመረ፡፡ መቀጠል ግን አልሆነለትም፡፡ ሳግ ተናነቀው፡፡ እዚያው በቆመበት ተንሰቀሰቀ፡፡ አዛኑን መቀጠል አልሆነለትም፡፡ ወደ ኋላ ተመለሰ፡፡ አቡበክር ድጋሚ ሊያስቸግሩት አልፈለጉም፡፡

ቢላል መዲና ውስጥ ከዚህ በላይ መቆየት አልቻለም። ምክንያቱም በመልእክተኛው ﷺ ትዝታዎች የተሞላች ከተማ ናትና። በመሆኑም ከሱብሂ ሶላት በኋላ ከተማዋን ለቆ ወደ ደማስቆ አቀና።

ቢላል ሸሂድ መሆንን በመሻት በበርካታ ጦርነቶች ላይ ተሳተፈ። ከረሱሉ ﷺ ተለይቶ መኖር አልሆነለትም። ከርሳቸው ጋር ቶሎ መገናኘት ፈልጓል። ግና የአላህ ውሳኔ ሆነና በእያንዳንዱ ዘመቻ ምንም ሳይሆን ከውጊያ ይመለሳል። በዚህ ሁኔታ ዓመታትን አሳለፈ። ደማስቆ 25ሺህ ልጆቿን ባጣችባት ወባ ስትጠቃም ቢላል ከሞት ተረፈ። እርሱ ግን ከወዳጁ ጋር ፈጥኖ ለመገናኘት ሞትን አጥብቆ ይፈልጋል።

አንድ ቀን በሕልሙ የአላህ መልእክተኛ ﷺ እንዲህ ሲሉት ያያል፡-

‹‹ቢላል ሆይ፣ ለምን ራቅከኝ፣ ልትዘይረኝ አይገባምን?››

ቢላል ልቡ በሐዘን ተሞልቶ ከእንቅልፉ ተነሳ። ግመሉን ጋለበና ወደ መዲና አመራ። መዲና ሲደርስ የመልእክተኛውን ﷺ ቀብር ጎበኘ። ፊቱን ከቀብራቸው ላይ ደፍቶም ለረዥም ጊዜ አለቀሰ። የነቢዩ የልጅ ልጆች እና የጀነት አራቲዎች የሆኑት ሐሰንና ሁሴን መጡና አቀፉት። ‹‹ቢላል ሆይ፣ አዛንህን መስማት እንፈልጋለን፡›› ሲሉም ተማጸኑት። እምቢ ሊላቸው አልፈለገም። ወደ አዛን ማድረጊያው ስፍራ ወጣ። ***‹‹አላሁ አክበር፣ አላሁ አክበር››*** ማለት ሲጀምር መዲና ተናጠች።***‹‹አሽሐዱ አንላኢላሐ ኢለላሁ››*** ሲል ይበልጥ ተናጠች። በነዋሪዎቿ አእምሮ ውስጥ ነቢዩ ﷺ የነበሩበት ወርቃማ ዘመን ትዝታ በረድፍ መጣ። ሕዝቡ ከየጎጆው በመውጣት ወደ ነቢዩ ﷺ መስጊድ እያለቀሰ አመራ። ከተማዋ በናፍቆት ዋይታ ተሞላች። ከነቢዩ ﷺ ሞት በኋላ መዲና ውስጥ እንደዚያን ቀን ለቀሶ አያውቅም።›› [1]

ይህ አፍቃሪ ሶሐባ ስልሳ አመትን የዘለለ እድሜ ከቆየ በኋላ ሊሞት ሲል መንፈሱ በደስታ ተሞልቶ እንዲህ አለ፡-

---

[1] ኢብን ከሲር፣ አሰዱልጋባህ ቅ 1 ገጽ 244-245

‹‹ነገ ወዳጆቻችን የሆኑትን ነቢዩ ሙሐመድንና ባልንጀሮቻቸውን እናገኛለን፡፡››

ባለቤቱ ‹‹ወይ መከራዮ›› እያለች ስታለቅስ እርሱሰ ግን ደስታ ውስጡን አድምቆት ‹‹ወይ መታደሌ› ይል ነበር፡፡[1]

ሶሐቦች ለነቢዩﷺ የነበራቸውን ፍቅር ሐዲስ በሚያወሩ ጊዜ በጉልህ እንመለከታን፡፡ ሐዲስ ሲያስተላልፉ ግድፈት እንዳይፈጽሙ በመስጋት ፊታቸው ይገረጣ፣ ልቦናቸው በፍርሃት ይናጥ ነበር፡፡ ለምሳሌ አብደላህ ቢን ሙሐመድ፡- ‹‹ቃለረሱሉላህ›› ሲሉ በፍርሃት ይንቀጠቀጡ ነበር፡፡ ከዚህ የተነሳ ብዙ ሶሐቦች አንድ ሐዲስ ከተናገሩ በኋላ፡-‹‹አው ከማቃለ ረሱሉላህ›› ይሉ ነበር፡፡ ይህን የሚሉት ሰው እንደመሆናቸው አንዳች ግድፈት ፈጽመው እንዳይሆን በመስጋት ነው፡፡ (ቢን ማጃህ)

የአላህ መልእክተኛﷺ ታላቅ ስብእና ናቸው፡፡ ቆመው ኹጥባ ያደርጉበት የነበረው የዘምባባ ግንድ እንኳ ከርሳቸው በመነጠሉ አልቅሷል፡፡ ከጣቶቻቸው መሐከል ውሃ ፈልቆ ሕዝባቸውን አጠጥቷል፡፡ በቀሪው ውሃ በሽተኞች ተፈውሰዋል፡፡ ከእጃቸው ላይ ያለች ጉራሽ ‹ተስቢህ› ስታደርግ አብረዋቸው ለምግብ የታደሙ ሁሉ ሰምተዋታል፡፡[2]

በእለተ ቂያማ የሰዎች መሪ ናቸው፡፡ የሐጢአተኞች አማላጅ ናቸው፡፡ ‹‹ኡመቴ ኡመቴ›› በማለት የሕዝባቸውን ስቃይ ይጋራሉ፡፡ የምስጋና አርማ በእርሳቸው እጅ ይሆናል፡፡ ሁሉም ነብያት በርሳቸው ስር ይሰለፋሉ፡፡ የጀነትን በሮች ቀድመው የሚከፍቱት እርሳቸው ናቸው፡፡

## ከሶሐቦች በኋላ

የነቢዩﷺ አፍቃሪዎች እርከን ከሶሐቦች በኋላም ቀጥሏል፡፡ የዚህችም ሆነ የመጭው ዓለም ደስታ እርሳቸውን በመውደድ ብቻ እንደሚገኝ የተገነዘቡ አፍቃሪዎች የዚያን ትውልድ የፍቅር ፈለግ ተከትለዋል፡፡

---

[1] ዘሐቢ፣ ሲየር አዕላሙኑበላእ ቅ 1 ገጽ 359

[2] እነዚህ እና ሌሎችም ተአምራት በቡኻሪ ውስጥ ሰፍረዋል፡፡

የአላህ መልእክተኛﷺ በአንድ ሐዲሳቸው የእርሳቸው አፍቃሪዎች እስከ እለተ ቂያማ ድረስ እንደሚኖሩ እንዲህ ሲሉ ተናግረዋል፡-

‹‹እኔን በጣም የሚወዱኝ ሰዎች ከኔ በኋላ ይመጣሉ፡፡ ከነርሱ አንዳቸው ቤተሰቡንና ገንዘቡን ሁሉ ሰውቶ እኔን ቢያየኝ ይወዳል፡፡›› (ሙስሊም)

አምላኬ ሆይ፣ እኛን ደካሞችን በዚህ ሐዲስ ውስጥ ከተካተቱት እድሎች መሐል አድርገን፡፡ አሚን!

የነቢዩﷺ ፍቅር ሕመምን፣ ስቃይን ሁሉ ይቋቋማል፡፡ መከራን ያቃልላል፡፡ አብደላህ ቢን ሙባረክ እንዲህ ሲሉ አውግተዋል፡-

ከኢማሙ ማሊክ ጋር ነበርኩ፡፡ በትምህርታቸው መሐል አንድ የነቢዩን ሐዲስ ሲያወሱ ከፊታቸው ላይ የመረበሽ ስሜት ተስተዋለ፡፡ ገጽታቸው ገረጣ፡፡ ግና ሐዲሱን ሳያቋርጡ ቀጠሉ፡፡ ትምህርቱንም አጠናቀቁ፡፡ ‹‹የአብደላህ አባት ሆይ፣ ዛሬ አስገራሚ ነገር ከርስዎ ላይ አየሁ፡፡››አልኳቸው፡፡ እንዲህ አሉኝ፡-

‹‹አዎ፣ ልክ ነህ፡፡ በማስተማር ላይ እያለሁ ጊንጥ ነደፈኝ፡፡ ለነቢዩ ሐዲስ ልቅና ስል ሕመሙን ታገስኩት፡፡››[1]

ኢማሙ ማሊክ መዲና ውስጥ መጓጓዣቸውን አይጋልቡም ነበር፡፡ የአላህ መልእክተኛﷺ የረገጡትን አፈር በማላቅ፡፡ አንድ ሰው ስለ ነቢዩﷺ ሐዲስ ከጠየቃቸው በመጀመሪያ ውዱእ ያደርጋሉ፡፡ ጥምጣም ይጠመጥማሉ፡፡ ሽቶ ያርከፈክፋሉ፡፡ ከፍ ካለ ቦታ ላይም ይቀመጣሉ፡፡ ከዚያ በኋላ ጥያቄውን ይመልሱለታል፡፡ ራሳቸውን በዚህ መንገድ ሳያዘጋጁ እና መንፈሳዊ መሰናዶ ሳያደርጉ ስለነቢዩ ሐዲስ አንዲት ቃል አይናገሩም፡፡ የአላህን መልእክተኛﷺ የተባረከ ንግግር በሚያስተላልፉ ጊዜ ከፍተኛ ጥንቃቄ ያደርጉ ነበር፡፡ ከተከበረው የነቢዩ መስጊድ ውስጥ በሚሆኑ ጊዜ ድምጻቸውን ዝቅ አድርገው እንጅ አይናገሩም፡፡ ኸሊፋው

---

[1] አልመናዊ፣ ፈይዱል ቀዲር፣ ቅ 3 ገጽ 333 እና ሱዩጢ፣ ሚፍታሁል ጃነህ ገጽ 52

አቡ ጀእፊረል መንሱር በከፍተኛ ድምጽ በሚናገር ጊዜ እንዲህ ሲሉ ገስጸውታል፡-

‹‹ከዚህ ቦታ ላይ ድምጽህን ዝቅ አድርግ፡፡ ከነቢዩﷺ ዘንድ በከፍተኛ ድምጽ መናገርን አላህ ከልክሏል፡፡ ይህ እቀባና ማስጠንቀቂያ የተሰጣቸው በልቅና ለሚበልጡህ ሶሐቦች ነው፡፡››

አንድ ቀን ኢማሙ ማሊክ የበደላቸውን የመዲና ሹም እንዲህ ሲሉ ይቅር አሉት፡-

‹‹ከአላህ መልእክተኛﷺ የልጅ ልጆች መካከል አንዱን ከአላህ ፊት መሟገት እፈራለሁ፡፡››

ለአላህ መልእክተኛﷺ የበረታ ፍቅር የነበራቸው ታላቁ ዓሊም ሰይድ አህመድ የሰዊ እድሜያቸው 63 ዓመት ከሞላ በኋላ ነቢዩ የሞቱት በዚህ እድሜ በመሆኑ ራሳቸውን እንደ ሟች በመቁጠር በምድር ላይ መዘዋወርን በማቆምና ቀብር ሊባል በሚችል ቦታ ውስጥ በመወሰን በማስተማር ስራ ላይ ብቻ አተኮሩ፡፡

ኢማም አልነወዊ ለነቢዩ ሙሐመድﷺ ከፍተኛ ፍቅር ስለነበራቸው በእያንዳንዱ ድረጊታቸው የነቢዩንﷺ አርአያነት ይከተላሉ፡፡ እርሳቸው ያልሰሩትን ስራ ላለመስራት ይጠነቀቃሉ፡፡ ከዚህ የተነሳ ነቢዩ ሐብሐብ በምን አይነት ሁኔታ ይመገቡ እንደነበር መረጃ ስላልነበራቸው እድሜ ልካቸውን ሐብሐብ ተመግበው አያውቁም፡፡

ሱልጧን ሰሊመል አህል በበኩሉ በወቅቱ የዓለም ገዥ የነበረ ቢሆንም ለነቢዩﷺ ከፍተኛ ውዴታ ስለነበረው እርሳቸውን መውደድ የሚያስገኘውን ልቅና እንዲህ ገልጾታል፡-

‹‹ዓለምን መግዛት ዘወትር በትግልና በፍልሚያ ውስጥ መሆን ሲሆን፣ የነቢዩﷺ እውነተኛ አፍቃሪና ተከታይ መሆን ግን ከየትኛውም ነገር የበለጠ ውድ ነው፡፡››

ይህ አባባሉ ወደ አላህ ለመቅረብ የነበረውን ጉጉት ያመለክታል፡፡

በቀድሞ ዘመን ከቀለበት ላይ አንዳች ጥበብ መጻፍ የተለመደ ነገር ነበር፡፡ ‹‹በዝምዓለም›› የተባለች የኡስማናዊው ኸሊፋ አንድ ባለስልጣን እናት እንዲህ የሚል ነገር ከቀለበቱ ላይ በማስፈር ለነቢዩﷺ የነበራትን ፍቅር ገልጻለች፡-

‹‹አላህ ይህን ዓለም ስለሚወደው ነቢዩ ሙሐመድንﷺ ገለጸለት፡፡ ሙሐመድ የሌለበት ፍቅር ከንቱ ነው፡፡ አላህ እርሳቸውን በማስነሳት ይህን ዓለም በመውደዱ ሰበብ እኔም ከአምላኬ ጋር ተገናኘሁ፡፡››

አንድ ገጣሚ ወደ መዲና በሚቀርብ ጊዜ የሚከተለውን መልእክት ያዘለ ግጥም ያነበንብ ነበር፡፡

‹‹ይህ ቦታ የአላህ ወዳጅ ማረፊያ ነውና አደብ እንዳትጥስ ተጠንቀቅ፡፡ አላህ በክብር የሚያየው የተመራጩ ነብይ ዙፋን ነው፡፡ ስለዚህም አደብ ሳትጥስ ቃል ገብተህ ወደ ውስጡ ዝለቅ፡፡ የተቀደሱ ሰዎች የሚገኙበት፣ ነብያት የሚያልቁት ቦታ ነውና፡፡››

ሰይድ ሙሐመድ አስዓድ የተባሉ ታላቅ ሸህ የአላህን መልእክተኛﷺ በብርቱው መናፈቃቸውን በመግለጽ ስንኞች ጽፈዋል፡-

ሌሎች ጸሐፊዎችና ገጣሚዎችም እንደዚሁ ፍቅራቸውን ጥፈዋል፡፡ ናፍቆታቸውን ከትበዋል፡፡

የሶሐቦች ስብእና እጅግ አንጸባራቂ ሆኗል፡፡ በዓለም በጉልህ የሚታዩ ከዋክብት፣ የሰው ልጆች ሁሉ ፈርጦች፡፡ ይህ የሆነው የአላህን መልእክተኛﷺ አርአያ አድርገው በመያዛቸው ነው፡፡ በሁሉም ነገር እርሳቸውን ተከተሉ፡፡ ዘልዓለማዊ ደስታም አገኙ፡፡ ከነርሱ በኋላ የመጡ ታላላቅ ሰዎችም ለነቢዩ ሙሐመድﷺ ባላቸው ፍቅር እና ቅርበት መጠን ልቅናን አግኝተዋል፡፡

አብደላህ ቢን ዘይድ፣ ቢላል፣ ኢማም ነወዊ እና ሌሎችም ታላላቆች ለነቢዩﷺ የነበራቸውን ፍቅር ክፋይ ከኛ ዘንድ ይገኛልን? በዚህ ረገድ ያለኝን ደረጃ ልንመዝን ይገባናል፡፡ የነቢዩ ሙሐመድﷺ ኡመት ለመሆን

ተገቢዎች ነን? ቀልባችን የረሱልን ሙሐባ በማግኘት ሊደምቅ፣ ሕሊናችን በዚህ ፍቅር ሊነቃ ይገባል።

የእስላም ትልልቅ ስብእናዎች ከነርሱ በኋላ በመጡ ትውልዶች ሁሉ እንዲደነቁ ያደረጋቸው፣ ታላቅነትን ያጎናጸፋቸው ከአላህ መልእክተኛﷺ ጋር ያላቸው የፍቅር ግንኙነት ነው። እርሳቸውን በጣም ይወዳሉ። በጣም ይናፍቃሉ። በጣም ይከተላሉ። ስለዚህም ታላቅ ሆኑ። ኮከብ ሆኑ።

ፍቅር ቀልብን በሚያገናኝ ገመድ እንደሆነ እናውቃለን። ጥሩ ሙእሚን እንሆን ዘንድ ዋነኛው መስፈርት ቀልባችንን በዚህ መልኩ ማዘጋጀት ነው። በአሁኑ ሰአት የሰው ልጅ ትልቁ ኪሣራ ይህን ዝግጁነት ማጣቱ ነው። ይህም በመሆኑ በርካታ እሴቶች እርቃናቸውን ቀሩ። በሸህዋ ስለት ተበጣጠሱ።

አስተሳሰቦች በሙሉ ዱንያዊና እንስሳዊ ሲሆኑ ሰዎች ለመንፈሳዊ ምጥቀት መፈናፈኛ ያጣሉ። የሰው ልጅ ይህን ፍቅር ሊያገኝ የሚችለው ልቦናውን ዘወትር በማለማመድ ነው። ሰዎች በአሁኑ ሰአት ይህ ፍቅር በጣም ያስፈልጋቸዋል። እጅግ የሚዘገንኑ ወንጀሎች ሁሉ መንስኤ የዚህ ፍቅር እጦት ነው። ሰዎች ነቢዩ ሙሐመድንﷺ ሲወዱና ሲከተሉ መንፈሳቸው ይመጥቃል። ልባቸው በጥሩ ስሜት ይደምቃል። ከወንጀል ይርቃሉ። ክፋትን ይታቀባሉ።

የፍቅር መጠን የሚለካው ለፍቅረኛ በማከፈል የመስዋእትነት መጠን ነው። በጣም የወደደ ለፍቅረኛው የከበደ መስዋእትነት ይከፍላል። ነፍሱን ሳይቀር ሊሰዋ ይችላል። ይህን ሁሉ አድርጎም መስዋእትነት የከፈለ ሳይሆን ያለበትን እዳ የተወጣ ያህል ይሰማዋል።

ይህን እውነተኛ ፍቅር የማያውቁ፣ ወደምሉእነት ለመድረስ የሚፈለገውን ያህል አልተዘጋጁም። ቀልቦቻቸውም ሰክረዋል። በሸህዋ ማእበል እንዲዋጡና እንዲጠፉ አድርገዋል።

ጋራዎች እንኳ ሊሸከሙት ያልፈቀዱበትን አደራ መሸከም ለሰው ልጅ የተሰጠ ልዩ ባህሪ ነው፡፡ ይህ ስጦታ በሚፈለገው መልኩ ይረጋገጥ ዘንድ ደግሞ እውነተኛ የነቢዩﷺ ፍቅር ያስፈልጋል፡፡ በሰው ልጅ መንፈስ ውስጥ የሚስተዋለው ተቃርኖና ትግል ሊቀልጥ የሚችለው በዚህ ፍቅር ብቻ ነው፡፡

የሰው ልጅ መንፈሱን ከእንሰሳዊ ዝንባሌ ሊያጸዳ የሚችለው በአላህና በመልእክተኛውﷺ ፍቅር ነው፡ አላህ እንዲህ ሲል የሰውን ልጅ መንፈሳዊ ገጽታ ያስታውሳል፡፡

﴿ فَإِذَا سَوَّيْتُهُۥ وَنَفَخْتُ فِيهِ مِن رُّوحِى فَقَعُوا۟ لَهُۥ سَٰجِدِينَ ﴿٢٩﴾ ﴾ الحجر: ٢٩

*"(ውብ አድርጌ) በቀረጽኩትና ከመንፈሴም በነፋሁበት ጊዜ ለርሱ ስገዱ፡፡" (አል ሂጅር 29)*

የሰው ልጅ አስኳል ይህ ነው፡፡ ይህ አስኳሉ ነቢዩንﷺ በማፍቀር ወደ ምሉእነት ደረጃ ከደረሰ ቀልቡ በመለኮታዊው ጎዳና እጅግ ከፍተኛ አመርታ አሳይቷል፡፡ ሰውየውም የጽዱ ቀልብ ባለቤት ሆኗል፡፡

አንድ ሰው ወደዚህ ብስለትና ምሉእነት ሲደርስ በርሱና በአላህ መካከል ግርዶ ሊሆኑ የሚችሉ የዝንጋታ ጉድፎችን እየለቀመ የማጽዳት ክህሎቱ ይጎለብታል፡፡ የዚህች ጠፊ ዓለም ውበትና ፍቅር ከልቦናው ይወገዳል፡፡ ጠፊና ተወጋጅ ነገር ሁሉ ከቀልቡ ይነሳለታል፡፡ ይህ ሲሆን መንፈሱ በቃላት ሊገለጽ የማይችልን ወደ አላህ የመቃረብ ለዛ ታጣጥማለች፡፡

የእውነተኛው ፍቅር ጣእም ያልገባቸው ግን በሰው ልጅ ስሪት ውስጥ የሚገኘውን እንስሳዊ ዝንባሌ ወይም ከንቱ ስሜት በመስበር ወደ መላኢካነት አለም አንዲት እርምጃ እንኳ መራመድ አይችሉም፡፡ ይህን ፍቅር የተነፈገ ቀልብ እህል የማያበቅል መሬት ማለት ነው፡፡ አላህን በትክክል ማወቅ የሚመነጨው ከዚህ ፍቅር ነው፡፡ የዚህ ፍቅር መሠረትም እውቀት ነው፡፡ የሕልውና ሰበብ ይህ ፍቅር መሆኑን መረዳት ጠቃሚ ነው፡፡

የሰውን ልጅ ከመከራ እና ከውድቀት በመታደግ ወደ ሐሴት የሚያሸጋግረው የአላህ እዝነት ለሰው ልጆች መልካም አርአያ በሆኑት በነብዩ ሙሐመድﷺ ይገለጻል፡፡ እውነተኛ ደስታ የሚገኘው እርሳቸውን በማፍቀር፣ ፈለጋቸውን በመከተልና በተግዙበት የፍቅር ጎዳና በመጓዝ ነው፡፡

የአላህ መልእክተኛﷺ የፍጡራን ሁሉ ፈርጥ፣ የሰው ልጆች ዓይነታ፣ የሕልውናቸው አብይ ነገር ናቸው፡፡ ከአላህ የተለገሱን ትልቅ እዝነት፣ ትልቅ ገጸ በረከት ናቸው፡፡ የሰውን ልጅ ከአምላኩ ጋር ያስተዋወቁ ስብእና ናቸው፡፡ አላህን በፍጹም ፍቅርና መተናነስ በማምለክ ለሰው ልጅ የእውነተኛ አምልኮ ተምሳሌት ሆነዋል፡፡

ባጭሩ ነቢዩ ሙሐመድﷺ ዓለማትን ሁሉ ያቀፈ ፍቅርና እዝነት መገለጫ ናቸው፡፡ ሁለንተናውን ለርሳቸው ፍቅር የሰጠ ልቦና በዚህች ዓለም ውስጥ እስካለ ድረስ በፍቅራቸውና በናፍቆታቸው መቃጠሉ አይቀሬ ነው፡፡

ይህ ፍቅር ብዙ ታላላቅ ሰዎችን አንገብግቧል፡፡ በቃላት ሊገለጽ የማይችል ሐሴትም ለግሷቸዋል፡፡ እነዚህ ሰዎች ጠፊ ከሆነው አካል እስረኝነት ተላቀቁ፡፡ ወደ አላህ በሚያደርጉት ጉዞም ብዙ እርከኖችን አለፉ፡፡ አዎ፣ በእውን ሊፈቀር የሚገባውን አካል ስታፈቅር ሐሴት ሐብትህ ይሆናል፡፡ ጀላሉዲን ሩሚ የተባሉ ታላቅ ዓሊም የደስታ ምንጫቸውን እንዲህ ሲሉ ተናግረዋል፡-

በሕይወት እስካለሁ ድረስ የቁርአን ባሪያ፣ የነቢዩ ሙሐመድﷺ የእግራቸው አፈር ነኝ፡፡ አንድ ሰው ይህን ቃሌን ትቶ ሌሎች ንግግሮቼን ቢያወሳ እኔ ከርሱም ሆነ ከንግግሩ ጋር ግንኙነት የለኝም፡፡››

የአላህ መልእክተኛﷺ የእግራቸው አፈር የመሆን ትርጉሙ ሁሌም፣ በሁሉም ጉዳዮች የርሳቸውን ሱንና መከተል፣ ከፍቅራቸው ጋር ተሳስሮ መኖርና በርሳቸው መንገድ ጊዜን፣ ጉልበትን፣ ሕይወትን መሰዋት ነው፡፡

ከአላህ መልእክተኛﷺ ጋር ያለንን የፍቅር ግንኙነትና የቀልብ ትስስር ከሚያጠናክሩልን ነገሮች መካከል አንዱ በርሳቸው ላይ ሰለዋት ማውረድ ነው፡፡ በየቀኑ ለተወሰነ ጊዜ ሰለዋት ማውረድን በራስህ ላይ እንደ ግዴታ ልትይዝ ይገባሐል፡፡

ሶለዋት ከርሳቸው ጋር የሚኖረንን ቁርኝት የበለጠ ያጠነክረዋል፡፡ ልቦናችንን በፍቅራቸው ብርሃን ያደምቀዋል፡፡

## በነቢዩﷺ ላይ ሶለዋት ማውረድ

አላህ በቁርአን ውስጥ በነቢዩ ሙሐመድﷺ ሕይወት ምሏል፡፡ ስሙን ከስማቸው ጋር አቆራኝቶ አውስቶታል፡፡ አንድ ሰው አማኝ ይሆን ዘንድ በርሳቸው ማመንን ዋነኛ መስፈርት አድርጎታል፡፡ ከርሳቸው አጠገብ ድምጽን ከፍ አድርጎ መናገርን ከልክሏል፡፡ ማእረግ ሳያክል በስማቸው ብቻ አንድም ጊዜ አልጠራቸውም፡፡ ከዚህ ሁሉ በላይ እርሱና መላኢኮች በእርሳቸው ላይ ሶለዋት እንደሚያወርዱ ተናግሯል፡፡ አማኞችም ሶለዋት እንዲያወርዱ አዟል፡፡ በተላቀው መጽሐፉ ውስጥ እንዲህ ብሏል፡-

﴿ إِنَّ ٱللَّهَ وَمَلَٰٓئِكَتَهُۥ يُصَلُّونَ عَلَى ٱلنَّبِيِّۚ يَـٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ صَلُّواْ عَلَيْهِ وَسَلِّمُواْ تَسْلِيمًا ﴿٥٦﴾ ﴾ الأحزاب: ٥٦

‹‹አላህና መላእክቱ በነቢዩ ላይ “ሶለዋት” ያወርዳሉ፡፡ እናንተ ያመናችሁ ሆይ! በርሱ ላይ “ሶለዋት” አውርዱ፡፡ የክብር ሰላምታ አቅርቡለትም፡፡›› (አል አህዛብ 56)

ታላቁ ሶሐብይ ኡበይ ቢን ከእብ እንዲህ ብሏል፡-

የሌሊቱ ሁለት ሦስተኛ ሲገባደድ የአላህ መልእክተኛﷺ ይነሱና እንዲህ ይላሉ፡-

‹‹እናንተ ሰዎች ሆይ፣ አላህን አውሱ፡፡ ተርገፍጋፊይቱ መጣች፡፡ ለጣቂይቱም ትከተላታለች፡፡ ሞት የያዘውን ይዞ መጣ፡፡ ሞት የያዘውን ይዞ መጣ፡፡››

‹‹የአላህ መልእክተኛ ሆይ፣ በርስዎ ላይ ሶለዋት አብዝቼ አወርዳለሁ፡፡ ከማደርገው ዚክር ምን ያህሉን ለርስዎ ላውል?›› አልኳቸው፡፡ ‹‹የፈለግከውን ያህል›› አሉኝ፡፡ ‹‹ሩቡን ላውለውን?›› አልኳቸው፡፡ ‹‹እንደፈለግክ፡፡ ግና ብትጨምር ላንተ የተሻለ ነው፡፡›› አሉኝ፡፡ ‹‹ግማሹንስ?›› አልኳቸው፡፡ ‹እንደፈለግክ፡፡ ብትጨምርም የተሻለ ነው›› አሉኝ፡፡ ‹‹ሁለት ሦስተኛውንስ?›› አልኳቸው፡፡ ‹‹እንደፈለግክ፡፡ ብትጨምር ላንተ የተሻለ ነው›› አሉኝ፡፡ ‹‹ሁሉንም ዱዓዬን ለርስዎ አድርጊያለሁ›› አልኳቸው፡፡ ይህን ካደረግክማ ከሃሳብ ተገላገልክ፡፡ ለወንጀልህም ምህረት አገኘህ›› አሉኝ፡፡ (ቲርሚዚ)

የአላህ መልእክበኛﷺ አፍቃሪዎች በዚህ መልኩ ምላሳቸውን በነቢዩ ላይ ሶለዋት በማውረድ ገርተዋል፡፡ ሶለዋት ከአማኞች ልቦና ውስጥ የነቢዩን ፍቅር ለመጨመር ጥሩ መንገድ ነው፡፡ የአላህን መልእክተኛﷺ በትክክል የመከተል እና ከመልካም አርአያነታቸው ተጠቃሚ የመሆን እውነታ ያለ ጥርጥር የሚረጋገጠው ቁርአንና ሐዲስን በአግባቡ በመረዳት ነው፡፡ ይህ ይሆን ዘንድ ደግሞ የሰይዳችንን የነቢዩ ሙሐመድንﷺ ጥልቅ ልቦናና ተምሳሌታዊ ስነ ምግባር በቅርበት መረዳት ያሻል፡፡

የአላህን መልእክተኛﷺ ታላቅነት በተሟላ መልኩ መግለጽ፣ ልዕልናቸውን መረዳት ይከብዳል፡፡ ሊቃውንት ይህን አውቀዋል፡፡ ጥበበኞችና የቀልብ ዓሊሞች ይህን በሚገባ ተረድተዋል፡፡ ክብር የሚገኘው የእርሳቸውን ፈለግ በመከተል እንደሆነ ተገንዝበዋል፡፡

እስልምና ባስተማረን አደብ መሠረት ዱዓ የሚጀመረው እና የሚጠናቀቀው በነቢዩﷺ ላይ ሶለዋት በማውረድ ነው፡፡ ምክንያቱም ለዱዓ ተቀባይነት ወሳኝ መሆኑ ስለሚታመን፡፡ ዑመር ቢን አልኸጧብ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹ዱዓ በሰማይና በምድር መካከል ቆሞ ይቆያል፡፡ በነቢዩ ላይ ሶለዋት እስክታወርድ ድረስ ወደ ላይ አይወጣም፡፡›› (ቲርሚዚ)

አንድ ሰው ከሶላቱ ውስጥ ዱዓ ሲያደርግ መልእክተኛው ﷺ ሰሙት። በርሳቸው ላይ ሶለዋት ሳያወርድም ዱዓውን አጠናቀቀ። ነቢዩም:- ‹‹ይህ ሰው ቸኮለ፡›› አሉ። ጠሩትና እንዲህ አሉት:-

‹‹ከናንተ አንዳችሁ ዱዓ በሚያደርግ ጊዜ በመጀመሪያ አላህን ያመስግን፣ ያወድሰም። ከዚያም በነቢዩ ﷺ ላይ ሶለዋት ያውርድ። ከዛ በኋላ የሚፈልገውን ዱዓ ያድርግ።›› (ቲርሚዚ)

አላህ መልእክተኛውን ﷺ ሲያናግር እንዲህ ብሏል:-

﴿ وَمَا كَانَ ٱللَّهُ لِيُعَذِّبَهُمْ وَأَنتَ فِيهِمْ وَمَا كَانَ ٱللَّهُ مُعَذِّبَهُمْ وَهُمْ يَسْتَغْفِرُونَ ٣٣ ﴾ الأنفال: ٣٣

*‹‹አንተ ከውስጣቸው እያለህ አላህ ፈጽሞ አይቀጣቸውም። ምሕረትን እስከጠየቁ ድረስም አይቀጣቸውም።›› (አል አንፋል 33)*

አላህ በዚህ አንቀጽ የተመለከተው ጣኦታውያንን ነው። ‹‹አንተ ከነርሱ ጋር እስካለህ ድረስ ወይም ምህረት እስከለመኑ ድረስ አላህ አይቀጣቸውም።›› ይላል። በዚህ አንቀጽ መልእክት መሠረት ጣኦታውያን ከነቢዩ ﷺ ጋር በአካል በመሆናቸው ብቻ ተጠቃሚ ሆነዋል፣ ማለት ነው። ስለዚህም ነቢዩ ﷺ ከነርሱ መሐል እስካሉ ድረስ የአላህ ቅጣት በጣኦታውያን ላይ አይወርድም። እነርሱ ነቢዩን ﷺ በአካል በመጎራበታቸው ብቻ ይህን ክብር ካገኙ በርሳቸው ያመነና የተከተላቸው ሰው ሊያገኝ የሚችለው መለኮታዊ ጸጋ ሊገመት ከሚችለው በላይ ነው።

ሙእሚኖች የነቢዩን ﷺ ልቅና ማወቅ ብቻ ሳይሆን የእምነታቸው መሠረት የሆነው እርሳቸውን የማፍቀር ባህሪ ባለእድሎች ናቸው።

የሙእሚን ቀልብ የመጭው ዓለም ደረጃው እና በዚህች ዓለም የሚያገኘው ሐሴት ለነቢዩ ﷺ ባለው ፍቅር መጠን ይወሰናል።

ለዚህ ሁሉ ሲባል በአላህ መልእክተኛﷺ ላይ ሶለዋት ማውረድን መዘንጋት የለብህም፡፡ በመጭው ዓለም፣ በታላቁ ድንጋጤ ቀን የርሳቸው አማላጅነት የግድ ያስፈልግሐልና፡፡

# ክፍል አራት

- የተምሳሌታዊ ስብእና አስፈላጊነት
- የአላህን መልእክተኛ (ሰዐወ) ምን ያህል እንወዳለን?

## የተምሳሌታዊ ስብእና አስፈላጊነት

## መለኮታዊ ስልጠና

አላህ ሰማያትንና ምድርን የሰውን ልጅ ያገለግሉ ዘንድ ፈጠራቸው፡፡ የሰውን ልጅም ስለራሱና ስለነዚህ ነገሮች ከተጠያቂነት ነጻ አላደረገውም፡፡

ይህውም የሰው ልጅ እና ተፈጥሮ በመለኮታዊ ሕግ ስር እንዲኖሩ ወሰኑ፡፡ የሰው ልጅ በነጻነቱና በተጠያቂነቱ መሐል በሚዛናዊነት ይኖር ዘንድም ደነገገ፡፡ ተከታዩ የቁርአን አንቀጽ ይህን የሚዛናዊነት ጽንሰ ሐሳብ ያመለክታል፡-

﴿ وَٱلسَّمَآءَ رَفَعَهَا وَوَضَعَ ٱلْمِيزَانَ ۝٧ أَلَّا تَطْغَوْا۟ فِى ٱلْمِيزَانِ ۝٨ ﴾ الرحمن: ٧ - ٨

*‹‹ሰማይንም ከፍ አደረጋት፡፡ ሚዛኑንም አስቀመጠ፤ ሚዛን ላይ አትበድሉ፡፡›› (አል ረህማን 7-8)*

ይህ አንቀጽ የሚያስተምረን የሰው ልጅ፣ አላህ ለዩኒቨርሱ ካስቀመጠው ሚዛን ጋር በተጣጠመ አኳኋን ሕይወቱን የመምራት ግዴታ እንዳለበት ነው፡፡ የዩኒቨርሱ ሚዛን ቅንጣት ታክል ጉድለት የለበትም፡፡ ለሰው ልጅ ሕይወት መመሪያ ይሆን ዘንድ የተቀመጠው የሸሪዓ ሚዛንም እንደዚሁ፡፡ ስለሆነም የሰው ልጅ ከሐቅ ሳያፈነግጥ ወደ አላህ የሚያደርገውን ጉዞ መቀጠል ይኖርበታል፡፡

ደጋጎች ሕይወታቸውን በዚህ ሚዛን መሠረት በልክ ስለሚመሩ ከማንም በላይ ደስተኞች ናቸው፡፡ ያለዚህ ሚዛን የሚኖሩ ግን ቀልቦቻቸው ጠፊ በሆኑ ነገሮች ፍቅር የተሞሉ ሆነው ይታያሉ፡፡ ወደዚህ ዓለም የመምጣታቸውን እና የመሞታቸውን ሚስጥር አያውቁም፡፡ እነዚህ በእርግጥም ታላቁ ፈጣሪ ለዩኒቨርሱ ካስቀመጠው ሚዛንና ከዘረጋው ስርዓት ጋር ሕይወታቸውን አላጣጣሙም፡፡ ይህን የሚዛናዊነት ሚስጥርም አልተረዱም፡፡ እድሚያቸው በሚያሳዝን ሁኔታ በጥልቅ ዝንጉነት፣ በአታላይ አዙሪት ውስጥ ያልፋል፡፡ በመጭው ዓለምም አስከፊ ኪሣራ ይደርስባቸዋል፡፡

ይህ እውነታ በሰው ልጅ ስሪት ውስጥ በጉልህ ተቀምጧል፡፡ ይህውም የሰው ልጅ ወደዚህች ዓለም ሲላክ የበጎ እና የክፋት ዝንባሌዎች ከውስጡ ተቀምጠዋል፡፡ ጥሩ ወይም መጥፎ የመስራት አቅም ተሰጥቶታል፡፡ ሕይወቱም ይህን ዝንባሌውን ተጠቅሞ ከበጎና ከክፋት ያሻውን የሚመርጥበት የፈተና ማእከል ሆናለች፡፡

የሰው ልጅ እድሜ የሚያልፈው በውስጣዊ እሱነቱና በውጫዊ ሕይወቱ፣ በበጎና በክፋት መካከል በሚደረግ ትግል ነው፡፡ ሁለቱም የሰውን ልጅ መቆጣጠር ይፈልጋሉ፡፡ ከውስጣችን የበጎነትም የክፋትም ሐይሎች ይገኛሉ፡፡ ተገቢውን ስልጠና ያላገኘች ያልተገራችና በመጥፎ የምታዝ ነፍስ ከክፋት ጎን ተሰልፋ ትታገለናለች፡፡

በዚህ ግብግብ ውስጥ በጎነት ክፋትን እንዲያሸንፍ ለማስቻል የሰው ልጅ አእምሯዊ እና ሌሎች አቅሞች ብቻ በቂ አይደሉም፡፡ እንዲያ ቢሆን ኖሮ ነብያት እና ወህይ አስፈላጊ አይሆኑም ነበር፡፡ ስለዚህም መለኮታዊ እገዛ ያስፈልጋል፡፡ አላህ ለሰው ልጅ ነብያትን በመላክና መጽሐፍትን በማውረድ ይህን እገዛ ሲሰጠው ኖሯል፡፡

የሰው ልጅ አእምሮ መንታ ስለት ያለው መሣሪያ ነው፡፡ ለክፋትም ለበጎ ነገርም ሊውል ይችላል፡፡ የሰው ልጅ በአእምሮው አማካይነት ***ከጥሩ አቋም (አህሰኒ ተቅዊም)*** ላይ ሊደርስ ይችላል፡፡ በሌላ በኩል በዚህ አእምሮው አማካይነት‹ ***‹አስፈለ ሳፊሊን›› (አዘቅጥ)*** ሊወርድ፣ ልክ እንደ እንስሳ ወይም ከነርሱ የባሰ ሊሆን ይችላል፡፡

ስለዚህም አእምሮ ለበጎ ይውል ዘንድ በአንድ በተለየ ስርዓትና ቁጥጥር ስር መሆን አለበት፡፡ እርሱም መንፈሳዊ ስልጠናና የነብያት አመራር ነው፡፡ አእምሮ በወህይ እገዛና ቁጥጥር የሰውን ልጅ ወደ ሰላም መስክ ይወስደዋል፡፡ ይህን አመራር ከተነፈገ ግን ለክፉ ፍጻሜ መንስኤ ሊሆን ይችላል፡፡

ከመጨረሻው የብክለት ደረጃ የደረሱ በርካታ በዳዮች ለሕሊና የሚከብዱ እጅግ ዘግናኝ ወንጀሎችን ምንም መስሎ ሳይሰማቸው ሲፈጽሙ፣ በደሎቻቸውን እንደ ብስለት ዳርቻ ሲቆጥሩም ተስተውለዋል፡፡ ለምሳሌ

‹ሆላስ› የተባለ አረመኔ ባግዳድ በገባ ጊዜ ከደጀላህ ውሃ አጠገብ አራት መቶ ሺህ ንጹሐን ዜጎችን ምንም መስሎ ሳይታየው ጨፍጭፏል፡፡ አረቦቹ ከነቢዩ ሙሐመድﷺ መነሳት በፊት ሴት ልጆቻቸውን ከነሕይወታቸው ሲቀብሩ ምንም አይመስላቸው፡፡ የእናቶች አንጀት የሚበላ ተማጽኖ አይገባቸውም፡፡ ለነርሱ ባሪያን መግደል እና እንጨት መቁረጥ እኩል ነው፡፡ ይህን ወንጀል እንደ ሕጋዊ መብታቸው አድርገው ይቆጥሩታል፡፡

እነዚህ ወንጀለኞች ልክ እንደኛው አእምሮ እና የስሜት ሕዋሳት ነበሯቸው፡፡ ግና ወደተቃራኒ አቅጣጫ እንዲሰሩ ተደርገዋልና ውጤታቸውም እንደዚያው ሆነ፡፡

እነዚህ ምሳሌዎች የሚያሳዩት የሰው ልጅ አዎንታዊና አሉታዊ ዝንባሌዎችን የሚያስለጥንለት እና የሚገራለት፣ ወደ ቅን አቅጣጫም የሚመራለት አካል እንደሚፈልግ ነው፡፡ ይህ ሊሳካ የሚችለው ደግሞ በወህይ አመራርና በነብያት ትምህርት ብቻ ነው፡፡ በአንጻሩ የሰው ልጅ ከተፈጥሮው የማይጣጣም አመራር ሲሰጠው ጥፋትና ክፋት ይከሰታል፡፡

በሰው ልጅ ስሪት ውስጥ በጎነት እና ክፋት አንዱ ሌላውን ለማጥፋት ይታገላሉ፡፡ በጎነት ካሸነፈ የክፋትን አቅም ያመነምናል፡፡ ክፋት ካሸነፈም የበጎነትን አቅም ያኮሰምናል፡፡ ይህ ትግል የሰው ልጅ በሕይዎት እስካለ ድረስ ይቀጥላል፡፡

ለዚህም ሲባል አላህ ለሰው ልጅ ነብያትንና የነርሱ ወኪሎች የሆኑ ዓሊሞችን በማስነሳት አዘነለት፡፡ የሰው ልጅ በብቁ ባለሙያዎች መንፈሳዊ ስልጠና ሲያገኝ ከውስጡ ያለው ውበት በአላህ ችሮታ ይከሰትለታል፡፡

ልጆቻቸውን ከነ ሕይወታቸው የሚቀብሩና ልክ እንደ አውሬ ይኖሩ የነበሩ ወገኖች እጅግ የመጠቀ ስብእና ባለቤቶች ሆነው ከሰብአዊነት ጣሪያ የደረሱት በእንዲህ ዓይነቱ የነቢዩ ሙሐመድﷺ ስልጠናና አመራር ነበር፡፡

የሰው ልጆች የነብያትን አመራር ሲከተሉ፣ አላህን የሚያስደስቱና ለሞገስ የሚበቁ በጎዎች ይሆናሉ፡፡ በበጎና በክፋት መካከል በሚደረገው ግብግብ ተሸንፈው የአምላክን ፈተና የወደቁት ደግሞ ‹‹*አስፈለሳፈሊን*›› ወደተባለው ደረጃ ይወርዳሉ፡፡ የምድራዊ ሕይወት አላማ የሰው ልጅ ከነዚህ ከሁለቱ ዓላማዎች መካከል አንዱን እንዲያረጋግጥ ነው፡፡ የሰውን ልጅ ወደነዚህ ዓላማዎች የሚመሩትም ከውስጡ ያሉ አዎንታዊና አሉታዊ ዝንባሌዎች ናቸው፡፡ ወደፈለገው ዓላማ ይዘነበል ዘንድም ሙሉ ነጻነት ተሰጥቶታል፡፡ ይህ ውጤት በበጎና በክፋት መካከል የሚደረገውን ትግል ተከትሎ እውን ይሆናል፡፡ የሰው ልጅ ይህን ሁሉ ሲያከናውን የብዙ ነገሮችን ተጽእኖ ያስተናግዳል፡፡

አንድ ሰው በአበቦች ከተሞላ አጸድ ውስጥ ሲሆን ጥሩ ማአዛ ባላቸው ሽታዎች መታወዱ የሚጠበቅ ነው፡፡ በአንጻሩ ከቆሻሻ ስፍራ ሲሆን በመጥፎ ሽታ ይበከላል፡፡ ይህም ማለት አካባቢ በሰው ልጅ ላይ ተጽእኖ ያሳድርበታል ማለት ነው፡፡ ስለዚህም ከማንም በላይ መንፈሳዊ አመራርና ስልጠና ያስፈልገዋል፡፡

የሰው ልጅ ሕይወቱን ከሚያመሰቃቅልበት ድርጊት ላይ የሚወድቀው ከውስጡ በሚተራመሰው የበረታ ተቃርኖ ሰበብ ክፋት በበጎነት ላይ ጉልበት ባገኘበት ቅጽበት ነው፡፡ የዚህ ተቃርኖ ሰበቡም በሰው ለጅ ስሪት ውስጥ ወደ አላህ የሚያቃርበው ድንቅ ባህሪ፣ ከእንስሳ በታችም ሊያደርገው ከሚችል እኩይ ባህሪ ጋር ተጣምሮ ስለሚገኝ ነው፡፡

ከዚህ የተነሳ ትክክለኛውን መንፈሳዊና ስነ ምግባራዊ ስልጠና ያላገኙ ሰዎች ውስጠት የብዙ አውሬዎች መተራመሻ እንደሆነ ጥሻ (ጫካ) ማለት ነው፡፡ እያንዳንዱ ሰው በውስጡ እንደየ ዝንባሌውና ፍላጎቱ የአውሬነትን ባህሪ ይዟል፡፡ ልክ እንደ ተኩላ መሰሪ አለ፡፡ ልክ እንደ ድብ አጥቂ አለ፡፡ እንደ ጉንዳን መሰብሰብና ማጋበስ የሚወድ አለ፡፡ ልክ እንደ እባብ መርዘኛ አለ፡፡ ልክ እንደ ቱሐን ደም መጣጭ፣ ግና ለስላሳ አለ፡፡ ከፊት ለፊትህ እየሳቀ ከኋላ መጥፊያ ጉድጓድህን የሚምስልህ አለ፡፡

እነዚህ ሁሉ በተለያዩ እንስሳት ውስጥ  የሚገኙ የተለያዩ ባህሪያትን ይዘዋል፡፡

ራሱን ከነፍስያና ከከንቱ ስሜት በመንፈሳዊ ስልጠና በማጽዳት ስብእናውን ያልገነባ ሰው በርካሽና ወራዳ ማንነት ውስጥ ይቀጥላል፡፡ የአንድ ሰው  እንስሳዊ ባህሪ ሲያይል በስብእናው ላይ  ይንጸባረቃል፡፡ ተግባር ውስጣዊ ማንነትን ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ የማይዋሽ መስታውት ነው፡፡

ከ20 ሚሊዮን ሰዎች አጽም ላይ የተገነባው ኮሚኒዝም የአውሪያዊ ልቦናዎች ስራት እንጽብራቂ አይደለምን? ለአንድ ፊርዓውን ሲባል ሺዎች ዜጎች የተቀበሩባቸው ፒራሚዶች ለሰው ልጅ ስቃይና በደል ጥሩ ማስታወሻዎች አይደሉምን? እነዚህን ቅርሶች ሰዎች እንዳስደናቂ የታሪክ አሻራዎች አድርገው ያዩአቸዋል፡፡ በእውነት መንገድ ሲታዩ፣ በሐቅ ማዛን ሲመዘኑ ግን ጨካኝ ነፍስ ገዳዮችን እንኳ የሚያሳፍሩና የሚያስገርሙ የአውሬነት ድርጊት ምልክቶች ናቸው፡፡

የእንቁራሪት ባህሪ ያላቸው ሰዎች ሕብረተሰብ እንዲመሩ እድል ቢሰጣቸው ከዚህ ሕብረተሰብ ውስጥ ለራሳቸው መወሸቂያ አረንቋ ያበጃሉ፡፡ የእባብና የጊንጥ ባህሪ ያላቸው ሰዎች ገዥዎች ሲሆኑ ሕብረተሰቡ ባጠቃላይ ይመረዛል፡፡ ሽብርና ሁከትም ይነግሳል፡፡ በአንጻሩ የጽጌረዳ ባህሪ የተላበሱ ሰዎች ከአመራር ቦታ ላይ ከተቀመጡ ሕብረሰቡ ወደ ጸአዳነት ይቀየራል፡፡ እውነተኛ ደስታና መረጋጋትም ይፈጠራል፡፡

ስለዚህም የሰው ልጅ መለኮታዊ እነጻ ያስፈልገዋል፡፡ ከዚህ እነጻ የራቁ ወገኖች ከላይ እንዳወሳነው ዓይነት የአውሬነት መገላጫዎችን ባይፈጽሙም፣ አውሬ ሊያሰኟቸው የሚችሉ ድርጊቶችን በየጊዜ ሲፈጽሙ ይስተዋላሉ፡፡ ከዚህ በተጓዳኝ ሌሎች መልካም ባህሪያት የሚታዩባቸው ቢሆንም፡፡

ምክንያቱም ከመለኮታዊው እነጻ ውጭ የሚገኙ ውብ ባህሪያት ጊዜያዊ ናቸው፡፡ በአስቸጋሪና ፈታኝ፣ እንዲሁም ሸህዋ በሚያይልበት ወቅት እውነተኛ ማንነቶቻቸው ፈጥነው ወደ ላይ ይዘልቃሉ፡፡ ትክክለኛ

የሞራልና መንፈሳዊ እነጻ ያላገኘች ነፍስ አይጥ በምታድን ድመት ትመሰላለች፡፡ ድመት ጥሩ ምግቦች ቀርበውለት እየተመገበ ቢሆንም እንኳ አይጥ ካየ ምግቡን ትቶ ወዲያው ወደርሷ መሮጡ አይቀሬ ነው፡፡ ትክክለኛ ስልጠና ያላገኘ ቀልብም እንደዚሁ ነው፡፡ ሐሴትን የሚሰጡት ብዙ ነገሮች ካጠገቡ ቢኖሩም የሚያያቸውን አይጦች ሁሉ እየተከታተለ ይጠፋል፡፡

ፊርዓውንና ኑምሩድ ያለ አግባብ ብዙ ደም አፍስሰዋል፡፡ ከነፍሳቸው ውስጥ ያሉ የሸህዋ አይጦችን ተከትለው ንጹሃንን በግፍ ጨፍጭፈዋል፡፡

በአንጻሩ ጥሩ ኩትኮታና እነጻ፣ ሰውን በግፍ መግደል ቀርቶ ለኢምንት የሰው ሐቅ ውስጣችን እንዲፈራ እና እንዲርገፈገፍ፣ እጅግ አናሳ ወንጀልን እንዲጠነቀቅ ያደርገዋል፡፡ የሻማ ነበልባል በጥቂት የነፋስ ሽውታ እንደሚርገበገበው፡፡

የአላህ መልእክተኛﷺ ሌላው ቀርቶ ዛፍ እንኳ ያለ አግባብ መቁረጥን ከልክለዋል፡፡ ወደ መካ በመጓዝ ላይ እያሉ አንዲት ውሻ ልጆቿን ስታጠባ አዩ፡፡ እርሷን ላለማስደንገጥ በሽዎች የሚቆጠር ሰራዊታቸው መንገድ አሳብሮ እንዲጓዝ አደረጉ፡፡

አንድ ቀን የአላህ መልእክተኛﷺ በእሳት የተቃጠለ የጉንዳን ጉድጓድ ተመለከቱና በጣም ደነገጡ፡፡ በጣምም ተቆጡ፡፡ ‹‹ይህን የጉንዳን ጉድጓድ ያቃጠለው ማን ነው?›› ሲሉም ጠየቁ፡፡

የኡስማናዊው ኸሊፋ አራማጆች ይህን የአላህ መልእክተኛﷺ የፍቅር ማእድ በመቋደሳቸው አዛኝነት መገለጫቸው ሆኗል፡፡ እናም ከሰዎች አልፎ ለእንስሳት አገልግሎት የሚውሉ ወቅፎችን በስፋት ዘርግተዋል፡፡ ውሻዎችና ድመቶች ከሚደረግላቸው እንክብካቤ የተነሳ በከተሞች እንደልብ ይዘዋወሩ ነበር፡፡ ከሌሎች አካባቢዎች ግን ይሸሹ ነበር፡፡ ይህን እውነታ ወደ ኢስላማዊው ኸሊፋ ከተሞች ለጉብኝት የመጡ ወገኖች መስክረዋል፡፡

ከላይ የተጠቀሱት ናሙናዎች ትክክለኛ እነጻ ያገኙና ያላገኙ ሰዎች ናሙናዎች ናቸው፡፡ ሁለቱም ወገኖች ሰዎች ተብለው መጠራታቸው ይገርማል፡፡ የሰዎችን ደም በግፍ እያፈሰሰ ምድርን የሚያጨቀይም ሰው ነው፡፡ ሕይወትን ለማትረፍ ደም የሚለግሰውም ሰው ነው፡፡

አዎንታዊና አሉታዊ ስብእና ያላቸው ሰዎች በምድር ላይ አብረው የመኖራቸው ነገር ይገርማል፡፡ ገርና ልስልስ ባህሪ ያለው ጥንቸል ጨካኝ ከሆኑ አውሬዎች መሐል በአንድ ቦታ ላይ እንዲቀመጥ ቢደረግ የሚሰማው አይነት መታወክ ከክፉዎች ጋር የሚኖሩ ደግ ሰዎች ይሰማቸዋል፡፡ አንዳንድ ጊዜ እኩይና ስስታም፣ ከደግና ቸር ሰው፣ መሐይም ከአዋቂ፣ ብልህ ከቂል፣ አዛኝ ከበዳይ ጋር ጎን ለጎን የሚኖሩበት አጋጣሚ ይፈጠራል፡፡

ቸሩ እና አዛኙ ሌሎችን ለማገልገል የሚተጋ ሲሆን፣ ቂሉና መሐይሙ ዓለምን አያውቅም፣ ግፈኛው እኩይ ድርጊቶቹን ከፍትህ ይቆጥራል፡፡ በዙሪያው ባሉ ሰዎች ላይ ሐይል ይጠቀማል፡፡ በጥቅሉ የጨካኝ ልቦና ባለቤቶች የመላኢካ መንፈስ ካላቸው ሰዎች ጋር በዚህች ዓለም ይኖራሉ፡፡ በጎው ሰው ሐቅን ለማወቅ፣ ወደ አላህ ለመድረስ እና እርሱን ለመታዘዝ ይኖራል፡፡ ሌላኛው ደግሞ ደስታ የሚገኘው ርካሽና ወራዳ የሆኑ ሰዎችን ስነ ምግባር በመከተል እንደሆነ ይገምታል፡፡ ሕይወቱም ለምግብ፣ ለወሲብና ለስልጣን በሚደረግ መስገብገብ የተሞላ ነው፡፡

እጅግ ተቃራኒ ስብእና ያላቸው ሰዎች በሚኖሩባት ዓለም ውስጥ መኖር የከበደ ፈተና ነው፡፡ ግና የሰው ልጅ ይህን ፈተና ያልፍ ዘንድ ግድ ይለዋል፡፡ የሰው ልጅ ዓይነተኛ ዓላማ ይህን ፈተና በማለፍ የአላህን ቀረቤታ ማግኘት ነውና፡፡ ስለዚህም የሰው ልጅ ከእኩይ ባህሪያት በመራቅ መልካም ባህሪያትን አጎልብቶ የሰብአዊነትን ክብር እና ልቅና መጎናጸፍ ግድ ይሆንበታል፡፡

የሰው ልጅ ከመንፈሱ አኳያ ሰማያዊ ቢሆንም ከአካሉ አኳያ አፈር ነው፡፡ ይህም በመሆኑ መንፈሱ ወደ አላህ፣ አካሉ ደግሞ ወደ መሬት (አፈር) ይመለሳሉ፡፡

የሰው ልጅ በአካላዊ እሱነቱ ሌሎች ፍጡራን ያላቸውን ዓይነት ባህሪ ይጋራል፡፡ ስለዚህም መንፈሳዊ ሕልውና በማግኘት ውስጡን ማጽዳት፣ ከንቱ ፍላጎቱን መቆጣጠር፣ መንፈሱን መመገብ ይጠበቅበታል፡፡ ይህን ካላደረገ ከውጭ በኩል በሰይጣን፣ ከውስጥ በኩል ደግሞ በነፍስያው መሸነፉ አይቀርም፡፡ በዚህ ጊዜ የመንፈሱ ጉልበት ይደክማል፡፡ አላህ ይህን በማስመልከት ሲናገር እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَنَفْسٍ وَمَا سَوَّىٰهَا ۝٧ فَأَلْهَمَهَا فُجُورَهَا وَتَقْوَىٰهَا ۝٨ قَدْ أَفْلَحَ مَن زَكَّىٰهَا ۝٩ وَقَدْ خَابَ مَن دَسَّىٰهَا ۝١٠ ﴾ الشمس: ٧ - ١٠

*‹‹በነፍስና አስተካክሎ (ኢስላማዊ ተፈጥሮ አስይዞ) በፈጠራት፤ አመጸዋን (የጥመትን ጐዳና) እና ፍርሃትዋን (የጽድቅን ፍኖት) ባሳወቃት (አምላክ) እምላለሁ፡፡ (ነፍሱን አላህን በማምለክና ከኃጢአት በማቀብ) ያፀዳት ስኬታማ ሆነ፡፡ (በኃጢአት) የሸፈናት ከሰረ፡፡›› (አል ሽምስ 7-10)*

መውላና ጀላሉዲን ሩሚ በአንቀጹ የተገለጸውንና በሰው ልጅ ውስጠት የሚገኘውን አላህን የመፍራት እና የሐጢአት ዝንባሌ እንዲህ ሲሉ በምሳሌ ያስረዱናል፡-

‹‹ወደ አላህ ፊትህን አዙር፡፡ ወንድሜ ሆይ፣ እውነታውን ለማወቅ ከፈለግክ ሙሳና ፊርዓውን አልሞቱም፡፡ ይልቁንም ባንተ ውስጥ እስከዛሬም ድረስ ተደብቀው ይኖራሉ፡፡በቀልብህ ውስጥ ጦርነት ቀጥለዋል፡፡ ከነዚህ ከሁለቱ ስብእናዎች መካከል ከየትኛው መወገን፣ የትኛውን መሆን እንደምትሻ ለራስህ ምረጥ፡፡››

እንዲህም ሲሉ ጽፈዋል፡-

‹‹ለአካልህ ከመጠን ያለፈ ትኩረት አትስጥ፡፡ ምክንያቱም እርሱ በመጨረሻ ለአፈር በመስዋእትነት የሚቀርብ ነው፡፡ ይልቁንም ከቀልብህ እነጻ ላይ አተኩር፡፡ ምክንያቱም እርሱ ወደ ላይ ይወጣል፡፡ አካልህን በመጠኑ መግብ፡፡ አካሉን ከተገቢው በላይ የመገበ በሸህዋ ማየል ይጠቃል፡፡ ደካማና ወራዳም ይሆናል፡፡ በአንጻሩ መንፈስህን በደንብ መግብ፡፡ ወደምትጓዝበት ቦታ በብርታት ትጓዝ ዘንድ የሚያስችልህን ሁኔታ አስብና አዘጋጅለት፡፡

ተገቢውን መንፈሳዊ እነጻ ያላገኘች ነፍስ ደካማ ስር እንዳላት ዛፍ ማለት ናት፡፡ የዚህች ዛፍ ድክመት ከቅርንጫፏና ከፍሬዋ ላይ ይገለጻል፡፡ የቀልብ በሽታም ከአካል እንቅስቃሴ ላይ ይንጸባረቃል፡፡ ጉዳትም ያስከትልበታል፡፡ ሕክምና ይበልጥ የሚያሻቸው በሽታዎች የሻህዋ ማየል፣ ጥላቻ፣ ምቀኝነት፣ ኩራትና ሌሎች የቀልብ በሽታዎች ናቸው፡፡ እነዚህን አሉታዊ ባህሪያት ለማከም ብልሐቱ መጀመሪያ የአላህን ወሰኖች ማክበር፣ በባህሪህ አላህን ማስደሰት፣ እርሱ እንዳዘዘህም መሆን እና ቀጥ ማለት ነው፡፡

ለሰው ልጅ አላህን የሚያስደስት ስብእና ለማነጽ የሚያስፈልጉት ሁለት መሠረታዊ አስፈልጎቶችና ባህሪያቶች፡- አንደኛ አርአያ (Role Model) መያዝ፣ ሁለተኛ፡- እርሱን መከተል ናቸው፡፡

## አርአያ የመያዝና የመከተል ዝንባሌ

የሰው ልጅ ከተወለደበት ቅጽበት አንስቶ የሚከተለው አርአያ ይፈልጋል፡፡ ሕይወቱን የሚያንጹ አስተሳሰቦችን ለምሳሌ ቋንቋ፣ ሐይማኖት፣ ባህልና ስነ ምግባራዊ እሴቶችን የሚቀዳው በአካባቢው እንደ አርአያ አድርጎ ከያዘው ሰው ነው፡፡ አንዳንድ የተለዩ ሁኔታዎችና አጋጣሚዎች ሊኖሩ ቢችሉም የአብዛኛው ሰው ስብእና የታነጸው በዚህ መልኩ ነው፡፡

ለምሳሌ አባትና እናት አንድ ዓይነት ቋንቋ የሚያወጉ ከሆነ ልጃቸው ያን ቋንቋ ያለ ጥርጥር ይማረዋል፡፡ በተመሳሳይ መልክም ሌሎች ቋንቋዎችን መማር ይችላል፡፡ በጥቅሉ የሰውን ልጅ ስብእና ማነጽ ማለት በዋነኛነት አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ነገሮችን ከሌሎች ሰዎች (አርአያዎች) መቅዳት ማለት ነው፡፡ መቅዳትና መከተል ከሰው ልጅ ስሪት ውስጥ የሚገኝ ዝንባሌ ነው፡፡ በእርግጥ ሌሎች ሁነቶችም በስብእናው ላይ የተወሰነ ተጽእኖ ይኖራቸዋል፡፡

የሰው ልጅ በዋነኛነት ያሳደጉትን ወላጆች ተጽእኖ፣ የቤተሰቡን፣ በመጨረሻም የአካባቢውን ተጽእኖ ያስተናግዳል፡፡ ወደ ሕብረተሰቡም የሚቀላቀለው በዚህ አይነት መልኩ የተዋቀረ ስብእናውን ይዞ ነው፡፡

የሰው ልጅ ቋንቋንና መሰል ግልጽ ነገሮችን መማር ይቀለው ይሆናል፡፡ ሐይማኖት፣ ስነምግባርና የርሱን ውስጣዊ ማንነት የሚመለከቱ ሌሎች ነገሮችን መማር ግን ለርሱ አስቸጋሪ ነው፡፡ ምክንያቱም አላህ ለፈተናና ለጥበብ የፈጠረው ሰይጣን፣ ነፍስያና ከንቱ ስሜት የሰውን ልጅ ከበጎ ነገር ለማራቅ አሰፍስፈዋል፡፡ እናም ወደበጎነት እንዲቀርብ በቀላሉ አይፈቅዱለትም፡፡

ይህም በመሆኑ ሰዎች በተፈጥሯቸው አርአያ የሚይዙና የሚከተሉ ከመሆናቸው አኳያ በመሪዎቻቸው በአዎንታዊ ወይም በአሉታዊ ገጽታው ይፈተናሉ፡፡ ስለዚህም ውስጣዊ ማንነታቸው በአላህ ነብያትና ወዳጆች እጅ ካልታነጸ መንገድ ከመሳት፣ ከጥመትና ከሐጢአት አይድኑም፡፡ ይህም ሲሆን ዘልዓለማዊ ደስታቸው ይጠፋል፡፡ ከግልጽ ኪሣራ ላይም ይወድቃሉ፡፡

በአሁኑ ሰአት ብዙዎቹ ሰዎች ርካሽ ስብእና ያላቸውን ታዋቂዎች (የፊልም አክተሮች፣ አርቲስቶች ወዘተ) አርአያ አድርገው መያዛቸው እና እነርሱን መስለው ለመገኘት የሚያደርጉት ሩጫ ወደር የማይገኝለት የስልጣኔ ንጥፈት ነው፡፡ የቀልብን ዙፋን ለርካሽ እና ወራዳ ስብእናዎች ይቀመጡበት ዘንድ መስጠት እጅግ የሚያስገርም ኪሣራ እና ብክነት ነው፡፡

ጀላሉዲን ሩሚ የነፍስያን የማታለየ ስልት ሲገልጹ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹በግ ከተኩላ መሸሹ አይገርምም፡፡ ምክንያቱም ጠላቱም አዳኙም እርሱ ነውና፡፡ በጣም የሚገርመው የበግ ልቦና ወደ ተኩላ መስሳቡ ነው፡፡

በርካታ አሳዎች ከባህሩ ስር በሰላም መኖር እየቻሉ በስግብግብነታቸው ምክንያት የመንጠቆ ራት ይሆናሉ፡፡››

በዚህ ሰበብ የሰው ልጅ ምንጊዜም የነፍስያንና የከንቱ ስሜትን ክፋት የሚያመላክቱ ባለንጹህና ስስ ልቦና መሪዎች ያስፈልጉታል፡፡

## የአላህ መልእክተኛﷺ ተምሳሌታዊ ስብእና

የሰው ልጅ ፈለጉን የሚከተለው የተሟላ ስብእና ማግኘቱ እጅግ አስፈላጊ ነገር ነው። የሰው ልጅ አንድን የተለየ ሰው ማፍቀሩና ማድነቁ፣ እርሱንም በአርአያነት ለመከተል መሻቱ ተፈጥሯዊ ነገር ነው። እናም ይከተለው ዘንድ የተሟላ ስብእና፣ አርአያና ናሙና በእጅጉ ይሻል። ይህን የሰውን ልጅ ባህሪ ጠንቅቆ የሚያውቀው አዛኙ አምላክ ለሰዎች መጽሐፍት ብቻ በመላክ አልተዋቸውም።

የነዚህን መጽሐፍት መልእክቶች ተግብረው የሚያሳዩና ሕያው ተምሳሌቶች የሚሆኑ መልእክተኞችንም አብሮ ልኳል።

ለሰው ልጅ እውነተኛ ናሙናዎች፣ ትክክለኛ አርአያዎች የአላህ መልእክተኞች ናቸው። ምሉእነት በሁሉም ገጽታው፣ በአነጋገር፣ በባህሪው፣ በተግባር፣ በእውቀትና በስነ ምግባር አንጸባራቂ በሆነ መልኩ በነርሱ አማካይነት ይገለጻል።

የእያንዳንዱ ነብይ ስብእና በሰዉ ልጅ ታሪክ ውስጥ የመጨረሻውን የምጥቀት ደረጃ ደርሷል። ነብያት ለሰው ልጅ ወደር የማይገኝለት አገልግሎት ሰጥተዋል። የነብያት ወራሾች የሆኑት ደጋግ ሰዎችና ሙእሚኖችም እንደዚሁ፡-

- የዲንን ውጫዊ እና ውስጣዊ እውነታ በአንድ አዋህደው በመያዝ ከስብእናቸው ውስጥ ጻፉት።
- በዙህድና በተቅዋ ጎዳና ብዙ ርቀት ተጉዘዋል። በባህሪም ምሉእነትን ተጎናጽፈዋል።
- የአእምሯቸውንና የቀልባቸውን አድማስ በማስፋት ይህችን እና መጭውን ዓለም እንዲያካትት አድርገዋል። የእምነትን ለዛ አጣጥመዋል። የስሜትን ጥልቀትና ርቅቀት ተክነዋል።
- ተግባሮቻቸው ከክፉ ባህሪያትና ከነፍስያ ጥመት ጸድተው ወደ ውብ ባህሪያት፣ ወደ ውስጣዊ ምሉእነት አድማስ ዘልቀዋል። በእርግጥም

በነብያዊው ጎዳና እና አመራር ወደ ላይ የዘለቁ፣ በባህሪያቸው የበቁና የመጠቁ ሰዎች በሁሉም ዘመናት ኖረዋል፡፡ ከነርሱ የነጠፈ ዘመን የለም፡፡ ነብያትን የማየት ልቅና ያላገኙ ግለሰቦች እነዚህን ታላላቅ ሰዎች በአርአያነት ሊይዙ ግድ ይላል፡፡ ምክንያቱም በእዝነት አንደበት ልቦናዎችን ሕያው የሚያደርገው ምክራቸውና አመራራቸው ከነብያት ምንጭ የፈለቀ መንፈሳዊ ማእዛ ነውና፡፡

ሰዎች በዚህች ዓለም ውስጥ ያላቸው ቦታ ምንም ይሁን ምን በፍትህ ከተዳኙ፣ በቀልቦቻቸው መሐል የእዝነት ትስስር ካለ፣ በየትኛውም ማሕበረሰብ ውስጥ ሐብታሞች ድሆችን ከረዱ፣ ብርቱዎች ከተበዳይ ጎን ከቆሙ፣ ጠንካሮች ደካሞችን ከደገፉ፣ የቲሞችን ከተንከባከቡ፣ እነዚህ በጎ ባህሪያትና ድርጊቶች ያለ ጥርጥር በነብያትና በተከታዮቻቸው አማካይነት የተላለፉ እሴቶች ናቸው፡፡

በአባታችን አደምና በእናታችን ሐዋ የተጀመረው የሰው ልጆች ቤተሰብ አባላት በሐይማኖታዊ ድባብ፣ መንፈስና ደስታ ስር ለመኖር ታቅዶላቸው ካእባን የመጀመሪያው ቤተ አምልኮ አድርገው ያዙ፡፡ ከዚያ በኋላ በምድር ላይ የተረጩ የአደም ልጆች ዲናዊ ሕይወታቸው ይቀጥል ዘንድ ነብያዊ አመራር ሲሰጣቸው ኖሩ፡፡ ሐይማኖትና መለኮታዊ እውነታ በበካዮች እጅ መብበከል ሲጀምር አላህ ብክለቱን ለማጽዳትና ዲኑን እንደ አዲስ ሕያው ያደርጉ ዘንድ ነብያትን ይልክ ጀመር፡፡

የሰው ልጅ በረዥሙ ታሪኩ ከግለሰባዊና ማሕበራዊ ቀውሶቹ በአላህ እዝነትና በረከት ሲፈወስ ኖሮ በመጨረሻም የነቢዩ ሙሐመድﷺ ዘመን ደረሰ፡፡ ይህ የደስታ ዘመን መጣ፡፡ ይህ ዘመን ልክ እንደ ጸሐይ መግቢያ የሰው ልጅ ምድራዊ ሕይወት መገባደጃ ነው፡፡ በዚህ ዘመን ሕይወት በጀመረችበት የመካ መሬት ላይ የሰው ልጅ የመጨረሻ ምልዓትን ተጎናጸፈ፡፡ የዚህ ምጥቀት አስኳልና ጥልቀት ነቢዩ ሙሐመድﷺ ነበሩ፡፡

ከነቢዩ ሙሐመድﷺ በኋላ ሌላ መልዕክት አይታሰብም፡፡ በነብያት አማካይነት ሲታደስ የኖረው እና አላህ የሚወደው ሐይማኖት ኢስላም ፍጻሜውንና ምሉእነቱን አገኙ፡፡

የአላህ መልእክተኛﷺ የሰውን ልጅ በተግባር በማስተማርና በመምራት ሂደት የመጨረሻውን ምሉእነት የያዙ አንጸባራቂ ናሙና ናቸው፡፡ ቁጥር ስፍር የሌለው የተግባር ትምህርታቸው ተመዝግቦ ተላልፎልናል፡፡

ነቢዩንﷺ የመከተል ዝንባሌ ተፈጥሯዊ እንደሆነ ጥርጥር የለውም፡፡ ግና እርሳቸውን በመከተል ሂደት ስኬታማነት ለርሳቸው ካለን የጠለቀ ፍቅር ጋር የተሳሰረ ነው፡፡

## የአላህን መልእክተኛﷺ ምን ያህል እንወዳለን?

## ቀልብንም አእምሮንም መጠቀም

አላህ የሰውን ልጅ በጥሩ አቋም ፈጥሮታል፡፡ ከሌሎቹም ፍጡራን ሁሉም አልቆታል፡፡ በሰማያትም በምድርም ያሉ ፍጡራንን ሁሉ ለርሱ ግልጋሎት ገርቶለታል፡፡ በእርግጥ ይህ ሁሉ የሚከሰተው ለሚያስተነትኑ ሰዎች ነው፡፡

የኛ የሰው ልጆች ትልቁ ተግባር ፈጣሪ የለገሰንን ጸጋዎች ማስተንተንና ለተገቢው አገልግሎት ማዋል መሆኑን መናገር እንችላለን፡፡ በተለይም አእምሯችንንና ቀልባችንን ይበልጥ መልካምና ውጤታማ በሆነ መንገድ እንጠቀም ዘንድ ታዘናል፡፡

## አእምሯችንን እንዴት እንጠቀም?

አእምሮ ለነፍስያና ለከንቱ ስሜት ልጓሙን ማስረከብና በነርሱ መመራት የለበትም፡፡ ይልቁንም በዚህች የፈተና ዓለም ውስጥ የመገኘቱ ዓላማ የአምላክን  እውነታ ማስተተንና መረዳት መሆኑን መገንዘብ ያሻዋል፡፡

## ቀልባችንን እንዴት እንጠቀምበት?

ቀልብ አላህን የመውደጃ ማእከል ነው፡፡ አላህ የሚመለከተው ቦታ ነው፡፡ ስለዚህም ከወንጀሎች ሁሉ ማጽዳት፣ አላህን በማስታወስና በተውሂድ መሙላት ተገቢ ነው፡፡ ይህ ሲሆን በሂደት ይጸዳና ***‹‹ቀልበን ሰሊም››*** ***(ንጹህ ቀልብ)*** ሆኖ ወደ አላህ አብሮነት ይሸጋገራል፡፡

## ተምሳሌታዊው ስብእና

አላህ በእዝነቱ ወደ ቅን ጎዳና የሚመሩን ከ124 ሽህ የሚበልጡ ነብያትንና መልእክኞችን ልኳል፡፡ የመጨረሻው የአላህ መልእክተኛ ነቢዩ ሙሐመድﷺ ሲሆኑ ከሁሉም ነብያት ይበልጥ ከአላህ ዘንድ ተወዳጅ እርሳቸው ናቸው፡፡ ሁሉም ሕዝቦች ለሚኖሩበት ተጨባጭ ሁኔታቸውና አወቃቀራቸው ተስማሚ የሆኑ ነብያትን አስተናግደዋል፡፡

ነቢዩ ሙሐመድﷺ ግን የተላኩት ለሰው ልጆች ባጠቃላይ ሲሆን መልእክታቸው እስከ እለተ ቂያማ ድረስ ይቆያል፡፡ ይህች ዓለም ካሳለፈቻቸው ጊዜያት ውስጥ ይበልጥ ጽልመታማ እና በመሐይምነት የተሞላውን ጊዜ አላህ እርሳቸውን በመለገስ በብርሃን አደመቀው፡፡ ነቢዩﷺ ለሰው ልጅ ልክ እንደ ጸሐይ ናቸው፡፡ አላህ እርሳቸውን በመላክ እጅግ የከበደ ባለውለታችን ሆነ፡፡

## ቁርአን -ታላቁ ተአምር

አላህ ለመልእክተኛውﷺ በርካታ ተአምራት ሰጥቷቸዋል፡፡ ይበልጥ ትልቁ ተአምር ግን ቁርአን መሆኑ ጥርጥር የለውም፡፡ ቁርአን እስከ እለተ ቂያማ እንደጸና ይኖራል፡፡ የአላህ የመጨረሻ ንግግር ነው፡፡ ነቢዩ ሙሐመድﷺ ይህን ተአምር አይተዋል፡፡ የሰውልጆችም እስከ አለም ፍጻሜ ድረስ የዚህን ተአምር ድንቅነት ይገነዘባል፡፡

የአላህ መልእክተኛ በቁርአን አማካይነት ድንቅ ማሕበረሰብ ገንብተዋል፡፡ ይህች ዓለም እንደዚያ ዓይነት ማሕበረሰብ አይታ አታውቅም፡፡ በዚያ ዘመን እጅግ የዘቀጡ የነበሩ ሰዎች ስብእናቸው ተለውጦ የሰብአዊነትን ጣሪያ ሲደርሱ ተስተውሏል፡፡ ያ ማሕበረሰብ ከቁርአን በፊት እንስት ልጆቹን ከነ ሕይወታቸው የሚቀብር አውሬ ነበር፡፡ በነቢዩﷺ መንፈሳዊ እነጻ እጅግ በጣም አዛኝ ሊሆን በቃ፡፡ ሌላው ቀርቶ ተኩላ ነፍሰ ጡር እንስሳትን ሲያድን በዝምታ መመልከት ያልፈቀደ ድንቅ ማሕበረሰብ

ተፈጠረ። የአላህ መልእክተኛﷺ ለሰው ልጅ ባጠቃላይ ሊከተላቸው የሚገቡ መልካም አርአያ ለመሆናቸው ይህ ብቻ በቂ መረጃ ነው።

## ዓይነ ስውር ጸሐይን ያማርራል

ቀልቦች ባይታወሩ ኖሮ የአላህን መልእክተኛﷺ በእርግጠኝነት ማየት ይችሉ ነበር። የማየት ሐይሉ ደካማ የሆነ ሰው ካልሆነ በቀር በነቢዩ ሙሐመድﷺ ስብእና ውስጥ አንዳች ጉድለት ማየት የሚችል የለም። እርሳቸውን በወጉ ማየትና ማድነቅ ያልቻለ ችግሩ ከርሱ ነው። ጉድለቱ፣ ነውሩ ከእይታው ነው።

የሰው ልጅ ታሪክ የተለያዩ ሕዝቦች በነብዮቻቸው ላይ የፈጸሟቸውን ግፎችና የፈበረኳቸውን እብለቶች በሚያሳዩ አጋጣሚዎች የተሞላ ነው። ምክንያቱም ለነብያት የደረሷቸው አምላካዊ እውነታዎች፣ ከነዚህ ሰዎች ከንቱ ስሜቶችና ዝንባሌዎች ጋር የሚቃረኑ ስለሚሆኑ ሰዎች በጣሙን ይታወካሉ።

እናም ለእኩይ ድርጊቶቻቸው ሕጋዊነትን ለማላበስ ድርጊቶቹን ወደ ነብያት ይለጥፋሉ። ዛሬም በአላህ መልእክተኛﷺ ላይ የሚሰነዘረው የሐሰት ዘመቻ የአስተባባሪዎችን ባህሪ እኩይነት ከማጋለጥ ባሻገር ሌላ ፋይዳ ለነርሱም እንኳ የለውም።

ሁሉም ፍጡር ለኑሮ በሚስማማው አካባቢ መኖርን ይወዳል። ይህ ለሰው ልጅ ብቻ የተለየ አይደለም። የንብ ምግብ ማር በመሆኑ ለርሷ ኑሮ ተስማሚው በአበቦች የተሞላ አካባቢ ነው። ከዚያ መውጣት አትችልም። በአንጻሩ በቆሻሻ አካባቢ ለመኖር የሚስማማት አይጥ በአበቦች የተሞላን አጸድ ልትላመድ አትችልም። ልክ እንደዚሁ መልካም ነፍሶች በሙሐመዳዊው ብርሃን የደመቀ መንፈሳዊ ድባብ ይሰማማቸዋል። መጥፎ ነፍሶች ደግሞ በቆሻሻ ክልል እንጅ መኖር አይችሉም።

አቡበክር የአላህን መልእክተኛﷺ ፊት ባዩ ቁጥር፡- ‹‹አምላኬ ሆይ፣ ምን ዓይነት ውበት አላበስካቸው፡›› በማለት መደነቃቸውን ይገልጻሉ፡፡ በእርግጥ የራሳቸውን ውስጣዊ ዓለም እና ስብእና በነቢዩ መስታውትነት ነው የተመለከቱት፡፡ ይህም በመሆኑ ነቢዩ አንድ ቀን፡- ‹‹የአቡበክር ገንዘብ የጠቀመኝን ያህል የሌላ የማንም ገንዘብ አልጠቀመኝም›› በማለት ሲናገሩ አቡበክር ሰሙና እያለቀሱ እንዲህ አሉ፡-

‹‹የአላህ መልእክተኛ ሆይ፣ እኔም ገንዘቤም የርስዎ አይደለንምን?›› (ቢን ማጃህ)

አቡበክር በዚህ ንግግራቸው ነፍሳቸውም ሆነ ገንዘባቸው ለአላህ መልእክተኛ ግልጋሎት መዋሉን ይፋ አደረጉ፡፡ አቡበክር ውስጣቸው ተቀይሮ የነቢዩﷺ ስብእና የሚታይበት መስተዋት ሆኗል፡፡

በሌላ በኩል የአላህና የመልእክተኛውﷺ ታላቅ ጠላት የሆነው አቡ ጀህል ነቢዩን ሲያይ ፊቱ በንዴት ይቀላል፡፡ በቁጭት ይቀያየራል፡፡ የነቢዩን ውበት ማጣጣምን ተነፍጓልና፡፡ የዚህ ልዩነት ሰበቡ አቡበክርም ሆነ አቡጀህል የአላህን መልእክተኛﷺ ሲያዩ በርሳቸው መስዋእትነት የሚመለከቱት ራሳቸውን ነበርና ነው፡፡

የአላህ ነብያት ልክ እንደ ንጹህ መስተዋት ናቸው፡፡ ሁሉም ሰው በነርሱ አማካይነት ውስጣዊ ማንነቱን ያያል፡፡ መስታውቱ አይዋሽም፡፡ ጥሩውን መጥፎ፣ መጥፎውን ጥሩ አድርጎ አያሳይም፡፡ የተመልካቹን ትክክለኛ ገጽታ ነው የሚያንጸባርቀው፡፡

አላህን እና መልእክተኛውን የሚቀናቀን ያለ ጥርጥር ፈጥኖም ይሁን ዘግይቶ መለኮታዊ ብቀላ አይቀርለትም፡፡ ምክንያቱም አላህ እስልምናን በሐይሉና በብልሐቱ ይጠብቀዋል፡፡ በልእልናው ይታደገዋል፡፡ ልቦቻቸው በነቢዩ ፍቅር የተሞሉ ሙስሊሞች በእስልምና ላይ የሚሰነዘሩ ትችቶች፣ የተቀሰሩ መርዛማ ብእሮችና ጥቃቶች ያንገበግቧቸዋል፡፡ ሕመሙ ይቆጠቁጣቸዋል፡፡ እነዚህ ብእሮች በጨለማ ውስጥ እንደምትኖር እና

ሰዎችን ለማወክና ለመበቀል በየጊዜ ከወዲያ ወዲህ እንደምትወናጨፍ እባብ ማለት ናቸው፡፡

አላህ በእዝነቱ የሰውን ልጅ ምንጊዜም ወደ ሐቅ የሚዘነበል አድርጎ ፈጥሮታል፡፡ ይህን ዝንባሌውን መፋቅ የሚቻል አይደለም፡፡ አምላክ የለሽነት ይህ ወሰንህ የማይባል የግፍ ተግባር ለማስፋፋት ብዙ ቢታገልም የሐይማኖትን ስሜት ከስር ፈንቅሎ ሊጥል ግን አልቻለም፡፡ ምክንያቱም ሐይማኖት በሰው ልጅ ነፍስና ሕሊና ውስጥ ጥልቅ መሠረት ያለው ስሜት ነውና፡፡ የሰውን ልጅ ወደ አምላክ የመቃረብ፣ የመከጀል ስሜት የመደምሰስ አቅም የለውም፡፡ በሕሊናው ውስጥ የሚገኘው ዘልዓለማዊውን ደስታ የመሻት ፍላጎት ሊታበል የሚችል አይደለም፡፡ አላህን የመፈለግና የሐይማኖት ስሜትን፣ አላህ ሊለወጥና ሊፋቅ የማይችለው የሰው ልጅ ስሪት አካል አድርጎታል፡፡

ራሳቸው እውር ሆነው የሐይማኖትን ብርሃን ለማጥፋት በከንቱው የሚደክሙ ወገኖችን ጀላሉዲን ሩሚ እንዲህ ገልጸዋቸዋል፡-

‹‹ዓለማችንን የምታበራውን ጸሐይ የሚያነውርና ከርሷ ጉድለት ለማግኘት የሚያነፈንፍ እርሱ ራሱ እውር ነው፡፡ ስለዚህም ራሱን ያነውር፡፡ ራሱን ይማ፡፡››

አላህ የአንድን ሰው ነውር ሊያጋልጥ ሲሻ ንጹሐንን የማነወርን ፍላጎት ከልቦናው ውስጥ ያኖርበታል፡፡

ስለዚህም የሰው ልጅ ወደ ነቢዩ ሙሐመድﷺ የተሰነዘሩ ትችቶችን ለርሳቸው ወደሚቀርብ ሙገሳ እንዴት መቀየር እንዳለበት ሊያስብበት ይገባል፡፡ የአላህ መልእክተኛﷺ የሰውን ልጅ ለማቅናት ስላደረጉት ጥረት ምስጋና ለማቅረብ ያልተዘጋጀ ቀልብ በእርግጥም ቀልብ አይደለም፡፡፡ የአላህ መልእክተኛ ﷺ ለኛ ለሰው ልጆች የነበራቸው ፍቅር ከእናት ከአባቶቻችን ፍቅር የበለጠ እንደሆነ እሙን ነው፡፡ ይህን በማስመልከት ሲናገሩ፡-

‹‹ለአላህ መንገድ ባደረግኩት የትግል ሂደት ከማንም በላይ መስፈራራትና መታወክ ደርሶብኛል፡፡ እኔና ቢላል ለቀናት ያህል የሚላስ የሚቀመስ ምግብ የምናጣባቸው ብዙ አጋጣሚዎች ተከስተዋል፡፡›› (ቲርማዚ)

ግና በዚህ ሁሉ መከራ አልታወኩም፡፡ እርሳቸውን ያንገበግባቸው የነበረው የኡመታቸው ጉዳይ ነበር፡፡ በእዝነት የተሞሉ ነብይ እንደመሆናቸው በዚህች ዓለም ሊያድኑን ተግተዋል፡፡ በመጭው ዓለም ደግሞ ከአላህ ዓርሽ ስር ሱጅድ በመውረድ ሊታደጉን ይጥራሉ፡፡ ትድግናቸው ተቀባይነት ካላገኘ በቀር ከሱጁድ አይነሱም፡፡ (ቡኻሪና ሙስሊም)

ታዲያ እኛን ከመከራ ለማዳን ይህን ያህል የለፉትን ነብይ ትምህርታቸውን በመተግበር፣ ፈለጋቸውን በመተከል እና ከራሳችንም በላይ በማፍቀር ማመስገንና ማሞገስ አይገባንምን?

እርሳቸው በዱንያም በአኼራም እኛን ለማማለድ ይህን ያህል ሲንገበገቡ እኛ እርሳቸው የሚፈልጉን አይነት ሙእሚኖች ሆነን ለመገኘት የተሳነን ለምን ይሆን? የርሳቸው አፍቃሪ ለመሆን ለምን አልቻልንም? ከራሳችን በላይ ለምን አልወደድናቸውም?

## አፍቃሪ ታዛዥ ነው

ነቢዩﷺ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹ሰውየው ከሚወደው ጋር ነው፡፡››

ነቢዩንﷺ ምን ያህል እንወዳለን? ፍቅር በአፍቃሪና በተፈቃሪ መካከል ያለ ግንኙነት ነው፡፡ ይህን ፍቅር መረዳትና መኖር ይጠበቅብናል፡፡

ሰውየው በንግግርም ሆነ በተግባር፣ በባህሪም ሆነ በስሜት፣ በስነ ምግባርም ሆነ በውሎ፣ በአጠቃላይ በሕይወቱ የሚወደውን አካል ለመሆን ይጥራል፡፡ ይህ ከሌለና ሁለቱም ወደ ተቃራኒ አቅጣጫ የሚጓዙ ከሆነ ፍቅራቸው እውነተኛ አልነበረም ማለት ነው፡፡

ከዚህ አኳያ የነቢዩን ﷺ ሱንና የመከተላችን መጠን ለርሳቸው ያለንን ፍቅር መጠን ያመለክታል፡፡ እርሳቸውን ምን ያህል እንወዳለን? ሱናቸውን ምን ያህል እንከተላለን? ለልጆቻችን ስለ ነቢዩና ስለ ቤተሰቦቻቸው ምን ያህል እናወጋለን? በቁርአንና በመንፈሳዊ ድባብ የተሞላው የነቢዩ ቤተሰቦች ጎጆ ከኛ ጎጆ ምን ያህል ድርሻ አለው?

## ነቢዩን ﷺ መከተል መንፈሳዊ ስልጠናን ይሻል

በሁሉም የሕይወት እርከኖች የአላህን መልእክተኛ ﷺ በአርአያነት መከተል ይጠበቅብናል፡፡ ይህ ሲሆን በዚህችም በመጭውም አለም እውነተኛ ደስታ እናገኛለን፡፡ በማሕበራዊ፣ በቤተሰባዊ እና በእውቀት መስክ፣ እንዲሁም በሌሎችም የሕይወታችን ዘርፎች እርሳቸውን አርአያ ማድረግ ግዴታችን ነው፡፡ በየትኛውም ደረጃ ላይ ለሚገኙ ሰዎች መልካም አርአያ ናቸው፡፡

የርሳቸውን አርአያነት የምንማረው እንዴት ነው? በጽሑፍ መማር በቂ ነውን? በፍጹም አይደለም፡፡ የዚህ ትምህርት ማእከሉ የቀልብ ዓለም ነው፡፡ አላህ የነቢዩን ﷺ አርአያነት መከተልን የምንማርበትን ስልት ሲገልጽ እንዲህ ይላል፡-

﴿ لَّقَدْ كَانَ لَكُمْ فِي رَسُولِ ٱللَّهِ أُسْوَةٌ حَسَنَةٌ لِّمَن كَانَ يَرْجُواْ ٱللَّهَ وَٱلْيَوْمَ ٱلْآخِرَ وَذَكَرَ ٱللَّهَ كَثِيرًا ﴿٢١﴾ ﴾ الأحزاب: ٢١

*‹‹የአላህ መልዕክተኛ፥ (ከመካከላችሁ) አላህንና መጭውን ዓለም ተስፋ ለሚያደርግ፥ አላህንም በብዛት ለሚያወሳ፥ መልካም አርአያ ነው፡፡›› (አል አህዛብ 21)*

የዚህ ትምህርት የመጀመሪያው መስፈርት አላህን መገናኘትን መመኘት ነው፡፡ ዘወትር በዚህ ስሜት ውስጥ ልንኖር ይገባል፡፡ ከአላህ ፊት ቀርበን የምንመረመር መሆኑን ማስታወስ ግድ ነው፡፡ ይህ ስሜት ለአፍታ እንኳ ከኛ ሊነጠል አይገባውም፡፡

ሁለተኛው መስፈርት የመጭውን ዓለም መኖር ከልብ ማመንና እርሱን ለመገናኘት ተስፋ ማድረግ ነው፡፡ ከጠፊና አላፊ ዓለም ውስጥ መሆናችንን መረዳት ግድ ነው፡፡ ይህች ዓለም ታልፋለች ፡፡ እኛም እናልፋለን፡፡ ጀላሉዲን ሩሚ እንዲህ ሲሉ ጽፈዋል፡-

‹‹ይህች ዓለም ልክ እንደ ሕልም ናት፡፡ በዚህች ዓለም ውስጥ ሐበታም የሆነ በሕልሙ ብዙ ገንዘብ እንዳገኘ ሰው ማለት ነው፡፡ ሰውየው ያልፋል፡፡ ዓለማዊ ሐብቱ ግን ከትውልድ ትውልድ ይተላለፋል፡፡››

በፈተና አገር ውስጥ መበርታትን መዘንጋት የለብንም፡፡ ስለዚህም ቀልባችን የሸህዋን እና የከንቱ ስሜትን እንቅፋቶች ተሻግሮ በሰፊው የአምላክ ዓለም ውስጥ መንፈሳዊ ቅኝት እንዲያደርግ ልንፈቅድለት ይገባል፡፡እንዲህ ከሆንን አላህ ጀነትን ሊሰጠን፣ የተላቀውን ፊቱንም ሊያሳየን ቃል ገብቷል፡፡

የነቢዩንﷺ አርአያነት ለመማር ሦስተኛው መስፈርት አላህን በብዛት ማውሳት ነው፡፡ የአላህን አብሮነት ምንጊዜም ማስታወስ ያሻል፡፡ ለምን ያህል መጠን? ተከታዩን አንቀጽ እንመልከት፡-

﴿ ٱلَّذِينَ يَذْكُرُونَ ٱللَّهَ قِيَـٰمًا وَقُعُودًا وَعَلَىٰ جُنُوبِهِمْ وَيَتَفَكَّرُونَ فِى خَلْقِ ٱلسَّمَـٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ رَبَّنَا مَا خَلَقْتَ هَـٰذَا بَـٰطِلًا سُبْحَـٰنَكَ فَقِنَا عَذَابَ ٱلنَّارِ ﴿١٩١﴾ ﴾ آل عمران: ١٩١

*‹‹እነርሱ አላህን ቁመውም ተቀምጠውም፥ በጐኖቻቸው ተጋድመውም የሚያወሱት፥ የሰማያትንና የምድርን (ድንቅ) አፈጣጠር የሚያስተነትኑት፥ “ጌታችን ሆይ! ይህን (ድንቅ ዓለም) እንዲሁ (ያለ ዓላማ) አልፈጠርከውም፤ ክብር ላንተ ይሁን፡፡ ከእሳት ቅጣት ጠብቀን፡፡” (የሚሉት ናቸው)፡፡›› (አሊ ዒምራን191)*

አላህን ዘወትር ማስታወስ ማለት እያንዳንዱ እንቅስቃሴያችን በመለኮታዊ ካሜራ እየተቀረጸ እንደሆነ አለመዘንጋት ማለት ነው፡፡ አላህ ከደም ስራችን ይበልጥ ለኛ ቅርብ ነው፡፡ እኛስ ለአላህ ያለን ቅርበት ምን ያህል

ነው? አዎ፣ የአላህን ቀረቤታ ለማግኘት መልእክተኛውን ﷺ አርአያ አድርገን መከተል ግድ ይሆንብናል፡፡

## የነብዩን ﷺ ደረጃ ምን ያህል ተረድተናል?

የነቢዩን ﷺ ፍቅር ሳናውቅ ወደ አላህ መጓዝ አንችልም፡፡ አላህ በቁርአኑ ለርሳቸው የሰጠውን የላቀ ደረጃ እንዲህ ሲል ገልጿል፡-

﴿ إِنَّ ٱللَّهَ وَمَلَٰٓئِكَتَهُۥ يُصَلُّونَ عَلَى ٱلنَّبِيِّۚ ﴾ الأحزاب: ٥٦

*‹‹አላህና መላእክቱ በነቢዩ ላይ "ሶለዋት" ያወርዳሉ፡፡››*

አላህና መላኢኮች በርሳቸው ላይ ሰለዋት ያወርዳሉ፡፡ የዚህን ሰለዋት ምንነት በተሟላ አኳኋን የመረዳት አቅም የለንም፡፡ አላህ ከፍጡራኑ በአንዱ ላይ እንዴት ሶለዋት ያወርዳል? ሰዎች መልእክቱን ለመረዳት የየራሳቸውን ጥረት አድርገዋል፡፡ ይሁንና መለኮታዊ ሚስጥር እንደሆነ ይቀጥላል፡፡ ይህ ድርጊቱ አላህ ነቢዩን ﷺ ከሌሎች ሰዎች በተለየ ሁኔታ እንደሚወዳቸው ያመለክታል፡፡ እኛም ይህን እውነት እንድንረዳ ይፈልጋል፡፡ በመሆኑም እንዲህ በማለት አዞናል፡-

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ صَلُّواْ عَلَيۡهِ وَسَلِّمُواْ تَسۡلِيمًا ٥٦ ﴾ الأحزاب: ٥٦

*‹‹እናንተ ያመናችሁ ሆይ! በርሱ ላይ "ሶለዋት" አውርዱ፡፡ የክብር ሰላምታ አቅርቡለትም፡፡ (አል አህዛብ 56)*

ይህ ሶለዋት በምላሳችን ብቻ መሆን የለበትም፡፡ ሕይወታችን ባጠቃላይ ለርሳቸው በማደር ወደ ሶለዋትና ተስሊም መለወጥ አለበት፡፡ ቤተሰባዊ፣ የስራም ሆነ ሌሎች እንቅስቃሴዎቻችን በሙሉ በርሳቸው ሶለዋት መቃኘት አለባቸው፡፡

እንዲህ በማለት ራሳችንን መጠየቅ እና ማሰብ አለብን፡፡ የአላህ መልእክተኛ ﷺ ቤተሰባዊ ሕይወቴን፣ ከሰዎች ጋር ያለኝን ግንኙነት፣ የስራ ባህሪየን ቢያዩ ይደሰታሉን? ልጆቼን የማሳድግበትን መንገድ

ቢመለከቱ ይደሰታሉን? ዒባዳዬ ያስደስታቸዋልን? እነዚህን ጥያቄዎች ለራሳችን ዛሬ አቅርበን ድርጊቶቻችንን ካልመዘንን የመጭው ዓለም ሚዛንና ምርመራ እጅግ አስፈሪ ይሆናል፡፡ በመጭው ዓለም ያለ ጥርጥር ተከታዩ መለኮታዊ ትእዛዝ ያናግረናል፡-

﴿ ٱقۡرَأۡ كِتَٰبَكَ كَفَىٰ بِنَفۡسِكَ ٱلۡيَوۡمَ عَلَيۡكَ حَسِيبٗا ١٤ ﴾ الإسراء: ١٤

*“(የሥራ) መዝገብህን አንብብ፡፡ ዛሬ ራስህን ለመመርመር አንተው በቂ ነህ፡፡” (ይባላልም)፡፡›› (አል ኢስራእ 14)*

የዚያን ቀን በስራ መዝገባችን ውስጥ ድብቅ ድርጊቶቻችን ሁሉ ይፋ ይወጣሉ፡፡ ሚስጥሮቻችን ይጋለጣሉ፡፡ ሕይወታችንን ልክ እንደ ሲኒማ ከፊት ለፊታችን እናየዋለን፡፡ እንዴት እንሰግድ፣ እንዴት እንጾም እንደነበር፣ ኢባዳ የምናደርገው በአካላችን ብቻ ነው ወይስ በመንፈሳችንና በቀልባችን ጭምር? የአላህን ቁጥር ስፍር የሌላቸው ጸጋዎች ለማመስገን በዱንያ ላይ ምን አደረግን? ከገንዘባችን፣ ከጊዜያችን፣ ከቀልባችን ምን ያህሉን ለአላህ ሰዋን? ምን ያህሉንስ አባከንን? ለአላህና ለመልእክተኛውﷺ ያለን ፍቅር ምን ያህል ነው? ከአላህ እና ከመልእክተኛው ባህሪ ጋር ያለን ትስስር ምን ይመስላል? ይህ ሁሉ በስራ መዝገባችን ውስጥ ይቀርባል፡፡ ይህ ሁሉ እንደሲኒማ ተቀርጾ ከፊት ለፊታችን ይሰደራል፡፡ ይህን በማስመልከት አላህ ሲናገር፡-

﴿ حَتَّىٰٓ إِذَا مَا جَآءُوهَا شَهِدَ عَلَيۡهِمۡ سَمۡعُهُمۡ وَأَبۡصَٰرُهُمۡ وَجُلُودُهُم بِمَا كَانُواْ يَعۡمَلُونَ ٢٠ ﴾ فصلت: ٢٠

*‹‹ወደርሷ በቀረቡ ጊዜም ጆሮዎቻቸው፣ ዓይኖቻቸውና ቆዳዎቻቸው ይሠሩት በነበረው ነገር በነርሱ ላይ ይመሰክሩባቸዋል፡፡›› (ፉሲለት 20)*

ስለዚህም ራሳችንን ከአሁኑ መመርመር አለብን፡፡ እንዲህ በማለት መጠየቅ አለብን፡-

- ዓይኖቻችን ምን እያዩ ነው?

➢ ጆሮዎቻችን የአላህን ወሕይና የነቢዩንﷺ ሐዲስ ምን ያህል ጊዜ ሰምተዋል?

➢ በአላህ መንገድ ለሚደረግ ትግል ምን ያህል መስዋእትነት ከፍለናል?

በጥቅሉ ጊዜው ከማለፉ፣ ቀኑ ከመምሸቱ በፊት ራሳችንን ፈትሸን፣ ሕይወታችንን መርምረን አስፈላጊውን የእርምት እርምጃ በመውሰድ መዘጋጀት ይጠበቅብናል።

## የፍቅር እና የአደብ ፈተና

የሰው ልጅ በፈተና ውስጥ ነው። ማለትም ይህች ዓለም የፈተና አለም ናት። ከፈተናዎች ሁሉ አስኳሉ ከነቢዩﷺ ፍቅርና ከርሳቸው ጋር ከሚኖር በአደብ የተሞላ ግንኙነት ጋር የተያያዘ ነው። አላህ ይህን በማስመልከት ሲናገር፡-

﴿ ۞ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓاْ أَطِيعُواْ ٱللَّهَ وَأَطِيعُواْ ٱلرَّسُولَ وَلَا تُبۡطِلُوٓاْ أَعۡمَٰلَكُمۡ ٣٣ ﴾ محمد: ٣٣

*‹‹እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ታዘዙ። መልዕክተኛውንም ታዘዙ። ሥራዎቻችሁንም አታበላሹ።›› (ሙሐመድ 33)*

እንዲህም ብሏል፡-

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ لَا تَرۡفَعُوٓاْ أَصۡوَٰتَكُمۡ فَوۡقَ صَوۡتِ ٱلنَّبِيِّ وَلَا تَجۡهَرُواْ لَهُۥ بِٱلۡقَوۡلِ كَجَهۡرِ
بَعۡضِكُمۡ لِبَعۡضٍ أَن تَحۡبَطَ أَعۡمَٰلُكُمۡ وَأَنتُمۡ لَا تَشۡعُرُونَ ٢ إِنَّ ٱلَّذِينَ يَغُضُّونَ أَصۡوَٰتَهُمۡ
عِندَ رَسُولِ ٱللَّهِ أُوْلَٰٓئِكَ ٱلَّذِينَ ٱمۡتَحَنَ ٱللَّهُ قُلُوبَهُمۡ لِلتَّقۡوَىٰۚ لَهُم مَّغۡفِرَةٞ وَأَجۡرٌ عَظِيمٌ ٣
إِنَّ ٱلَّذِينَ يُنَادُونَكَ مِن وَرَآءِ ٱلۡحُجُرَٰتِ أَكۡثَرُهُمۡ لَا يَعۡقِلُونَ ٤ ﴾ الحجرات: ٢ - ٤

*‹‹እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ድምጻችሁን ከነቢዩ ድምጽ በላይ ከፍ አታድርጉ፤ እርሱን ስታናግሩም፥ አንዳችሁ ሌላኛውን ሲያናግር እንደሚጮኸው፥ አትጩሁ፤ ሥራዎቻችሁ ሳታውቁት እንዳይበላሹባችሁ። እነዚያ ከአላህ መልዕክተኛ ዘንድ ድምጾቻቸውን ዝቅ የሚያደርጉት -አላህ ልቦቻቸውን ለ"ተቅዋ" ያሰናዳቸው ናቸው። ለነርሱ*

*ምሕረትም፥ ታላቅ ምንዳም አላቸው። እነዚያ ከጉጆዎች ውጭ ሆነው የሚጠሩህ ብዙዎቹ አስተዋዮች አይደሉም።›› (አል ሁጁራት 2-4)*

ከአላህ መልእክተኛ ﷺ ጋር ያለንን ግንኙነት አደብ ማስያዝ፣ ሱንናቸውን መከተል፣ እርሳቸውን በትክክል ማወቅ ለቀልባችን የተቅዋ ፈተና ነው፡፡ ለርሳቸው ያለንን ፍቅር ለመፈተሽ የሚያስችል መመዘኛ ነው፡፡ እንደዚሁም ወደ አላህ መቃረቢያ መንገድ ነው፡፡

የአላህን መልእክተኛ ﷺ ያለ ስርዓት የሚያናግሯቸው፣ ከሩቅ ሆኖ በከፍተኛ ድምጽ የሚጠሯቸው፣ አደብ ባጣ አኳኋን የሚቀርቧቸው ሰዎች በእርግጥም ቂሎች ናቸው፡፡ አስተዋይ አእምሮ የላቸውም፡፡

የአላህን መልእክተኛ ﷺ በአርአያነት መያዝ ምን ያህል አስፈላጊ ነው? ሕይወታችንን በርሳቸው ሕይወት እንዴት እንመዝን? በዚህ ረገድ በቁርአን ውስጥ የሰፈረው ግልጽ መልእክት ይህን ይመስላል፡-

﴿مَّن يُطِعِ ٱلرَّسُولَ فَقَدۡ أَطَاعَ ٱللَّهَۖ وَمَن تَوَلَّىٰ فَمَآ أَرۡسَلۡنَٰكَ عَلَيۡهِمۡ حَفِيظٗا ٨٠﴾

*‹‹መልዕክተኛውን የታዘዘ አላህንም ታዟል። (ከዚህ መንገድ) ያፈገፈገ ግን (አያሳስብህ) እነርሱን (ከኃጢአት) ጠባቂ አድርገን አልላክንህም።›› (አል ኒሣእ 80)*

## ረሱሉን ﷺ የመውደድ መመዘኛ

ለአላህ መልእክተኛ ﷺ ያለንን ፍቅር ደረጃ ከሚያሳዩን ነገሮች መካከል ታላቁ ሶሐባ አብደላህ ቢን ሂሻም ያስተላለፉት ሐዲስ ይጠቀሳል፡፡ እንዲህ ሲሉ አውግተዋል፡-

ከአላህ መልእክተኛ ﷺ ጋር ነበርን፡፡ የዑመርን እጅ ይዘዋል፡፡ ዑመር፡- ‹‹የአላህ መልእክተኛ ሆይ፣ እርስዎ ከኔ ዘንድ ከራሴ ሲቀር ከሁሉም ነገር በላይ ተወዳጅ ነዎት፡፡›› አላቸው፡፡ ነቢዩም፡- ‹‹አይሆንም፡፡ ነፍሴ በእጁ በሆነችው ጌታ እምላለሁ፣ ከራስህም በላይ ካንተ ዘንድ ተወዳጅ

መሆን አለብኝ›› አሉት፡፡ ዑመርም፡- ‹‹ከራሴም በላይ እወድዎታለሁ›› አላቸው፡፡ ‹‹ዑመር ሆይ፣ አሁን ጥሩ ሆነ›› አሉት፡፡ (ቡኻሪ)

እኛም የአላህን መልእክተኛﷺ ልክ እንደ ዑመር ከራሳችን በላይ መውደድ፣ የቀልባችንን ዙፋን ለርሳቸው ማስረከብ፣ እርሳቸውን የሕይወታችን መሪ አድርገን መያዝ ግድ ይሆንብናል፡፡ ምክንያቱም እርሳቸውን መውደድ በኛ ላይ ግዴታ ነውና፡፡

የአላህ መልእክተኛﷺ ለሙእሚኖች ከራሳቸውም በላይ ተወዳጅ መሆን እንዳለባቸው አላህ ሲናገር፡-

﴿ ٱلنَّبِيُّ أَوۡلَىٰ بِٱلۡمُؤۡمِنِينَ مِنۡ أَنفُسِهِمۡۖ وَأَزۡوَٰجُهُۥٓ أُمَّهَٰتُهُمۡۗ وَأُوْلُواْ ٱلۡأَرۡحَامِ بَعۡضُهُمۡ أَوۡلَىٰ بِبَعۡضٖ فِي كِتَٰبِ ٱللَّهِ مِنَ ٱلۡمُؤۡمِنِينَ وَٱلۡمُهَٰجِرِينَ إِلَّآ أَن تَفۡعَلُوٓاْ إِلَىٰٓ أَوۡلِيَآئِكُم مَّعۡرُوفٗاۚ كَانَ ذَٰلِكَ فِي ٱلۡكِتَٰبِ مَسۡطُورٗا ٦ ﴾ الأحزاب: ٦

*‹‹ነቢዩ ለአማኞች ከነፍሶቻቸው ይበልጥ የቀረበ ነው፡፡ ሚስቶቹም እናቶቻቸው ናቸው፡፡ በአላህ መጽሐፍ ውስጥ የሥጋ ዝምድና ያላቸው ሰዎች (በውርስ ረገድ) ከፊሉ ለከፊሉ ከአማኞችና ከሙሃጂሪን (ወንድሞቻቸው) የበለጠ ትስስር አላቸው፡፡ ግና ለወዳጆቻችሁ (በኑዛዜ ወይም በሌላ መልኩ) መልካም ብትሠሩ ይፈቀዳል፡፡ ይህ (ድንጋጌ) በአላህ መጽሐፍ ውስጥ (ጥንትም) የሰፈረ ነው፡፡›› (አል አህዛብ 6)*

ነቢዩንﷺ መውደድ የእውነተኛ ኢማን መመዘኛ መስፈርት መሆኑ በሐዲስ ተገልጿል፡፡ ነቢዩﷺ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹ከናንተ አንዳችሁ ከርሱ ዘንድ ከወላጆቹ፣ ከልጆቹና ከሰዎች ሁሉ ባጠቃላይ ይበልጥ ተወዳጅ እስካልሆንኩ ድረስ አላመነም፡፡›› (ቡኻሪ)

በዚህ ምክንያት ሶሐቦች አንዳች ነገር እንዲፈጽሙ በአላህ መልእክተኛﷺ ሲታዘዝ እንዲህ ይሉ ነበር፡-

فداك أبى وأمى يارسول الله

‹‹የአላህ መልእክተኛ ሆይ፣ እናቴም አባቴም ለርስዎ ፊዳ (መስዋእት) ይሁኑ፡፡››

በአንጻሩ ከአላህ መልእክተኛﷺ ጋር በተያያዘ ዝርክርክና ግዴለሽ መሆን መሐይምነት ነው፡፡ ይህን ፍቅር አጥብቆ መያዝና በርሱ መገለጽ ደግሞ የመዳኛ መንገድ ነው፡፡

## ነቢዩንﷺ የመውደድ ምልክት

ሰዎች ስለሚወዱት አካል አዘውትረው ይናገራሉ፡፡ ንግግራቸውንም በዚያ አካል ይጀምራሉ፡፡፡ በርሱ ዙሪያ የሚሽከረከሩ ወጎች ያስደስቷቸዋል፡፡ በንግድ ስራ የተመሰጠ ነጋዴ ስለንግድ አውግቶ አይጠግብም፡፡ ይህን አተረፍኩ፣ ይህን ከሰርኩ፣ ይህ ስራ ይህን ያህል ትርፍ ያስገኛል ወዘተ ማለት ይወዳል፡፡ ልጆቹን በጣም የሚወድ ሰው በሁሉም ቦታና አጋጣሚ ስለነርሱ ማውጋት ይቀናዋል፡፡

ሶሐቦችና ደጋግ የአላህ ባሮችም የአላህን መልእክተኛﷺ በጣም ከመውደዳቸው የተነሳ ስለርሳቸው ተናግረው አይጠግቡም፡፡ ስማቸው ሲነሳ በልዩ ሐሴት ይሞላሉ፡፡ በመጭው ዓለም ከርሳቸው ጋር እንሆን ዘንድ ይህ ፍቅር በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ አላህ ሆይ፣ ነቢዩን ይበልጥ እንድናውቅና እንድንወድ አድርገን፡፡ አሚን!

ከፍቅር ሚስጥሮች መካከል አንዱ አፍቃሪ የተፈቃሪን ስብእና ለመላበስና እርሱን ለመምሰል የሚያደርገው ጥረትና ሩጫ ነው፡፡ አፍቃሪው የቱን ያህል ደካማና አቅም የለሽ ቢሆንም ከተፈቃሪው ልቅና ድርሻ ይኖረዋል፡፡

## ነቢዩንﷺ መግለጽ አስቸጋሪ ነው

ኻሊድ ቢን ወሊድ ለአንድ ዘመቻ ወጣ፡፡ ከአንድ ቀዬ ውስጥም ረፍት አደረገ፡፡ የቀዬው አለቃ የሙሐመድን ማንነት ግለጽልን›› አለው፡፡

በዝርዝር ማስረዳት አልችልም፡፡ ሲል መለሰ፡፡ እሺ ጠቅለል አድርገህ ንገረን›. አለው፡፡ ኻሊድም ‹‹መልእክተኛ በላኪው መጠን ነው›› አለ፡፡[1]

ነቢዩንﷺ የላካቸው የፍጡራን ሁሉ ፈጣሪና የተላቀ ሐይል ባለቤት የሆነው አላህ ከመሆኑ አኳያ የርሳቸውን ደረጃ አስተንትን፡፡ አላህ ሆይ፣ ሶሐቦች ለነቢዩﷺ የነበራቸውን ፍቅር ክፋይ ለኛም ስጠን፡፡ ሕይወታችንን በርሳቸው ፍቅር በማስዋብ ውለታ ዋልልን፡፡ አሚን!

---

1 መናዊ፣ ፈትሁል ቀዲር

# ማጠቃለያ

የነቢዩን ﷺ አማላጅነት እናገኝ ዘንድ ሕይወታችንን በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ባብራራናቸው ነብያዊ ሚዛኖች መመዘን፣ እርሳቸውን በመከተሉ ረገድ ያለንበትን ደረጃ ማወቅ ግዴታ ይሆንብናል፡፡ ከምር የምናስብበት ሁኔታ መፈጠር አለበት፡፡

ለነቢዩ ሙሐመድ ﷺ ኡምማ ተገቢ የሆነ ሕይወት ለመኖር በደስታና ስሜት መንቀሳቀስ ይጠበቅብናል፡፡፡ የነቢዩ ﷺ አምሳያ የሌለው ስብእና በኢባዳችን፣ በግለሰባዊ፣ በቤተሰባዊና በማሕበራዊ እንቅስቃሴያችን፣ በስሜትና በአስተሳሰባችን፣ በዓለማዊም በመንፈሳዊም ሕይወታችን ሁሌም መንጸባረቅ አለበት፡፡ አፍቃሪ እንደ ፍቅሩ መጠን ተፈቃሪን መከተሉ፣ እርሱን ለመምሰል መጣሩ የሚጠበቅ ነው፡፡

ነቢዩን ﷺ በትክክል መከተል እንችል ዘንድ ሁለንተናዊ ማንነታቸውን ለማወቅ ያለንን ጉልበትና ክህሎት ሁሉ መጠቀም ይኖርብናል፡፡ አርአያዊ ስብእናቸውን በወጉ መረዳት ግድ ይለናል፡፡

አፈር የቱን ያህል ለም ቢሆንም እንኳ ዝናብ ካላገኘና የጸደይ ጸሐይ ካላረፈበት እህል አያበቅልም፡፡ ግና የትኛውም ቀልብ የፍጡራኑን ፈርጥ በአርአያነት በመከተል ፍሪያማ ልቦና ሊሆን ይችላል፡፡ ነቢዩ ሙሐመድ ﷺ ከርሳቸው በፊት ከነበሩት፣ ወደፊትም ከሚመጡት ሰዎች ሁሉ የላቁ ናቸው፡፡ የመልካም ስነ ምግባርም እሴቶች የማይነጥፍ ምንጭ ናቸው፡፡ ለዓለማችን የበረካና የእዝነት ምክንያት ናቸው፡፡ እጅግ አስደናቂ በሆኑ እውነታዎች የተሞላው ቁርአን የእምነትን ዓለም ሊመራ በርሳቸው ላይ ወርዷል፡፡

ለአላህ መልእክተኛ የቱን ያህል ክብር ብንቸር፣ በጥቃቅን ነገሮች እንኳ ሳይቀር እርአያነታቸውን ብንከተል ከርሳቸው ደረጃ አኳያ ምንም ማለት አይደለም፡፡ እጅግ ኢምንት ነው፡፡ አላህ ‹ወዳጄ› በማለት ያናገራቸው ነብይ ደረጃቸው ልንገምተው ከምንችለው በላይ የበዛ፣ ስብእናቸው የመጠቀ፣ ልቅናቸው ከፍጡራን ሁሉ በላይ የዘለቀ ነው፡፡ በደካማ

አቅማችን የርሳቸውን ምሉእነት መድረስ አንችልም፡፡ የፍጡራን ሁሉ ፈጣሪና ቁጥር ስፍር የሌላቸው መላኢኮቹ ሶለዋት ያወረዱባቸውን ነብይ ሁለንተና መረዳት ይከብደናል፡፡

ስብእናቸውን ለማብራራት አንደበት አቅም የለውም፡፡ ቃላት ጉልበት ያንሳቸዋል፡፡ እስካሁን በዚህ መጽሐፍ ያሰፈርነው ገለጻ ውቅያኖስን በጭልፋ ከመሆን የዘለለ አይደለም፡፡ ‹‹የታላቆች ሁሉ ታላቅ›› መሆናቸውን ከተናዘዝን ይበቃል፡፡ እርሳቸውን ከልብ የወደዱ፣ ለፍቅራቸው ያረገዱ አማኞች ምንኛ ታደሉ! የርሳቸውን መንፈሳዊ ድባብ በእያንዳንዱ የአካላችን ሴል አስርጸን ወደ ጌታችን እንመለስ፡፡

- የፍጡራን ሁሉ አለቃ በሆኑት በምርጡ ነብይ በሙሐመድﷺ ላይ የአላህ እዝነትና ሰላም ይስፈን
- ለሰዎችም ለአጋንንትም በተላኩት ምርጥ ነብይ ላይ የአላህ እዝነትና ሰላም ይስፈን
- የሁለቱ ሐረሞች ኢማም በሆኑት ምርጥ ነብይ ላይ የአላህ እዝነትና ሰላም ይስፈን፡፡
- የሐሰንና የሁሰይን አያት በሆኑት ምርጥ ነብይ ላይ የአላህ እዝነትና ሰላም ይስፈን፡፡

አላህ ሆይ፣ በሙሐመድﷺ፣ በቤተሰቦቻቸውና በባልንጀሮቻቸው ላይ እዝነትህንና ሰላምህን አስፍን፡፡

አላህ ሆይ፣ የዘልዓለማዊ ደስታችን ምንጭ የሆኑትን ምርጡን ነብይ ፈለግ የምንከተል አድርገን፡፡ ልዩና አንጸባራቂ ስብእናቸውን በአርአያነት በመከተል አንተን የማስደሰትን እድል ለግሰን፡፡

ዱንያችንንም አኼራችንም በነብዩﷺ ብርሃን አድምቅልን፡፡ በውበታቸው ሸልምልን፡፡ ከሰፊው መንፈሳዊ አጸዳቸው እንቋደስ ዘንድ አስችለን፡፡ ቀልባችንን ሁሌም ያንተና የነቢዩ ፍቅር ማረፊያ አድርግልን፡፡

ጌታችን ሆይ፣ ሁላችንንም በነብይህ ታላቅ የአማላጅነት ሂደት (ሸፋአቱን ዑዝማ) አካትተን። አሚን!

**= ተፈጸመ =**